# አጥቢያ

ዓለማየሁ ገላጋይ

© የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው

የሁለተኛ እትም - ሐምሌ 2007 ዓ.ም

የፊት ገፅ ዲዛይን፡ ዮሐንስ ሰረቀ

የጀርባ ገፅ ዲዛይን፡ዓለማየሁ ገላጋይ

**የደራሲው ቀደምት ስራዎች**

- ✓ አጥቢያ
- ✓ ቅበላ
- ✓ ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ሕይወትና ክህሎት
- ✓ ኩርቢት
- ✓ የፍልስፍና አፅናፍ
- ✓ ኢህአዴግን እከስሳለሁ
- ✓ መልክአ-ስብሐት
- ✓ የብርሃን ፈለጎች



# ለማስታወስ

አዲስ አበባ ላይ እንደ ጭጋግ በቀስታ የምንሳፈፍ መሰለኝ:: አሥራ አንደኛውን ፎቅ ተፈናጦ አዲስ አበባ ጉተና ላይ ቁቢብ ያለው ኮከብ ሬስቶራንት ዓላማው ይህ ሳይሆን አይቀርም ስል አሰብኩ:: የአዲስ አበባ ከፊል ደቡብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜንና ከፊል ምሥራቅ ፍንትው ብሎ ይታያል::

አዲስ አበባ እንደብረት ቁና ዓይን በሚያዳልጥ ግድግዳ የተከበበች ጎድጓዳ ከተማ ነች:: ወጨጫ... ጉስቋም... እንጦጦ... አይነምሣ... የካ... የረር... የተራራ አጥሮቿ እንደ ሲኦል አጋፋሪ ደረታቸውን ነፍተው ከሚነፍሩት ጥሬ ነፍሶች አንዱም ተፈናጥሮ እንዳያመልጥ በጭካኔ የሚጠባበቁ ይመስላሉ::

ኮትቻ ቁርበት ላይ የተዘራ ድፍን ምስር የመሰለው ከተማ ላይ የበለጠ አተኮርኩ:: አንዱን ከሌላው መለየት ተሳነኝ፣ እንደ አዛባ ማከማቻ ጉድጓድ ተነካክቶና ተቀባብቶ ደህናውም መጥፎ የመሰለበት ከተማ:: አፈርን ከምስር መለየት እንደተሳነው አጣሪ ይበልጥ ለመቅረብ ወደታች አሰገግኩ:: ከተማዋ እንደተበተነ ልም መስታወት አልፎ አልፎ ብርሃን የሚረጩ ዘመናዊ ቤቶች አሉባት:: በተረፈ ሰደድ አዝረክርኮ እንደተወው መስከ ልምላሜ የራቀው፣ አዲስነት የተጣላው፣ ስሜት ደስ የማያሰኝ ዕይታ ይጋረጣል::

የአራት ኪሎን አካባቢ በአይኖቼ ፈለኩ:: ድንኩ የሚያዝያ ሃያ ሰባት መታሰቢያ ሐውልት አይታይም:: ከቅድስት ማሪያም ቤተክርስቲያን ዝቅ ብሎ የተገነቡት ሁለቱ ህንፃዎች እንደ ባለጌ ምላስ ሰማይ ላይ ያላግጣሉ:: የፓርላማ የሰዓት ማማ እንደ ማጥ ከዋጠው የላይኛው ቤተ-መንግሥት ዳለቻ ደን ጭንቅላቱን ብቅ አድርጓል:: አጠገቡ የቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ጉልላት ካባ የለበሰች ሴት ወይዘሮ መስሎ ይታያል:: በእውኑ እጅግም የማትርቀው የበአታ ቤተክርስቲያን ወርቃማ የራስ ወርቅ እንደደፋች ፈንጠር ብላ ትታያለች:: በተረፈ እርጋጭ፣ ብካች፣ ትቢያ... የከተማ ገላ::

«እዚች ከተማ ውስጥ ህይወትም እኝዲሁ ናት» ስል አሰብኩ:: የከፋው ከተደሰተው፣ ያልሞላለት ከደላው፣ የተራበው ቁንጣን ካፍተለተለው... ላይዋሃዱ

የተቀላቀሉባት ከተማ:: ይሄ ሃሳብ ጭኔ ላይ ያስቀመጥኩትን ረቂቅ ጽሁፍ አስታወሰኝ:: በእጄ ዳሰስኩት:: ደስ የሚያሰኝ ስሜት አሳደረብኝ:: እዚህ «ሬስቶራንት» የመጣሁት ስለዚሁ ረቂቅ ጽሁፍ ዕጣ ፋንታ ብቻዬን አስቤ ለመወሰን ነበር:: ይታተም?! ከታተመስ አቀራረቡ እንዲህ መሆን አለበት? የእኔ ታሪክ እዚህ ረቂቅ ውስጥ መካተቱ ተገቢነት አለው? የአባቴስ?...

በረጅሙ ተንፍሼ ወደ «ሬስቶራንቱ» ውስጥ አተኮርኩ:: አረፋዱ ላይ የመጣሁ ቢሆንም ምሣ ሰዓት ተቃርቦ ነበር:: ጭር ያለው የምግብ አዳራሽ በሰዎች ለመሞላት ዳር-ዳር እያለ ነው:: አየሩ በጥብሳ-ጥብስ ሽታ መታወድ ጀምሯል:: እርቦኝ እንደሆን እራሴን ሰለልኩ:: አላሰኘኝም::

ያሰኘኝ በረቂቁ ዕጣ ፋንታ ላይ መወሰን ነበር:: አሁን የሚያመችበት ሰዓት እያበቃ ነው:: «ሬስቶራንቱ» በሰዎች ሊሞላ ነው:: እንደውም አንዳንዶቹ እኔ ወዳለሁበት በመስታወት የተከፈለ በረንዳ እየመጡ መቀመጥ ጀምረዋል:: ምግብ ያዘሉ ብዙዎቹ የቀረበላቸው ምግብ ቁልል ውስጥ ተደፍተው መተንፈስ እስኪሳናቸው ያላምጣሉ:: ሰው በእንዲህ ያለ ሁኔታ ሲበላ ሳይ ይጨንቀኛል:: ምግብ የቁንጥ አካል ሆኖ አካባቢን ለማድመቅ ሲቀርብ ነው ደስ የሚለኝ:: ያኔ መብላት እንደ ማንጎራጎር፣ እንደማህሌት መቆም፣ እንደ ሽብሸባና እንደቅኔ መዝረፍ ጥበብን የመዘከር ባህርይ ይይዛል ብዬ አስባለሁ:: ከዚያ ውጭ መብል እንደ ኩይሳ ተቆልሎ ፈጣን እጆች ሲተገትጉት ሳይ የሰው ልጅ ካንቀላፋ እንሰሳነቱ ድንገት የባተተ ይመስለኛል:: ለጥቂት ጊዜ ከምግብ ጋር እኳረፋለሁ::

ቀልቤን ጭኔ ላይ ላስቀመጥኩት ረቂቅ ሙሉ ለሙሉ ለማውረስ ተናዝገኔ ብመጣም የተለያዩ ጉዳዮች እየተቀራመቱ አዳገቱኝ:: ረቂቁ በውሃ ሰማያዊ ከላሰር ተለብጧል:: እንደ ድንቡሽቡሽ ህፃን ቀልብን ለመጥባት በመፍጨርጨር ወደ ላይ የሚያየኝ መሰለኝ::

«ወደድኩህ እንጂ አልወለድኩህ» እንደሚል መሃን አሳዳጊ ያለ ስሜት አደረብኝ:: በእርግጥም ይሄን ረቂቅ ከፉኛ ወድጄዋለሁ:: ረቂቁ አራት ኪሎ አካባቢ ስላለች ስለአንዲት መንደር በማስታወሻ መልክ የተጻፈልኝን ደብዳቤዎች አካቶ ነው ለህትመት የተዘጋጀው:: ላሳትም ማሰቤን የማስታወሻዎቹ ፀሐፊ አያውቅም::





በደፈናው «እንዳሻሽ አድርጊያቸው» የሚል ፈቃድ ነው የሰጠኝ:: እኔ ደግሞ የሰማችውን ወሬ ለማውራት አድማጭ እንዳጣች ሆኜ እስኪታተም አከለፍልፎኛል -- ሆዴን ቆርጦኛል:: ትንሽ ቅር ያሰኘኝ ማስታወሻው የተፃፈበትን ምክንያት ለመተንተን ሲባል የተደነጎረው የእኔ ታሪክ ነው::

ምን ማድረግ እንዳለብኝ ሳልወስን የቦዘዙ ዓይኖቼን ወደ ግራ አሽራምሜ ደማቅ ቀይ ቲሸርት ያደረገ ወጣት ላይ አንቃኳቸው:: ወጣቱ ያዘዘው ምግብ እስኪመጣ ብቻ ሳይሆን እኔ እስካየው ሲጠብቅ የቆየ ይመስላል:: ያልደመቀ ሪዝ የከበበው ከንፈሩን አሸሽቶ ጥርሶቹን አሳየኝ:: ተናደድኩ:: ቀልቤን ለማንም ማጋራት አልሻም::

ድንገት «ለምን ይሄን የሚያብራራ አጭር መግለጫ አልጽፍም?» ስል አሰብኩ፣ ሃሳቤ ተገቢ ሆኖ አገኘሁት:: ወዲያው ከቦርሳዬ ውስጥ እስክሪብቶና ትንሽ የማስታወሻ ደብተር አውጥቼ መፃፍ ጀመርኩ::

*በመጀመሪያ ደረጃ ደራሲ አለመሆኔን መናዘዝ ሳያስፈልገኝ አይቀርም:: ጥሩ ተራኪ እንዳይደለሁም ይሰማኛል:: እኔ የሕብረተሰብ ጥናት ባለሙያ ነኝ:: ከዚህ ቀደም ያቀረብኳቸው አንዳንድ ማህበራዊ ጥናቶች ጥሩ ተራኪ አለመሆኔን ከመጠቆማቸው ውጭ እንደ ሒሳብ መረጃዎችን ቁልቁል የሚደምሩና የሚቀንሱ የሐሳብ ስሌቶች ብቻ ነበሩ::*

ደግሜ ለማንበብ ተሰናዳሁ:: የዘባረቅሁም መሰለኝ:: በሀሳቤም ልጓም የተጠመዱት ዓይኖቼ አሁንም ወደግራ ተሽራምመው ደማቅ ቀይ ቲሸርት ያደረገው ወጣት ላይ ወጡ:: ወጣቱ በፈገግታ ቀለበኝ:: ሴት በመሆኔ ብቻ ወንድ ልጅ እንዳልተቀጠቀጠ አውራ በግ ምንጭሩን ሲገሽልጥብኝ አልወድም:: ብዙ ወንዶችን ሳላላምጥ የምተፋቸው ለዚህ ነው:: ቀልቤን በወቀሳ ልምጭ አሰባስቤ ጅምር ጽሁፌን እንዴ ተወጣሁትና መፃፌን ቀጠልኩ::

*የዚህ መጽሐፍ መነሻ የአንድ ሰው ማስታወሻ ነው:: መድረሻውም:: መጽሐፉ ውስጥ ስለራሴ ላለመተረክ ተመሰጋኝ ጥረት አድርጌ ነበር:: እራሴንም እንደ አንድ አጋፋሪ ቆጥሬ የተዘጋጀውን ማስታወሻ ለእናንተ በማቅረብ ላይ ተገድቤ ለመዝለቅም ጥረት አድርጌ ነበር:: ነገር ግን*

ማስታወሻው አንዳንድ አያያዥ ታሪኮችን ተነፍጎ ቢቀርብ ብጥስጣሽ ሃሳብ ይሆንና ግንዛቤ ያጓድላል የሚል ሥጋቴ አየለብኝ:: በመሆኑም ከማስታወሻው ጋር ግንኙነት ያላቸውን የእኔን ታሪኮች ብቻ ለማካተት ወሰንኩ:: ድግሱ ማስታወሻውን የጻፈው ሰው ብቻ መሆኑን ካለመዘንጋቴም በላይ ታሪኬን ከጽሁፉ ጋር ተዳባይ አድርጌ ማቅረቤ እንደ ድግስ ኩዴታ እንዳይቆጠርብኝ አለምናለሁ:: የተወጠረው አካሌ ሲረግብ ተሰማኝ::





# ወደ ማስታወሻ

## አንድ

ሐሳብ ተጫጭኖኝ ከአልጋዬ ተነሳሁ:: እንዲህ ያለ ስሜት ሲያድርብኝ አባቴ ዕድሜ ላይ ሮጬ የደረስኩበት ይመስል እኩያነት ይሰማኛል:: የወትሮው ባህሪዬ እንደደመና ተገፎ ግጥጥ ያለ እውነት ግንባሬ ላይ ይወጣል:: ይሄን የአዘቦት ባህሪዬን አባቴ በዘዴ ያልፈዋል:: አብዛኛውን ጊዜ ከተጫጫነኝ ሐሳብ የሚያወጡኝ የአነጋገር ፈሊጦች አሉት::

«ከአባት ጋር መፋጠጥ ለሴት ዝንጀሮ ማን ሰጣት!? የወንድ ዝንጀሮ ድርሻ ነው»

ንግግሮቹ ድንገተኞችና ያልተጠበቁ ስለሚሆኑ የእውነቴን ጨረሮች አቅጣጫ ይስታሉ:: ሳልወድ በግድ ቧልታዊ ንግግሩን የማመናተል ባተሌነት ይጠናወተኛል::

«እውነቴን እኮ ነው - ታፌ» እለዋለሁ:: አባቴን ለምን ታፌ እንደምለው አላውቅም:: ስሙን አሳጥሮ መጥራት መቼ እንደጀመርኩም አላስታውስም:: ምናልባት ገና ኮልታፋ እያለሁ ለአጠራር ስለማያዳግት ያኔ ጀምሬ በዚያው ቀጥዬ ይሆናል:: አንዳንድ ጊዜ ጥሩ ስሜት ሲሰማኝና መቃለድ ሲያምረኝ «ታፈስ ሀብቱ» ብዬ በሙሉ ስሙ እጠራዋለሁ:: ይሄኔ ፊቱ መስመር ሳያወጣ የውስጥ መፍነክነኩን እየገለጸልኝ «እርጥባን ታፈስ» ሲል ሙሉ ስሜን ጠርቶ ብድሩን ይመልሳል::

«አንዲት ዝንጀሮ ለአባቷ የምታቀርበው እውነት ይኖራታል፣ አቀራረቧ ግን ከወንዱ ዝንጀሮ ይለያል» ይለኝና «መጀመሪያ የሌሊት ልብሷን ትቀይራለች:: ብዙ ጊዜ ቤት ውስጥ ቁርስ መብላት አያስኛትም፥ ስለዚህ «ሬስቶራንት» ሄዳ ብርሃናማ በረንዳ ላይ አባቷን እያጎረሰች ጥያቄዋን ታቀርባለች:: አባት ጉርሻውን እየተቀበለ ጥያቄውን ከቻለ ይመልሳል፣ ካልቻለ ብቸኛ የበላዩ ለሆነው ለእግዚአብሔር ‹ሪፈር› ይጽፋል»

ቁርስ ላይ እስከንቀመጥ መንገዱ ሁሉ ለዛ ያለው ቀልድ ነው:: አልፎ አልፎ ፀጉራም ቀይ እጁን ከመኪናው መሪ ላይ እያነሳ አንገቴን ዳበስ ያደርገኛል:: ይሄ የአባቴ ድርጊት ለእኔ ትልቅ መልዕክት አለው:: የመመካትና በሰዎች የመታጀብ ስሜት ያሳድርብኛል:: እዚህ ባለአስራ አንድ ክፍል መኖሪያ ውስጥ እኔና እሱ ብቻ

ከሰራተኞቻችን ጋር የመኖር መገለል የሚፈጥርብኝ ነጠላነት በዚህ ሰዓት ፈጽሞ ይወገዳል:: ጥያቄዬ የመነጠል፣ የባይተዋርነትና ሰው የመናፈቅ ከሆነ ምላሽ አገኘና ምን እንደምጠይቀው ግራ ይገባኛል:: ብዙ ጊዜ ግን ተስፋ መቁረጥ ተጫጭኖኝ ነው አባቴን የማገኘው:: አንድ ቀን «ለምንድነው የምማረው?» ድንገት ጠየኩት አባቴን:: ምንም አይነት ጥያቄዬ አያስደነግጠውም «ለምን አላቆምም??»

አባቴ ምላሽ ከመስጠቱ በፊት አፉን አጉረሺኝ የሚል ምልክት አሳየኝ:: ለምን እንዲህ እንደሚያደርግ ያወቅሁት አሁን በቅርብ ነው:: ከሱ ምላሽ ይልቅ ለቅርበታችን፣ ለአባትነቱ፣ ለልጅነቴ ክብደት እንድሰጥ ነው:: አጎረስኩት፤ ጥያቄዬንም ጉርሻውንም ሲያላምጥ ቆይቶ እንዲህ አለኝ::

«እኔ አባትሽ ነኝ:: ልጅነትሽን ብቻ ተመክተሽ ከቀረብሽኝ ከኔ የምታገኚው ነገር የተመጠነ ነው:: ማለቴ አባትነቴ የሚያሳድርብኝ ፍቅር እስከሚያስገድደኝ ድረስ:: ያ-- አይበቃሽም:: ከዚያ በላይ ከኔ ለመውሰድ እውቀት ሊኖርሽ ይገባል:: ከልጅነትሽ ይልቅ በመማር ከኔ የምታገኚው ተጨማሪ ነገር ነው ለራስሽ ያለሽን ግምት ከፍ የሚያደርገው:: ስለዚህ ከእኔም ጭምር ነፃ ለመውጣት መማር አለሽ»

ግራ የሚያጋባ ምላሽ ነበር:: የአባቴ ፍቅር እስከምን ጥግ ድረስ የሚንጠራራ ነው? ስፍር አለው? ከዚህ በመለስ የሚባል ድንበር አለው? እንደ አገር? እንደ አህጉር? እንደ ዓለም? የአባቴን ፍቅር የሚበቃኝን ያህል ስለማገኘ መጠኑን ለማረጋገጥ ርቄ ተጉዤ አላውቅም:: ቀና ብዬ እንዳየሁት ትዝ ይለኛል:: እኔን ማየት ትቶ ወደሌላ አቅጣጫ ዓይኖቹን ተክሎ ነበር:: አባቴ የክልስ መልክ አለው:: ሰውነቱ ሞላ ያለ ቢሆንም የፊቱ አጥንት ያፈጠጠ ነው:: ጉንጮቹ ሲጃራ እንደሚስብ ሰው ሰምጠው የቀሩ በመሆናቸው ጺሙን እራሱ ከላጨው ብዙ ጊዜ የሚቆረጠው ጉንጩ ላይ ነው:: ስለዚህ ፀጉር አስተካካይ ቤት መላጨት ያዘወትራል:: በረዥሙ ተንፍሶ---

«እኔ አባቴን የረታሁት ትምህርቴን መጥኝ በማለቴና ጠንካራ ሰራተኛ በመሆኔ ነው:: እንደምታውቂው፤ በመካከል ድንገት የወለደኝ ስለነበርኩ ካደኩ በኋላ ነው ቤተሰቡን የተቀላቀልኩት:: በዚህ ላይ ከትዳሩ ውጭ ወስልቶ ስለወለደኝ እኔን ማየት ወቀሳ ነበር የሚሆንበት:: ያም ሆኖ በስተመጨረሻው ዘመን ብቸኛ መመኪያው እኔ ሆኜ ነበር:: የተቀሩትን ልጆቹን በሰበብ ባስባቡ ከሀብቱ ላይ ገለል ሲያደርጋቸው





የነበረው እኔ ጠንካራ ሰራተኛና የተማርኩ መሆኔ ስለረታው ነበር:: እሱ በምስጢር ያስቀመጠልኝን ሀብት የማካካሻ ክፍያ አድርጌ ነው ድርጅቱን ከውርስ መቀራመት ያዳንኩት:: ይሄን ሁሉ ያተረፍኩት የአባቴ ልጅ በመሆኔ ብቻ አይደለም:: በማወቄ፣ በመማሬና በጠንካራ ሰራተኛነቴ ነጥቄ ያስቀረሁት ነው::»

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተረዳሁት የአባቴ እንከን ይሄ ነው:: የህይወትን ግብ ከሀብት ጋር ብቻ ማላጠፉ:: የኑሮ፣ የደስታ፣ የበላይነትና የአሸናፊነት ልኬቱ በሱ ቤት ሀብት ብቻ ነው:: ሀብትን በሚያንቋሽሹና በሚያሳንሱ ክርክሮች ላይ አይታደምም:: ከታደመም ፊቱ ተለዋውጦ ኃይለ ቃል ይናገራል:: «ሀብትን ዋጋ ቢስ አድርጎ የሚቆጥር መጋኛ ብቻ ነው::» ይላል:: ለዚህ ይሆናል ደጋግሞ የጥንት ጓደኛውን፣ የእኔን አስተማሪ ዶክተር ማርቆስን «ያ መጋኛ ደህና ነው?» እያለ የሚጠይቀኝ:: ከሀብት ጋር በተያያዘ ክርክር ብገጥመው ሌላው ቀርቶ የሀብት ጥቅም ያልገባኝ ቢመስለው ኃይለ ቃል እንደሚናገረኝ ስለምገምት እጠነቀቃለሁ::

እንደውም አንድ ጊዜ አሥራ ሁለተኛን በጥሩ ውጤት ማለፌን ሲሰማ እራሱ መኪና አለማምዶ ችሎታዬን ካረጋገጠ በኋላ መንጃ ፈቃዱን እቤት ድረስ ይዞልኝ መጣ:: በመንጃ ፈቃዱ ተደስቼ ሳልጨርስ አንዲት «ዲ ኤክስ» ቶዮታ መኪና ለትምህርት ቤት መመላለሻ አበረከተልኝ:: ይቺን መኪና ለስድስት ወር ያህል በወረት ነዳኋት:: አንድ ቀን ዶክተር ማርቆስ ቢሮአቸው አስጠርተው ግሳጼ የተሞላበት ምክር ለገሱኝ:: «ጫማ በሌላቸው ጓደኞችሽ መካከል መኪና አጉል መኩራራት ነው:: ቢያንስ እዚያው እውጭ አቁመሽ ግቢ» አሉኝ መኪና መያዙን ተውኩት::

አባቴ ጠየቀኝ:: ትምህርቴን እስከጨርስ እንደማያስፈልገኝ ነገርኩት:: አሽሟጠጠኝ ልበል?

«የሶሲዮሎጂ ትምህርት ክፍል ዩኒፎርሙ ድህነት ነው?» አለኝ:: ቀይ ፊቱ ላይ ያነበብኩት ደግ ነገር አልነበረም:: «ድህነትን ኤክስፒሪያንስ ማድረግ (በልምድ ለማወቅ መሞከር) የሚያስቅ ነገር ነው:: የሌብነትን የተዋረደ ስሜት ለማወቅ ለመስረቅ የመሞከር አይነት የሚያስቅ» ምንም ሳያናግረኝ ስድስት ኪሎ አድርሶኝ ተመለሰ::

ከሰዓት በኋላ ዶክተር ማርቆስ እንደዘበት በአጠገቤ እያለፉ «አባትሽ አብዷል፤ በልጁ ጉዳይ ከገባህ እገድልሃለሁ ይላል» አሉኝ:: ፍርሃት ያነበብኩባቸው መሰለኝ:: ከመደንገጤና ከማሰቤ በፊት ሳቄ ነው የመጣው:: ከልክ በላይ ቁመት የተሰጠው ሰው ከልክ በላይ ሲፈራ አስቂኝ ይሆናል::

ዛሬ ግን ቁርጥ ጉዳይ መጥቷል:: ለዚህ ነው ሐሳብ ተጫጭኖኝ ካልጋዬ የተነሣሁት:: አሁን ከአባቴ ጋር ልጋፈጥ የተዘጋጀሁበት ጉዳይ በአባቴ እንዴት እንደሚስተናገድ አውቃለሁ:: ግራ እጁ ላይ እንደሚያስረው ወርቅማ ሰዓት ይግማል፤ ደረቱ ላይ እንዳለው ሁብል እሳት ይደፍቃል... ከዚያ ከታገሥኝ ያሸሚጥጠኛል፤ ካልቻለም ኃይለ ቃል ይናገረኛል:: ይመታኛል ብዬ ግን አልጠረጥርም::

ከአባቴ ጋር ያጋፈጡኝ ዶክተር አይነ-ህሊናዬ ላይ ተጋረጡ:: የመመረቂያ ጥናቴን ለመስራት በአማካሪነት የተመደቡልኝ ዕለት ቢሮአቸው ሄድኩ:: በሩ ላይ «የሶሲዮሎጂና የሶሻል አትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል ኃላፊ» የሚል ተለጥፏል:: ስገባ ያኮረፉ መስለው «በምን ላይ ለመስራት አሰብሽ?» አሉኝ::

ለምን እንደመጣሁ ሳይጠይቁኝ ማወቃቸው አንድ ነገር እንድጠረጥር አደረገኝ:: ነገር-ሸተተኝ «በልመና ላይ» አልኳቸው፤ ለወራት ያንገዋለልኩት ርዕስ ነበር::

«ኦ» ብለው ወደሚያነቡት መጽሐፍ አቀረቀሩ:: አማክሩኝ ሳይሆን አዝለው አድርሱኝ ያልኳቸው ያህል ተሰማኝ:: ፊቴ ላይ የጋረጡትን የተወጠረ የእናት ላይ አብረቅራቂ ቆዳ ተንሸራታች ማሽን እንደተገጠመለት ሁሉ ወደኋላ ጎትተው አኩራፊ ፊታቸውን ደቀኑብኝ:: ዶክተር ማርቆስ ቢሮአቸው እንግዳ ሲመጣ እንደሰስታም ሰው ለምን እንደሚያኮርፉ አይገባኝም:: በሩ ሲንኳኳ «ይግቡ» አይሉም:: ሲከፈት ቀና አይሉም:: ቀና ሲሉም «ቁጭ በሉ» አይሉም:: እንዲያውም እንግዳውን የሚያውቁትም አይመስሉም:: በተደናገረ ፊት እያዩት «ምን ነበር?» ይላሉ::

ዶክተር ክፍል ውስጥ እንደዚያ አይደሉም:: ሲያስተምሩ የሁሉም የቅርብ ጓደኛ ይሆናሉ:: በስም ለይተው ይጣራሉ:: ይሄን የለመደ ተማሪ ቢሯቸው ሲመጣ በሚያየው ፊት ይምታታበታል:: ሲፈትኑ ደግሞ ሌላ ናቸው:: ሁሉንም ያለአመሳሶ የሚጠሉ ይመስላሉ::





«ኦ» አሉ ደገሙና «ልመና ላይ ብዙ ተሰራበት፤ ሌላ አስቢ» አቀረቀሩ:: ልስን እናታቸውን ጋረጡብኝ::

ልወጣ ስል «ቆይ» የሚል ልምዝግዝግ ቃል ጀርባዬ ላይ ልክክ አለብኝ:: ሸገገኝ:: ስዞር ቆመው ነበር:: ቁጭ ሲሉ አጭር ይመስላሉ:: ሲቆሙ ባለሶስት ቅልጥም ቁመት ይሆናሉ:: በሰዎች መካከል ሲሄዱ ለሳቸው ብቻ በተዘጋጀ ድልዳል ላይ የሚራመዱ ይመስላሉ::

ቁመቴ ከማይደርስበት መንደርደሪያ ላይ አገላብጠው አንድ መጽሐፍ አነሱ:: ለጥቂት ጊዜ ያጠኑት መሰሉና አቀበሉኝ «ውሰት ነው፤ ይሄንን አንብበሽ ስትጨርሺ በጥናትሽ ላይ እናወራለን» አሉኝ::

መጽሐፍ ሲያውሱ ሁኔታቸው የአራጣ አበዳሪ ነው::

መጽሐፉ «ዘ ሲቲ ኦፍ ጆይ» በሚል ደማቅ ዓይኖቹ አሻቅቦ የሚያየኝ መሰለኝ:: ለሶስት ቀንና ሌሊት አንብቤ ጨረስኩት:: ርዕሱ ብርሃናማ ነው፣ ይዘቱ ግን የድህነት «እኝኝ ብላ» ነው:: «የፈንጠዚያ ከተማ» ሲባል የትኛውም አንባቢ መልካም ነገር ለማንበብ ይዘጋጃል:: ምናልባትም ምርጫው ያልሆነውን ርዕስ ጉዳይ እንዲያነብ ይገደድ ይሆናል:: ደራሲው ህንድ ካልካታ ከተማ ውስጥ «የፈንጠዝያ ከተማ» የምትሰኝ መንደር ውስጥ የሚኖሩ ድሆች አነጋግሮ የፃፈው ነው:: ድሆቹ በዚህ ላይ የሥጋ ደዌ ተጠቂም ናቸው:: በተጨማሪ ፈረስ ተክተው ጋሪ የሚጎትቱ የጋሪ ፈረሶች::

መጽሐፉ ጭንቅላቴን ከፉኛ ተጫጫነው:: ጥቂት የህንድ ሀብታሞች ወደፊት ለመስፈንጠር ሲሉ በመቅዘፊያዎቻቸው ወደኋላ ያሽቀነጠሩዋቸው ድሆች፣ በሽተኞች፣ መፃተኞች... የተትረፈረፈ ሕይወቴን በጥርጣሬ እንድመረምር ያደረገኝ መጽሐፍ ነበር:: ቀጥ ያለውን የሸሮ ሜዳ መንገድ ሳይ እነዚህ የካልካታ ሰዎች በፈራረሰ አካላቸው ጋሪያቸውን እየጎተቱ ተሳፋሪዎቻቸውን ጭነው የሚመጡ መሰለኝ:: ሰው እንዴት ከከብት አረከሶ ከብት ይተካል?

ዶክተር ማርቆስ ቢሮ እንደገባሁ «ምን ነበር?» አሉኝ እንግዳ ፊት እያሳዩኝ:: የተጫጫነኝ ሐሳብ ስላለቀቀኝ ዶክተር ዕድሜ ላይ ሮጭ የደረስኩበት ይመስል አኩያነት ተሰማኝ:: እንደወትሮው ባልተሸቆጠቆጠ ስሜት ያለግብዣ ተቀምጩ መጽሐፉን ጠረጴዛው ላይ አኖርኩላቸው::

ዶክተር እኔና መጽሐፋን እያፈራረቁ ባኮረፈ ፊት ካዩን በኋላ «አቋረጥሽው?» አሉኝ:: ፊቴ አልተፈታም፤ ዝምታዬ ከማስገረም አልፎ ሳያስፈራቸው አልቀረም:: «ቆዳ መልስ ነበር ያዋስኩሽ» አሉኝ ደገሙና በቀልድ መልክ:: ይሄ የአባቴ ባህሪይ ነበር:: እኔ ሳመር ማጣጣቅ::

«ጨርሼዋለሁ»

«እንዴት አገኘሽው?»

«የመጨረሻ ጉልበቱን አንጠፍጥፎ የጨረሰ የጋማ-ሰው ተስፋ በቆረጠ ባለቤቱ ሲጨፈጨፍ አይተው ያውቃሉ? ያ ስሜት ተሰማኝ» አልኳቸው:: ምን ማለቴ ይሆን?

አንዲት የነካቻቸውን ቃል ሲደጋግሙ ቆዩ «የጋማ-ሰው --- የጋማ-ሰው ... የጋማ-ሰው...» ለረዥም ደቂቃ በአኩያነት ዝም ተባባልን:: እኔ በበኩሌ ለውጫዊ ስሜት ተገዢነቴ ተቋርጦ ነበር:: እንዲህ በማለት ከውስጤ አናጠቡኝ::

«አንድ ጥሩ ሥራ እንስራ:: በዚህ መጽሐፍ ስሜት:: የመመረቂያ ጽሁፍሽ የሚያተኩረው አባትሽ ሰሞኑን በገዛው የድሆች መንደር ላይ ነው:: እዚህ አራት ኪሎ አካባቢ:: ሰምተሽ የለም? ታውቂው የለም? ስለነሱ ድሆች ዕጣ ፈንታ ታጠኚያለሽ:: ምን አይነት ሕይወት እንዳላቸው፣ ገቢያቸው ምን እንደሆን፣ የሚዘወሩበት አካባቢ ለኑሮዋቸው ያለው ተጽዕኖ፣ ሌላውንም ነገር::» መስማማቴን ሳያረጋግጡ «የጥናትሽን አጭር መግለጫ በዚህ ሳምንት ይዘሽልኝ ነይ:: አባትሽ-ጋ ብዙ መረጃዎችን ታገኛለሽ:: ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት እዚያው መንደሩ ውስጥ ቤት ተከራይተሽ ለመኖር ብትወስኚ ጥሩ ነው:: ጥሩ ነው ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ ነው::»

በግርምት አስተዋልኳቸው:: ከዚህ ቀደም ዶክተር አባቴን የፈሩ የመሰለኝ ተሳስቼ ኖሯል:: ሀሳባቸው መሰጠኝ፣ በዓላማው ማሎ የጋመ፣ እሣት ውስጥ የሚጣድ ተራ-ወታደር ሆንኩ:: እንደ ካልካታዎቹ የጋማ-ሰዎች ሰረገላዬን ለመጎተት የፈራረሰ የመሰለኝን ገላዬን አነቃቃሁ::

ሐሳብ እንደተጫንኩ ጎበደድ ብዬ ከአልጋ ወረድኩ:: እንዲህ ያለ ስሜት አጥንቴን ለምጦ፣ ሥጋዬን ደፈጣጥጦ ከዕድሜ መግፋት ጋር መሣ-ለመሣ ያቆመኛል::





አዛውንቶች ስመለከት የኔ ስሜት የተጫጫናቸው እንጂ ዘለግ ያለ ዕድሜ የኖሩ አልመስልሽ ይለኛል::

አባቴን ከማግኘቴ በፊት ሁኔታዬን ለመሰለል ወደ ቋሚ መስታወት ጠጋ አልኩ:: የመስታወቱ ከፈፍ እንደ ፀደቀች ነፍስ በወርቃማ ብርሃን ከበበኝ:: ሮዝ አበባ ያካፋበት ቢጫ የሌሊት ልብሴ እንደምቀኛ ወዳጅ የፊቴ መጠውለግ ያስደሰተው ይመስላል:: የጉንጮቼ ወደ ውስጥ ማፈግፈግና የፊቴ አጥንት በጥቂቱ ማፍጠጥ የአባቴ የሕይወት ዱካ አንድ ትውልድ አልፎ መታተሙን የሚያረጋግጥ ይመስለኛል:: ከዚያ በተረፈ መልኬ የአባቴ ተቃራኒ ነው:: የአባቴ ዓይኖች የከልስ ናቸው:: የእኔ ግን ጥቁር፣ የአባቴ ፀጉር የከልስ ነው:: የእኔ ግን ወደ አበሻነት ያዘነበለ መካከለኛ ነው:: በተለይ በእዚህ ሰዓት ዓይኖቼን ስመለከታቸው ከአባቴ ይልቅ ከፋት የሚነበብባቸው ይመስለኝና ስሜቴን ለማርገብ እሞክራለሁ::

የመኝታ ክፍሌ በር ተንኳኳ:: ማን እንደሆነ አውቃለሁ:: ቦቹ ነበር:: ቦቹ ውሻዬ:: ፀጉራም ድንክ የሳሎን ውሻ፣ መኝታ ቤቴን የሚደፍረው እሱ ነው:: አባቴ እንኳን ግድ ካልሆነበት በራፋን አይረግጥም:: መምጣት ግድ ከሆነበት በእጅ ይቆረቁርና ወደ ሳሎን ይመለሳል:: ቦቹ ግን ይሉኝታ በማያውቅ አፈጣጠሩ መጥቶ በሬን በጭራው ማወናወን ያንኳኳል:: ብዙ ጊዜ አባቴ ሳሎን ቆሞ እኔን የሚጠብቅ ከሆነ ነው ቦቹ በሬን የሚደበድበው::

ቦቹ በፀጉር የተሞላ ፊቱ ላይ ጭልጭጭ የሚሉ ጥቋቁር የብርሃን ኩሬዎች አሉት:: ጆሮው ወገቡን እንደተመታ አባብ ይላወሳል እንጂ አይቆምም:: የሚገርመኝ ስሜት የማጥናት ችሎታው ነው:: ከተቆጣሁ ጣቢያው የተሳሳተ ሬዲዮ ዓይነት ድምጽ እያሰማ ፊቱን ይሸፍናል:: ስሜቴ ከተነቃቃና ጨዋታ ካማረኝ ደግሞ ይቀበጣል:: እግሬን፣ እጄንና ያገኘውን አካሌን ሁሉ ከማመም ይልቅ ሳቅ በሚያመጣ አኳኋን ይነከሰኛል:: ይሮጣል - ይደበቃል - ድንገት ብቅ ይላል:: እንስሳ መሆን ያማረኝ ቀንና አባቴ ቤት ውስጥ በሌለበት ሰዓት ሳሎን ውስጥ ከቦቹ ጋር እሯሯጣለሁ፣ እደበቃለሁ፣ ድንገት ብቅ እልበታለሁ...

አንድ ቀን ውሻውን ባወጣሁለት ስም ስጠራው ሰምቶ «ለምንድነው የደሃ ሥም ያወጣሽለት?» አለኝ «ውሻሽ 'ኮ ያንቺ በሆነ ሰዓት ካለሽ ሀብት ላይ በተወሰነ

መብት አለው፡፡ ስለዚህ ከአንድ መጠነኛ ገቢ ካለው ሰው የተሻለ ሀብት ውሻሽን አውርሰሽዋል፡፡ እንዲህ አይነት አኗኗር ያለውን ውሻ ደረጃውን ዝቅ አድርጎ የደሃ ሥም መስጠት ተገቢ አይመስለኝም፡፡ ቦቹ አንድ የደሃ ደቦል ስም ነው፡፡ ሳይበላ የወፈረ ሀጻን አይነት»

የእኔስ ስም? የድሃ አይደለምን? እርጥባን-ለምን አልከኝ?... አልተከራከርኩም፡፡ አምሰለሰልኩ'ጂ «የደሃ ሥም፣ የሀብታም ሥም» የእነዚህ የሁለቱ መደቦች መንፈስ እስከምን እንደሚወርድ በመገረም አሰብኩ፡፡ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ እሸት የነበረውን ስሚን አስፍቃ ሸዊት በሚል አስተካከለች፡፡ ይሄው የድሀነት መንፈስ ጭንቅላቷ ላይ መጥፎ ስሜት ስላሳደረባት እንደሆነ አውቄአለሁ፡፡

ሸዊት አንዳንዴ (እንደውም ብዙ ጊዜ) የውሻዬን ባህርይ እኔ ላይ ታሳያለች፡፡ ፊቴን አጥንታ ነው የምትንቀሳቀሰው፡፡ ስወድ ቲፎዞዬ ናት፡፡ ስጠላ ቲፎዞዬ ናት፡፡ ዝም ስልም ቲፎዞዬ ናት፡፡ አማራጭ በማጣቴ አስከትላታለሁ እንጂ ጓደኝነቷ ተሟልቶ አይሰማኝም፡፡ እንደውሻዬ ጭልጭል የሚሉ ጥቋቁር የብርሃን ኩሬ ዓይኖቿን እያርገበገበችና አማርኛዋና ከእንግሊዘኛ ዘይቤ ጋር እያዳቀለች....

«የሆነ ነገር መውሰድ አለብኝ» ትላለች «መብላት ሲያምራት» እኔ፣ ማለት የፈለገችውን ትክክለኛ አማርኛ በውስጤ እደግምላታለሁ፡፡ «እንዴት እርቦኛል መሰለሽ? የሚበላ ባገኝሁ?» የእኔና የእሷ ግንኙነት ወደ አማርኛ ክፍለ ጊዜነት ያደላል መሰል?

አሁንም በተንደፋደፈ እኳኋን በር ተንኳኳ፡፡ አባቴ ሳሎን አለ ማለት ነው፡፡ ፈጠን ብዬ ፀሩን ስከፍት፡፡ ቦቹ ቀና ብሎ እያየኝ እግሬ ሥር ተልወሰወሰ፡፡ ከቁመቱ ጅርባው ይሰፋል፤ ፀጉሩ አከርካሪ አጥንቱን ተከትሎ ይከፈልና ወደ ሆዱ ይረዝማል፡፡ እሱን እያየ ለመደሰት ሲል እግዚአብሔር የፈጠረው መሰለኝ፡፡

መኝታ ቤቴ ያለበት የግራ ፎቅ እያቆለቆለ ወደ ሳሎን የሚመራ ደረጃ አለው፡፡ ከፎቁ ደረጃ ሥር አንድ ሰፋ ያለ ከፍል አለ፡፡ ይሄን ክፍል አባቴ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ይዘት ሰጥቶት አስር ወንበሮች አስገብቶለታል፡፡ ቤታችንን መኖሪያ ሳይሆን ትንሽ መስሪያ ቤት ከሚያስመስሉት ክፍሎች ዋነኛው ይሄ ነው፡፡ በተለይ እኔ በሴሚስተሮች መካከል ከትምህርት እረፍት ሲኖረኝ አባቴ ሆን ብሎ የሥራ





ስብሰባዎቹን ሁሉ እዚህ ክፍል ውስጥ ያደርጋል፡፡ አምስት ወይም ስድስት ያህል ሥራ አስኪያጆቹን ከየድርጅቶቹ አስጠርቶ አጠቃላይ ስብሰባ ይመራል፡፡ አዳራሹ ውስጥ እነዚህ የተማሩ ሰዎች አባቴ እየተጫናቸው ሀሳብ ሲያቀርቡ እንድመለከት ስብሰባው ላይ ይጋብዘኛል፡፡ ሥራውንና ሀብቱን ወደእኔ ለማሸጋገር ሲያበቃኝ እንደሆነ አላጣውም፡፡

ቤታችን የብር ቤተ-መቅደስ ነው፡፡ ዘወትር የሀብት አምልኮ ይካሄድበታል፡፡ ገንዘብ እንደ ከባድ ጦር መሳሪያ ከዚች ቤት ወደ ከተማው ሲተኮስ ብዙ ጊዜ እመለከታለሁ፡፡

ቤታችን ካሉት ከፍሎች ውስጥ ወደአሻን ክፍል የመዘዋወር መብት ያለን እኔና ቦቹ ብቻ ነን፡፡ አባቴ እኔ መኝታ ክፍል መግባት አይችልምና እዚህ ውስጥ አይመደብም፡፡ እኔና ቦቹ ግን እንኳኩተን ሲከፈትልን አባቴ መኝታ ክፍልም እንገባለን፡፡ አባቴ ቢሮና ንባብ ክፍሉ አድርጎ ያበጀው ሌላ ክፍል ደግሞ የአዳራሹን ትይዩ ኮሪደር ይዞ ይገኛል፡፡ አንድ ትልቅ የመጽሐፍ መደርደሪያና ኮምፒዩተር አለበት፡፡ ወደዚህ ክፍል ከሄድኩ አባቴ ተሽከርካሪ ወንበሩን ይለቅልኝና በኔትወርክ የተያያዙትን ሁሉንም ድርጅቶቹን ባህርይና መጠን ሊያስረዳኝ ይሞክራል፡፡ ብዙ ስለተደጋገመብኝ «ጥናት አለብኝ» እለዋለሁ፡፡

«ያን ያህል ዕውቀትሽን ትምህርት ላይ ብቻ አትጣጂ» ይለኛል፡፡ «ዘላቂ ዕውቀት ያለው እዚህ ነው» የኮምፒዩተሩን መስታወት በጣቶቹ ግንባር ይተመትማል፡፡

የሌሊት ልብሴን ከፍ አድርጌ ወደሳሎን የሚያመራውን ደረጃ መውረድ ጀመርኩ፡፡ ቦቹ ስንዝር በማይሞሉ እግሮቹ ደረጃውን ከእኔ እኩል ለመውረድ ይፍጨረጨራል፡፡ ሌላ ቀን አሳዝኖኝ አቅፈው ነበር፡፡ ዛሬ ዝም አልኩት፡፡ በተስፋ መቁረጥ እግሮቹን ከአቅሙ ጋር እያማጠነ መውረድ ጀመረ፡፡ ቅር እያለኝ ቀደምኩት፡፡ ለእሱ የሚመቸው ከደረጃው ትይዩ ባለው የጓሮ መተላለፊያ አድርጎ ከቢሮው በስተቀኝ ወደ ሳሎኑ መምጣት ነበር፡፡ እኔን ላለመነጠል ብሎ ወደኋላ መቅረቱ ቆጨ፡፡

ሳሎን ስደርስ አባቴ እኔን በመጠበቅ እኳኋን ቆሞ አገኘሁት፡፡ ቡላማ ሙሉ ልብስ አድርጓል፡፡ ከነጭ ሸሚዙ በስተጀርባ ሐብሉ ከእንቅልፏ አሁን እንደነቃች ሁሉ ትስለመለማለች፡፡ ትከ ብሎ በመቋጨም አይነት ኳለባበሴን ቃኘው፡፡

«ዛሬ ትምህርት የለኝም የመመረቂያ ጽሁፌን አጭር መግለጫ እየሰራሁ ነው›› አልኩት::

ከረጅሙ ኮርኒስ ላይ እንደ ሸንጣም እባብ ወደታች በማስገግ ጌጠኛ ባርኔጣ የደፋው አምፑል እንደበራ ነበር:: የአባቴ ዘለግ ያለ ቁመት ከመሬት ተተኩሶ አማካኝ ቦታ ላይ ከአምፑሉ ጋር የገጠመ ይመስላል:: «የመመረቂያ ጽሁፍ?» ብሎ በመገረም ሲያየኝ ቆየ:: «ይገርማል፣ ጊዜው እንዴት ይበርራል» ሲል እንደአይነሥውር ሳንቲም ቁልፎቹን እጁ ላይ ያንቀረቅብ ጀመር::

በዚህ መካከል ቦቹ ደረሰ:: ሰላማዊ ንግግር ስናደርግ የሚያሳየውን ባህርይ ቀና ብሎ እኔንና አባቴን በፍርቅርቅ ያይ ጀመር:: ብዙም ሳልቸገር የምፈልገው ርዕሰ ጉዳይ በመነሳቱ እየተቻኮልኩ «እ - እንደውም አንዳንድ የምትረዳኝ ጉዳይ አለ:: ጥናቱ የሚያተኩረው በተፈናቃይ ሰዎች ዕጣ-ፋንታ ላይ ነው...» ተቻኩሎ ትኩስ ድንች እንደጎረሰ ሰው ቃላቶቹ አፌን ያነፈሩት መሰለኝ::

«የምን ተፈናቃይ? የምን ዕጣ-ፋንታ?...» እጁ ላይ የሚያንገዋልለውን የመኪና ቁልፍ ለጥቂት ጊዜ አቋረጠ::

«መኖሪያቸው ለኢንቨስትምንት እየተፈለገ ወደሌላ አካባቢ ስለሚዛወሩት...» አባቴ ከቆመበት ወደኋላ ያፈገፈገ መሰለኝ:: የአንገት ሐብሉ የአምፑሉን ብርሃን ስላገኘች ከመስለምለሚ ነቅታ መንተግተጓን ቀጠለች «አሁን ያሉበትን ሁኔታ፣ አካባቢያቸው ለኑሯቸው ያለውን አስተዋጽዎና የሚዘዋወሩበት...» አባቴ አቋረጠኝ::

«መጥፎ ቦታን ለማቅናት ስትወሰኒ የምታካሂጂው ምንጣሮ ሙጃ ላይ ብቻ ሳይሆን አካባቢውን መጥፎ ያደረጉ ሰዎችም ላይ ያርፋል:: ይሄ ምኑ አዲስ ሆኖ ነው እንደ አንድ ማህበራዊ ምስቅልቅሎሽ የሚቆጠረው?» አባቴ እንደተናደደ የገባው ቦቹ የአሮጌ በር ድምጽ እያሰማ መቅበጥበጥ ጀመረ::

አባቴን በእኩያ አይነ ውሃ አየሁት:: በእንዲህ ያለ ወቅት የሚያሳየኝን የወትሮው ስሜቱን የማጤን ባህርይ አልተመለከትኩበትም:: ቀጠለ...

«የየትኛውም ሀገር ሀብት የተከማቸው በጥቂት ሙጃዎችና ድሆች መጨፍጨፍ ነው:: ሁለቱም የማያፈሩበትን ለም-መሬት ሙጥኝ ይላሉ:: ያ-መሬት ደግሞ ተፈላጊ ነውና የሁለቱም ሕይወት አደጋ ላይ ይወድቃል:: መሬትን ለሙጃና





ለድሃ መተው ጠፍ ሀገር ያስታቅፋል» አባቴ ሀብትና ደሃ ሲነሳ ለምን እንዲህ የሰሉ ቃላትን እንደሚተፋ አይገባኝም:: በከርከሩ ተላዝቤ ካልቀረብኩ ምን ሊወስን እንደሚችል ሁሉ አላውቅምና ማፈግፈግ ተመኘሁ:: ግን ስሜቴ የፍላጎቴ ተገዢ አልሆን አለኝ:-

«ሙጃና ደሃን ምን አንድ አደረገው?» አልኩት

ለጥያቄዬ ከመመለስ ይልቅ ትክ ብሎ አስተዋለኝ:: ትኩታው እንደብረት የማይታጠፍ ነበር:: ጭንቅላቴን ከሰነገኝ ሀሳብ ድንገት ተነጥቄ የአባቴን እኩያነት ያጣሁ ሆኖ ተሰማኝ «ሙጃ... ደሃ አታፈላስፊኝ! ያም ሆነ ይህ ከእኔ ጋር ግንኙነት ያላቸው ድሆች ሙጃዎች ጋ ሄደሽ ምንም እንድትሰሪ አልፈቅድም:: ከተማው በድሆች ምንጣሮ ላይ ተግቷል:: ወደ አንዱ ጠጋ ብለሽ ጥናትሽን ስሪ...» ብሎ ፊቱን ወደ በሩ መለሰ:: ወደፊት ከላካቸው ቃላቶች ውስጥ ጥቂቶቹ ወደኋላ ቀሩ «ምን አይነት ዕዳ...» ቦቹ አባቴን ሸኝቶ ወደኔ ተመለሰ::

# ሁለት

ከሌሊት ልብስ ያልተሻለ የስፖርት ቱታ ለብሼ ከመኝታ ቤቴ ወጣሁ:: በቶ በሩን ስለዘጋሁበት እዚያው ሆኖ አለቀሰ:: ሰራተኞቹ ይከፈቱለት ብዬ የሳሎኑን ደረጃ ትቼ በጓሮ በር ብቅ አልኩ:: ፊት ለፊት ያለው የመኪና ማቆሚያ ውስጥ አንድ መኪና ብቻ ቆማለች::

ግቢያችን አጥሩ ረዥም ከመሆኑ የተነሳ ፀሐይ እንኳን እንደልቧ አትገባበትም:: በውስጥ በኩል የአጥሩን ግንብ እየታከከ ከፍ ያለ የድንጋይ መደብ ተበጅቷል:: መደቡ ሆዱ በለም አፈር ተሞልቶ አበቦች ተተክለውበታል:: የፈዘዙት ሽማግሌ ዘበኛ እነዚህ አበቦች ላይ ተደፍተው ሲነቅሱ ይውላሉ:: እሳቸውን የምቆጣጠር እንዳይመስላቸው ብዬ አበቦቹን ቀረብ ብዬ አይቼ አላውቅም:: እኔን ሲያዩ በመሽቆጥቆጥ ኮፍያቸውን ከጭንቅላታቸው ላይ እንደ በግ ቆዳ ይገፋሉ:: አንገቴን ቀንጠስ አድርጌ እልፋለሁ::

ለእኚህ ሽማግሌና ለአባቴ ሾፌሮች ስል ግቢያችንን ጠልቼዋለሁ:: ሾፌሮቹ በፈረቃቸው ሰዓት ከፈዘዙት ሽማግሌ ጋር በሹክሹክታ ያወራሉ:: እኔ ወደ ግቢው ከወጣሁ መኮንኑን እንዳየ ተራ ወታደር በመሽቆጥቆጥ ስሜት ሰላምታ ያቀርባሉ:: ይጨንቀኛል:: ወሬያቸውን አቁመው የጎረሰውን ሳይውጥ እንደተያዘ ወጥቤት አፋቸው እንደተከፈተ ከንፈሮቻቸውን ገጥመው ወደ ሌላ አቅጣጫ ያያሉ:: አባቴ ቤት ውስጥ ከዋለ እነዚህ ሰዎች እንዲህ እንደተሳቀቁ ይውላሉ:: ስለዚህ ወደግቢው ለመውጣት ይከብደኛል::

አባቴ እነዚህን ሰዎች ከምንም እንደማይቆጥራቸው አውቃለሁ:: ቀሰስተኛው ዘበኛ አባቴን ሲያዩት ቀስ ብለው የጨርቅ ኮፍያቸውን ከጭንቅላታቸው ላይ ይገሽልጣሉ:: ከዚያም እጃቸውን እስከ ኮፍያቸው ደረታቸው ላይ አመሳቅለው ወገባቸው እስኪታጠፍ አጎንብሰው ሰላምታ ይሰጣሉ:: አባቴ ልብ አይላቸውም:: ወሬ ከያዘም ለአመል እንኳ አያደናቅፍም:: ሾፌሮቹም ከዚህ የተሻለ ትኩረት ከአባቴ አያገኙም:: እንዲያውም አንዳንዴ አባቴ መኪና ውስጥ እኔ ኖሬ ድንገት የቤተሰብ ጉዳይ ከተነሣ መንገድ ላይ ያስቆምና ሾፌሩን አስወርዶ እሱ እየነዳ እንሄዳለን::





በእንዲህ ያለ ጉዳይ አባቴን ወቅሼ አላውቅም:: ያለበት የሥራ ጫና ለጥቃቅን ጉዳይና ለጥቃቅን ሰዎች ትኩረት ለመስጠት የሚያበቃው እንዳልሆነ አውቃለሁ:: እሱም አዘውትሮ «ወደፊት የዚችን አገር ዕጣ-ፈንታ ከሚወስኑት ጥቂት ሰዎች ውስጥ አንዱ እሆናለሁ:: ቀጥሎ አንቺ አልጋ ወራሼ»ይላል::

ከግቢያችን ወደ አሎምፒያ መብራት የሚያወጣውን ቀጭን ኮሮኮንች መንገድ ተያያዝኩት:: ይሄ መንገድ ምቾት አይሰጠኝም:: ጭር ያለና በብዙ መኖሪያ ቤቶች ቅርጫ የገባ ነው:: ጭር-ጭር....

ዶክተር ማርቆስን ቢሮአቸው አገኘኋቸው:: ለልማዳቸው ያህል ባኮረፈ ስሜት «ምን ነበር?» ካሉ በኋላ «አባትሽ አብዷል:: አሁን ደውሎልኝ ነበር:: የጨካኝ ሀብታም መግለጫም አደረገልኝ:: 'ሆዱን ለመሙላት የሚንጠራወዝ ሰው ያው እንስሳ ነው፣ እንስሳ ደግሞ ለመዝገብ የሚበቃ ምንም ታሪክ የለውም' ይላል:: ይኸውልሽ ሀብት ወደ በሽታ ሲለወጥ እንዲህ ነው::»

ዶክተር አባቴን እኔ ፊት ሲናገሩት መልስ ሳይኖረኝ የተቃውሞ ስሜት ብቻ አበቀልኩ:: ሥጋነት ትርጉሙ ይሄ ይሆን? ምክንያቱም አባቴ ደጋግሞ ዶክተርን «ያ-መጋኛ ደህና ነው?» ሲለኝ ይሄ ስሜት አልተሰማኝም ነበር:: ዛሬ ግን...

«ይቅርታ» አሉ ዶክተር ስሜቴን በማጤን:: ወዲያውም ሁኔታቸውን ለመሸሸግ በራ-ጭንቅላታቸውን ጋረጡብኝና «ታዲያ ምን ትያለሽ? አባትሽ እሱ ቦታ ላይ ጥናት እንዲሰራ አይፈልግም»

ዶክተር ላይ ባሳደርኩት ስሜት ፀፀት ተሰማኝ «እኔ እንጃ... ሌላ አማራጭ አለ?» ቀና ብለው በትዝብት ተመለከቱኝ «ማለቴ...» ከጦር ሜዳ የሸሸ ወታደር የሚያድርበት ስሜት ተሰማኝ::

«ማለትሽ ገብቶኛል!» የተቆጡ መሰለኝ «ከእንግዲህ አንቺ ልጅ አይደለሽም:: አባትሽም ሆነ እኔ አሳማኝ ምክንያት ሲኖረን ነው ልትቀበይን የሚገባው:: የአገራቱ ግንባር ቀደም ዩኒቨርስቲ በክብር የሚያስቀምጠው ጥናት ነው የምትሰሪው::» ቆሙ በእቅድ ያልተሰራው የግብር ይውጣ ቁመናቸው ከፍሉን ሞላ:: «ይሄ የሚያሳየው የጥናቱና ሀሳብ ቀደም ሲል አለመቀበልሽን ነው:: ሌል አስበሽ ነይ፤ ጨርሰናል»

ከክፍሉ አልወጣሁም:: እንደውም ተቀመጥኩ:: እውነቱን ለመናገር የጥናቱን ሀሳብ ወድጄዋለሁ:: የሚያስከፍለው መስዋዕት የአባቴን ልብ ማሻከር ሲሆን ግን ፈራሁ::

«የጨረስን መሰለኝ» አሉ ዶክተር በኩርፊያ:: ትልቅ ሰው፣ ያውም ግዙፍ አካል ያለው ሰው እንደትንሽ ልጅ ማስገደዱ በኩርፊያ ሲሆን ያስቃል:: ዶክተር «ተዉት» ብዬ ብወጣ እንኳን እንደማይለቁኝ አውቃለሁ:: በምን እንዳወቅሁ አላውቅም:: ብቻ አውቃለሁ:: ነገር ግን ከማፈንገጤ በኩርፊያ ልምጭ ሊያግዱኝ ይሞክራሉ::

«እሰራዋለሁ» አልኩ::

«እርግጠኛ አትመስይኝም ለሌሎች ልጆች እሰጠዋለሁ»

«እሰራዋለሁ፣ ጥሩ ሀሳብ ነው:: በጉዳዩ ላይ ከዚህ ቀደም አልተሰራበትም:: ወደፊትም አሳሳቢ ከመሆኑ አንፃር ብሰራው እወዳለሁ:: ይኸው የጥናቱ አጭር መግለጫ» ብዬ ቱታ ኪሴ ውስጥ አጣጥፌ ያስቀመጥኩትን ሦስት ቅጠል ወረቀት ሰጠኋቸው:: ሁኔታዬ ልክ አለመሆኑ የተሰማኝ ካደረኩት በኋላ ነበር:: በኮምፒውተር ሳይፃፍ ረቂቁን ሥነ-ሥርዓት በጎደለው መልክ መስጠቴ በንቀት ሊተረጎም ይችላል ብዬ ደነገጥኩ:: ዶክተር ኩርፊያቸውን ለመገላገል እያማጡ ረቂቁን አነበቡና የትንፋሽ ድንገተኛ ደራሽ ለቀቁ::

«የሚስተካከለውን ከነገሩኝ በኋላ በአግባቡ አፅፌ አመጣዋለሁ» አልኳቸው::

«እ-» አሉና «ጥሩ ነው ግን ሰሻል እስታተስ-አይሚን የኑሮ መግለጫ በመቶኛ ቢጨመርበት ጥሩ ነው:: በተለይ ምግብ፣ መጠጥና አልባስ ከየት እንደሚያገኙ፣ ለምን ያህል ጊዜ? የሚለውን ከነመጠየቂያው አካቺበት»

«እሺ» ብዬ ረቂቁን ተቀብዬ ልወጣ ስል:-

«ቆይ» የሚል በቀፋፊ ስሜት የታጀበ ቃል ጆርባዬን ታከከኝ:: ዞር አልኩ፤ ዶክተር ከመሳቢያቸው ውስጥ አንዳች ነገር እየፈለጉ ነበር:: ግንጣይ ጋዜጣ ይዘው ወጡ «ይኸውልሽ፣ ይኼ አሁን ጥናት የምታደርጊበት ፈራሽ መንደር ላይ የተፃፈ ነው::





መነሻ ይሆንሻል:: የፃፈው ሰው ስለመንደሩ በደንብ ያውቃል:: በብዕር ስም የተፃፈ ይመስለኛል:: ፀሐፊውን ብታገኚውማ...»

የአዲስ-ዘመን ጋዜጣ አንድ ግንጣይ ነበር:: ጽሁፉ የገጹን ግማሽ ሸፍኖታል::

«ፀሐፊው ሙቼም 'ቦርን ሶሲዮሎጂስት' ነው:: የማህበራዊ ጥናት ዝንባሌ ያለው:: ሶሲዮሎጂ የተማረ እንኳ አይመስለኝም:: ከቻልሽ አግኚው:: እንደምንም ብለሽ አግኚው» ጉጉታቸው ወደ ጉጉትነት የቀየታቸው መሰለኝ:: የግንባር ቆዳቸው ወደ ላይ ተሸማቆ ዓይኖቻቸው ፈጠዋል::

ከቢሮ እንደወጣሁ መናፈሻው ውስጥ ቁጭ ብዬ ማንበብ ቀጠልኩ:: በልቤ ሽዊት እንዳትመጣ ፀለይኩ:: የውሻዬን የመሰለውን ዓይኖቿን እያቁለጨለጨች እንደውሻዬ እንዳታስቸግረኝ:: ካልባሰብኝ በስተቀር መጥፎ ፊት ማሳየት አልፈልግም:: ሙቼም እዚህ ግቢ ከእርሷ ውጭ የሚደፍረኝ የለም:: የጽሁፉ ጭብጥ በአራት ኪሎ ፈራሽ መንደር ላይ ያተኮረ ነበር:: የፀሐፊው መነሻ የመንደሩ መፍረስ የሚያስከትለውን ሰብዓዊ ቀውስ ማሳየት ቢሆንም ጽሁፉ እንደበተሃ ጠጅ ከመድረቅ ይልቅ ወደ ልስላሴ ያደላ ነበር:: «እንዴት ምሬት በመለሳለስ ይገለፃል?» ስል አሰብኩ:: ፀሐፊው የተለሳለሰው በመላዘብ እንዳልሆነ ያስታውቃል:: ምክንያቱም የአራት ኪሎ መፍረስ የሚያስከትለው ሰብአዊ ቀውስ ከፍተኛ ነው የሚል አቋም ቢኖረውም በሌላ አንፃር መንደሩ መፍረስ የለበትም አይልም:: ታዲያ ምን ይሁን? ለሚሉትም ፀሐፊው አማራጭ አይሰጥም:: ብቻ አጠገብ ሆኖ በሚያወጋ ሰው ሁናቴ ሀሳቡን ያወርዳል:: ለጥናቱ ይጠቅመኛል ያልኩት የጽሁፉ መግቢያ ላይ አተኩሬ ዳግም ማንበብ ቀጠልኩ::

*የአራት ኪሎና የአካባቢዋ መሥራች አፄ ምኒልክ እንደሆኑ ይታወቃል:: የላይኛውን ቤተ-መንግሥት መኖሪያቸው አድርገው እንደጨረሱ አካባቢውን ለሥራየ-ቤቶቻቸው አከፋፈሉ:: ይህም ቦታ አሁን የትምህርት ሚኒስቴር ህንፃ ካለበት አንስቶ ቁልቁል በፊት በር አድርጎ እስከ ፍልውሃ ራስጌ ድረስ ነበር::*

*የዚያን ወቅት የቦታ ስያሜዎች ይህንኑ እውነታ የሚጠቁሙ ናቸው::*

*ለምሳሌ:- «ሠፈ ሠፈር (የአፄ ምኒልክ የበቅሎ ኮርቻ የሚሰፉና ጋሻ በቆዳ የሚለጉሙ) 'ልምጭ ያዥ ሠፈር' (በግብር ወቅት ልምጭ ይዘው በር ላይ የሚያስተናብሩ) 'ቋሚ ሠፈር' (የቤተ-መንግሥቱ አንጨት ፈላጮች) 'ለጓሚ ሠፈር' (በቅሎ ጠባቂዎችና ጫኞች)... ወዘተ*

ንባቡን አቋርጬ ስለፀሐፊው ማሰብ ቀጠልኩ:: በማብራሪያው ከዕድሜው ገፋ ያለ የቤተ-ክህነት ሰው ነበር አይነህሊናዬ ላይ የተጋረጠብኝ:: ኩታውን አጣፍቶ የድሮ ወግ እየሰለቀ የጠላውን ገፈት በምላሱ የሚያስፈነጥር:: ወደ ንባቡ ተመለስኩ::

*አራት ኪሎ በቦታ አመሠራረቷ እንዲህ ስትጠናቀቅ ደመቅመቅ ማለቷን ደግሞ ባንዳንድ ምክንያቶች ልታገኘው ችላለች:: ከአፄ ምኒልክ አስተዳደር ጋር ቅርበት ያለው ሥራ የነበራቸው አንዳንድ የዘመኑ ሰዎች ከሥራዪ ቤቶቹ ላይ ቦታውን በብልሃትም፣ በጉልበትም እያስለቀቁ መያዝ ጀመሩ:: በእጃቸው ያስገቡትን ቦታ ለግል መኖሪያቸው ብቻ ሳይሆን የአካባቢውን ለንግድ አመቺነት ለመረጡ ሰዎችም አከራዩት:: መሸታ ቤቶችም በዚሁ ሳቢያ ተስፋፉ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አራት ኪሎ ደመቅመቅ ያለችና ሁካታ የማይጠፋባት ሆነች::*

እራሴን ፀሎቱ እንደተሰማለት አማኝ ቆጠርኩት:: ለምሰራው ጥናት የአካባቢውን አዛውንቶች የማነጋገር ዕዳ በዚህ ጽሁፍ ተቃልሎልኝ ነበር:: ጽሁፉ ስለ አካባቢው ሥረ መሰረት የሚያስፈልገኝን ሁሉ አካቶ አገኘሁ:: አራት ኪሎ እንድትፈርስ በሁለት ያለፉ መንግሥታት ዕቅድ መያዙንና አለመሳካቱን፣ አሁን ግን «እንጃ!» በሚል ተስፋ ቆራጭ ስሜት ፀሐፊው ይቀጥላል::

*መኖሪያችን ዕድሜዋ የማጠሩ ጉዳይ እርግጥ እንደሆነ ይወራል:: አሁን ነዋሪዎቿን እያስጨነቀን ያለው «እንዴት? መቼ?» የሚሉት ሁለት ጥያቄዎች ብቻ ናቸው:: ምኞታችንም «እሟሟቴን አሳምርልኝ» ከማለት የተሻለ ተስፋ ያለው አይደለም::*

አባቴ ሙጃና ደሃን አንድ አድርጎ በሁብት ለመጨፍጨፍ የተዘጋጀበት ዕቅድ ስለቱ አብለጨለጨብኝ:: ከአባቴ ስሰማው እንደነብይ በምሳሌ የመናገር ፍላጎቱ ነገሩን ያገዘፈው መስሎኝ ነበር:: ግን ፀሐፊው እያብራራ ሲተነትነው አባቴ የሞት ፍርድ ፈፃሚ ባለካራ ሆኖ ታየኝ:: «እንደሚታወቀው» ብሎ ይቀጥላል ፀሐፊው:-





*«እንደሚታወቀው አራት ኪሎዎች ከአራት ኪሎ የአኗኗር ይትበሃል ተነቅለን ሌላ ቦታ ብንተከል የሚጸድቅ ባህርይ የለንም ብለን እናምናለን:: እንደውም ዕጣ-ፈንታችን ጠውልጎ መጥፋት እንደሆነ ተቀብለነዋል:: ይሄ ስሜት ያደረብን ያለምክንያት አይደለም:: አካባቢ በሰው አስተዳደግ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ልንክደው አይገባም:: የአራት ኪሎ ነዋሪዎች አብዛኛዎቻችን ቋሚ ገቢ የሌለንና ደመቅመቅ ማሊቷን ተማምነን የምናድር ነን:: ምሽት ላይ ቆሎ፣ ማስቲካ፣ ሎተሪ እና የተቀቀለ እንቁላል በያዙ ህፃናት ትወረራለች:: ህልውናቸው ከቤት ውጭ በሆነ ተራ ነገር ላይ የተመሰረተ ቤተሰቦች በጣም ብዙዎች ናቸው:: ወላጆች የወለዷቸው ልጆቻቸውን አቅፎ ለመያዝ እጆቻቸው ሲያጥሩ እንደ ድንጋይ ወፍጮ እያንሸራተቱ ወደ ማህበረሰቡ ቁልቁል ይደባልቋቸዋል:: ማህበረሰቡ ውስጥ ደግሞ ለህፃናት የተመረጠ ነገር ሊገኝ አይችልምና ዕድሜያቸው ያልፈቀደውን ሁሉ ያለተቆጣጣሪ ይቀስማሉ:: ወደ ተግባርም ለማለወጥ ይፈጥናሉ::»*

እንዳይደላም፣ እንዳይቆረቁርም ተደርጎ ተለስልሶ የተዘጋጀው የድንጋይ መቀመጫ ላይ ተደላደልኩ:: እግረ መንገዴንም አካባቢውን ቃኘሁ:: ከዕውቀት ይልቅ ስሜቶቻቸውን ልብ የሚሉ የሚመስሉ አጥኚዎች ተቃራኒ ፆታዎቻቸውን አጠጋግተው መጽሐፍቶች ላይ አፍጠዋል:: እንዲህ ያለ ጥናት ተገቢ መስሎ አይታየኝም:: ጉራ ሳይሆን ለዚህ ብዬ አንድም ወንድ ሳልጠጋ መመረቂያ ዓመቴ ላይ ደርሻለሁ:: ቀልቤን ከንባብ ውጭ ማድረጌ ከድንጋዩ መቀመጫ በላይ እየቆረቆረኝ ዓይኖቼን መለስኩ::

*አራት ኪሎዎችን ከመኖሪያነት ይልቅ ለመዝናኛነትና ለአሸሼ ገዳሜ መምቻነት ተመቻችታ በመፈጠሯ እንደ ድግስ ቤት የጋራ ማዕድ የሠራም ያልሰራም እኩል እጁን ያሾልባታል:: «ከጨፋሪው» የሚንጠባጠበው ብዙ ነው:: በዚህም «የአራት ኪሎ እድባር ጠም አያሳድርም» የሚል ፈሊጥ አለ:: ይህም የአራት ኪሎንና የነዋሪዎቿን ገጽታ የሚያመላከት ይመስለኛል:: እኛ አራት ኪሎን የተጣባን ነዋሪዎች የአኗኗር ይትበሃላችን በአካባቢው ተጽዕኖ ሥር ወድቋልና በመኖሪያ ለውጥ ከሚጸድቀው የአራት ኪሎ «ተከል» ይልቅ የሚጠፋው ያመዝናል የሚል ግምት አለኝ:: የትኛውም ጥሩ አካባቢ፣*

*የትኛውም የተሻለ ሁኔታ ለኛ ሕይወት ፀር ነው፡፡ ለሌላው ሰው ፀር የሚመስለውን የአራት ኪሎ ባህርይ እኛ ተላምደነው ወደ መኖሪያ ግብአትነት ቀይረነዋልና እሱን ስናጣ ይበርደናል፣ ይርበናል፣ ይጠማናል፣ ጤና እናጣለን… እንሞትም አለን፡፡*

አባቴ ለእነዚህ ሰዎች መታረዝ፣ መራብና መጠማት ምክንያት መሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም ለእነሱ ማለቅ፡፡ ጭንቅላቴን ተጭኖ የነገሩ ክብደት ተሰማኝ፡፡ ጥናቴን ከማክናወን ይልቅ አራት ኪሎዎችን የመማለድ ስሜቴ ጠናብኝ፡፡ አባቴን ምን አድርግ እንደምለው በቅጡ አላወኩም፡፡ እኔ ብቻ ሳልሆን የዚህ ጽሁፍ አቅራቢም ምን መደረግ እንዳለበት ያወቀ አይመስልም፡፡ እንዲህ በማለት ያጠናቅቃል፡፡

*«ታዲያ ምን ይደረግ?» ትሉኝ ይሆናል «አራት ኪሎንና አራት ኪሎዎችን ከማፍረስ አለፉን አልልም፡፡ ከእዚህስ «እንጃ!» ማለትን እመርጣለሁ፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር ከወዲሁ መታወቅ አለበት፡፡ አራት ኪሎ ለውበትም ሆነ ለሥነ-ምግባር ትርፍ ስትፈርስ የምንጠፋው እኛ ኪሣራዎቻችሁ መሆናችንን፡፡*

አራት ኪሎዎች ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ሞቱን የተቀበለ ፍርደኛ መስለው ታዩኝ፡፡ አባቴ በነገሩ ውስጥ ተሳተፈም አልተሳተፈም እነዚህ ሰዎችና መኖሪያቸው ከመፍረስ አይድኑም ስል የመጽናኛ ስሜት አበቀልኩ፡፡ ግን ይህ የሚያጽናናኝ አልሆነም፡፡ አባቴ ለመኖር ብቻ የመነኮሱ የሕይወት እመበለቶችን በማንአለብኝነት ለመጨፍጨፍ እጁን አንስቷል፡፡ እኔም የእርሱ ዘር በመሆኔ እንደ ድርጊቱ ተካፋይ የተቆጠርኩ መሰለኝ፡፡ ለሦስት ዓመት ልብ ያላልኩት የዩኒቨርስቲ ውስጥ ባይተዋርነቴ ከዚህ ድርጊት ጋር ተያያዘብኝ፡፡ እዚህ ግቢ ከሸዊት በስተቀር ማንንም ለማነጋገርና ለመቅረብ ጥረት አድርጌ አላውቅም፡፡ የትኛውም ተማሪ እኔን ለመቅረብ ሞክሮ አያውቅም፤ ከአንድ ተማሪ በስተቀር፡፡ እሱ ያቀረበልኝ የፍቅር ጥያቄ ከዚህ ታሪክ ጋር ተያያዥነት የሌለው በመሆኑ ባልፈው ይሻላል፡፡ ነገር ግን ለሦስት ዓመት ያስተናገድኩት ባይተዋርነት ከአሁኑ የአባቴ ድርጊት ጋር ተያይዞ አብከነከነኝ፡፡

«ሸዊትም ትሁን ብቻ አንድ ሰው በመጣ» ስል አሰብኩ፡፡





# ሦስት

ነገሮችን ማሳጠር እንዳለብኝ እየተሰማኝ ነው፡፡ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ላቅ ያለውን ሥፍራ መያዝ ያለባቸው ማስታወሻዎቹ እንደሆኑ እሙን ነው፡፡ ግን ማስታወሻዎቹን ከማቅረቤ አስቀድሞ ያሉት የእኔ ጉዳዮች መጨበጫ ልጓም ታጥቆላቸው ይንፎለፎሉ ጀመር፡፡ ያም ሆነ ይህ ያለፈው ትረካዬን ትቼ መጪውን ለማሳጠር ልሞክር፡፡

ለአንድ ሳምንት ያህል በአባቴና በዶክተር ማርቆስ መካከል የምመላለስ ባዶ የሸማኔ መቂናጥ ሆኜ ነው ያሳለፍኩት፡፡ አባቴ የተለመደ ምሳሌያዊ አነጋገሮቹን ያዥጎደጉዳል፡፡ ከቀን ወደ ቀን ለእኔ ያለው የተመጠነና የተቆጠበ ስሜቱ እየጠፋ በምትኩ እንደ አቋም ተቀናቃኙ ጠንከር ያሉ ቃላቶቹን ይወረውርብኝ ይዟል፡፡ እንደውም አንዳንዴ የያዝኩትን ጥናት ካልተውኩ መአት እንደሚወርድ በነብዩ ኤርምያስ ልሳን ያስፈራራኛል፡፡

ይህን የአባቴን ሁኔታና የእኔን አቋም ዶክተር ማርቆስ ሲሰሙ ከመላጣቸው ጀምሮ ያለው ሾጣጣ ፊታቸው ይበራል፡፡ መሐል አናታቸው ጉብ ያለ ስለሆነ ግንባራቸው ረጅም ይመስላል፡፡ «አባትሽ ወጣት እያለም ደሃ ይጠላ ነበር፡፡ ሀብትን ለሰው ልጅ እንደ አንድ አስፈላጊ አካሉ ይቆጥረዋልና ድሆችን 'በፈቃዳቸው እራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች' እያለ እስከመሳደብ ይደርሳል፡፡ ሳር ቅጠሉ ኮሙኒዝምን በሚያንቆለጳጵስበት በዚያ ዘመን እንኳ ብቻውን አንድ ጎራ ይዞ ይከራከር ነበር» በቦዙ ዓይኖቻቸው ያለፈ ዘመን ለመጥራት ትንቅንቅ ይገጥማሉ፡፡

«ብዙ የኮሙኒስት አፍቃሪ ወጣቶች እሱን ለመግደል ይፈልጉ ነበር፡፡ ንግግሩ አበሻቃጭ ስለሆነ የተቀደሰ ሀሳብሽን መጥፎ ሽታ ሰጥቶ ለውሻ የሚጣል ያደርገዋል፡፡ እኔንማ ማርቆስ ብሎ ጠርቶኝ አያውቅም፡፡ ማርከስ ነው የሚለኝ፡፡ ይሄንን ወደፊት በሰፊው አጫውትሻለሁ፡፡»

ያለፈ ትውልድ የርዕዮተ አለም ንትርክ ውስጥ የገባሁ መሰለኝ፡፡ ያም ሆነ ይህ ይሄን ትተን ወደ ዋናው ጉዳይ እንግባ፡፡ አዲስ-ዘመን ጋዜጣ ላይ ስለአራት ኪሎ የጻፈውን ሰው ለማግኘት እጅግ ጣርኩ፡፡ የአምዱ አዘጋጅ ረድታኝ በመጨረሻ ስልኬን ሰጠችው፡፡ ደወለልኝ፤ ድምጹ ጎርነን ያለ ነበር፡፡

«ባለጉዳይ ነበር መደወል ያለበት» አለኝ:: ስልኩን እንዳላገኘሁና እሱን ፍለጋ አራት ኪሎ ሁለት ጊዜ መሄዴን ነገርኩት::

«ጥሩ፣ ከእንግዲህ ይደውላል ብለሽ እንዳትጠብቂ» አለኝ:: የማያውቃትን ሴት የሚያናግር አይነት ድምጸት የለውም::

«ግዴለም እኔ እደውልሎታለሁ» አልኩት

ተቀጣጠርን፣ ምልክቱ አስገርሞኝ ነበር:: «የነተበ ሱፍ ኮት እለብሳለሁ:: ኮሌታውን አቆማለሁ::» አለኝ::

ከኑሮ ጉብታ ወደ ኑሮ አዘቅት ወርጄ ጥቂት ፍተሻዎችን ላደርግ እንደሆነ ስረዳ ልቤ እንደመደንገጥ አለ:: ሰው ኑሮውን ይመስላል በሚለው ብሂል አምናለሁ:: ባላምንም የሚታየው ይሄው ነው:: በየመንገዱ ለኩበራቸው ደንታ ሳይኖራቸው ካገኙት ጋር እየተናቾፉ የሚጓዙት ብዙውን ጊዜ ዝቅተኛ አኗኗር ውስጥ ያሉ ሰዎች ናቸው:: ካካባቢው የተነጠለ ቁመት ባለው ቀውላላ የኑሮ ማማ ላይ ተንጠልጥዬ መቅረት እንደሌለብኝ ግን አምናለሁ:: እድሉ ደግሞ ይሄ ጥናት ነው:: ዶክተር ማርቆስ እንዳቀዱልኝ ቤት ተከራይቼ መካከላቸው መኖር ግን የማይታሰብ ነው:: ምናልባት እጅግ መቅረብ ሳይኖርብኝ አይቀርም:: ይሄም ቢሆን ያስፈራል:: አራት ኪሎን ካንዴም ሁለት ጊዜ ሰልዬዋለሁ:: ያየኋቸው ሰዎች ሁሉ የሚያስቀርብ ፊት የላቸውም:: የኑሮ ጣጣቸው የሥጋ ምርጊታቸውን ጦዳድሶት በተመልካቹ ላይ ስጋት ያሳድራል:: ተስፋ-መቁረጥ፣ ጭካኔ፣ እምነት አልባነት፣ ወንጀለኝነት... ግን እነዚህ ሁሉ ለምን ድሆች ላይ ይነበባሉ? ችግሩ ከተመልካቹ ይሆን?...

የቀጠረኝን ሰው ለማግኘት ስጓዝ ብዙ መጥፎ ሁኔታዎችን እያብሰለሰልኩ ነበር:: ሰውየው ከጽሁፉ አንጻር ከታየ አመዛዛኝና ትሁት፣ አዋቂም ይመስላል:: ግን ተስፋ የቆረጠ:: ለጊዜው ሸዊት ትዝ አለችኝ:: ባስከትላት ኖሮ የሚለው ሀሳቤ መልሶ እኔኑ በጥገኛነት ስሜት ተነኮሰኝ:: መጠንቀቅ ይኖርብኛል:: የናቅኩ፣ የተጸየፍኩ፣ የጠላሁ ላለመምሰል መጠንቀቅ ይኖርብኛል:: መፍራት ግን በፍፁም!!

ቀጠሮ ቦታ ቀድሞኝ የተገኘው እሱ ነበር:: በቁመ ጭስ የጠጣ የወይራ እንጨት ይመስላል:: አንዳች ጭጋግ መሰል ነገር እሱ ላይ ብቻ የሚያንዣብብ ሆኖ ታየኝ:: አንቱታ የሚገባው ዕድሜ ላይ እንዳልሆነ ያስታውቃል:: ጠይም ነው፣ ጎራዳም





ሰልካካም ብሎ ለመደምደም ግራ ያጋባል:: ቀምቀም ሪዙ ከመንገጭላው ግርጌ ያለው ጢሙ ብን ብሎ ያለቀ ነው:: ዓይኖቹ የአንባቢ አለያም የሰካራም ወይንም የሁለቱም አይነት ናቸው:: ግንባሩን ነጥለው ሲመለከቱት ተኮፋትሮ የአዛውንት ይመስላል:: ፀጉሩን በእጭሩ ቢስተካከልም በወጉ አልተያዘም:: እውነትም የነተበ ኮት ለብሶ ኮሌታውን ቀና አድርጎታል:: የኮሌታው ገበር የብርድ ልብስ አይነት ጭገር አውጥቷል:: ለምልክት ኮሌታውን የገለበጠው ቢሆንም ስንገናኝ አስታውሶ አልመለሰውም::

የተቀጣጠርነው ጆሊ ባር አካባቢ ነበር:: ምንም ሳያናግረኝ ወደታች ይዞኝ ወረደ:: ፓርላማ አካባቢ ያለው የትራፊክ መብራት ጋ ስንደርስ ወደቀኝ ታጠፍን:: ይሄ ሰው የሚያስከትለውን ሰው ፍላጎትና ስሌት ሳይረዳ ወዳቀደው አካባቢ መጓዙን አልወደድኩለትም:: ቢያንስ ወዴት እንደምንሄድ መናገር ነበረበት ስል አሰብኩ:: ቅሬታዬን ግን ወዲያው ቀጥቼ ተከተልኩት::

በሥጋ ቤቶቹ መሃል ለመሃል እየተጓዝን ነው:: ሥጋ ቤቶቹ ብርሃን የተሞሉ የህፃናት ራስ የሚመስሉ አምፖሎቻቸውን ያንተገትጋሉ:: ሥጋዎቹ ያንፀባርቃሉ፤ አንዳንድ ተልከስካሽ ውሾችና ህፃናት ውር ውር እያሉ እግር ሥር ይገባሉ:: ፌስታል የያዙ አዛውንትና ጎረምሶች ተኮልኩለው ወደ ሥጋ ቤቶቹ ያፈጣሉ:: የነሱ ፊታውራሪ የሚመስል አንድ ጎልማሳ ነጠል ብሎ ቆሟል:: በቀኝ እጁ የሱሪውን መታጠቂያ አንቆ ይዟል:: ጆፍ ያለ ጺሙ የሸበት ወረራ እየተካሄደበት ነው:: አንድ እግሩን እየጎተተ ወደ ሥጋቤቶቹ ይበልጥ ቀረበ:: ሲራመድ ግራ እግሩን እንደግንድ እየጎተተ ቀኝ እግሩን አስቀድሞ ነው:: የእግሩ ዳና «ሸጠጥ-ጓ» ይላል::

«ዘወር በል!» አለ ባለልኳንዳው::

«እራስህ ዘወር በል! ከነሥጋ ቤትህ» አለ ሱሪውን ከፍ ከፍ እያደረገ:: «አላግባብ ምግብ አከማችተሃል፤ አከፋፍል!»

እምባጓሮ ሊነሳ መሰለኝ፣ ፈራሁ:: አብሮኝ ወዳለው ሰው ጠጋ አልኩ:: ቁመቴ ከጆሮው ጋር ተነፃፃሪ ነው::

«ፈራሽ? አይዞሽ» አለኝ

ድምፁ በስልክ ከሰማሁት በላይ የጎረነነ ነው::

ወዲያው ፊታውራሪው የኔብጤ ወደኛ አቅጣጫ መጣ:: ፈራሁ:: ግንዛቤ የማይነበብበት ፈገግታ እያሳየ «ኮምሬድ!» አለ አብሮኝ ወዳለው ሰው አትኩሮ

«ኮምሬድ፣ ዕውቀቴን ወደ ገንዘብ መለወጥ እፈልጋለሁ» አለ::

አብሮኝ ያለው ፍርሃቴን ስለተረዳ ወደሌላኛው ጎኑ እያሸጋገረኝ እሱም «ኮምሬድ ዕውቀት መሸመቻ ገንዘብ የለም» አለው::

ሲቀርብ ያኮፈኮፈ ፊት አለው:: ከሩቅ ልስን ጥቁር የሚመስለው መልኩ ከቅርብ ሲመለከቱት የእድፍ ምርጊት መሆኑ ያስታውቃል:: ሱሪውን ሰብስቦ የያዘበት እጁ ከእንብርቱ ጋር የተሰፋ ይመስላል:: «ኮምሬድ ምንም የለህም?»

«ምንም» አለው

«ፈላጊ ማጣቴ ነው'ጂ ዕውቀቴ ዋጋ አለው:: በርካሽ ለማፍሰስ እገደዳለሁ፣ በአንድ ጣሳ ጠላም ቢሆን...»

«እሱም ሲኖር ነው ኮምሬድ! አታስቸግር» አለው

በተሰፋ መቁረጥ እንዳጎበደደ ቀኝ እግሩን ተጭኖ ቆመ::

«እብድ አይደለም» አለኝ «ነገሮችን በደንብ ያውቃል:: ፖለቲከኛ ነበር:: ቤተ-መንግሥቱ ውስጥ ብዙ አመት ታስሮ እንደተለቀቀ እዚሁ አካባቢ ቀረ:: ከየት እንደመጣ፣ ማን እንደሆን የሚያውቅ የለም:: ጥሩ የማርክሲዝም ኢኮኖሚ እውቀት አለው:: አንድ ጊዜ የገረመኝን ጥያቄ አቀረብኩለት:: ለምን ሱሪህን በገመድ አታስርም? አልኩት:: ከአስራ አምስት አመት በላይ አወቀዋለሁ:: ሱሪውን በእጁ ይዞ ነው የኖረው:: ምን አለኝ መሰለሽ? 'ሱሪዬን በገመድ አስሬ እጄ ምን ይስራ? ለመለመን ግራ እጄ ይበቃል... ኮምሬድ' ብዙ ነገር አሰብኩ»

ትንሽ እንዳቆለቆልን ብዙም ሳንርቅ አንድ የቀበሌ መዝናኛ ውስጥ ይዞኝ ገባ:: አስፈሪ ፊቶች የድራፍት ብርጭቆ እያንፀባረቀባቸው ወደወርቅማ ቀለም የተለወጡበት ቦታ ነበር:: ለሱ ድራፍት ለኔ ለስላስ አዘዘልኝ:: ድራፍት ቢያዝልኝም አልጠጣም ነበር:: ሳይጠይቀኝ ለስላሳ ሲያዝልኝ ከዕድሜዬ በታች የቆጠረኝ መሰለኝ:: ቢሆንም ምንም አይነት ቅሬታ ፊቴ ላይ መነበብ እንደሌለበት እራሴን አስታወስኩ::





«ተማሪ፣ ያውም መመረቂያ ወረቀቱን የሚሰራ ቢራ አያስፈልገውም ብዬ ነው» አለኝ ሳልጠይቀው:: ቀና ብዬ አየሁት አፍንጫው ብቻውን ቨርኒሽ እንደተቀባ እንጨት ያብረቀርቃል «ስምሽን ከስልክሽ ጋር ሳልጽፈው ቀርቼ ጠፋኝ» አለኝ::

«እርጥባን» አልኩት

«የእኔ ሙሉጌታ ነው::» ጥቂት ቆየና «ምን አይነት ሥም ነው? እርጥባን... እርጥባን... እርጥባን...» የቀረበለትን ድራፍት አንዴ አጋመሰው:: አረፋው ሳይሰክን ስለጠጣው አፉ ዳርቻና ጢሙ ላይ የበረዶ ብናኝ መሰለ::

«አባቴ ነው ያወጣልኝ:: ስጠይቀው እናትሽ ለምኖት አንቺን ተረጠበችኝ ይላል:: ማግባት አይፈልግም ነበር:: እናቴ ሳያገባት ልትወልድ ተስማማች:: እኔን ወልዳኝ ሞተች» የራሴን ታሪክ አሳጥሬ ሳወራው የማላውቀውን ያህል ሆዴን በላኝ:: እናቴ እንዴት የምታሳዝን ምስኪን ኖራለች? ስል አሰብኩ:: አባቴስ? አባቴ እዚህ ላይ ጨቋኝ ሆኖ ነው የሚታየኝ:: እናቴን በሁቡቱ ሳይጨቁናት አይቀርም:: ቆንጆ ግን ደሃ ሆና ነው ሁሌም የምትታየኝ:: ደሰስ ካለ ቤት ውስጥ ተሸቀርቅራ የምትወጣ ሴት:: ችግሯ አባቴ ያቀረበላትን አማራጭ እንድትቀበል አስገድዷታል:: አለበለዚያ እንዴት ያለጋብቻ ለመውለድ ትስማማለች? በዚህ ሀሳብ መቀጠል አልፈልግም ሁሌም::

በግራ እጁ መዳፍ አፉን ሞዠቀና እንደ ድመት ምላስ በቀላ አውራ ጣቱ ብናኝ ጢሙን አስተካከለ:: ለሌለ ጢም መጨነቁ ገረመኝ:: እንዲሁም አውራ ጣቱ ብቻ መቅላቷ:: «እኔ መመረቂያ ጽሁፍ አቅርብ ብባል ባንቺ፣ በእናትሽና በአባትሽ ላይ ጥናት አካሂድ ነበር:: የሚገርም ስም፣ የሚገርም አባት፣ የምትገርም እናት» አለና ያጋመሰውን ድራፍት አጠናቀቀ:: የአይኑ ቅላት ከንባብ ይልቅ ወደ መጠጥ እንደሚያደላ የተገነዘብኩ መሰለኝ:: ጣቱቹን አስጩኾ ሁለተኛ ድራፍት አዘዘ::

ለስላሳዬን ቀመስኩ:: «የሚገርም ስም፣ የሚገርም አባት፣ የምትገርም እናት» እውነቱን ነው:: የጠላሁት ሐሳብ ዳግም እንዳይጠልፈኝ ተፍጨረጨርኩ:: በኑሮ የተጎሳቆሉ ሰዎችን ሳይ እናቴን ጠንቅቀው የሚያውቋት ያህል ይሰማኛል:: እናቴ ደሃ ነበረች:: ያለጥርጥር ደሃ ነበረች:: ግን ለምን አባቴ አይነግረኝም? ለምን ስጠይቀው ይቆጣል? የሙሉጌታ ንግግር አቋረጠኝ፣ ደስ አለኝ::

«ምንድነው የምታጠኚው?» ሲል ጠየቀኝ::

«ሶሲዮሎጂ-የሕብረተሰብ ጥናት ነው»

የማዳነቅ ፉጨት አሰማና «ከሕብረተሰብ ጥናት ጋር የተያያዙ መጽሐፎች ለእኔ ብርቅ ንባብ እየሆኑ ነው። ሕብረተሰብ ጥናትን ከሥነ-ልቡና አንፃር የሚያቀርቡ ፀሐፊዎች አሉ። አንዳንዶቹ ፀሐፊዎች ደግሞ ከዝግመተ ለውጥ አንፃር ያያሉ» በደንብ ለማውራት ይመስላል ተቁነጠነጠ «ውመንስ ኢቮሉሽንን አንብበሻል?» ሲል ጠየቀና መልሴን ሳይጠብቅ ቀጠለ።

«ውመንስ ኢቮሉሽንን የፃፈችው ኤቭሊን ሪድ ናት። ጥቂት ኋላ ቀር ማህበረሰቦችን እያጠናች ወደኋላ ተሽቀንጥራ የጥንቱን የሰው ልጅ የአኗኗር ሥርዓት ታሳይሻለች። ግሩም ነው። የጥንቱ እማዊ ሥርዓት እንዲያዳግን አድርጋ ነው የፃፈችው። ሴቶች ሕብረተሰብን ሲመሩ ሰላም ነው፣ ፍትህም አለ። ሥልጣን ወንዶች እጅ ሲገባ ነው ነገር የተበላሸው። ያኔ ደካማና ጠንካራ ተለየ። ጡንቻ ያለው ብዙ ሚስት፣ ብዙ ሀብት ማሰባሰብ ጀመረ። ክፍፍል ጠፋ። በጋራ መሥራት ተነወረ። ሕብረተሰብ ሕብረተሰብን ለማጥፋት እዋጅ ማስነገር፣ መስፋፋት፣ ባሪያ መፈንገል፣ ብዙ መጥፎ ነገር በወንዶች ተፈጠረ። ሪድ ስለእማዊ ሥርዓት ስታወራሽ ስለኛ ሠፈር የምትነግርሽ ነው የምትመስለው። እኛ መንደር ልጆች የጋራ ናቸው። ይሄንን ነው እዚያ መጽሐፍ ውስጥ የምታገኘው» ከድራፍቱ ቀመስ አድርጎ «ይሄን ነው የምትማሩት?» ሲል ጠየቀኝ

«ነው» አልኩት።

«መማር አይደለም መዝናናት ነው በይኝ»

ጉጉቱ ድፍርስ ዓይኖቹ ላይ ታየ «አሁን ቶፍለር የፃፈውን ማሕበራዊ ጥናት ሳነብ ብድግ ነው ያደረገኝ። «ፊውቸር ሾክ» ይባላል። ይገርማል። ማህበራዊ ለውጥ ላይ ተንተርሶ መጪውን ጊዜ ሲተነትንልሽ ስልጣኔ የሚሉትን ጣጣ ትጠያለሽ። እግዚኦ የማህበራዊ ለውጥ ፍጥነቱ! አሁን ያለነው በአስፈሪ የማህበራዊ ለውጥ ፍጥነት ውስጥ እንደሆነ ያሳምንሻል። ሰው የመሆን ጣዕምሽን እያጣሽ ተንጦዝጡዘሽ እንደምትኖሪ ያሳይሻል። የእሱን መጽሐፍ ሳነብ ነው መንደሬ ገነት ሆና የታየችኝ። ባንቺ ጉዳይ እየገባ በመፈትፈት የሚያበሳጭሽ ጎረቤትሽ ሁሉ ለካ ፍሰሃ ነው። ወደፊት ሕመም አይደለም፣ አለመታየት ነው የሚገድለን። ሁሉም ሀብት ለመሰብሰብ





ይንጦዘጦዛል። ታዲያ ማን-ማንን ልብ ይላል? ሀሜተኛ አታሳጣኝ፣ አሽሟጣጭ አትንሳኝ፣ የእለት እሽሙረኞችን ስጠን ማለት ደግ ነው» አማተበ።

ሳልወድ በግድ አሳቀኝ

«አንቺ ምን አነበብሽ?» ሲል ጠየቀኝ

«እኔ ብዙ የማነበው ልብወለድ ነው» አልኩት

«ልክ ነሽ፣ ትምህርትሽ መዝናኛሽ ሊሆን አይችልም»

«ግን አሁን በቅርብ 'ዘሲቲ ኦፍ ጆይ' የተሰኘ መጽሐፍ አንብቤ ልቤን ነካኝ። ህንድ ውስጥ ካልካታ ከተማ ስለሚኖሩ ድሆች አስከፊ ሕይወት ነው የሚተርከው»

«ዘ ሲቲ ኦፍ ጆይ?» ሲል ጠየቀኝ

«አይገርምም? ርዕሱና ጭብጡ አይሄድም። ድሆቹ የሚኖሩበትን የመከራ መንደር 'የፈንጠዝያ ከተማ' ብለው ነው ስም ያወጡለት። ያንን ይዞ ነው ፀሐፊው «ዘ ሲቲ ኦፍ ጆይ» ያለው

«እሺ?» አለኝ ለመስማት ሁለመናውን ጆሮ አድርጎ።

ይሄን መጽሐፍ አለማንበቡ ደስ አለኝ። መልሼ በደስታዬ አፈርኩ። ምቀኝነት እንዲህ ነው የሚበቅለው ስል አሰብኩ «በጣም የወደድኩት መጽሐፍ ነው፣ ያስጨንቃል። አንድ ሰሞን ተበጥብጬ ነበር። ሰው ጋማ-ከብት ተክቶ ጋሪ ሲጎትት የሚውልበትን ጨካኝ ዓለም ያሳይሃል። በዚህ ላይ ሥጋ ደዌ።» የሱን ያህል የራስ-በራስ ተመስጥኦ አላሳየሁም ነበርና ንግግሬ የጣፈጠልኝም አልመሰለኝ። ሙሉጌታ ግን በኔ ትረካ ይሁን በሌላ ሳይገባኝ በሐዘን ትክዝ እንዳለ ነበር።

«ሰው በሰው ላይ የሚጨክነውን ያህል በእንስሳትና በአራዊት ላይ አይጨክንም» አለኝ። ቀዘዝታው እንደተጫጫነው «አንዲት ባለምግብ ቤት አውቃለሁ፣ ልጅ ያዘሉ ነዳያን በራቸው ላይ ተኮልኩለው ሲጠባበቁ እሳቸው ግን የምግብ ቤታቸውን ትርፍራፊ ለሰፈር ሁሉ ውሾች ይዘው ይመጡ ነበር። አንድ ሰሞን የውሾች ቁጥር ከነዋሪው በላይ ሆኖ እንደነበር አስታውሳለሁ» እኔ ከነገርኩት ጋር ምን እንደሚያያይዘው አልገባኝምና ቀልቡን ያልሳብኩት መሰለኝ፡-

«ሰው የጋማ ከብት ተከቶ አሪፍ አገላለጽ ነው:: የጋማ ከብትኮ አልጠፋም:: ሀንድ ውስጥ አለ:: ግን ሰው በሰው ላይ የሚጨክነውን ያህል በእንስሳት ላይ አይጨክንምና ሰውን በጋማ ከብት ተካው፣ ግሩም»

ግንዛቤውና ትንታኔው አስደነቀኝ፣ መምህሬ ቢሆን ስል አሰብኩ:: ተማሪውን የሚያዳምጥና ያዳመጠውን የሚተነትን መምህር:: ስለመመረቂያ ጽሁፌ ድንገት ጠየቀኝ:: ለማስረከብ አምስት ወር ያህል እንደቀረኝ ስነግረው መጣደፍ እንደማያስፈልግ መከረኝ በአንክሮ መመልከት ያለብኝን ነገሮች ጠቆመኝ:: የአራት ኪሎን አመሻሽ ላይ መሟሟቂቅ፣ የሀገናዮቹን ለሽቀጥ ሽያጭ መራኮት፣ የመጠጥ ፍጆታ፣ የሥጋ ፍጆታ፣ የሽርሙጥናው ገበያ መድራት.... ይሄን በተመስጦ ከጠቋቆመኝ በኋላ አንድ የሚያስገርም ታሪክ አከለልኝ፤ ኢያቱ እንደነገሩት አልደበቀኝም::

«በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ነው» አለና ብናኝ ጢሙን ከድራፍት አመዳይ በቀይ አውራ ጣቱ አጽድቶ «እዚህ ከፓርላማ ጀርባ ያለውን የባለወልድ ደብር ያስተዳድሩ የነበሩት አለቃ ቤተ-መንግሥት ተጠሩ፣ ፓትርያርኩ ከጃንሆይ ጋር በመመካከር ነበር ያስጠሩዋቸው:: እንዲህ አሏቸው:-

«የባለወልድን ደብር ገዳም-ልናደርገው አሰበናል:: ለእርስዎ የኡራኤልን ደብር እንድታስተዳድሩ ልንሰጥዎ ነው:: እርስዎን ማማከሩ ተገቢነት ስላለው ነው የጠራንዎ፣ እና ምን ይላሉ?

«ጥሩ ነዋ፣ አሉ የባለወልድ አስተዳዳሪ ጥሩ፣ መቼም ለኔ እልቅና የኡራኤል ደብር አያንሰኝም:: ይሁንና ግን የባለወልድን ገዳም ማን ብላችሁ ልትጠሩት ነው? መቼም አራት ኪሎ ብሎ ገዳም የለም:: አሏቸው አሉ» አለና ድራፍቱን ቀምሶ «ይኸውልሽ አራት ኪሎ ለእግዚአብሔር የቅድስና ስፍራ የምትመች አይደለችም ይሏታል:: ምናልባት ለሰይጣን» ብሎ ፈገግ አለ::

ሙሉጌታ እንደጽሁፉ ንግግሩም ለዛ አለው:: እንደአዲስ ሰው አይከብድም:: አቀራረቡ እንግዳነትን ወደጎን ገሸሽ ያደረገ ነው:: የበለጠ የገረመኝ ሒሳብ ሊከፍል ሲል ላግደረድረው ቱታ ኪሴ ውስጥ እጄን ስከት «ተሜ ከየት አመጣሽ? አራት ኪሎ ውስጥ ማግደርደር የለም:: ይሄን እኔ ልክፈልና ካለሽ ተጨማሪ እንዘዝ» አለኝ::





ንግግሩ አባቴ በፀጉራም እጁ አንገቴን ሲነካኝ የሚሰማኝን በሰው የመከበብ ስሜት አሳደረብኝ:: ደስ አለኝ::

«ሊብር አትጨነቅ - እዘዝ» አልኩት

«ተሜ፣ የወር አስቤዛሽን እንዳይሆን? ካባትሽ የተላከ» አለኝ:: መግደርደር ሳይሆን ማሳሰብ አይነት ነበር::

«ግዴለም» አልኩት

«በነገራችን ላይ ሽንትሽ ከመጣ ሳትፈሪ ንገሪኝ» አለኝ ግር ተሰኘሁ::

ነፃነቱ ፈር የለቀቀ ወይም የሰከረ መሰለኝ «ብዙ ሴት ጓደኞች ነበሩኝ:: በመጀመሪያ ቀን ትውውቅ ሽንቴ መጣ ላለማለት ተጨንቀው እንደነበር ካለፈ ይነግሩኛል» ሌላ ድራፍት አዘዘ:: ብናኝ ጢሙን በባዕድ አውራጣቱ ለማስተኛት ሞከረ::

የሚበቃውን ያህል ከጠጣ በኋላ ሁሉንም ሂሳብ ለመክፈል ስሞክር እምቢ ብሎ ቸከ:: ያለችውን አራግፎ የእኔን ለስላሳና የራሱን ግማሽ ሂሳብ ዘጋ:: ስንለያይ «የጠጣሁት ቀበሌ ስለሆነ እርካሽ ነው፣ ከተገቢው በላይ የጠጣሁ ቢሆንም እንዳልጎዳሁሽ ተስፋ አለኝ» አለኝ::

ስለእውነት ሆዴ ውስጥ ገባ::

«ኮምሬድ!» እግሩን እየጎተተ መጣ:: «ኮምሬድ!»

«ቻው» ብሎኝ በሥጋ ቤቶቹ ግርጌ ወደ ውስጥ ዘለቀ:: ሁኔታው ግር ያሰኘኝ ቢሆንም አልጠላሁትም:: በተለይ በዚያ ምሽት አራት ኪሎ መካከል ጥሎኝ ሳይሸኘኝ መሄዱ::-የገባበትን ሽንቁር ለጥቂት ጊዜ አየሁት:: ታጥቦ መጠጥ እንዳለ ጋቢ አንዲት ሴት ተከምራ መግቢያው ላይ ተቀምጣለች:: ኮምሬድ እንደማይደርስበት አስቦ ገደድ እንዳለ ቆሚል አልፈራሁትም::

* * *

በሁለተኛው ቀን ግንኙነታችን ሙሉጌታ ላይ የተቀየረ ነገር አላየሁም:: የነተበ ኮቱን ለብሶ ኮሌታውን ቀና እንዳደረገ መጣ:: ጫማዎቹ ማሰሪያቸው ሳይጠብቅ እንደተወሰወሱ ተቋጥረዋል:: የሰነፍ ሰዎች ጫማ እንደዚሁ ነው:: ትምህርት ቤት ውስጥ እንደነዚህ አይነት ውስውስ ማሰሪያዎች ማየት የተለመደ ነው:: ማሰሪያ

ከመፍታት ይልቅ እንደ ስከ ጫማ ወለቅ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ ወደተለመደችው የቀበሌ መዝናኛ ይዞኝ ሄደ፡፡ እንዳኮረፈ ሰው ዝም ብሎኝ እየደጋገመ በዚያች አውራ ጣቱ የደኸየ ጢሙን አስተኛ፡፡

«እዚሁ ነው የተወለድከው?» አልኩት ለንግግር መክፈቻ ያህል፡፡

«እ» ብሎኝ አውራ ጣቱን ብናኝ ጢሙ ላይ አግለበለበ፡፡ እንደ መስተዋት መጥረጊያ የአውራጣቱ ንቅናቄ የመጠን መቆጣጠሪያ ቁልፍ ያለው መሰለኝ፡፡ ለዶፍ ዝናብ የሚያስፈልግ ቁልፍ ላይ ነው - አውራ ጣቱ ስል ከራሴ ጋር ተጫወትኩ፡፡

«እ» አለኝ ደገመና፤ በፊት «እ» እንዳለኝ ረስቷል ማለት ነው ስል አሰብኩ፡፡ ድራፍቱን አንዴ ይጎነጭና አስር ጊዜ ገለባ ጢሙን ያስተኛል «የተወለድኩት እዚሁ ነው፣ ያደግሁትም፡፡ ለአንድ አመት ከስድስት ወር ያህል አራት ኪሎን ተነጥዬ የገጠር መምህር ሆኜ ነበር፡፡ አላስችል አለኝ፡፡ በትውልድ መንደር መለከፍ፣ አራት ኪሎ ውል ይልሻል፡፡ ስትነጠይ አንዳች የቀረብሽ ነገር ያለ ይመስልሻል፡፡ አብሮ አደጎችሽ በፌሽታ ላይ ሆነው ሲሳሳቁ፣ ወጉ ሲደምቅ ይታይሻል፡፡ ስትመጪ ያ-የተለመደ አዚም ነው፡፡ የማያቋርጥ አዚም፡፡ ግን ከዚህ ስትነጠይ አካባቢሽ በፌሽታ ሁካታ ውስጥ ሆኖ አንዳች የማይደገም ነገር ሲያመልጥሽ ይታይሻል» አለና እንደመባነን ብሎ «ኧረ ትፍረስ እኛም ነፃ እንወጣ ይሆናል፡፡ ካልሆነም እናብዳለን ወይም እንሞታለን»

የወየበ ፊቱ ላይ ስሜቱን ለማጥናት ሞከርኩ፡፡ እንደ ገንፎ ሙብያ የእንጨት ማንኪያ አፍንጫው ብቻ እንደወዛች ነው፡፡ ድራፍቱን ደጋግሞ ተጎነጨና መጨላለም የሞከረውን ባሻገር በመስኮት ቃኘ፡፡ የመስኮቱ መስታወት የከፍሉን መብራት ማንፀባረቅ ስለጀመረ አሻግሮ ለማየት አዳጋች ነበር፡፡

«ዛሬ መንደራችንን የገዛው ድርጅት ተወካዮቹን ልኮ ነበር» አለኝ ቅዝዝ ብሎ «እየዞሩ ቅያሪ አካባቢያችን የት ቢሆን እንደምንመርጥ ጠይቀው መዘገቡ፡፡ አይን ምሣ... ወለቴ... ቦሌ ቡልቡላ... ማነው ደግሞ አንዱ? ለኛ ተመሳሳይ ነው፡፡ ግን ምናለ አንድ አካባቢ አድርገውን እንኳን ተላቅሰን ብንቃበር?» የወየበ ፊቱ የወየበ ስሜት ታክሎበት ጭራሹን አቡጀዲ መሰለ፡፡





አባቴ አብዷል ማለት ነው ስል አሰብኩ፡፡ ወይንም ከኔ ጋር እልህ ተጋብቷል፡፡ ትናንት ባሴረ ዓይን እያየኝ «ተይ ብልሽ እንቢ አልሽ አይደል?» አለኝ ዝም አልኩት፡፡

«እየሰማሽኝ ነው?» አለመግባባት ሲነሳ ቦቹ ይቅበጠበጣል፡፡ የእንጨት በር ድምፅ አሰማ፡፡

«አዎ፣ ግን ጥናቱን እስመዝግቤዋለሁ» አልኩት «ካሁን በኋላ ማስቀየር አልችልም»

«ይቅራ! እኔ ዕውቀት እንጂ ዲግሪሽን አልፈልግም፡፡ እኔ ዲግሪ አግኝቼ ምን ተጠቀምኩበት? ያው ቁጭ ብሏል፡፡ ላንቺ የሚጠቅምሽ የተማረ ሰው ሥነ-ልቦና ማዳበርሽ ብቻ ነው፡፡ ኮርሶቹን በሙሉ ትኩረት ሰጥተሽ አጠናቂ፡፡ መመረቂያ ጥናትሽን በሚቀጥለው አመት በሌላ «ታይትል» (ርዕስ) ታሚያለሽ»

ቀና ብዬ አየሁት

እንቢታዬን ከአተያዬ ተረዳ፡፡

እልህ እንዳጋባሁት ከዛሬ እርምጃው አወቅሁ፡፡ ሁኔታውን አፋጥኖ መረጃዎቼን ሊያድፈነፍንብኝ እንደሆነ ገባኝ፡፡ መፍጠን አለብኝ፣ መፍጠን፡፡ በዚህ ውሳኔዬ በሙሉጌታና በተጎራባቾቹ ላይ ያሴርኩ ያህል ተሰማኝ፡፡ ለስላሳዬን ተጎነጨሁና አየሁት፡፡ እሱም ሁኔታዬን ሲያጤነው ኖሯል፡፡ ቀጠለ....

«ጥናትሽን አፋጥኚ፡፡ በዚህ አይነት በቀናት የሚቆጠር ቀን ነው የሚቀርሽ» አለና በረጅሙ ተንፍሶ የበራ እራስ ፀጉር የመሰለ እላቂ ጢሙን ሞዥቆ «የኛ ነገር፣ እንደተሸጠ በሬ እድሜያችን ከገበያ እስከ ቄራ ያለው እርቀት ሆኗል፡፡ ከከተማ አውጥተው እንደወረወሩን እራሳችንን መቀለብ አቅቶን እናልቃለን»

ንግግሩ ውስጥ እራሱን ያካትት እንጂ እውነታው እንደማይመለከተው የሚያውቅ መሰለኝ «ስራብ አብልታችሁኛል?» እንዳለው መሲህ ሙሉጌታም ስለአቅመ ደካሞዎቹ እንደሚብከነከን ሆኖ ተሰማኝ፡፡ «ስጠማ አጠጥታችሁኛልን?» የሚል የሚያስተጋባ መልዕክት ውስጤ ገብቶ ስሜቴን አጣበበው፡፡

የሙሉጌታ ሁኔታ ከጥናቴ ጋ የተያያዙ ጥያቄዎቼን እንዳቀርብለት የሚጋብዝ አልነበረም፡፡ እጅግ ተጨንቋል፡፡ እሆንም አውራ ጣቱ አላረፈችም፡፡ ሲያስብና

ሲጨነቅ አውራ ጣቱ መፍጠን ትጀምራለች ማለት ነው ስል አሰብኩ:: እንደ መጀመሪያው ቀን ሆዱን ከፍቶ መጠጣት አልቻለም:: ሦስት ድራፍት እንደመጣለት የእኔን ለስላሳ ጨምሮ ከፈለና ይዞኝ ወጣ:: ከቀበሌው መዝናኛ ብዙም ሳንርቅ አቁሞኝ ወደ ማዶ እያመለከተ ባለፈው የገባበትን የመንደር ሽንቁር ጠቆመኝ:: ነጭ የተቀባ ቋጥኝ የመሰለች ሴት ተኮፍሳ መግቢያው ላይ ቁጭ ብላለች::

«ያ-መግቢያ መቆሚያ-ጣቢያ ይባላል:: መንደራችን ውስጥ ያሉት ሴተኛ አዳሪዎች ስለሚቆሙበት ነው የሽሙጥ ስሙ የወጣለት:: ከዚያ አንስቶ እስከ አራት ኪሎ ሆቴል ግርጌ ድረስ ፈራሹ መንደር ይመለከተዋል» አለኝና «ከዚህ ጀርባ ያለው ኩታንኩት መንደር ውስጥ ለውስጥ ከመቶ በላይ ቤተሰቦች ይኖሩበታል:: ጦር ሜዳ የተፋጠጠ ጠላት እንኳ ይቺን ያህል ኩርማን መሬት ለማስለቀቅ የዚህን ያህል ሰው አይፈጅም:: ቤተሰቡን ቢያንስ በአምስት አባዥው» አለኝ::

ሙሉጌታ የተቅበጠበጠ መሰለኝ:: እጅግ ተረብሿል:: እኔን በማሰብ እንጂ ከዚህ በላይ የሚረበሽ ይመስላል:: የሚያደርገው በማጣት አትኩሮ ተመለከተኝ:: ፊቴ ላይ ምን እንዳነበበ እንጃ ያዘነልኝ መሰለኝ:: የሚያደርገው ሲያጣ...

«ኮምሬድ!» የሚል ጥሪ ሰማን::

ሙሉጌታ «ጎሽ ና!» አለው:: ኮምሬድ ቆሎ በጥብቆው እንዳሳቀፉት ልጅ ሱሪውን ጨምድዶ አንድ እግሩን እየጎተተ መጣ:: የግራ እጁ ትንሿና ተከታይ ጣቶቹ ታጥፈው ሳንቲም ይዘዋል:: በሦስቱ ጣቶቹ ጨበጠን::

«ዕውቀቴን ወደ ገንዘብ ለመለወጥ ነው የመጣሁት»

«ጥሩ፣ ምን አዲስ ዕውቀት አለህ?» እያለ ወደ መንገድ ዳር ይዞት ወጣ:: ከስሜቱ መገላገያ ሰበብ አድርጎ ተቀብሎታል ስል አሰብኩ::

«ስለ ሰው» አለ ኮምሬድ

«ጥሩ፣ ሰው ምንድነው?»

«ሰውማ ሸቀጥ ነው:: ተነፃፃሪ ልውውጥ ይኖረዋል:: ከዱር ያለከልካይ ሄደህ ከምትለቅመው አቃቅማ ይልቅ የጓሮ ጎመን ዋጋ አለው::» በድባባማ ብርሃን ውስጥ እድፍ የተለደፈበትን ፊቱን አየሁት:: ንግግሩ በስሜት የታጀበ አይደለም «የጓሮ ጎመን ከዱር ፍሬ በላይ ዋጋ የሚኖረው ጊዜና ጉልበትህን ስላፈሰስክበት ነው:: ሰውም





እንደዚያ ነው:: እንደ ዱር ፍሬ፣ ወፍ እንደዘራው የሚበቅል፣ ምንም ዕውቀት ያልፈሰሰበት የሰው አቃቅማ አለ:: ከዚህ ሰው ይልቅ የኔታ ጋር የተማረው እንደ ጓሮ ጎመን በጥቂት ዕውቀት ላይ የተመሰረተ ጉልበትና ጊዜ የፈሰሰበት ሰው የተሻለ ዋጋ አለው:: እነዚህ ሁለት ሰዎች በንጽጽሮሽ ልውውጥ ገበያ ቢወጡ የአምስት ቁና አቃቅማ ዋጋ አንድ ነጠላ ጎመን ብቻ ሊሆን ይችላል:: እንዲያ ነው፣ ሰው ሸቀጣዊ ባህርይ አለው» ያብሰለሰለ መስሎ ቀጠለ...

«እኔ በራሴ ላይ ካፈሰስኩት ዕውቀት ውጭ ነጥለህ ከተመለከትከኝ አርባ አምስት ኪሎ ሥጋና አጥንት ብቻ ነኝ:: በቃ! ሊያውም ስለማይበላ ጠያቂ የሌለው፣ ለመግማትና ለመበስበስ የተዘጋጀ 45 ኪሎ ሥጋና አጥንት»

ኮምሬድ እራሱን የሚያስበው ከሃያ አመት በፊት ባለው ኪሎ ነው ስል አሰብኩ::

ሙሉጌታ 'አዳምጪው' እንደማለት ጎሸም አድርጎ አነቃኝ:: እሱ ላይ ያደረውን መጥፎ ስሜት እኔ ላይ አጋብቶ እንዳይለየኝ የኮምሬድን ዲስኩር የዘየደበት ሆኖ ተሰማኝ:: ኮምሬድ ቀጥሏል...

«ማርክስ እራሱ ምንድነው? ለሰላሳና ለአርባ አመት አድፍጦ መንፈሱን ባያበረታ፣ በራሱ ላይ ዕውቀት ባያከማች ኖሮስ? ጢም ያለው በግ ነበር የሚሆነው:: በቃ! እንደወረደ የተፈጥሮ ሰው በሁለት እግሩ የሚሄድ ያልታረደ በሬ ነው...»

«እዚህ ሰፈር የተከማቹ፣ ምንም አይነት ዕውቀት ያልታከለባቸው አስር ሰዎች የአንድ ደብተራ ዋጋ የላቸውም:: የዚህ ሠፈር ሰዎች መሪ ከመሆን የሰለጠነ አህያ መንዳት ያዋጣል:: ሰውነታችሁ ለምን ክብር አጣ? ጉልበታችሁ ስለምን ዋጋ ተነፈገው? እንደምንስ እንደአይጥ ጎሬ ውስጥ ለመኖር ተገደዳችሁ? የረጋ ዕውቀት ስላልተከማቸባችሁ አይደለም? ታዲያ እንዴት ልጆቻችሁን ዕውቀት ትነፍጋላችሁ? ልጆቻችሁ የረጋ ዕውቀት ካልተከማቸባቸው በግ ለመሆን በሂደት ላይ ያሉ ግልገሎች አይደሉም?»

ግንድ እግሩን እየጎተተ እንደፎካሪ ተቁነጠነጠ...

«ሀብት በግለሰቦች እጅ ተከማችቷል:: ብዙሃኑ በእጦት ላይ ነው:: ስለፍትሃዊው የአለም ሀብት ክፍፍል ጩኸት ስትላቸው አይገባቸውም:: ያልተከማቸው

ዕውቀት ከየት ይምጣ? በአንድ ነጠላ ጎመን እንደሚለወጠው አምስት ቁና አቃቅማ ብዛት እንጂ የረጋ ዕውቀት የለባቸውም:: ስለዚህ ዋጋ አጡ፤ የሚያስፈራው ብሶታቸው ወደ አመጽ እንዳያመራ ነው:: ያኔ አምስት መቶ ኪሎ ግራም የሚመዝን በሬ ዳግም ደነበረ ማለት ነው:: ኮምሬድ አይበቃም?» ሲል ጠየቀ::

«ይበቃል» አለውና ወደኔ ዞሮ «አንድ ብር ስጪው» አለኝ

እጄን ወደ ቱታ ኪሴ ውስጥ አስገባሁ::

«ተው'ጂ ኮምሬድ!» አለ «ልክ አይደለም! ፈላጊ ማጣቴ ነው'ጂ ዕውቀቴ ዋጋ አለው:: ካለ ሁለት ብር አልቀበልም::» እያለ በድን እግሩን በንጭንጭ ጎተተ::

ሙሉጌታ ለጥቂት ጊዜ ሲመለከተው ቆየና በግንባሩ «ምን ታደርጊዋለሽ» እንደማለት ምልክት አሳየኝ:: ሁለት ብር አውጥቼ ሰጠሁት::

«ዕውቀቴን ያሻሻጥክልኝ ለእሷ ነው ማለት ነው?» ሲል ጠየቀው::

«አዎ» አለው ሙሉጌታ::

«ዕውቀትና ገንዘብ ፈላጊዎችን ማገናኘት በራሱ ዋጋ አለው:: አስራ አምስት ከመቶ እንዲከፈለው ህግ ያዝዛል::» ብሎ በግራ እጅ ሁለት ጣቶች እጥፋት ውስጥ የቆነጠጣቸውን ሳንቲሞች ወደ ሙሉጌታ ዘረጋለት::

«ግዴለም» አለው::

«በዝባዥ አደረከኝ - ኮምሬድ ተቀበል» አለው::

ተቀበለ:: አንድ እግሩን እያንሻጠጠ በሌላው እየደበደበ ሱሪውን ከፍ አድርጎ ወደ ሥጋ ቤቶቹ ብርሃን አመራ:: ሲሄድ ንፋስ ከግራ እግሩ ላይ ነቅሎ ወደፊት የወረወረው ይመስላል:: ሙሉጌታ በቅሬታ ፈገግ እንዳለ ሳንቲሞቹን ወደ እኔ አሸጋገረ:: ሁለት ባለአስርና አንድ ባለአምስት ሳንቲሞች ነበሩ:: ለረዥም ጊዜ ስለተያዙ ሞቀዋል::





# አራት

እንዳሰብኩት እግሬን አልቆጠብኩም:: በዚያው ሰሞን ተመልሼ ወደ አራት ኪሎ አመራሁ:: እንደተሳቀቅሁት ሳይሆን ሙሉጌታ ጥሩ ፊት አሳየኝ:: ጠይም ብርሃን የፈነጠቀበት:: ቀድሞ ስንገናኝ ያንገበገበበት የነበረው ጥቁር ጭጋግ ዛሬ አልታይሽ አለኝ:: ሁኔታው ደስ አሰኘኝ:: ማስቸገሬ ያሳደረብኝን ስሜት አቀጠነልኝ::

ከከርኔ ከፍ ብሎ ያዘኝ:: መዳፉ ያቃጥላል:: የቀበሌው መዝናኛ በጊዜ የሞላ ቢሆንም መስኮቱ አጠገብ ያለው ቦታ አልተያዘም ነበር:: ተቀመጥን::

«ጥናትሽ እንዴት ነው የሚሰራው -- እኔ የማግዝሽ ምንድነው?» ነገርኩት:: «ጥሩ ነው» ብሎ የድመት ፀጉር የመሰለ ብናኝ ፂሙን በአውራ ጣቱ እያስተኛ ተካከዘ «ጥሩ ነው» አለ ደገመና:: ካለፈው ረባሽ ስሜት ፈጽሞ የተላቀቀ አይመስልም:: የአካባቢ ምዝገባው መንደሩ የምትፈርስበትን ጊዜ ካሰበው እጅግ አቅርቦበታል:: ለረጅም ጊዜ ዝም ተባባልን:: ሙሉጌታ ሲባንን አጨብጭቦ አስተናጋጅ ተጣራ:: እኔ ያለ ለስላሳ እምቢ አልኩ፣ ለሱ ድራፍት አዘዘ::

«ይኸውልሽ» አለኝ ከመደበቱ ሳይላቀቅ «በዙውን ቁጥር ነክ መረጃ መንደራችንን አንዴ ብትዞሪው ታሰባስቢዋለሽ:: ይሄ አይቸግርም» አለና ድራፍቱን ከአስተናጋጁ እጅ ላይ ቀልበ ሳያስቀምጥ አጋመሰው:: የአረፋ ብናኙን ከአፉ ላይ በግራ እጁ መዳፍ አስወግዶ ቀጠለ...

«ግን እንዴት እንደምትጠቀሚበት አላውቅም:: የመንደራችን ነዋሪዎች ይቺን መንደር ሙጥኝ የሚሉበት ከቁጥር ባሻገር እንደነፍስ ያለ ምክንያት አላቸው:: እንዴት እንደሚገለጽ አላውቅም...»

ለመግለጽ ያለመቻሉ ምክንያት ቀልቡን መሰብሰብ ስላቃተው መሰለኝ::

አሁንም ከብዙ ጊዜ በኋላ ቀጠለ:-

«መንደር፣ አካባቢ፣ ቀዬ... መሬትና አየር ብቻ አይደለም:: ቦታና አቅጣጫ ብቻም አይገልፀውም:: በተለይ ለነዋሪዎቹ የተለየ ትርጉም አለው:: ነፍሱን፣ መንፈሱን የመረዳት» አውራ ጣቱን ብናኝ ፂሙ ላይ አውለበለባት:: ድራፍቱንም በመጠጣት ጊዜ ወሰደና የማይቀርለትን ትንታኔ ገባበት::

«ላንቺ ማስረዳቴን ትቼ እኔ እንደሚገባኝ ላውራው፡፡ መንደሬ ለኔ መኖሪያዬ ብቻ አይደለችም፡፡ የቤቴ መገኛ ጣሪያና ግድግዳ ያቆምኩባት ብቻም አይደለችም፡፡ ከዚያ በላይ ናት፡፤ መንደሬ ለእኔ «ለአምላኬ» የተመረጠች ልዩ መቀመጫው ናት፡፡ አድባራችን፣ አውጋራችን፣ ቆሌያችን፣ አውሊያችን፣ አዋያችን ሁሉ የሚታሰቡኝ የመንደራችንን መተላለፊያ ሲሽሎከሎኩ ነው፡፡ መሄጃ የላቸውም፡፡ መንደራችን ለነዋሪዎቿ የእነዚህ ሁሉ ቅዱስ መናፍስቶች ማስቀመጫ ሙዳይ ናት፡፡ ከልጅነት ጀምሮ መናፍስታዊ ገድሎችን የምንሰማው መኖሪያቸውን እኛ መኖሪያ ላይ እንዳደረጉ ነው፡፡ አድባራችን የምትታዘበን አማካኝ ቦታ በስሟ የተሰየመላት ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብላ ነው፡፡ አዋያችን የምትጠብቀን የቤታችን ምሰሶ አናት ላይ ፊጥ ብላ ነው፡፡ ለአዋይ ብለን ቁራሽ የምናስተርፍላት ሞሰባችን ውስጥ ነው፡፡ ለቆሌያችን የምንገብረውን ቡና የምንፈነጥቀው፣ ማሽላ የምንበትነው በራችን ወጋግራ ስር ነው፡፡ ተሲአት ላይ በጠራራ የማንሄድበት አተላ መድፊያ ቦታ እዚያችው መንደራችን ውስጥ አለን፡፡ ተልከሰካሹ የሚያዘወትረው... ቀን እኛ እንደምንሆነው ሌሊቱን እንዲያ ይሆናሉ አሉ፡፡ የሚፈርደው መንፈስ ሲፈርድ፣ የሚጠብቀው መንፈስ ሲጠብቅ፣ የሚተናኮለው መንፈስ ሲተናኮል የኖረው እዚችው እኛ መንደር ውስጥ ነው፡፡ የሚፈርሰው፣ የሚታረሰው፣ ይሄ የሰውና የአምላኮች መቀላቀያ ሰፍራ ነው፡፡ እናም በዚህ የታነፀ ማንነት» ድራፍቱን ጨለጠና አይገባሽም! እኔም አልገልፀውም፡፡ አልችልም!» አለ፡፡

«ገብቶኛል» አልኩት

ቀና ብሎ ተመለከተኝ፡፡ ሁኔታው ህመሙ እንዳልታወቀለት አፍ ያልፈታ ህፃን ሆኖ ተሰማኝ፤ ቀጠለ፡-

«ሌላው ቀርቶ አገር እንኳን የዚች መንደር ነፀብራቅ ነች፡፡ መንደሬ በውስጤ የደረጀ መሰረት በመጣሏ እርሷ በተናጋች መጠን ሰብዕናዬ ይሰነጣጠቃል፡፡ ሰው ሁሉ ለአገሩ የሚሞተው መንደሩን እያለመ ነው፡፡ የነባር መንደር መፈራረስ የሚሞቱለት አገር ማጣት ነው፣ የሚያመልኩት አምላክ መነጠቅ ነው፦»

በዚህ መካከል ከወደመስኮቱ አንድ ድምፅ ጣልቃ ገባ፡፡

«ኮምሬድ! ኮምሬድ!»





ሙሉጌታ ሳያስበው ስሜቱ ለጥሪው ታዘዘ፡፡ እንደመነሳት ቃጥቶት መልሶ ተቀመጠ፡፡ አንባቢያችን ላይ ያሉ ሰዎች ለድምፁ ቀልባቸውን ሰጡ መሰለኝ፡፡

«ኮምሬድ»

ስላላስቻለው ብድግ ብሎ መስኮቱን በመክፈት ወደውጪ አሰገገ፡፡ ጎላ ያለው ድምፅ ለዝቦ «ኮምሬድ ስሜን አገኘሁት» አለ ጥቂት ሳቆች ከወደውስጥ ተሰሙ፡፡

«የት አገኘኸው?» አለ ሙሉጌታ ሳቅ የሰማበትን አካባቢ በጅምላ ገላምጦ

«ድሮ የሚያውቀኝ ሰው ነገረኝ፡፡ ሀዲስ እባላለሁ፡፡ በደስታ የአባቴን ስም ሳልጠይቀው መጣሁ፡፡ ካገኘሁት ጠይቄ እነግርሃለሁ»

ሙሉጌታ ቁጭ ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ፡፡ ተከፍቶ በቀረው መስኮት ቀዝቃዛ አየርና የመኪና ድምጽ ጎረፈ፡፡

«ያለውን ሰማሽ?» አለኝ፡፡

እራሴን ወዘወዝኩለት በአዎንታ፡፡

«ስሜን አገኘሁት ነው የሚለው፡፡ የሥም ባለቤትነት ምን ያደርግለታል? መጠሪያ ብቻ አይደል? ግን እንደኛ መንደር መንፈሳዊ ፍቺ ሳይኖረውም አይቀር፡፡ ይሄን እውነተኛ ስሙን ያጣ ነው የሚያውቀው» ሌላ ድራፍት አዘዘና ከፍቶ የተወውን መስኮት ዘጋ፡፡

ተበጥብጫለሁ፡፡ ለስላሳዬን ተጎነጨሁ፡፡ እሱ የሚያወራልኝን ሳይሆን ሌላ ነገር የማዳምጥ ይመስለኛል፡፡

«ዛሬ መቼም ያለመግባባት ቀን ነው» አለና ጥቁር አረፋ የመሰለ ፂሙን ሊፒስቲክ የተቀባ በመሰለ አውራ ጣቱ ዳመጠ፡፡

እኔ ደግሞ መረበሹ በራሱ ያስረዳኝና የገባኝ ነገር ከሌላው ቀን ይልቃል ባይ ነኝ፡፡

«ባለመግባባት እንቀጥል» አለና ባዶ የድራፍት ብርጭቆውን ብድግ አድርጎ ለአስተናጋጇ አሳያት «የመንደራችን መናፍስት በሚነግሩን ስሜት ነክ መረጃ ነው እርስ በእርስ የምንተዋወቀው፡፡ ነገሩን ማርቀቄ አይደለም፡፡ ስለአንቺ ሳያውቁ ትከሻዬን ከበደችኝ ብለው ያርቁሻል «ቀፋኛለች» ሊሉም ይችላሉ፡፡ የሚወዱሽ ቆሌዬ

ተቀብሏታል ብለው ነው፡፡ በእነዚህ ሰሜቶች አማካኝነት ነው የመንደሯ አባል መሆንም አለመሆንም የሚቻለው»

የመጣለትን ድራፍት ከመጠጣት ይልቅ ጠረጴዛ ላይ እያሽከረከረ ተካከዘ፡፡

«ለምሳሌ ኮምሬድን እይው፡፡ ከየት እንደመጣ፣ ማን እንደሆነ፣ ሌላው ቀርቶ ስሙ እንኳ አይታወቅም፡፡ ሌላ ማህበረሰብ ዘንድ ቢሆን ለመቀላቀል እነዚህ መረጃዎች አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ እኛ ሠፈር ግን እነዚህ መረጃዎች ላይ ማተኮር በከንቱ መታከት ነው፡፡ ኮምሬድ እንደመጣ ነው ሽልጦ በዱቤ የተሰጠው፡፡ ጠላ የተጋበዘው፡፡ ማህበር የተጠራው፣ ቀብር የሄደው... የእሱ ማንነት እንኳን ለኛ ለእሱም አያስፈልገውም»

ድራፍቱን በጠገበ ሰው አኳኋን ቀምሶ አስቀመጠ፡፡ ልማድ ነውና ፂሙን አልዘነጋም፡፡ «ማታ ይሄንኔ ሳብሰለስል ነው ያደርኩት፡፡ እኔ እንኳን ኮምሬድ አብሮ አደግ ጓደኛዬ ይመስለኛል፡፡ ተደባድበን፣ ተቃምተን፣ ተሻምተን ያደግን ለምን መሰለኝ? አሰብኩት ቆሌ ምናምን ተአምራቸው እኔ ላይ ሰርቶ አይደለም፡፡ ግን ኮምሬድ እኛ መንደር ያደጉ ልጆች ዕጣ-ፈንታ ላይ ስለሚገኝ ከእነሱ ጋ ተደበላልቆብኝ ነው፡፡ አንድ የኛ አብሮ አደግ የጀመረውን ህይወት እየጨረሰ፣ እያጠናቀቀ ይመስለኛል፡፡ ከኮምሬድ ሕይወት ጋር የተቀላቀለብኝን የአንድ ጓደኛዬን ታሪክ ልንገርሽ»

እንደመባነን ብሎ መፈለግና አለመፈለጌን በሚፈትሽ አኳኋን አየኝ፡፡

«እሺ» አልኩት «ንገረኝ እፈልጋለሁ» አሰብ አድርጎ በምሰጣ መናገር ጀመረ፡፡

«በአጠቃላይ ስለኛ መንደር ልጆች ሳስብ አንድ ጥቅስ ይመጣብኛል፡፡ ጥቅሱ የቻይናዊው የላኦ-ዡ ነው Look at the rivers, look at the stars and you will understand action less action ላኦ ዡ አለመመልከቱ ነው'ጂ እንቅስቃሴ አልባ እንቅስቃሴ ፍንተው ብሎ የሚታየው የእኛ መንደር ልጆችጋ ነው»

ትካዜው የሚጫጫን ሆነብኝ፡፡ ቀጠለ

«...የኛ ሰፈር ልጆች እንደ ዛፍ ዕድገት ወይም እንደ ንጋትና፣ ውድቅት ድንበራቸውን ሳትለይላቸው አድገው፣ ጎርምሰውና በስተመጨረሻ ወድቀው ታያቸዋለሽ፡፡ ለጥቂት ጊዜ ካልተለዩዋቸው ለውጣቸው ልብ ሳይባል ነው የሚከናወነው፡፡ አንድ ቀን ተወልዷል፣ አንድ ቀን አድጓል፣ አንድ ቀን አስፋልት ወጥቷል፣ አንድ ቀን ሰክሮ ታይቷል፣ አንድ ቀን ትምባሆ ጨብጦ ታይቷል፣ አንድ ቀን





ጫት ቅሞ ተስተውሏል፣ አንድ ቀን ታስሯል፣ አንድ ቀን ችግር ጠንቶበት ታይቷል፣ አንድ ቀን ታሞ ተጠይቋል፣ አንድ ቀን ሞቷል... ይሄ የአብዛኛው የሰፈራችን ልጆች አጭር የሕይወት ታሪክ ነው»

ድራፍቱን ለኮፍ አድርጎ ተወው፡፡

«ልጆች እያለን በዕድሜ የሚበልጠኝ ደመኛዬ ነበር፡፡ መሳፍንት ይባላል፡፡ በቅጥል ስም ‹ከንቱ› ይባላል፡፡ ደመኛዬ የሆነው በድሎኝ አልነበረም፡፡ እንዲሁ ሳየው የምወግረው ይመስለኛል፡፡ ሆዱ ወደ ውስጥ የሰመጠና ሲራመድ ልምጥ ልምጥ የሚል ነበር፡፡ እና ሳየው ልቤ ይንቀዋል፡፡ ነገር ፈልጌ ስያያዘው አልችለውም፡፡ «እማማ!» ብዬ እጮሃለሁ፡፡ እያቴ ይወጡና ይጣሉታል፡፡ ከኑሯቸው መከፋት የተነሳ እናቱ እሱኑ ተቆጥታ ነገር ማብረድ ትመርጣለች፡፡ በዚህ መሳፍንት ጥቃት ይሰማውና ጭንቅላቱን ግራ ቀኝ እያማታ የቴኒስ ኳስ የሚያካክል እንባ ያዘንባል-ደስ ይለኛል»

ይሄ ሰው ስለከፋቱ እያወራ ነው፡፡ ግን አይመስልም፡፡ ሐዘን የተጫጫነው ግንባሩ ላይ እንደደመና ፀሐይ ብልጭ ያለች ፈገግታ ታይታ እፍታም ሳትቆይ ጠፋች፡፡

«እሱ ያኔ ጎረምሳ ነው፡፡ እኔ ገና ከመንደር አልወጣም ነበር፡፡ አባቱ በሥራ ጅማ ነው የኖረው፡፡ እናቱ ከመሳፍንት በታች አምስት ሴቶች ከሌላ ወልዳ ነው አባቱን የጠበቀችው፡፡ ቤታቸው ሁልጊዜም በሊጥ የተቀባባ ነበር፡፡ እናቱ ኖራ የመሰለ ጤፍ እያቦካች ትጋግራለች፡፡ ጫማው፣ ልብሱ፣ መጋረጃው፣ ድስቱ ሁሉ በሊጥ የተነካካ ነበር፡፡ እናትየው ጥንቃቄ አልባነቷ አከሰራት፡፡ ጠብጠቦ የሚል ቅጽል ስም ወጣላት፡፡ ወሬ ከጀመረች ማባሪያ አልነበራትም፡፡ ዘወትር እየተንጠለጠለ የሚያስቸግራትን ለሃጯን ለመሳብ ስትል ብቻ ነበር ወሬዋን ገታ የምታደርገው፡፡ በዚህ «ጠብ-ጠቦ» የሚል ቅጽል ስም በስተርጅና ወጣላት፡፡ ማን እንጀራ ይግዛ? «ጠብ-ጠቦ» የሚለውን በማሰብ፡፡ እና የቤተሰቡ ኑሮ መናጋት ጀመረ፡፡

«መሣፍንት ከንቱ የአሥራ ሁለተኛ ክፍልን ፈተና ከችግር ጋር በመከራ ወሰደ፡፡ ከሰፈራችን የሚጠበቅ ጎበዝ ተማሪ ቢሆንም ውጤት ሳይመጣለት ቀረ፡፡ ከዚች ዕለት ጀምሮ ኑሮው ፍሬ እንደከበደው ማሽላ ዘለስ ማለት ጀመረ፡፡ የመሳፍንት የጉርምስናና የወጣትነት ዕድሜ እንዴት እንዳለፈ ትዝ አይለኝም፡፡ ዘወትር ይጠጣል፣ እያጓራ መሬት ለመሬት ሲንፏቀቅ እንግቶ ጠዋት ላይ ገብቶ ይተኛል፡፡ «ገርል-ፍሬንድ»

የሚባል ሞክሮ ማወቁን እጠራጠራለሁ:: ብቻ ጎረቤታችን የተከራየች አንዲት ሴተኛ አዳሪ «ልባርጉ! ከበሬ ላይ ሂድ!» እያለች ስታሳጣው ትዝ ይለኛል:: ይቺ የተጎለጎለ ጥቁር ልቃቂት የመሰለች ሴት ነጠላ ጫማ በጨርቅ ተቀጣጥሎ ታደርግ ነበር:: ውሽማው መሆኗ ነው»

ትረካው ፊልም ከማየት ጋር ተነፃፀረብኝ፤ ቀጠለ...

«መሣፍንት ከማንም የማያንስ የቀን ገቢ እንደነበረው መንደራችን ውስጥ ይወራል:: የገቢ ምንጩ ከድለላ ጋር የተያያዘ ወዳጅነት መፍጠር ነበር:: ጥሩ-ጥሩ የእንግሊዘኛ መጻሕፍትን አነፍንፎ በማግኘት ያነባል:: ዋነኛ አላማው ግን ማንበብ አልነበረም:: መጻሕፍትን ለሚወዱ ሰዎች እያቀባበለ ወዳጅነት ይፈጥራል-ይላላካል:: ሴት ለሚለው ሴት ያቀርባል:: በዚህ ይተዳደራል:: ደንበኞቹ እስተዋዮች በመሆናቸው የሚበቃውን ያህል አጠጥተው ለጠዋት ቁርሱ ገንዘብ ሰጥተው ይሸኙታል:: ከዚህ ኑሮ ጋር እጅና ጓንት በመሆኑ ሥራ አይፈልግም:: ሥራ እናስገባህ የሚሉ ብዙ ወዳጆቹን እየቀጠረ በመጥፋቱ ተቀያይሟል:: ሥራ ከመግባት ከወዳጆቹ ከፊሎቹን አጥቶ ከተለመደ ኑሮው ጋር ማዝገሙን ይመርጣል::»

«መሳፍንት ከንቱ ለቤተሰቡም ያለው እሱው ነበር:: ባገኛት ገንዘብ ምናምኑን ገዝቶ ሲንፏቀቅ ያድርና ጠዋት ለእናቱ ያቀብላል:: ወደመጨረሻ ሰሞን መሳፍንት አንድ ጠላት አዘዘበት:: ማታ በደንበኞቹ ግብዣ ተንበሽብሾ ያገኛትን ቋጠሮ እየተንፏቀቀ ሊገባ ሲል አንድ አግረልውስ ልጅ «ልሽከምልህ!» እያለ ይመጣል:: መሳፍንት ኡኡታውን ያቀልጠዋል:: «ዝም በል ካልተጣላሁ ነው'ዴ?» እያለ እንደ ገላጋይ ተሸክሞት ከፍ ዝቅ እያለ ወደ ሰፈራችን ጭለማ ይገባል:: ገንዘቡ የት እንዳለ ማወቅ አይቸግርም:: ምክንያቱም መሳፍንት ገንዘብ ያስቀመጠበት ኪሱን ይዞ ነው የሚጮኸው:: ቢጮህም አይቀርለት ይዘረፋል፤ ጠዋት ያንን ልጅ በድብቅ ያማዋል:: ከኛ ተመሳሳይ የሆኑ ወመኔ ሽማግሌዎች ይልከበታል:: ሲያፈጥበት ይፈራና ዝም ይላል:: ማታ ያው ነው::»

«አንድ ጊዜ የሳንባ በሽታ ይዞት ከፋኛ ታመመ:: ሰውነቱ ከማለቅ በታች አሽቆለቆለ:: መርፌውን እንዴት ተቋቁሞ እንደጨረሰ አላውቅም... የእግዚአብሔር ተአምር መሆን አለበት:: ያም ሆኖ ያለቀ ነጠላውን እየለበሰ ወደደጅ በመውጣት





ደንበኞቹ እንዳይዘነጉት ይታያቸዋል:: ደንበኞቹ እስታመው ቢያድኑትም በመቀጠል «አልማዝ ባለጭራ» (Herps) ያዘችው:: በሽታው እንደ ውሻ ህመም ሲያስጮኸው ያድር ነበር:: ከወራት በኋላ ድኖ ተነሳ:: አገገመ:: ለስንበት ይመስል ነበር:: አንድ ምሽት በውርርድ ብዙ መለኪያ ጅን ጠጥቶ «ተቃጠልኩ» እንዳለ አድሮ፣ ሲነጋጋ ሞቶ ተገኘ::»

የድራፍት ብርጭቆውን አንስቶ አፉ ላይ ደቀነው:: ከመጠጣት ይልቅ ብርጭቆውን ለፊቱ መጋረጃ እየተጠቀመበት እንደሆን ገብቶኛል:: የሀዘን ጭጋግ የወረደበት ፊቱን ከእኔ ለመከለል እየተጣጣረ ቢሆንም ጨዋታው አልተቋረጠም::

መንደራችን በብዙ ወጣት ጥላዎች ወለብታ የተሞላች ናት:: መሳፍንት ከንቱ ከነዚህ ጽላሎቶች አንዱ ነው:: ጥላን ማን ያስታውሳል? እንደዚያ ሁሉ መሳፍንት ማንም አያስታውሰው:: ጎበጥ ብሎ እንዳቀረቀረ የመንደራችንን ሾሎክላካ መንገድ እንደጥላ እየታከከ ያለፈ አንድ ጽላሎት አበቃ:: እንኳን በኑሮ ሽምቅቆ የታበተው የኛ መንደር ነዋሪ ፈጣሪውም የሚያስታውሰው አይመስለኝም»

የድራፍት ብርጭቆውን አስቀምጦ ለመጀመሪያ ጊዜ በሙሉ አይኑ እያየኝ:: «ኮምሬድ፣ ከንቱ ያቋረጠውን ሕይወት ድንገት የቀጠለ ይመስለኛል:: እንደ ተጠባባቂ ተዋናይ:: ስሜን አገኘሁት ሲለኝ መኳንንት ይለኛል ብዬ ነበር::»

የተፃፈ የሚያነብ ሰው እንኳ እንዲህ ሐሳብ አይሰላለትም::

* * *

በአጭር ጊዜ ደጋግሜ አገኘሁት:: ከሙሉጌታ ጋር የፈጠርኩት ቅርርብ ፍርሃት እየለቀቀብኝ መጣ:: በተመሳሳይ አቀባበል እጅግ ለሴትነቴ ትኩረት ሳይሰጥ በብዙ ነገሮች ላይ ነፃ ሆኖ ያጫውተኛል:: ስፈልግ ይቀበለኛል:: ፍላጎቱን ማወቅ አዳጋች ነበር:: እንደተለመዱት ወንዶች ባልተቀጠቀጠ እውራ በግ ባህርይ ምንጭሩን ገሽልጦ ቢቀርበኝ ቦታም ባልሰጠሁት ስል አሰብኩ:: በሳምንቱ ይመስለኛል ሸዊትን ከትምህርት በኋላ ይዣት ወደ አራት ኪሎ ሄድኩ:: ሸዊት ገና ሥጋ ቤቶቹን በመደዳ ተሰልፈው ስታይ «ማይ ጋድ!» አለች «ምን ነው ይሄ?» እንደለመድኩት አማርኛዋን መንቀስ ጀመርኩ «ምን አይነት ሰፈር ነው? ነው የሚባለው»

ኮምሬድን ሥጋ ቤቶቹ አካባቢ በአይኔ ፈለኩት:: የለም:: በተራቆተ አይኔ ዞር ብዬ ሽዊትን ሳያት መንፈሷ ተረብሾ ነበር:: ቦቹንም እዚህ ይገፍው ብመጣ እንዲህ እንደሚሆን አልተጠራጠርኩም:: «ምነው?» አልኳት::

ግራ ቀኙዋን በጥርጣሬ እያየች «ፍርሃት ይሰጣል» አለችኝ:: 'ያስፈራል' ስል አማርኛዋን አቃቂር አወጣሁለት «ኢ-ሙች» አለችኝ:: የስሜ ዘመናዊነት ስለማይዋጥላት «ኢ» ነው የምትለኝ:: እሷ ግን «ለአሪፍ ጓደኞቿች ስምሽ አይመችም» ትላለች እውነቱን መናገር ስለምትፈራ::

ከልቧ ፈርታለች:: ፍርሃቷን መቀበሌን ስታይ ባሰባት እንደቦቹ «እንዴት የታረደ ነገር ዘወትር እየተመለከተ ሰው ሊደላው ይችላል?» አለች:: ዓይኖቿ የቦቹ ይሁን እንጂ ፊቷ ሙጥጥ ያለ ነው:: ቆዳዋ ሳስቶ ግንባሯ ላይ ቀጫጭን ሰማያዊ ደም ስሮች ዝናብ የደበደበው ለጫ ፀጉር መስለው ይታያሉ:: ቀዮች ተወካይ ቢያስፈልጋቸው የሚመርጧት አይነት ነች:: በዚህ ላይ ደማቅ ከለር ያላቸው ልብሶችን ታዘወትራለች:: ዛሬ እንኳን ቀይ እስካርብ፣ ቀይ ጫማ፣ ቀይ የእጅ ጌጥ፣ ሰማያዊ ቦዲ፣ ሰማያዊ ቦርሳ... የደበዘዘ ነገር የለባትም::

«እውነቴ -አሳዘንሺኝ ሁሌ የምትመጪው» አለችኝ:: የምትረግጠው ላይ ሁሉ ጥርጣሬ እያሳየች ቀበሌው መዝናኛ ደረስን:: ሙሉጌታ እኔን ብቻ ስለቀጠረኝ አንድ ወንበር ብቻ ትርፍ ይዞ ነበር የጠበቀን:: ሽዊትን ሲመለከት ከሰላምታ በፊት አንድ ወንበር ባይኑ መማተር ጀመረ::

«ምናልኩሽ-ኢ፣ እዚህ?»

«ዝም በይ» አልኳት በምልክት:: የተንቀጠቀጠች መሰለኝ:: ሙሉጌታ ከወዲያ ማዶ አንድ ወንበር ይዞ መጣ:: ሆን ብዬ መካከላችን አስቀመጥኳትና ማንን ነው የምፈትነው? ስል እራሴን ጠየኩ:: ከራሴ ስሜት ጋር ትንቅንቅ እንደገጠምኩ ገባኝ:: ሙሉጌታን ማግኘት እፈልጋለሁ:: ፍላጎቴ ያናድደኝና በመቅረት አደናቅፈዋለሁ:: መምጣቴ ግድ ሲሆን ደግሞ ሽዊትን የመሰለ እንቅፋት ይዤ እመጣለሁ::

ሽዊት ሙሉጌታን እንደተጠየፈችው ገባኝ:: እሷና እኔ መካከል የተፈጠረው የስሜት ልዩነት ግራ ሆነብኝ:: መጀመሪያ እኔን ሲያገኝ በነበረበት ሁኔታ ላይ ነው





አለባበሱ:: በሀሳቡ ወደድኩት እንጂ ሳገኘውም አልተፀየፍኩትም ነበር:: ሽዊት ቦታ እንድቀይራት በጠረጴዛ ስር እየነካካችና አገጭዋን ገፋ ሳብ እያደረገች ትለምነኛለች::

«ጓደኛሽ ናት?» በአውራጣቱ ጢሙን አስተኝቶ:: ለካ አላስተዋወኳቸውም:: «አዎ ሽዊት ትባላለች» አልኩት

«አንድ ላይ ነው የምትማሩት?»

እሷን የጠየቀ ቢሆንም እኔ እስከመልስላት ድረስ አውቃ ዝም አለችው:: ሽዊት እንዲህ ናት:: ደስ ያላትን ደግሞ ቀርቧት ሳይጨርስ ትጠመጠምበታለች::

«አዎ፣...» መቀጠል ብፈልግም የምለው አጣሁ:: ለሰላሳ መጣልን::

ለረጅም ጊዜ ዝም ተባባልን:: ሽዊትን ያህል እንቅፋት ይዤ መጥቼ ስላደናቀፍኩት ሀዘን ተሰማኝ:: ይህን ጊዜ ከኔ ጋ የሚያወራውን ሲያሰላ ቆይቶ ይሆናል:: ሽዊትን ሲመለከት እንዴት ወሽመጡ ይቆረጥ? አሻግሬ አየሁት::

ዓይኖቹን ማሳረፊያ ያጣ ይመስላል:: ቀጥ ብሎ የመጣ አይታው ከኔ ዓይን ጋር ሲገጣጠም እንደሚበር ተርብ ድንገት ይታጠፋል:: ርብሽብሽ እላለሁ:: ምን ልሆን ነው? እራሴን በኩርኩም ብገጨው በወደድኩ::

«አንቺ የተሰጠሽ የጥናት... መመረቂያሽን የምትሰሪው በምን ላይ ነው?»

ተርበተበተ እንዴ? ስል አሰብኩ:: አሁንም ሽዊት መልስ ላለመስጠት የለስላሳ ጠርሙሷን አነሳች:: እያናደደችኝ መጣች:: ሆን ብላ ነው በብርጭቆ የተቀዳላትን ትታ የጠርሙሱን የምትጠጣው:: የንጽህና ጥርጣሬ እንዳደረባት ለማስመሰል::

«በምን ላይ ነበር?» አልኳት ቃላቶችን አጥብቄ:: ፊት በማንበብ የተካነች ነች:: እንደ ቦቹ:: ለመስተካከል እየሞከረች «የሀብታም ልጆች ከአገራቸው... ኢይሚን ሃይር ክላስ ልጆች ያለባቸው ከአገር ውስጥ ባህል ጋር ቅራኔ» ቦቹ ሲፈራ የሚያሰማውን የመሰለ የመዝጊያ ድምጽ ተጠቀመች::

የቋንቋ ምግዚቷ እኔ አማርኛዋን አርሜ አቀረብኩት «በከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ወጣቶች ከነባሩ ባህል ጋር ያላቸው ቅራኔ ላይ ነው የምትሰራው» አልኩት::

እንደቋንቋው የማላርመው ስህተት እንደፈጸምኩ ገባኝ:: ከራሴ ምኞት ጋር እልህ ተጋብቼ ቅደም ተከተሉ እንደተፋለሰ ምግቧ ሁለመናው እንዳይሆን ሆነ ቀኑ::

ሙሉጌታ «እ» ብሎ ዝም አለ። ቆይቶ ቆይቶ «ደህና ነሽ አይደል?» አለኝ

ስሜቴን አጢኖ የደረሰበት ስለመሰለኝ ተረበሽኩ። በእሱ ላይ ያደረብኝን የማናገር፣ አብሮ የመሆንና የመተያየት ፍላጎት ያወቀው ሲመስለኝ ብስጭትጭት አደረገኝ።

«ደህና ነኝ። ምነው?»

ቦቹ እኔንና አባቴን እያፈራረቀ እንደሚያየን ሸዊትም በዚሁ ተጠምዳለች። ይቺ ምኗ ነው የኔ ጓደኛ? ስል አስቤ በዚህም ተበሳጨሁ።

«እ» ብሎ ዝም አለ።

«እ» ማለቱም አበሳጨኝ። ግን ምን ሆንኩ? ምንድን ነው እንዲህ እራሴን የምጠራጠረው? ቦቹ ሲያስቸግር አቅፌ ወስጄ መኝታ ቤት እንደምዘጋበት ሸዊትንም አጣጥፌ አንድ ቦታ ወሽቄ ከሙሉጌታ ጋር ብሆን ተመኘሁ። ግን እንዲሁ እንደተብከነከንኩ ቀኑ ተብከንክኖ አለፈ።

* * *

ፍቅር ሲጀምር እንዴት እንደሚያደርግ አለማወቄ መሰለኝ ለሙሉጌታ ያለኝን ፍላጎት ሁሉ እንድጠራጠር ያደረገኝ። ሸዊት ከኔ ጋር ለመሆን የምትጥረውን አይነት ጥረት እንደሆነስ ለሙሉጌታ ያለኝ ስሜት? አላውቅም «ፍቅር ሲጀምር እንዴት ያደርጋል?» ሸዊትን ጠየኳት።

«እ - ዌል፣ ምን መሰለሽ...» እያለች ነገሩን ጎለጎለችው። ግንባሯ ላይ እንዳለው ሰማያዊ ደም ስር የምትናገረው ነገር ሁሉ ይወሳሰብባታል። ጉልህ ሆኖ የሚታየው ደማቁ አለባበሷ ብቻ ነው። ሸዊት ብዙ ጊዜ አፍቅራለች። ጊቢ ውስጥ እንኳን ከአንዴም ሁለት ሦስቴ ፍቅር መስርታ እንዳፈረሰች አውቃለሁ።

እኔ ስሸሽ «ምንም አያስፈራም» ትለኝ ነበር።

«ኬር ትሰጪዋለሽ፣ ምቾት እንዲሰማው ይከፋሽና እናቱ ሲቆጡት ታለቅሻለሽ፣ እኔን ምቱኝ ትያለሽ ቢመቱት፣ ይቅርብኝ እኔ ብላ አንተ ትይዋለሽ... እንደነገሩ ሊፒስቲከሽን ትቀቢያለሽ፣ ማች አልሆን ይልሻል ልብስሽ፣ ሲያጠና እሱ አንቺ እቅፍ አርገሽው ትከሻውን...»





ምንም የያዝኩት የለም። በደፈናው እንደስካር፣ እንደ እብደት፣ እንደ መሞላቀቅ፣ እንደ ረሃብ... ነው ብትለኝ ይሻል ነበር። ሁሉንም ባላውቃቸውም ለመገመት ግን ቅርቦቼ ናቸው።

ስለሙሉጌታ ጠየኳት

«ብሎሽ እንዳይሆን አጣብሺኝ?» አለችኝ

«እሱን በኋላ እነግርሻለሁ» አልኳት

«እንዳትነግሪኝ በኋላ ያስፈራል፣ ይቀፋል፣ ምቾት አይሰማሽማ፣ አይጠብቅማ እራሱን፣ ኢቨን ኢፍ አያበጥረውም ፀጉሩን። ክብር እንዲሰማው እራስሽን የምታደርጊው ባለማነጋገር ነው። ከደረጃሽ ዝቅ ያሉትን ኢቨን ኢፍ አልፎ-ተርፎ ላፍቅርሽ ቢል ደርሶ ደፍሮሻል፣ ንቆሻል፣ ሰድቦሻል ማለት ነው»

ከንግግሯ ጋ ሀሳቧን በአቀማመጥ ታፋልሰው እንጂ አንዳንድ ጊዜ ትክክል ነች። በተለይ አንድ ነገር ላይ ጓጉቼ ከጠየኳት አማርኛዋን የሚያስተዳድረው የእንግሊዘኛ ሰዋሰው ይከፋል። የእሷን ቋንቋ እያረሙ ማሰብ እንዴት የሚሰለች ነው ብዬ አሰብኩ። ቢሆንም አቋሟ የሚናቅ አልነበረም። የክብር ጉዳይ ማንኛውም ሰው መስፈርት ውስጥ መካተት ይኖርበታል። ምን ሳስብ እንደቆየሁ፣ ካሰብኩት ምን እንዳገኘሁና ምን አቋም ላይ እንደደረስኩ መመዘን አቃተኝ።

# አምስት

ለሦስት ቀን ሙሉጌታን አላገኘሁትም። መንደሯ ከቀራት አጭር ዕድሜ አንፃር ከታየ ትልቅ የጊዜ ኪሳራ ነው። ግን ደግሞ ጥናቴ ላይ ከማተኮር ይልቅ በተናጠል ለሙሉጌታ ዕጣ-ፈንታ መበከንከኔ አቁስሎኛል። ተልዕኮዬ መመረቂያ መስራት መሆኑን ዘንግቼ የእነ-ሙሉጌታን አኗኗር ለመታደግ ከአባቴ ጋር ተነታረኩ። አባቴ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ረጋ ብሎ የነብይ ምሳሌውን ሳያዥጎደጉድ የፍላጎቱን ቸረኝ።

«አየሽ ይቺ አገር በግለሰብ እጅ የነበረ ጥሪቷን ለደሃ ደግሳ በማብላት አባከናለች። ለብዙ ሺህ አመታት በቅዱሳንና በፖለቲካ ሥም ሀብታም የተባለው ለደሃው ግብር ሲያበላ ነው የኖረው። ይሄ ባህል ድሆችን ከማጥፋት ይልቅ እያንሰራፋ መጣ። ግዛቶች ሁሉ በድሆች ተወረሩ። ያለፈው መንግሥት ደግሞ ጭራሽ ድሆችን ባለእርስት የሚያደርግ ፖሊሲ ይዞ መጣ። ድሆች ብቻ አይደሉም እነዚህ ሰዎች ሰነፎችም ናቸው። ርስታቸው ላይ ተኙበት። በስንት ድካም የለማ እርሻ በመንግሥት ከለላ የነጠቁትም የገጠር ሰነፎች እንደከብት ያለሀሳብ በመራባት ለመጋጥ ተሰማሩ። ይሄ አንድ ቦታ ላይ መቆም አለበት። ያ ቦታ ደግሞ ይሄንን ቤት ያጠቃልላል። እኔንም ያካትታል። አንድ ባለሀብት ሺህ ሰነፎችን አዝሎ መጓዝ የለበትም። የእኔ አቋም የዚህችን አገር ዕጣ-ፈንታ ይወስናል»

«የዚች አገር ዕጣ-ፈንታ የሚወሰነው በመጨካከን ነው? ሰብአዊነትስ? ፍትሃዊነትስ?» ስል ልጋፈጠው ሞከርኩ።

አባቴ እርጋታው ሳይናወጥ ኃይለ ቃል ማፍለቅ ጀመረ...

«ስለሰብአዊነት መጮህ ያለበት ማነው? ስለፍትህ አቤቱታ ማቅረብ የሚገባውስ ማነው? እኛ? እነሱ? እኛ ነን። ሰብአዊነትን የተነፈግን፣ ፍትህ ያጣን እኛ ባለሀብቶች ነን። ሳይሰራ፣ የለፋንበትን ካልበላሁ በሚል ፍትህ አጉዳይ የተከበብን እኛ ነን። የሰው ልጅ ከሥራ ከተነጠለ ለሙብላት መሰማራት ያለበት የሳር መስክ ላይ ብቻ ነው። እዚያ እናት ተፈጥሮ ያዘጋጀችው ነፃ የምንጭ ውሃ ይኖራል። የሚያሳዝነው እሱንም መጠነኛ ሥራ የሰሩ ቀድመው በንብረትነት አጥረውታል» በሚያንኳስስ አይነት አይቶኝ አሁንም ሳይናወጥ ቀጠለ፡-





«ዳቦ ዋጋ ያለው ቁስ ነው። የተጋገረ የሰው ጉልበት! ሰው ሳይሰራ እንዴት የተሰራ ዳቦ ይበላል? ይሄ ፍትህ ነው? አትጠራጠሪ አንድ ሰው ሳይሰራ አንድ ዳቦ ከበላ ሌላ ሰው ጉልበቱን በነፃ እንዲያፈስ በባርነት ተፈንግሏል። ዳቦ ለሰነፎች በነፃ እየቀረበ ከሆነ ባርነት ቀርቷል ለማለት ይቸግራል። ባርነት አልቀረም። ስንዴው ይሁን በወፍ-ዘራሽ በቀለ እንበል፣ ለመድረቁም እድሜ ለፀሐይ ይደርቃል፣ እንዴት ተፈጨ? እንዴት ተቦካ? እንዴትስ በሰለ? እዚህ ዳቦ ጋገራ ላይ የፈሰሰው ጉልበትና ጊዜስ? ይሄንን ታታሪዎች በሰነፎች የሚበዘበዙበትን ባርነት ነው ሰብአዊነት የምትይው?!! የዓለም ፍትሃዊነት የሚረጋገጠው ያልሰራ ባለመብላቱ ብቻ ነው!!

«በነፃ የሚበላ ሁሉ ባክኖ ያባክናል። እኛ በአገርነትም፣ በሕዝብነትም ደረጃ ወደኋላ የቀረነው በነፃ የሙብላትና በነፃ የማብላት ባህላችንን ስላልተውን ነው። አንድ ዳቦ ገዝተሽ ለለማኝ ትሰጪ ይሆናል። ፊት ለፊት ካየሽው ዳቦ ሻጭ ዋጋውን አግኝቷልና የሀገር ሀብት አልባከነም ትይ ይሆናል። ነገር ግን መፅዋቿ አንቺ የአንድ ዳቦ የስራ ዋጋሽን ቁጭ ብሎ ለዋለ ሰው ስትይ ባክኖ እንዲቀር ገደል ጨምረሽዋል። ስለዚህ አገርና ወገን ለዚያ ዳቦ ዋጋ ወደኋላ አንድ እርምጃ ይንሸራተታሉ። ለሰነፎች ሲባል! ይሄ ነው ሰብአዊነት? ይሄ ነው ፍትሐዊነት?»

«አንተ ባልከው መንገድ አይደለም የሚተነተነው» አልኩት። ·

«እህስ? እንዴት ነው?»

«ሰነፎች ይራባሉ፣ ጠንካሮች ይጠግባሉ የሚለው አቋም የጥንታዊዎቹ ኢኮኖሚስቶች ቀመር ነው። ተጨባጩ እውነት ከዚህ ይለያል። ዓለም የሸሚያ ቦታ ናት። ግን በዚህ ሸሚያ መነጣጠቅ ያለብን ትርፍ ሀብትን እንጂ ሕይወትን መሆን አይገባውም።»

አባቴ እንደ አይነ ስውር ሳንቲም ቁልፉን እጁ ላይ እያንቀዋለለ በአንክሮ አየኝ። አልተናደደም፣ አለመናደዱ አስፈራኝ። የጨበጠው የተማመነበት አንድ ዕቅድ እንዳለው ጠቆመኝ።

«ትርፍ ሀብቷ ዳቦ ብቻ በሆነ ደሃ አገር ውስጥስ? ለዚህ ተጨባጭ እውነት ዘመናዊዎቹ ኢኮኖሚስቶች ምን ተነጣጠቁ ይላሉ? ምን ተነጣጥቃችሁ ሀብት አብጁ ይላሉ?» በዓይኖቹ ንክስ አድርጎ ስለያዘኝ መንቀሳቀስ አቃተኝ «በሃያኛው ክፍለ ዘመን

መጀመሪያ ፈረንጆቹ ጋ የሆነው ነው እዚህም የሚሆነው፡፡ ብዙ ድሆች በሥራ እስኪነቃቁ ያልቃሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ሥራ ዘላለማዊ መገበያያችን ይሆናል፡፡ ይሄ የተፈጥሮ ግዴታ ነው፡፡ ካለሥራ በሰዎች መካከል የቁሶች ልውውጥ ሊኖር አይችልም፡፡

«ሥራ ብቻ አይደለም፣ አመጽም የቁሶች ልውውጥ ሊያመጣ ይችላል» አልኩት፡፡ ለማናደድ በጣርኩ ቁጥር የበለጠ እየተረጋጋ ይታየኛል፡፡ ዛሬ ግን ምን ሆንኩ?

«አብዮት ማለትሽ ነው? የድሆች አብዮት ለራሳቸው ለድሆቹም ሳይበጃቸው ተጠናቅቋል፡፡ ግማሾቹ የወረሱት ጭቃ ቤት ውስጥ በረሃብ አለቁ፣ ግማሾቹም የወረሩት ጠፍ እርሻ ላይ እየተባረሩ ተጋደሉ፡፡ ከደሃ አብዮት የተገኘው ይሄው ነው፡፡ ለድሆች አመጽ እድል የሰጠው ዘመን የወረርሽኝ መነሻ ከመሆን ውጭ ካደፈ ልቦናቸው የተጨመቀ ንጽህና ታጥቷል፡፡ ጭለማ ብቻ! ከኛ ህልም ነው ብርሃን የሚፈልቀው፡፡ ያጎነቆለ ባለሀብትንና ሀብቱን በመጨፍጨፍ የተካሄደው የድሆች አብዮት ውጤት ታይቷል፡፡ አሁን ደግሞ ድሆች ላይ ልጓም የሚያጠልቀው የብልጽግና አብዮት መሞከር አለበት»

አባቴን በክርክር አውቄ የምተወው እንጂ የሚረታኝ አይመስለኝም ነበር፡፡ አሁን ግን ባለኝ ዕውቀት ሁሉ ተጠቅሜም ንቅንቅ የማይል ድባብ አባቴ ላይ ያንዣብባል፡፡ ሙሉጌታና የድህነት ደቀመዛሙርቱ በእኔ በጠበቃቸው ስንፍና ሞት ሲፈርድባቸው ታየኝ፡፡ ውስጤ አሁንም ለአባቴ አልተረታም፡፡ ግን ያ-ያልተረታ ስሜቴ የቱ ነው? ምክንያቴ ምንድነው? ማውጣት ያለብኝ እሱን እውነት ነበር፡፡ ግን...

«አሁን እኔ ተምሬአለሁ?» ስል በራሴ ላይ ተነጫነጭኩ፡፡

አባቴ ድንገት «ስንት ክሬዲት ሀወር ይቀርሻል?» ሲል የክርክራችንን ጭብጥ ቀይሮ ጠየቀኝ፡፡

«አሥራ አራት ወይም አስራ አምስት ይመስለኛል» አልኩት፡፡ ትምህርቱ ላይ የነበረኝን ትኩረት እየቀነስኩ መመረቂያ ጽሁፌ ባመጣብኝ ጣጣ ውስጥ ተዘፍቄያለሁ፡፡





«ጥሩ፣ በቅርብ ጊዜ የስራ ልምምድ ትጀምሪያለሽ፡፡ ደሞዝ ይኖርሻል፣ በቀን ቢያንስ አራት ሰዓት ስራሽ ላይ ትገኚያለሽ፡፡ የስራ ቦታሽ ማተሚያ ቤቱ ውስጥ ነው፡፡» ብሎኝ መልስ ሳይሰጠኝ ወጣ፡፡ ከአባቴ ጋር በመንፈስ እየተራራቅን መምጣታችን ታወቀኝ «ታፈ» ብዬ ከጠራሁት እንኳን ቆየሁ፡፡ ለካ «ታፈ» ስም-ቃል ብቻ ሳይሆን የፍቅር ጠብታም ኖሯል? አባቴን የሸኘው ቦቹ እኔን አንጋጦ ያየኝ ጀመር፡፡ አንቺም ውጪ እና ልሸኝሽ'ጂ ያለኝ መሰለኝ፡፡

ቀጠሮ ሳይኖረኝ ወደ አራት ኪሎ ለመሄድ ተነሳሁ፡፡ ከቦሌ አሎምፒያ ወደ አራት ኪሎ ታክሲ ያዝኩ፡፡ አባቴ ሊያደርሰኝ እንደሚችል ባውቅም አልፈለኩም ነበር፡፡ ታክሲው አራት ኪሎ ካምፓስ ደጅ ላይ አወረደኝ፡፡ ቁልቁል በእግሬ ወረድኩ፡፡ የሥጋ ቤቶቹ መደዳ ሲገባደድ ያለው ሆቴል ደጃፍ ላይ ኮምሬድ በጀርባው ተንጋሎ ተኝቷል፡፡ ፀሐይ በመሆኑ ፊቱ ተቅለጥልጧል፡፡ ቀኝ እጁ የሱሪውን መታጠቂያ እንደጨመደደ ነው፡፡ ግራ እግሩ በድን ግንድ እንደመሰለ ተዘርግቷል፡፡ አንድ ህፃን ፈልጌ ወደ ሙሉጌታ ቤት ላኩት፡፡ ጥቁሩ ጭንቅላተ ከባዳ ህፃን ብዙም ሳይቆይ መጣና «ግቢ ብሎሻል» አለኝ፡፡

አላመነታሁም፡፡ ህፃኑን ከፊቴ አድርጌ በመቆሚያ ጣቢያ ዘለቅሁ፡፡ መንደሩ እንደ ጠርሙስ አንገት መግቢያው ቀጥኖ ወደ ውስጥ እየሰፋ ይሄዳል፡፡ ህፃኑ በጥቋቁር እግሮቹ እንደ ሳንባ ደምስር የተወሳሰቡትን የውስጥ-ለውስጥ መንገዶች አንዱን ካንዱ እየመረጠ ይመራኛል፡፡ በየመንገዶቹ ግራና ቀኝ ግንባራቸው ሊገጥም ጥቂት የቀራቸው ቤቶች እንደሻገተ ጥርስ ተወላጋግደውና ፈርሰው ተደርድረዋል፡፡ ኮባ፣ ግራዋና ሀረግ መሳይ ቅጠል ለየቤቶቹ ድንበር በየደረጃቻቸው ላይ ተተክለዋል፡፡ እኔ ሳልፍ ብዙ የወየቡ ፊቶች እንደ ጥቁር ምላስ ድንገት ብቅ እያሉ ያዩኛል፡፡ ገርበብ እንዳለ አፍ ጭለማ ከዋጠው ቤት ውስጥ ድንገት ብቅ የሚሉት ፊቶች የሚነበብባቸው ስጋት ነበር፡፡ የመፈናቀሉ ዱብዳ በእያንዳንዱ መንደርተኛ ልብ ውስጥ እንዴት ተስተናግዶ ይሆን? ስል አሰብኩ፡፡

እንደተለበለበ እንጨት ጠቁሮ የከሸለለውን ህፃን እንዳልረግጥ እየተጠነቀቅሁ እነ ሙሉጌታ ቤት ደረስኩ፡፡ ቤቱ የመንደሩን ቤቶች ዩኒፎርም የለበሰ ነበር፡፡ ማለቴ ከፈራረሱት ጥርሶች አንዱ፡፡ ያኰፈኰፈ ግድግዳ፣ ማገሩ እንደ ረሀብተኛ ደረት ያገጠጠ፣

ብዙ ዓይኖች ያሉት ጣሪያ፣ ቤቱ ለስሙ ሁለት ክፍል ነው፡፡ መንደሩ ውስጥ ካየኋቸው ፊቶች አንዱን የመሰሉ ባልቴት አፋቸውን በነጠላ እየጠራረጉ ሰላምታ ሰጡኝ፡፡ ሙሉጌታ ሽንቁር መግቢያው ከሚያስጎነብስ ጓዳ ወጣና «አያቴ ናቸው ተዋወቂያቸው» አለኝ፡፡

«እሱ ግድ የለው፣ ሳንዘገጃጅ እንግዳ...» እያሉ ወለሉ ላይ የተደረደሩ ዕቃዎችን በማግለል ሥራ ተጠመዱ፡፡ በከሰል ምድጃ ላይ የተጣደ ሸክላ ድስት፣ የምስር ክክ የተዘራበት ሰፌድ፣ መከተፊያ ጎድጓዳ ሰሃን...

የሙሉጌታ አለባበስ ያው ነበር፡፡ ከተዋወቅን ጊዜ አንስቶ ያቺ የነተበች ኮት ኮሌታዋን ዝናብ እንዳነፈነፈ የአህያ ጆሮ ቀጥ አድርጋ ሙጥኝ ብላዋለች፡፡ ድንገት እሱን የማሽቀርቀር ፍላጎት አደረብኝ፡፡ ምን ይመስል ይሆን? ስል አሰብኩ፡፡

ድብዳብ የለበሰ ሳጥን ላይ ተቀመጥኩ፡፡

ሙሉጌታ በጣሳ ውሃ ቀድቶ ፊቱን ታጠበ፡፡ ገረመኝ ከቀኑ አስር ሰዓት አልፏል፤ ታዲያ እስካሁን ተኝቶ ነው ወይስ? እያልኩ ሳስብ ሌላ አስገራሚ ነገር አየሁ፡፡ አያቱ «ጉድ ጉድ» ሲሉ የለበሱትን አዳፋ ነጠላ ጉተት አድርገው ፊቱን አደራረቁበት፡፡ በወላለቁ ጥርሶቻቸው ፈገግታ መግበውት «እስኪ ፀጉርህን ውሃ አስነካው» አሉት፡፡

«ተዉት እባክዎት» ብሎ ወደ ጓዳ ገባ፡፡

ሁኔታቸው እንግዳ ሰው ቤታቸው ያለ አይመስልም፡፡ የተጣደውን ድስት አውርደው ያንን ህፃን ልጅ የመሰለ የሻይ ጀበና ጣዱ፡፡ የተላከልኝ ልጅ ሳንቲም ሳልሰጠው መሄዱ ትዝ አለኝ፡፡

«እማማ እሷ አትቀይም፡፡ የሻዩን ጀበና አውርደው ድስትዎትን ይጣዱ» ሲል ሙሉጌታ ተከላከለ፡፡

«ይልቅ ስኳርና ሻይ ቅጠል ግዛልኝ» ብለው ካሰሩት ቀይ ሻሽ እጥፋት ውስጥ የተጣጠፈች አንድ ብር አወጡ፡፡

«ያንተ ነገር ይሉኝታ ቢስ'ኮ ነህ» አሉት፡፡

ምንም ሳይናገር በጥቅሻ እንውጣ ብሎኝ ቀደመ፡፡





ባልቴቷን ተሰናብቼ ተከተልኩት፡፡ እንዳስጎብኘ ከፊት-ከፊቴ እየተራመደ «ፈራሹ መንደር ይሄ ነው» አለኝ «የአካባቢው ጌታ ገብሬ ባቄሎ ይባሉ ነበር፡፡ ቤተ-መንግሥት ወር ተራ ለመጠበቅ መጥተው ነው ይቺን ቦታ የገዙት ይባላል፡፡ አሁንም የመንደሩ ሰዎች የገብሬ ባቄሎ አድባር እያሉ ለግንቦት ልደታ ይዘክራሉ፡፡ ገብሬ ባቄሎ ሲሞቱ ለአምስት ልጆቻቸው ርስታቸውንና እኛን አከፋፈሉን፡፡ አንድ ተሳዳቢ ልጅ ነበራቸው፡፡ እሱ ላይ ደርሻለሁ፡፡ ህፃን ብሆንም እሱ ሲመጣ እንንቀጠቀጥ እንደነበር ትዝ ይለኛል፡፡ ወላጆቻችን ይንቀጠቀጡ ነበራ፡፡ እኔ ጥላሁን፣ የማንንም ልቃሚ ሰብስቤ እያለ በመጣ ቁጥር ይደነፋ ነበር»

ሙሉጌታ በጊዜ ብዛት በተደለደሉት እቧራ የለበሱ ድንጋዮች ላይ ያለ ስህተት ይጓዛል፡፡ እከተለዋለሁ፡፡ የተለመዱት የመንደርተኛው ፊቶች እንደ ሽኮኮ ብቅ ጥልቅ ይላሉ፡፡

«ፈርተዋል» አለኝ «የመኖሪያ አካባቢውን ከንጥቂያ ለመከላከል የማይዋጋ እንስሳ ሆነ ነፍሳት የለም፡፡ ሰው የሚሉት ከእነዚህ ያነሰ ፍጡር መኖሪያን ያህል ማንነት ሳይተላለቅ በውል ይረካከባል፡፡»

ከበስተኋላው የኮሌታውን ሆድ ዕቃ እያየሁ ተከተልኩት፡፡ የመንደሩን አንገት እንደጨረስን «ይሄ ቦታ መቆሚያ ጣቢያ ይባላል፡፡ የመንደራችን ሴተኛ አዳሪዎች የሚቆሙበት ነበርና ነው መቆሚያ ጣቢያ የተባለው» አለኝ፡፡

ነግረኸኝ ነበር አላልኩትም፡፡ ንፋስ ያመጣው እፉዩ-ገላ የሚመስል ጢሙን በባዕድ አውራ ጣቱ ለማስተኛት ሞከሮ «ካልመሸ አራት ኪሎ ለምንም አይመችም፡፡ የት ቁጭ ብለን እናውራ?» እያለ ተነጫነጨ «ዝም ብሎ ቁጭ አይባል ነገር አይፈቅዱ፡፡ ለቡናና ለሻይ የሚወጣው ፍራንክ የሚቆጭ አይነት ነው፡፡»

ኮምሬድ እንደተንጋለለ ነው፡፡ ሙሉጌታ ዓይኖቹን ኮምሬድ ላይ ለአመል ያህል አንሸራትቶ አወረዳቸው «በገንዘብ የሚታለፈው ኬላ በዛ» አለ፡፡

ከእንደዚህ ያሉ ጥቃቅን ስጋቶች በአባቴ ልግስና እምልጫለሁ፡፡ ገና ጨቅላ እያለሁ ጀምሮ በእኔ ስም ባንክ የሚያስቀምጠው ብር ነበር፡፡ ድርሻሽ ነው ይበል እንጂ ነፍስ እስካውቅ ድረስ የባንክ ደብተሩን አልሰጠኝም ነበር፡፡ ከስምንተኛ ወደ ዘጠነኛ ክፍል ሳልፍ የባንክ ደብተሩን ሰጡኝ፡፡ ለሁለት ዓመት ያህል የገንዘብ አያያዝ እስካውቅ

ድረስ የማወጣው ብር ካለ ሪፖርት እንዳደርግ ያስገድደኝ ነበር፡፡ ቆይቶ ተወው፡፡ እኔም ከባንክ ከማወጣ ከእሱ መቀበል ስለሚቀለኝ አስቤው አላውቅም፡፡

«ግዴለም፣ እዚህ አካባቢ ሬስቶራንት ካለ እዚያ እንሂድና እንቀመጥ፡፡ ወዲያውም ቁርስህን ትበላለህ» አልኩት፡፡

ሽሙጤ ገብቶት «ቁርስም ምሳም የተኛሁበት ሆኜ በልቻለሁ፡፡» አለኝና ወደ አንድ ቡና ቤት ይዞኝ ገባ፡፡ ለሱ ቡና ለእኔ ማኪያቶ አዘዝን፡፡ ቡና ቤቱ ሰፊና የብርጭቆ ኳኳታ የሚያስተጋባበት ነበር፡፡ ግድግዳ ላይ አንዲት የወፍ ስዕል ተሰቅሎአል፡፡ ከአፏ የሚወጣ ፊኛ በሚመስል ውስጥ «እኔ ስዘምርላችሁ ዱቤ መውሰድ ትችላላችሁ» የሚል ጽሁፍ ይነበባል፡፡ መቼ ትዘምር ይሆን? ስል አሰብኩ፡፡ የእሷን መዘመር የሚጠብቁ ብዙ ነሆለል ጠጪዎች በአይነ-ሕሊናዬ ታዩኝ፡፡ «በቁስል መቀለድ»

«ነገር አለሙን ተውሽው?» አለኝ ድንገት፡፡

እውነቱን ነው፡፡ ዛሬም የመጣሁት እሱን ለማግኘት እንጂ ስለጥናቴ ለመወያየት አልነበረም፡፡ አባቴ የፈጠረብኝ የመሸነፍ ስሜት ገና አልተገፈፈልኝም፡፡ እሱን ለመግፈፍ ይሆን ወደ ሙሉጌታ ጋ የመጣሁት? ብቸኝነት፣ ባይተዋርነት ዙሪያዬን አጥሮብኝ መሄጃ የነሳኝ መሆኑ ዛሬ ተሰማኝ... ብሶት... እዚች ዓለም ላይ የምቀርበው ሰው ተመጥኖ የተሰጠኝ... እናቴ ማን እንደሆነች እንኳ ለማወቅ ያልቻልኩ... ብሶት... አልቅሽ አልቅሽ የሚል ስሜት ድንገት ቅልብሽ አለኝ፡፡

ሙሉጌታ ሲያየኝ ቆይቶ «ምን ሆንሻል?» አለኝ፡፡

«ምን ሆንኩ?» ብዬ አፈጠጥኩበት፡፡ ምክንያቴ እንደምክንያት ሳይከብድልኝ አልቅሽ አልቅሽ አለኝ፡፡

«እ-ም» አለና አውራጣቱን ወደከንፈሩ እናት እያሾለ «ማልቀስ የፈለግሽ ይመስላል ታለቅሺ?» አለኝ፡፡ ያሾለውን ጣቱን መለሰ፡፡

ቀና ብዬ አየሁት፣ ምን አይነት ፈቃድ ይሆን?

«ፊትሽን ወደኔ አዙሪና አልቅሺ፡፡ ማንም አያይሽም»





«አላለቅስም!» አልኩት እልህ ተጋብቼ፡፡ ግን ምን እልህ አጋባኝ? እንደ ቅቤ ማውጫ የቀንድ ማንኪያ የወረዘው አፍንጫው ላይ አተኮርኩ፡፡ ላልቅስ ይሆን? ስል አሰብኩ፡፡ ጅልነት መሰለኝ «አላለቅስም! አላለቅስም»

«እሺ»

ወረቱ የተዘረፈበት ነጋዴ፣ ምርኩዙ የተሰበረበት ደካማ፣ ባሏን የተነጠቀች ሴት፣ በሬው የሞተበት ገበሬ፣ ፈተና ያመለጠው ተማሪ፣ ጊዜ የከዳው ጦረኛ.... የሆንኩ መሰለኝ፡፡ እንዳለቅስ ከመፍቀድ ይልቅ የከፋኝን አይጠይቀኝም? ስል ተቁነጠነጥኩ፡፡

«ልሂድ» አልኩት ድንገት

ግር እየተሰኘ «እሺ» አለኝ፡፡

እንዴት ለምን አይለኝም? በማለት ለመሄድ ቆረጥኩ፡፡ ያዘዝነው እየመጣ ተፈናጥሬ መውጣት ጀመርኩ፡፡ አስተናጋጂ ያዘዝነውን እንደያዘች ፈዝዛ ቀረች፡፡

«ሲፈልግ ጥናቱ ገደል ይግባ» ስል አሰብኩ፡ ከዚህ ሰው መራቅ አለብኝ... መራቅ... መራቅ... መራቅ፡፡

* * *

ጥርሴን ነክሼ ሦስት ቀን ቆየሁ፡፡ ስልኬን ያውቃል ግን አልደወለልኝም፡፡ ለምን? በቅርርብ ላይ ጤናማ ባህርይ ከሌለው ሰው ጋር እንደተፋጠጥኩ ገባኝ፡፡ የመራቅ ፍላጎቴ ከፍተኛ ቢሆንም ለመተግበር ግን የምቸገርበት ምክንያት አልተነተንልሽ አለኝ፡፡

ወደአራተኛው ቀን ልሽጋገር ትንሽ ሲቀረኝ የሰጠኝ ስልክ ላይ ደውዬ መልዕክት አስቀመጥኩ፡፡ ሱቋ ከመንደር ውጭ ስለሆነች ለማስጠራት አይመችም፡፡ በሁለት ሰዓት ልዩነት ውስጥ ድባብ መናፈሻ እንድንገናኝ መልዕክቴ ያዝዘዋል፡፡

ሄድኩ፣ ቀድሞኝ ነበር፡፡ ደስ አለኝ ደግሞም አይደውልልኝ እንጂ ስልኬን በጽኑ ሲጠብቅ ነበር ብዬ አሰብኩ፡፡ በየደቂቃው «መልዕክት አለ?» እያለ ወደ ሱቋ ሲመላለስ ነበር ማለት ነው፡፡ ደስ አለኝ፡፡ ይሄ ምኑ ያስደስታል?

ጥቂት የመሽኮራረም ወሬዎችን ተወራወርን፡፡ ድንገት...

«ነገር አለሙን ተውሽው?» አለኝ

የኔ ነገር አለም ሌላ ሳይሆን አይቀርም ስል አሰብኩ፡፡ ሁኔታዬ ሁሉ የፍቅር እንደሆነ እየተገለጸልኝ ነው፡፡ የተሸማቀቀ ግንባሩ ላይ አተኮርኩና የተጠየኩትን ትቼ...

«አፍቅረህ ታውቃለህ?» አልኩት፡፡

ደነገጠ መሰለኝ አውራ ጣቱን በስራ ጠመዳት፣ ጢሙን ዳመጠ፡፡ መደንገጡ የጥያቄዬን ትክክል አለመሆን የሚጠቁም መሰለኝ፡፡ ሲፍተለተል ቆይቶ «አዎ» ብቻ አለኝ፡፡

«እንዴት ያደርጋል?» ትምህርት አስተዳደግን እንደማይገሰው ዛሬ ገባኝ፡፡ ስለፍቅር ለማውራት እንዲህ መጨነቅ ነበረብን? ስል እራሴን ጠየቅኩ፡፡ ማህበረሰባችን ለምን ፍቅርን እንደማያበረታታ ትምህርቴን ተንተርሼ ምላሽ ልሰጥ እችል ይሆናል፡፡ ግን ደግሞ ማህበረሰቡ ላይ እንደጉድለት ያየሁትን ከትንተና ባሻገር በተግባር ለመተርጎም ችግሩ በኔ ላይ ይገለጻል... ምናልባት ግን የፍቅር ስሜት ውስጥ ስላለሁ ይሆናል የከበደኝ ስል አከልኩበት፡፡

«እንዴት ይገለጽ ይሆን?» እያለ አድፈነፈነብኝ፡፡ ያ ድንገት ግንፍል የሚልብኝ ሀዘን ቅልቅል ብስጭት መጣብኝ፡፡ በዚህ ብስጭት ምክንያት ዛሬም በድጋሚ ከሙሉጌታ እንዳልለይ ተጠነቀቅኩ፡፡ «ምን እንዳማረኝ ታውቃለህ?» አልኩት የብስጭቴን ማስተንፈሻ ስፈልግ ቆይቼ «አንተ አስከትስከር አጠገብህ ሆኜ ማጠጣት፡፡ እኔም መጠጣት፡፡ ግን ጠጥቼ አላውቅም»

«ጥሩ ነበር» አለኝ፡፡ ግን ገንዘብ የለም ሊል እንደሆነ ገባኝ፡፡ ግልጽ ሲሆንልኝ፣ ችግሩን ሲነግረኝ ለምን መውደዴ እንደሚጎር አላውቅም፡፡

«እዚህ አካባቢ አይደለም የምንጠጣው፣ አራት ኪሎም አይደለም፣ ራቅ ያለ ቦታ... እኔንኛ በኮንትራት ታክሲ እንሄዳለን...» ይገፍው የመጥፋት ፍላጎቴ በሌላ አቅጣጫ ሲመጣ ይሆን? «ብር አታስብ»

«እሺ» አለኝ፡፡

«ከባንክ እናወጣለን» አልኩት፡፡

«አስር ሰዓት ሆኗል ባንክ ይዘጋል» አለኝ፤፡

«ከቤት አመጣለሁ፡፡»

«እሺ»





«በኮንትራት ታክሲ እንሄዳለን»

«እሺ»

«በር ላይ ትጠብቀኝና አመጣለሁ»

«እሺ»

እሺ... እሺ... እሺ፣ ለክርክር አልመች አለኝ «ለምን? ማለት አያውቅ ይሆን?» ስል አሰብኩ፡፡

«እሺ» እንዳለኝ አመሸን አቅጣጫ ሳንለይ ከተማው ውስጥ በኮንትራት ታክሲ በረርን፡፡ «ፐብ» የሚል ጽሁፍ ሳነብ እንግባ እለዋለሁ «እሺ» ይለኛል፡፡ እሱ ቢራ እኔ ወይን አዛለሁ፡፡ ያስቀዳሁትን ብርጭቆ ሁለቴ እንደተጎነጨሁ እንውጣ እለዋለሁ «እሺ» ይለኛል፣ «ባር» የሚል ጽሁፍ ሳይ እንግባ እለዋለሁ «እሺ» ይለኛል፣ «ባርና ሬስቶራንት» እንግባ እለዋለሁ፣ «ናይት ክለብ» እያለሁ «እሺ» ይለኛል፡፡ እሱን ለማስከር ያቀድኩት ብዙ ፉት እያልኩ እራሴ ሰከርኩ፡፡ የወይኑ መጎምዘዝ እየቀረልኝ መጣ፡፡ የስካር ስሜት ምላስ ላይ ያለ መሰለኝ፡፡ የምላስ መደንዘዝ ደግሞ ያሻን ለመናገር ያደፋፍራል ልበል?

«ለምን ቀኑን ሙሉ ትተኛለህ? አትተኛ!» እለዋለሁ፡፡

«እሺ»

«ደግሞ ሥራ ፈለግ»

«እሺ»

«በዚህ ላይ ጫማህን አታስርም፣ እሰር»

«እሺ»

እሺ... እሺ... እሺ ብዙ እሺ፡፡ «ለምንድነው ዝም ብለህ እሺ... እሺ የምትለው? እሺ አትበል፡፡»

«እሺ»

«አሁንም እሺ ትለኛለህ?»፡፡

«ጥቅሙን ስለማውቅ» እሱ አልሰከረማ፡፡

«ጥቅሙ ምንድነው?» እኔምኮ አልሰከርኩም፡፡ ምክንያቱም ደስ ያለኝን ማድረግና መናገር ቻልኩ እንጂ እራሴን አልሳትኩም፡፡

«ጥቅሙማ የእንቢታ ተቃራኒ መሆኑ ነው» ሳቅ አለ። የፈዘዙ ሰልፈኛ ጥርሶች አየሁ። የማላውቃቸው፣ ሰቆ አያውቅም ነበር ማለት ነው? ስል አሰብኩ። «እናቴ ለሁሉም ነገር መልሷ እንቢ ነበር። አያቴ ደግሞ እሺ። እንደ እናቴ ቢሆን ኖሮ እኔ ሰው አልሆንም ነበር ብዬ አስባለሁ። አያቴ ግን ሁሉንም በእሺታ እየተቀበሉ አነጹኝ»

ንግግሩን እያብሰለሰልኩ ዝም አልኩ። ጭንቅላቴ እንደወትሮው አልፈጥንልሽ አለኝ። ስካር ይሄ ይሆን?

«እንሂድ በቃ» ብናኝ ጊሙን አስተኛ።

«ሳትጠጣ?»

«በቃ እንዴት ይሁን? አንቺ ‹ሰባት እንገት› ጠጥተሽ ቀድመሽ ሞቅ ያለሽ መሰለኝ» አለና «ወይ ከእንግዲህ እኔ ልጠጣ፣ አንቺ እየተጫወትሽ ብቻ ቆይኝ» የፈረደበትን ጉዳተኛ ጢሙን ዳመጠ።

«እንዴት?»

«አንቺ በቃሽ እኔ ልጠጣ»

«እሺ» እሺታ እንደተሰቦ የተጋባብኝ መሰለኝ። ቀዝቃዛ አምቦ ውሃ አዘዘልኝ

«ጥያቄ ግን መጠየቅ ይቻላል?» አልኩት

«እሺ ግን መታወቂያ አሳዩ፣ የጋዜጠኝነት» ብሎ ጉንጩን ቆንጠጥ አደረገኝ። አባቴ እንገቴን ዳበስ ሲያደርገኝ የሚሰማኝ በሰው የመከበብ ስሜት መጣ። ይሄ ሰው ማነው? እንደአባቴ የባይተዋርነት መድኃኒት የሆነኝ?

«እየቀለድኩ አይደለም» አልኩት።

«እሺ»

«ለምንድነው... እዚያ.... አራት ኪሎ ሆነን ሊያስለቅሰኝ የነበረውን ጉዳይ ያልጠየከኝ?»

«ያንቺ ጉዳይ ነው ብዬ። መጠየቅ ነበረብኝ?»

«አዎ»

«እሺ»





«እሺ ምን?» ቀዝቃዛውን አምቦውሃ ተጎነጨሁ በጋመው ጉሮሮዬ መካከል ሲያልፍ አንድ ገለል ያለ ነገር ሲሰፍን ተሰማኝ።

«እሺ'ማ ንገሪኝ ነዋ!»

«እንዲሁ እንዴት እነግርሃለሁ፣ ትንሽ እንኳ አታግደረድረኝም?» የሚያቅበጠብጠኝ ምን እንደሆነ አላወኩም። ብቻ ሙሉጌታን ፈትፈ ስይዘው ደስ አለኝ።

«ንገሪኝ፣ ምን ሆነሽ ነበር?» አለና ጢሙን እንደ መስታወት ላይ ጉም በአውራጣቱ ጠርጎ «ይኸው አግደረደርኩሽ» ደስ የሚል የፊት ብርሃን ተጎናጸፈ።

አልቅሽ-አልቅሽ የሚለኝ ምክንያት አልባ ስሜቴ መጣብኝ «ይቅርታ ግን፣ አይ-ፊል ሶሪ በቃ አዘንኩ። መንደራችሁን ገዝቶ የሚያፈናቅላችሁ አባቴ ነው። ይሄን ቀደም ሲልም አውቅ ነበር። ግን እንደማላውቅ ሆኜ ቀረብኩህ» ይሄን ተናግሬ ለመሰለል ለማወቅ ደብዘዝ ባለው ብርሃን አተኮርኩበት። ያዘነ መሰለኝ፣ አዝኖ ሲጨርስ ጥሎኝ ይሄድ ይሆናል። ከማውቃቸው፣ ከቀረብኳቸው ጥቂት ሰዎች አንዱን ላጣ ነው። ግን ለምን ነገርኩት?

«ምነው ዝም አልክ? ተቀየምከኝ? እንደከዳሁህ ቆጠርከው?» አፍንጫው እንደ አርባ ሻማ አምፑል በርቶ ፊቴ ላይ የተደቀነ መሰለኝ። ቅድም ሰክሬ ከነበረና ስካር ያ-ከሆነ በደነገጡ፣ በፈሩና ግራ በተጋቡ ሰዓት ጥሎ የሚሸሽ ከዳተኛ ስሜት ነው ማለት ነው። በረደኝ።

ጭንቅላቱን እንጋሎ ወደላይ እያየ «አውቃለሁ» አለኝ።

ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ «እንዴት? እንዴት ልታውቅ ቻልክ?» እስኪነግረኝ ድረስ ያለችው አፍታ አንድ ሺህ ጊዜ የምታስተነፍሰኝ አረጅም ሆነችብኝ።

«አባትሽ መጥቶ አነጋግሮኛል፣ ትናንት»

«ምን ብሎ?... ኡፍ! ቶሎ ንገረኝ»

«መነጋገር አይባልም... ማስፈራራት አይነት ነው። ከልጄ ጋር ያለህን ግንኙነት አቁም አለኝ። ቀላል አይደለም ለኔ ከባድ ፋው አለኝ። እንቢ ካልክ አደጋው ይከፋል ምናምን አለኝ...»

«የምን አደጋ...?» ቅዝቅዝ አለኝ ደሞ ያልበኛል

«አደጋ ያልኩሽ እኔ ነኝ:: እሱ እገድልሃለሁ ነው ያለኝ»

መጥፎ ስሜት ለአፍታ ውልብ አለብኝ:: ወደዚያ ቤት ያለመመለስ... አባቴን የመጥላት... ሙሉጌታን ደግሞ የመውደድ...

«ታዲያ ከኔ ጋ ያለህን ግንኙነት መቼ ልታቆም ነው?» አልኩት ቅዝዝ እንዳልኩ::

«አንቺ ስታቆሚ፣ ወይም ስሞት» አለኝና የተረበሸ መንፈሱን መደበቅ ተስኖት «ሲጋራ እናጭስ? ማለቴ ላጭስ፣ አጫሽ'ኳ አይደለሁም... ብቻ...» እያለ ተደነቃቀፈ::

«እሺ» አልኩት ትከሻዬን ወደ ትከሻው እያቀረብኩ «በርዶኛል ትታቀፈኝ?»

«እሺ»

ለስላሳ መዳፉን በትከሻዬ ላይ አሻገረውና ክርኔን ጠበቅ አድርጎ ወደሱ አስጠጋኝ:: በጆሮዬ «አባትሽ በጣም ይወድሻል» አለኝ «በጣም! የእሱን ያህል በወደድኩሽ»

እስሩ እንደተሸነጥኩ ቀና ብዬ አየሁት፣ አቆልቁሎ ተመለከተኝ:: ትይዩ የነበሩት ከንፈሮቻችን ገጠሙ፣ ሳመኝ:: የተሰማኝን ይሄ ነው ብዬ የምገልጸው አልነበረም:: አላውቀውማ... ብቻ ድንገት እንደፈነዳች አበባ ሁለመናዬ ፍ ት-ት-ት-ት ሲል ታወቀኝ:: ምኞት ምኞት ብቻ ሆንኩ:: ምኞቱ ሲያልፍልኝ ሀፍረት ተከለብኝ:: በዚያ ሀፍረት ውስጥ ሆኜ «ይሄንን መሳሳም ነው እንደቀልድ ፊልም ውስጥ የሚያሳዩን?» ስል አሰብኩ::





# ስድስት

እኔ የሚሰማኝን ልንገራችሁ:: እናንተ የምትፈልጉትን ትርጓሜ ስጡት:: ከዚህ ቀደም ያልነበረ አገልጋይነት ይሰማኛል:: ሙሉጌታን በጽኑ የማገልገል ስሜት ውስጤ ገብቷል:: እንደ ሀንዳዊዎቹ የካልካታ የጋሪ ሰዎች እሱን አሸበልብዬ እኔ ብዳከር ብማስን እመኛለሁ:: ስንገናኝ ግን ሁኔታዬ ስሜቴን ሳይከተል ቀርቶ እሱን ማስጨነቅ ያረካኛል:: እንዳልተገራች ባዝራ ስቅበጠበጥ እኔን ለማረጋጋት የሐሳብ ልጓሙን ጠበቅ-ላላ ሲያደርግና በኔ ጉዳይ ሲጠመድ ደስ ይለኝ ጀምሯል:: ደስ ብሎኝ ደግሞ አይቀርም፣ ያሳዝነኛል::

«ጥናቴን ተውኩት» እለዋለሁ ድንገት

«እሺ» ይላል ላመሉ:: ቀጥሎ ጉዳዩን ያብሰለስልና «እኔ ብሆን ግን አልተወውም ነበር» ይለኛል::

«እኔ አንተን አይደለሁም» እለዋለሁ:: የሆነ አካሉ ስብስብ፣ ኩርምት ሲል ይታየኛል:: የበለጠ ያሳዝነኛል:: «በሚቀጥለው ዓመት እመረቃለሁ:: ኮርሶቹን ብቻ በዚህ ዓመት እጠናቅቃለሁ::»

«እሺ» ይለኛል ለአፍ ልማዱ:: ሲጨነቅ እንደሚያደርገው ሊኳኩል እንዳሰበ ቀይ ዶሮ አውራ ጣቱን ወደ ጢሙ ያስግጋል:: መካከል ላይ እይዝበታለሁ::

«ይሄን ልማድ እንድትተው እፈልጋለሁ»

«እሺ»

«እሺ... እሺ-እሺ» እዚህ ላይ የእውነት እበሽቃለሁ:: በእሱ ላይ ለራሴ የሰጠሁትን ስልጣን ባግባቡ መያዝ እንዳለብኝ እያሰብኩ የተንጠራራ መንፈሴን ለመሰብሰብ እጣጣራለሁ:: እውነቱን ለመናገር እጅግ አድርጎ ያሳዝነኛል:: ከቅብጥብጥ ባዝራ ላይ ተስፈንጥሮ የወደቀ፣ በእሺታ ለመግራት የሚሞክር ፈረሰኛ ሆኖ ይታየኛል:: ባቅፈው፣ አይዞህ ብለው ያምረኛል:: ሁኔታዬ ግን አምሮቴን አይከተለውም:: በመቅበጥበጤ እቀጥላለሁ:: ለእሱ ያረቀቅሁትን ከውሃ የቀጠነ ደንብ ለማስፈጸም እፍጨረጨራለሁ::

መቅበጥበጤና ደንቤ ሰቅዘው ሲይዙት ከዚህ ማምለጫ ጨዋታ ያመጣል:: ስላነበበው መጽሐፍ ይነግረኛል:: ወይንም አንዳንድ ውስብስብ ሐሳቦችን

ያፍታታልኛል:: ይሄን ጊዜ እንደሰማይ ሰፍቶ እንደ ወፍ የለቀቀኝ ያህል ይሰማኛል:: መቼም ቢሆን ከእሱ አድማስ ጋር የመጋጨት አቅም እይኖረኝም ብዬ እደመድማለሁ:: አንድ ጊዜ ድንገት በጨዋታ መሃል...

«ባዮ-ዳይቨርሲቲ ታውቂያለሽ?» አለኝ

«አዎ::» አልኩት

«ምንድነው?» አለኝ

የማያውቀውን ሲጠይቀኝ የዕውቀት እኩያው ያደረገኝ መሆኑ ተሰማኝና ደስ አለኝ «ባዮ-ዳይቨርሲቲ ብዝሃ-ሕይወት እየተባለ የሚተረጎመው ነው:: የአካባቢ ጥበቃ ፅንሰ-ሀሳብ ነው:: ለምሳሌ አንድ ዛፍ ቢቆረጥ አካባቢያችን የሚያጣው አንድ ዛፍ ብቻ አይደለም:: እላዩ ላይ ጎጆ የሰሩ ወፎች ይሰደዳሉ፣ ነፍሳቶች ይወድማሉ፣ አፈር የሚያለሙ ትላትሎች ይጠፋሉ፣ ዛፉን ጥላ አድርገው የሚበቅሉ ብዙ ዓይነት ተክሎች ይወድማሉ:: የዚህን ህብር ነው ባዮ-ዳይቨርሲቲ ወይም ብዝሃ-ሕይወት የሚሉት::»

እየተካከዘ አውራ ጣቱን ወደ አፍንጫው ገደማ ሲሰድ መካከል ላይ ያዝኩበት:: ብንን እንደማለት ብሎ አየኝና ፈገግ አለ-በሩህ ፈገግታ:: ቀጥሎም:-

«ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እኛ መንደር ላይ ይሄ ህብር ሲናጋ ይታየኛል:: ጠቀመም ጎዳም መንደራችን ሲፈርስ አብሮ የሚጠፋ ሕብር አለ:: እንደትላትልን እንደነፍሳት ልትቆጥሪያቸው ትችያለሽ:: ግን አንድ የመንፏቀቅ ገድል ጨርሶ ሊጠፋ ነው:: መንደርተኛው ብቻ እንደ አንድ ቤተሰብ ሆኖ ሲያቦካው የኖረ፣ ምናልባትም የተዘነጋ የሰው ልጅ ሁሉ ታሪክ:: ኤቨርሊን ሪድ «ውመንስ ኢቮሉሽን»ን ስትጽፍ ከአንድ ኋላ ቀር መንደር ተነስታ የሴቶችን ሁሉ ታሪካዊ አመጣጥ እንዳሳየችው:: የኛም መንደር የሰው ልጅ የአንድ ሰሞን ታሪክ የመጨረሻ ማሚጠጫ ትሆን ይሆናል» አለኝ::

ከዚች ዕለት ጀምሮ «የመንፏቀቅ ገድል» ሲል የሰየመውን ማስታወሻ እየጻፈ ይሰጠኝ ጀመር:: ማስታወሻዎቹ እኔ ላይ ያሳደሩብኝን ስሜት መግለጽ እናንተ ንባብ ላይ ተፅዕኖ ማድረግ ሆነብኝ:: ስለዚህ በሌጣው እንድታነቡት መልቀቅ ተገቢነት ሳይኖረው አይቀርም::





# ማስታወሻ

## ፩

መንደራችን ለቤተ-መንግሥት ቡና የሚያጣጣ ርቀት ላይ ነው ያለችው:: ለፓርላማ ተጎራባቾች ነን:: እንደውም በየቤቶች ሽንቁር አጮልቀን የምንመለከተው የፓርላማን ሰዓት ነው:: በየሩብ ሰዓቱ የሚደውለው የፓርላማ ሰዓት ሳንጠራው በየቤታችን ጎራ እያለ ጊዜውን ያስታውሰናል::

ከአቧሬ ተነስቶ በፓርላማ ግርጌ አድርጎ ወደ አራ በከንቱ የሚዘልቀው የአስፓልት መንገድ ገና የትራፊክ መብራቱን ሻገር እንዳለ በስተግራ ከሥጋ ቤቶቹ መደዳ የመጨረሻው ጫፍ ላይ ነው የመንደራችን መሿለኪያ ያለው:: ይሄ የመንደራችን መግቢያ በር «መቆሚያ ጣቢያ» ብለን ነው የምንጠራው:: የመንደራችን ሴተኛ አዳሪዎች የሚቆሙበት በመሆኑ ነው «መቆሚያ ጣቢያ» መባሉ:: ያ እንደጉሮሮ የቀጠነው መንደራችን መግቢያ ብዙ በጣም ብዙ ሴተኛ አዳሪዎችን አስተዳድሯል:: ዛሬ-ዛሬ ያሉት ነባር ሽርሙጦች በጣም ጥቂትና በዕድሜያቸው መግፋት ብዙ መቆም ስለሚቸግራቸው በርጩማ ላይ የሚቀመጡ፣ ብርዱንም ስለማይቋቋሙ እሳት በማንደጃ የሚታቀፉ ናቸው:: ሁሉም የሲጋራ ሱስ ያለባቸው በመሆኑ የመንደሩ ወንዶች ሲገቡ «እስኪ ሲጃራ ግዛልኝ» የሚል የመረታት ጥያቄ ያቀርባሉ::

ሴተኛ አዳሪዎቹ የአንድ ዘመን ትውልድ መሆናቸውን የሚያሳይ አንድ ዓይነት ፀጉር አበጣጠርና አኳኋል አላቸው:: የዚህ አይነቱን የፀጉር አበጣጠር በጥንቱ የነብዙነሽ በቀለ የቴሌቪዥን ዘፈን ላይ ተመልክቼዋለሁ:: ዘመን ያልሻረው የጥንት ሴተኛ አዳሪዎች ባህሪም አላቸው:: እያስካኩ በመሳቅ ቀልብ መሳብ፣ ብክትክት ያለ ስድ ማከናነብ... «ሴቶ! ነይ እስኪ ሱሪሽን አውልቂው!» እያሉ ወንዱን መሳደብ:: በፍቅር ጊዜ እፍ እፍ ብሎ ሳምንት ሳይሞላ መሰዳደብ::

አንድ ሦስቱን በአካል ባስተዋውቅሽ አይሻልም?

አንዷ አልማዝ-ሚኒቄ ናት:: ቅጭጭ ባለው አካሏ ላይ ድፍን የድሮ ሂል ጫማ አድርጋ ስትሄድ ስለምትጫቅ ነው ሚኒቄ ያሏት:: ሌላዋ ማሚ-ባሊ:: ባሊ

የተባለውን ቅፅል ሥም ያገኘችው በሁለት ጉዳይ ነው ይባላል፡፡ አንዱ ወገን ባሊ ሰርቃ ነው ሲላት ሌላኛው ወገን ግን ብዕሬ ሜፍ ባልደፈረው ጉዳይ ነው «ባሊ» የተባለችው እያለ ያማታል፡፡ ሦስተኛዋ ምንጊዜም እንደ ልጃገረድ የምትሽኮረመመውና የምትሞላቀቀው ሮማን «ሲ» ናት፡፡ «ሲ» ያሏት የአካባቢው ወጣቶች ናቸው፡፡ እሷ ቆማ የምታመሽበት (የምታድርበት ማለት ይቻላል) አካባቢ የተደረገውን አንድም፣ ሳይቀር ስለምታወራ የተዘረፈ፣ የተቀማ፣ የተነጠቀ ሳይቀር ስለምትናገር ለዚህ ፀባይዋ «ሲለዩ» (ኢቃጣሪ) አሏት፡፡ ሲያሳጥሩት «ሲ»፡፡

እነዚህ ሦስቱ አንዷ ከአንዷ ጋር አትጣላ! ከተጣሉ ዓለም ትበከታለች፡፡ ሰው መሆንሽን እንድትፀየፊ ነው የሚያደርጉሽ፡፡ እኔ አንዳንዴ ስድባቸውን ስሰማ «ሰው የሚሉት ፍጥረት እንዲህ የበከተ ነገር ነው ይዞ የሚዞረው?» እልና ለተወሰነ ጊዜ ሰውን ሁሉ እፀየፋለሁ፡፡ የነዚህ ሴተኛ አዳሪዎች ፍቅራቸውም እንደዚያው «ብን» ያለ ነው፡፡ አብሮ በልቶ፣ አብሮ ጠጥቶ እየተጋገዙ ሌላውን በስድብ ማቡነን፡፡

ከእነዚህ ከሦስቱ ሴተኛ አዳሪዎች አንዷ አልማዝ-ሚኒቁ በቅርብ የሞተች ሲሆን ሁለቱ ግን ከተቀናናሽ ኑሮአቸው ላይ ይበልጥ ተቀናንሶ የዘቀጠ አኗኗር ላይ ይገኛሉ፡፡ ማሜ-ባሊ ሲበዛ ሱሰኛ ናት፡፡ ሲጃራ ጫት፣ መጠጥ... ከሙተለቁ የተነሳ የሚያስፈራ ዓይን አላት፡፡ ፊቷን ዓይን ብቻ የሚያስመስለው የአካሏ መቀጨጭና የቁመቷ ማጠር ይሆናል፡፡ ሥራዬ ብላ ወንድ ጥበቃ አሳቷን ታቅፋ የምትቀመጠው ከምሽቱ አምስት ሰዓት በኋላ ሰማይ-ምድሩ ሲሳከር ነው፡፡ ከዚያ በፊት ግን የአካባቢውን ወጣቶች እሮጣ በማነቅ አንድ-ሁለት ብር እየለመነችና እያጠራቀመች ነው የምታመሸው፡፡ አካባቢው ላይ ኖራ ወደማርጀቱ የተቃረበች በመሆኑ የሚጨከንባት የለም፡፡

ከምሽቱ አምስት ሰዓት ከሞላ በኋላ እሳቷን ታቅፋ እንደተቀመጠች በቁመቷ ማጠርና በአካሏ መቀጨጭ ልጅ እየመሰለቻቸው ሰካራሞች አብረዋት ለማደር ይስማማሉ፡፡ ይሄኔ ወንዱ ከሚሰጣት ብር ሌላ የሰካራሙን ቀሪ ገንዘብ መዝረፏ የማይቀር ነው፡፡ ገንዘብ ካገኘች ደግሞ እስኪነጋ አላደርስ ስለሚላት ሰውየውን ባዶ ሽቦ አልጋ ላይ አስተኝታ ፍራሹን በማውረድ ጫት ገዝታ እሜጭሳ ብርችንችን ያለ ሌሊት





ለማሳለፍ ትሞክራለች፡፡ በሽቦው ቅዝቃዜ ያ-ሰካራም ሳይነጋ ሊበርድለትና ሊነቃ ይችላል፡፡ ኪሱን ሲፈትሽ ባዶ፡-

«እንዴ?...? ገንዘቤስ?»

«እንጃ አባክ!!» ማሜ ባሊ ከወሰደችበት ወንድ ጋር ከመደራደር ይልቅ ፀብ ትመርጣለች፡፡ ወንዱ ሰው እንዳይሰማበት የሚፈልግ ከሆነ ዝም ብሎ እንዲሄድ፣ አለበለዚያም ለሰው ደንታ የማይሰጠው ከሆነም መግለብለቧን ትቀጥላለች፡-

«የትም በየቦታው ስትደፋ፣ እኔም ወንድም አለኝ ብዬ አልጋዬን ለቅቄ ባሳደርኩ? እፀድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች አለ፡፡ አሰፍስፈው ሲጠብቁህ የነበሩት ማጅራት መቺዎች ጥርስ በገባሁ እንደገና እኔኑ ሌባ??... እንዲህ ከሆነ ያደርክበትን ሳትከፍል ከዚህ ቤት አትወጣም!!...» ተለማኝዋ እሷ ትሆናለች፡፡

ሮማን ሲ ጠይም፣ መልከ-መልካም፣ የሴት ወይዘሮ ውፍረትን ቁመት ያላት ናት፡፡ ሲጃራዋን እየሳበች በረጅሙ ትኳልና በሲጃራው ጭስ አንድ ዓይኗን ጨፍና በጊዜ ወጥታ እስኪደከማት መገተር ነው፡፡ ከዛ በኋላ ነው በርጩማና እሳት የሚያስፈልጋት፡፡ ሮማ ሲ-ስለራሷ ያላት ግምት ሊገርምሽ ይችላል፡፡ «ልጅ ነኝ» ከማለቷ የተነሳ ሰው ስታናግር (በተለይ ወንድ) ለመኮለታተፍም ይዳዳታል፡፡ ለኔ አዋቂ መስላ የምትታየኝና እሷም ትልቅ አዛውንትነት የሚሰማት አመሻሽ ላይ ከሽንት ቤት ስትወጣ ወደ ጀንበር መውጪያ ፊቷን መልሳ እግዚአብሔርን ስትወተውት ብቻ ነው፡፡ ከመንደሩ የጋራ ሽንት ቤት አለፍ ብሎ ያለው ቀጭን መተላለፊያ ለሮማን-ሲ ቤተክርስቲያኑዋ እሱ ነው፡፡ ዕድሜ ልኳን ቤተክርስቲያን ስትሄድ አይቻት አላውቅም፡፡ ብቻ አመሻሹ ላይ ቀጭኑን መተላለፊያ ሙጥኝ ብላ ማነብነብ ነው፡፡

ሮማን አዘውትራ የምታወራው ወንድን ለማስተናገድ አካሏ እንደማይችልላት ነው «ማህፀኔ ጠባብ ነው» ትላለች፡፡ ለራሷ ሁሌም ልጅ ናት፡፡ ወንድ ሲያነጋግራት ካጋጠመኝ ምንም የማታውቅ ልጃገረድ ትመስለኝና የምመለከተውና የማውቀውን የገረጀፈ አቋሟን እጠራጠራለሁ፡፡ ለካ የተዋናዮች ሜካፕ እና አልባስ የድክመታቸው ማገገሃ ነውና፡፡ ሮማን «ሲ» ሁልጊዜም ንጭንጭ ይቀናታል፡፡ የመንደር ሰዎች «መቆሚያ ጣቢያ» ጋ ሰው አግኝተው ለትንሽ ሰከንድ ቆም ካሉ፡-

«ወንዱ በየት በኩል ይግባ?» ብላ ትነጫነጫለች:: እኔ አመሏን ስለማውቅ እዚያ አካባቢ ላለመቆም እጠነቀቃለሁ:: ሾከክ ብዬ ሳልፍ «ሙልዬ ደህና አመሸህ?» ትለኝና «እስኪ ሲጃራ ግዛልኝ?» ትለኛለች:: ብችል ገንዘብ አይደለም ለሷ መስጠት የምፈልገው፣ የሲጋራ ሲሷን መንጠቅ::

ሮማን-ሲ ሲበዛ ጉልበተኛና በቴስታ ስለምትማታ ከመንደራችን ውስጥ የምትፈራው የላትም:: ከኛ ሠፈር እንደልቧ የምትናገራት አንድ ቲያትር ቤት በጽዳት ሥራ የምታገለግል የነበረችው አባይነሽ-ዲናሞ ብቻ ናት:: ዲናሞ የፊት ጥርስ የሌላት በመሆኑ ስትናገር እየተኮላተፈች ምራቋን እየረጨች ነው:: በይበልጥ ሰው ለማማት ሆነ ሳንቲም ለመለመን ወደ ጆሮ ጠጋ ብላ ስታወራ ጆሮሽን ኮርኩራ-ኮርኩሪ ያሰኝሻል:: ከመንደሩ ወጣቶች ጋ ሲበዛ ስለምትግባባ ነው ሮማን የምትፈራት:: ግንኮ እሷም ሀይለኛ ናት::

«ዲ-ዲ-ዲ-ዲ...» የመንደሩ ጎረምሶች ይወዷታል::

ዲ-ሮማን-ሲ የቆመችበት ሄዳ የሲጃራ እሳት ትካፈላትና አብረዋት ለማይጠፉት ወጣቶች እንዲህ ትላቸዋለች እየተጣቀሰች

«አንተ «ኤ» ነህ፣ አንተኛው «ቢ» ሮማን ደግሞ «ሲ» እኔ «ዲ» ትልና በቅኔ ተሳድባ ሮማን ሲን በማይወዷት ጎረምሶች ታስቀባታለች::

አባይነሽ-ዲ በይበልጥ የደምዝ አካባቢ ጠጥታ ስትመጣ ማንንም አትፈራም:: ኃ/ሚካኤል እፉፉ ንኳ ቢሆኑ ጠርታ ትሳደባለች:: «ነፍናፌ፣ የዘንድሮ ሽታ እንኳን ላንተ አፍንጫ ለኛም ያዳግታል» ትላለች:: እፉፉ በመናደድ ለአንድ ሰሞን ሆን ብለው በመስከር ይጠብቋታል:: ዲ-ትጠነቀቃለች::

«እኔ ቀጭኗ ማንንም አልፈራማ!» እየተውረገረገች:: እውነቷን ነው ማንንም አትፈራም:: እኛ መንደር ያልሰደበችው ሁለት አዛውንቶችን ብቻ ነው:: «እኔ ቀጭኗ! እንቆቆ ሁሉ! የመንግሥት ሠራተኛኮ ነኝ» እያለች በጥርስ አልባ ድዷ በምትከረታትፈው ንግግሯ በጅምላ ሠፈርተኛውን ትሳደባለች::

እሷ ቤት የሚገቡት ወጣቶች እየተሳሳቁ ሲከቧት ዲናሞ ከሰከረች ወጥ በምትሰራበት ድስት ሽንቷን ትሸናበታለች ይላሉ:: ግድ የላትም:: ቡና ካፈላች የቡና ሲኒ ስለሌላት በፊሊት ቆርቆሮ ከዳን ነው የምትጠጣው፣ ምሰሷ የላውንደሪ ወረቀት፣





የቤቷን አይጦች እንደ ልጅ ትቀጣቸዋለች አሉ:: እሷ ከውጭ ስትገባ ትርምስምሳቸው ይወጣል፣ «ማናባታችሁ! ምናባታችሁ!» እያለች ለመለኮፍ ትሞክራለች::

አባይነሽ-ዲ አራድነቷ ለወጣቶች የሚስማማ ነው:: ገንዘብ ካላት ወጣቶቹን መጋበዝ ነው:: የምትጠጣበት ግሮሰሪ ደግሞ ማምታታት፣ ማጭበርበር፣ በሰዎች ማሾፍና መተረብ:: ከቻለች ፀብ ማስነሳት... ስለዚህ ወጣቶች ሲበዛ ይወዷታል::

«ዲ-ዲ-ዲ»

ለምን «ዲናሞ» እንደተባለች አላውቅም:: እኛ ሠፈር ከመምጣቷ በፊት ነው ስሙ የወጣላት:: ተወልዳ ያደገችው ከኛ መንደር በስተጀርባ ካለው «ኮባ ሠፈር» ነው:: እየሰከረች ስትበጠብጥና ሠፈሩ የሰላማዊ ሰዎች መኖሪያ በመሆኑ አምጥተው እኛ መንደር ከመሰሎቿ ጋር ቀላቀሏት:: አንድ ሀብታም ነጋዴ ወንድም አላት:: ዞር ብሎ አያያትም እሷም ካጋጠማት ሙልጭ አድርጋ ትሰድበዋለች:: ታዲያ ወንድሟ የጉራ መንፊያዋና የዱቤ መጠየቂያ ደረሰኟ ነው::

«የእናቴ ልጅ ከዳር አገር ዕቃ አምጥቶልኛል:: የዚህ ሠፈር ሰው ዓይን እንደሆነ የምታውቁት ነው:: ምቀኝነታቸውስ? እኔ ምኔ ሞኝ ነው? እሱን ቸብ! አደርግና ለሰፈሩ ተስማሚ ሶፋ እገዛለሁ:: በተራረፈው ደግሞ ለደስ-ደሱ አንድ ሌሊት ሙሉ መጨፈር ነው...» እያለች የምድረ ካቲካላ ሻጭ ጉሮሮ ማሾህ ነው:: በብዙ ዱቤ መብቸንቸን...!

ወይንም:-

ከወጣት ጓዶቿ አንድ ሁለቱን ይዛ እቤቷ ትገባና እፉፉን በውሸት ስታጓጓ «...ወንድሜ ያስገባልኝ ቅርጫ ነው:: ያውልህ ቋንጣ አውርድና ብላ:: ኧረ ብላ! ጠላታችን አፈር ይብላ! ብላ! ያውልህ እዚያ ሳጥን ውስጥ አሳይኝ ያልከኝ ወንድሜ የላከልኝ 20 ሜትር ጨርቅ:: እድሜ ለወንድሜ! ቴሌቪዥኑ አንተ ጋ ይቆይ ብዬዋለሁ... የኛን ሰፈር ሰዎች ታውቃቸው የለ? ይሄንን በሬን ሳላሰራ አምጥቼ ምን አደርገዋለሁ?... ያውልህ እዚያ ጠርሙስ አረቄ ከፈትና ጠጣ?...» ትልና በመጨረሻ «ማን አፍንጫ አለውና ያሸታል ብለህ ነው የፈራኸው?» ትመርቅበታለች:: ይሄኔ እፉፉ ካልሰከሩ ይችሏታል:: ከሰከሩ ግን በወዲያ ይዞሩና በሯን በቡጢ፣ ነርተው-ነርተው አልከፈት ሲላቸው ጥለው ይሄዳሉ:: ዲ በተዘጋ ድምጿ ለመጮህ ትሞክርና

ቀበሌ... አብዮት ጠባቂዎች ስለሰለቻቸው «አዝማሪ ሠፈር አንሄድም!» ማለት ጀምረው ነበር፡፡ እሺ ብለው ከመጡም ከነሱ ጀርባ ሆና ጣቷን አፍንጫዋ ላይ እየጣደች እፉፉ ታሳያቸዋለች፡፡ እፉፉ ቱግ! ይላሉ፡፡ «ይኸዋ-ይኸዋ ገና ሲያዩኝ ቱግ! ይላሉ እኔ ምን እንዳደረኳቸው እንጃ!» ትላለች፡፡

አባይነሽ-ዲ ከእፉፉ ጋር ከተጣላች ይደበድቡኛል ብላ ስለምትፈራ ከሚወዷት ወጣቶች አንድ ሁለቱን ይዛ በመምጣት እቤቷ ታስገባና፡-

«ሻለቃ ዝም ብለው ይስሙልኝ! ይሄ ቆራጣ አፍንጫ የሚለውን ለመስማት አይደል የመጡት?... አብዮት ጠባቂማ አልቻለውም ያው እንደተነጋገርነው እዛው ከርቸሌ ስደዱት...» ትላለች እፉፉ የሰከሩ ከሆነ፡-

«ቆይ አንቺ ሬብ አፍ! እኔ ኃይለሚካኤል...» ይላሉ፡፡ እኛ ስለለመድነው እንጂ የሚሉትስ አይሰማም፡፡ ብዙ ፊደሎች እየከሸፉ አይተኮሱላቸውም፡፡ «ሽ-ሽ-ሽ-ፉ--ፉ--» የሚል ይበዛዋል ንግራቸው፡፡

ልጆች ሆነን እኔና ጓደኞቼ እንደምንም እናጠራቅምና ሃምሣ ሳንቲም ሲሞላ ዲናሞጋ መብረር ነው፡፡ እሷ ታዲያ ትሰበስበንና ወደ ትኬት በጫቂዎቹ ጋ ታቀርበናለች፡፡

«ጋሼ መሐሪ፣ ይኸውሎት የእህቴ ልጅ ያልኮት ይሄኛው ነው፡፡ ከአዲሱ ቄራ ድረስ ጓደኞቹን ሰብስቦብኝ መጣ!» ትልና ወደኔ ዞራ በውሸት ቁጣ «አንተ? አፈር ብላና ጉልበት አትስምም?» ብላ ጉልበት ካሳመች በኋላ እንደምንም ተለማምጣ ታስገባናለች፡፡ ወዲያው ከበስተኋላችን ትመጣና እንደ ንግድ በግ ቆጥራ በሃምሣ ሳንቲም ሂሳብ ትቀበለናለች፡፡ እኛ ሃምሳ ሳንቲም ካላጣን ነጋ ጠባ ይሄው ነው፡፡ በተለያየ ምክንያት ጉልበት ስሞ መግባት፡፡ አንዳንዴ ህጻናቶች አሥር-አስራአምስት ሳንቲም ከያዙ ፊልም ልታስገባቸው ቃል ትሰጥና ሲጃራ ገዝተህ ና ትላቸዋለች፡፡ ...ከባሰም አመሻሽ ላይ መቆሚያ ጣቢያ ወጥታ ትቆማለች፡፡

«የበለጣችሁኝ እንዳይመስላችሁ ዲ እኔ ቀጭኗ ምን አጥቼ!» ትላለች ለችግር ጊዜ ሽርሙጥና ማስተባበያ፡፡

አንድ ጊዜ አዲሱ ቄራ አካባቢ ቡና ቤት የነበራት እህቷ ትሞታለች፡፡ ወንድሟ ስላልፈለገ ያለ የሌለውን የእህቷን ዕቃ ጠራርጋ እቤቷ ታስገባለች፡፡





እንዳሰበችው ለሳምንት ይሁን ለአስራ አምስት ቀን ቤቷ በውድ ዕቃዎች ይሞላል፡፡ የእህቷን ዕቃ በክብር ማስቀመጧን ታወራ ነበር ተሽጦ እስኪያልቅ ድረስ፡፡

«እህቴ የእናቴን ውቃቢ የተቀበለች ናት፡፡ የሷን ዕቃ አክብሬ ካላስቀመጥኩ መቅኖ ቢስ እሆናለሁ» ትል ነበር፡፡ በእርግጥም ዕቃውን ለመጠጥ ሸጣ እንደጨረሰች አልጋ ላይ ዋለች፡፡ አንድ እጇና እግሯ በድን ሆነ፡፡ መናገር የማትችል አገጯን የማትሰበስብ፣ ለሃጯ የሚዝረበረብ ቃማሚ... አንዳንድ ቀን እንደ ዲ ያሉ ሰዎች ከዚህ ሠፈር ተነቅለው ምንድነው የሚሆኑት እያልኩ እብከነከናለሁ፡፡ እውነት ዛሬ ዲ ሕይወት ያለው ሙቀጫ ሆናለች፣ እና ከአራት ኪሎ ተነቅላ እዚያ ስትተከል የሞት ፍርድ አይሆንባትም?

# ፪

አሥፋ ይርጉ አዋጅ የሚያነበው ጋዜጠኛ ከማርሽ ሙዚቃ በኋላ «ከጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የተሰጠ መግለጫ

«ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

በአምባገነንነትና በማን አለብኝነት የአገርህን ዳር ድንበር በመድፈር ተጠብቆ የቆየውን የነፃነት ታሪክ...

«...ሁሉም ወገን እራሱን፣ ቤተሰቡንና አገሩን ለመከላከል ዝግጅቱን ማጠናቀቅ አለበት...»

መቼም የዚህን ጋዜጠኛ ድምጽ ሲሰማ የማይርድ የለም፡፡ ሱማሌ የኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ክፍል በመውረርና በወቅቱ የነበራት ኃይል አዲስ አበባ ሊያስገባት ይችላል ተብሎ ስለተፈራ በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት በኩል ይሄ መግለጫ ተሰጥቶ ነበር፡፡

በዚህ ሠዓት ላይ እኛ ቤት አያቴ አልጋው ላይ ቁጭ ብሏል፡፡ እኔ ሁልጊዜም የምቀመጥበት እግሩ ስር ካለች በርጩማ ላይ ተቀምጫለሁ፡፡ አያቴ በንዴት የያዘውን በአረቄ የፈላ ሻይ ለኔ ሰጥቶ ጊዜውን ይረጋግም ጀመር፡፡

ሴት አያቴም እየተርበተበቱ መላ-መላ ያሉትን ሁሉ ለወንድ አያቴ ያማክራሉ፡፡ ወንድ አያቴም አልፎ አልፎ «ፍሬ-ፈርስኪሽን ተይው!» እያለ ይቆጣቸዋል፡፡

ትዝ ይለኛል ከሴት አያቴ መላ አንዱ በረብሻ ምክንያት ከቤት መውጣት ባይቻል የመንደራችንን ቤቶች ግድግዳ እየቀደዱ (ተያያዥ ነውና) አንዱን ቤተሰብ ከሌላኛው ቤተሰብ ጋ ውስጥ ውስጡን ማገናኘት ነበር፡፡ በእርግጥም መንደራችን ካቀፈቻቸው ከሰባ በላይ ቤቶች ግድግዳዎቻቸው ቢነደሉ አንድ ጥሩ ዋሻ ይወጣቸዋል፡፡

ያለማጋነን አንድ ሰው ከጣሪያ ላይ ሳይወርድ መንደራችንን ሊያካልላት ይችላል፡፡ የአንድ እርምጃ ያህል'ኳን መራራቅ በየቤቶቹ መሀል አይገኝም፡፡ እንደቤቶቹ አሰራር ሁሉ የመንደሩ ነዋሪዎች ገመናቸውን ሳይቀር ደበላልቀው ነው የሚኖሩት፡፡





«ጎረቤት እያወቀው ምስጢር፣

ወንፊት እያጠራው አፈር፣ የለም» ይሉሻል እኛ መንደር ነው፡፡ እያንዳንዱ የመንደሯ አባል ማን-ምን እንደበላ እና ማን ጾሙን እንዳደረ በየጎረቤቶች መዝገብ ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ከዚህ ድብልቅልቅ ማህበራዊ አኗኗር ውስጥ ማፈንገጥ አይቻልም፡፡ መንደርተኞቹ ሲያድሙ እና ሲተባበሩ እንደ አንድ ሰው ሆነው ነው፡፡

የመንደራችን ነዋሪዎች ኑሮ እየሸነቆጡች የምታሯሩጣቸው በመሆኑ እንደ ግራዋ አበባ በየአቅጣጫው ይረጫሉ፡፡ በዚህም ምንም ተደብቃ የምትደረግ ነገር የለችም፡፡ ከተበተኑበት ሲሰበሰቡ አፋቸውን ገጥመው ስላጋጠማቸው መረጃ መለዋወጥ ነው፡፡

-ዛሬ አገሌ ከእገሌ ሚስት ጋር እዚህ ቦታ ታይተዋል፡፡

-የእገሌን ልጅ ፖሊስ እያዳፋ ወስዶታል፡፡

-እትዬ እከሊት ውቃቢ ቤት አድረው ሲወጡ ታይተዋል፡፡

ትዝ ይለኛል፣ ልጅ ሆኜ ከት/ቤት ከፎረፍኩ አንዷም ሳትቀር የነበርኩበትና ያደረኩት ለሴት አያቴ ጆሮ ይደርሳል፡፡ እኔ አገር ሰላም ብዬ ስመለስ...

- ዛሬ ቢያሳ ምን ታደርግ ነበር?

- መርካቶ ያየህ ሰው አለ፡፡

- ይሄ ሲሊማ አይቀርም?

- የምን ባስቴ ነው ስትበላ የነበረው? ይሉኛል፡፡ ማን እንዳየሽ እንኳን ሳታውቂ ትታያለሽ፡፡ በመረጃ አሰባሰብ በኩል የመንደራችን ነዋሪዎች ለሌላ መንደር ይተርፋሉ፡፡ አንዳንዴ አካባቢው በአሉባልታ እሳት ይጋያል፡፡

የመንደራችን ሴቶች ትብብራቸው ወሰን የለውም፡፡ አንዷ በአንዷ የግል-ሕይወት ላይ ያላት ሙበት ዳር-ድንበር አልባ ነው፡፡ አንድ ጊዜ አንዷ የመንደራችን ሴት ወዴት እንደሆነ እንጃ ትሄዳለች፡፡ በዚህ ጊዜ እጅሬ ባል ሲያደፍጥ ቆይቶ ሲመሻሽ አንዲት ሴት ይዞ ይመጣል፡፡ በሴቶቹ ታይቷል፡፡ ምን አገባን? አላሉም «ለኛም ጊዜ ይኸው ነው» ተባባሉ፡፡ በነጋታው በሌሊት ተቀሳቅሰው ሰውዬው በር ላይ ቁጭ፡፡ ሴትዮዋ በየት ትውጣ? ግራ ገባት! ቢጨንቃት ጋቢ ተከናንባ ለመውጣት ትሞክራለች፡፡ ከዚያማ ምኑን ትጠይቂኛለሽ? ጨንዶቹ ናቸው ነፍሷን ያተረፉት፡፡ ያ-

አጋጣሚ የመንደራችንን ወንዶች እንዲማሩ እጃቸውን ይዞ ነው የሥነ-ምግባር ፊደል ያስቆጠራቸው፡፡

የመንደራችንን ጉዳንጉድ በአንኳሩ ካልሆነ በዝርዝሩ የሚዘልቀው የለም፡፡ ሴት አያቴ ሲነግሩኝ ከሰላሳ እና ከአርባ ዓመት በፊት የኛ መንደር የከተማችን ሁሉ አዝማሪዎች መኖሪያ ነበረች አሉ፡፡ አሁንም የምትታወቀው በዚሁ ስሟ «አዝማሪ ሰፈር» በመባል ነው፡፡

የስም ነገር ሆኖ እንጂ አሁን እንኳን ያሉት አዝማሪዎች ብዛት ከአንድ እጅ ጣት የሚዘሉ አይደሉም፡፡ በፊት ግን አሁን በባህል ዘፈን ታዋቂ የሆኑት እነ አሰፋ አባተ እና አንድ በዋሽንት ስርቅርቅታው የሚወደድ እዚሁ እኛ መንደር ኗሪና ተመላላሽ ነበሩ፡፡

አሁን በኔ ዕድሜ እንኳን መንደራችን የነበሩት አዝማሪዎች በጣም ብዙ ነበሩ፡፡ አንድ ቤት ውስጥ እስከ ሰባት ቤተሰብ ድረስ በደባልነት ሲኖሩ አስታውሳለሁ፡፡ ታዲያ እነዚህ አዝማሪዎች በነበሩበት ጊዜ ሌሊቱን በእንቅልፍ ማሳለፍ የመንደራችን ባህርይ አይፈቅደውም ነበር፡፡ አዝማሪዎቹ በየመጠጥ ቤቱ ሲዘፍኑ አምሽተው እኩለ-ሌሊት ላይ ሲመለሱ የገንዘብ ክፍፍል ፀብ አይቀርም፡፡ የሚገርምሽ ባልና ሚስት ሆነው'ኳን ያገኙትን ይከፋፈላሉ፡፡ ትዳር እንዲመሰርቱ የሚያደርጋቸው ማሲንቆው ብቻ ነው፡፡ አለበለዚያ ሴቶቹ በሽርካ ለመዝፈን ብዙ ጣጣ አለባቸው፡፡ ወንዶቹ ማሲንቆ መምታት ብቻ ሳይሆን መዝፈኑንም ስለሚችሉ ሴቶቹን በሚስትነት ካልሆነ በስተቀር በሽርካት ማስከተልን አይፈልጉም፡፡ ሴቶቹ ወንዶቹን ስለሚንቋቸው ማግባት ግድ ይሆንባቸዋል፡፡

ታዲያ ያኔ እነሱ በብዛት በነበሩበት ጊዜ ሌሊቱን በድብድብ ወይንም በዘፈን ገትረው ያነጉት ነበር፡፡ ለሥራቸው ሲዘፍኑ አምሽተው እቤታቸው ሲገቡ ደግሞ ለስሜታቸው ይጀምራሉ፡፡ ይህን ጊዜ ወንድ አያቴ

«አንተ ምናምንቴ፣ አንተኛበትም?» ሲል ድምጹን ከፍ አድርጎ ይሳደባል፡፡ ይፈሩታል ወይንም ሲቸግራቸው እሱጋ ለብድር ስለሚመጡ የግዳቸውን ያከብሩታል፡፡ ወይንም ዝም ይሉታል ወይንም...





እነዚህ አዝማሪዎች የዋዛ አይደሉም፡፡ ሲበዛ አሽሙረኞችና አብሻቂዎች ናቸው፡፡ እርስ በእርሳቸውም ሆነ ሌላውን ሲያበሽቁ ነው የሚውሉት፡፡ አንዱን ጀባ ልበልሽ...

...ሁለት አዝማሪዎቻችን ወደ አንድ ግሮሰሪ ለመጫወት ሲገቡ አንዱ ጠጪ ይመለከታቸውና «በዝንጀሮ ተወረርን አይደለም'ዴ?» ይላል አሉ፡፡

ሰውዬው በእርግጥም ትክክል ነበር፡፡ ወንዱ አዝማሪ አቦዬ ይባላል ጥቁር፣ መላጣ እና ፊቱ ላይ ፀጉር የማይጠፋ ጎስቋላ የጠጣ ሳቅ ያለው ቀንጥንጥ ሰው ነው፡፡ ቀልዱ ሙዝዝ ያለ ከመሆኑ የተነሳ ሰው ለማሳቅ ሲል በላይም በታችም እስከ ማግሣት ይደርሳል፡፡

ሴቷ አዝማሪ አሰለፈች ትባላለች «ቅምቅም» ብለው ቅጽል ስም ያወጡላት አዝማሪዎቹ ናቸው፡፡ አፏን ስትመለከችው የተቀመቀመ ጠይም ጨርቅ ስለሚመስልሽ ነው ቅምቅም ብለው የሚጠሩዋት፡፡ ቂጢኝ ይመስለኛል ፊቷን ጠባብሶ አበላሽቶታል፡፡ ሰውየው ለዚህ ነው «በዝንጀሮ ተወረርን አይደልዴ?» ማለቱ፡፡ የቅምቅምን ድምጽ አታንሺው (ጣት የሚያስቆረጥም ነው - ለዘፈን ባይባልም) አዝማሪዎቹ ሲያበሽቋትም ይሁን እንጃ አንዳንዶቹ ጠጪዎች ፊትሽን ወደ ግድግዳ መልሰሽ ዝፈኝ ይሏታል አሉ፡፡

ሁለቱ አዝማሪዎች ያንን ተሳዳቢ ሰው እንዳልሰማ ሆነው ይቀመጡና ዘፈን ሲጀምሩ፣ ቅምቅም ነጠላዋን እየቋጨች እንዲህ ስትል የግጥም መልስ ሰጠችው፡፡

«ሆዱ እንደርጉዝ ሴት ከተንገፈጠጠው
ዝንጀሮ ይሻላል ሮጦ የሚያመልጠው»

የዚያ ተሳዳቢ ጓደኞች ከቱኛ ተንፈቀፈቁ፡፡ ግጥሙን አስደግመዋት ብዙ ብር ሸለሟት፡፡

ይኸውልሽ አሰለፈች ከሞተች ወደ አራት ዓመት ሳይሞላትም የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ድሮ-ድሮ ኢትዮጵያ ሬዲዮ ሄዳ የተቀረፀችውን ዘፈኗን አልፎ አልፎ በባህል ሙዚቃ ፕሮግራም ላይ እሰማዋለሁ፡፡ እሷ በሬዲዮ ከዘፈነች ሴት አያቴ፡-

«ምናለ የሞተ ባያስለፈልፉ» ይሉና ያማትባሉ፡፡

ቅምቅምን ባሰብኩ ቁጥር ትዝ የምትለኝ ትንሽ ከከፋት እና ከሰው ከተጣላች እኛ ቤት ፊት-ለፊት የተተከለችውን ያድባር ድንጋይ እያማረረችና እየተለማመነች የምታለቅሰው ነው።

«ምናባሽ አንቺ አድባር፣ ኧረ ተይ ኧረ ተይ...» ትላታለች እንባዋ በጥብስብስ ፊቷ ላይ እየተንዠቀዠቀ። ይቺ አድባር ሆና የምናመልከባት ድንጋይ በፊት የአያቴ የድንጋይ ሙቀጫ ነበረች። ወገቧ ላይ ቀበቶ ያሰረች የሚያስመስላት ቅረጽ ተበጅቶላታል። አፏ ስለተሸራረፈ ነው አያቴ የጣሏት። ወንድ አያቴ ደግሞ በአፏ ተከላት። እሱ እዚያ ቦታ የተከላት ለመቀመጫነት ነበር። ነገር ግን ቦታው በፊት የግንቦት ልደታ ማክበሪያ ሰፍራ ስለነበር ቀስ በቀስ ቅቤ ሲቀቧት፣ ሰንደል ሲያጨሱባት፣ በመጨረሻ ያች ሙቀጫ የምናመልካት አድባራችን ሆነች። ያቺን ድንጋይ ቅምቅም ስለምታለቅስባት ዛሬ ድረስ የቅምቅም አድባር እያሉ ይጠሩዋታል። በዋነኛ ግን የጉበሬ ባቂሎ አድባር ነው የምትባለው።

ስለአድባሯ ካነሳሁ አይቀር ስለሚያስገርሙኝ አንድ ሰው ላጫውትሽ ኃይለሚካኤል ሳቦሬ ይባላሉ። ጫማ ሠፊ ናቸው። አፍንጫቸው እንደቀነጨረች ባቄላ ቁጥርጥር ብላ ተኮማትራለች። የቂጥኝ ግርሻ አፍንጫቸውን ጥንጣን ሆኖ እንደበላው ይነገራል። ቂጥኙ ብሽሽታቸውን ስለአበላሸሸው ሲሄዱ ፈንገል ፈንገል እያሉ ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ «የለም፣ ቂጥኝ አይደለም» ይላሉ። «እርግማን ነው» የአንዲት ባለውቃቢ ገንዘብ ተበድረው በማስቀረታቸው ነው አሉ። አበዳሪዋ ወ/ሮ ሚልኮ የተከዱት ገንዘብ ስላበሳጫቸው አገራቸው ድረስ ነገሩን አጥብቀውባቸው መጡ። አሳቀሉዋቸው ተባለ። ኃይለሚካኤል ይታመሙ ይታመሙና ሊያገግሙ ሲሉ ወይዘሮ ሚልኮ ውቃቢያቸውን እንደ ልጅ ይቆጡታል።

«እ ሰርቶ ሊበላ? የለህማ፣ ጨሌዬን አበጥሳለሁ!» የዛችውን ቀን ጀንበር ሳትጠልቅ ኃይለሚካኤል ሽምቅቅ አድርጓቸው ያድራሉ። እንዲህ እንዲህ ብለው በመጨረሻ አፍንጫቸው ከሰመች። መከሰም ብቻ ሳይሆን በአግባቡ ፊደል አልተኩስ አለች። ብዙ ፊደል ይከሽፍባቸዋል። «ቱሽ!» እንዳለ ጥይት በፊደሎቹ ትንፋሽ ይበዛባቸዋል። ልጅ ሲያጫውቱ «እፋፋ» እያሉ ነው። ስለዚህ «እፋፋ» እንላቸው ነበር። አይቀየሙም «ሬብ ሁሉ» ብሎ የመሳደብ ልምድ አላቸው እኛ ተርጉመን





አወቅነው እንጂ እሳቸው «ዮብ ሁሁ» ነው የሚሉት። እንዴት እንዳወቅነው እንጃ'ጂ አንድ ቀን ጽፈው ሳይሰጡን አይቀሩም። ካልሰከሩ ጥሩ ሸማግሌ ናቸው። ትንሽ ከቀማመሱ ግን በደህና ጊዜ ችላ ብለው ያለፉትን ሁሉ እያነሱ መጣላት ነው። «ሬብ ሁሉ» ፈንገል ፈንገል እያሉ መጥተው «እኔ ኃይለሚካኤል» ካሉ ሰው ሁሉ ገሸሽ ነው።

አድባራችን ትዝ ባለችኝ ቁጥር እኚህን ሰውዬን ማስታወሴ አይቀርም። የግንቦት ልደታ በጠዋት ተነስተው የአድባር መዋጮ ብር ይሰበስባሉ። በግ ይገዛል። በተረፈው ጠጅ በባሊ፣ አረቄ በጠርሙስ። ሴቶቹም በፊናቸው ዱቄትና ጥራጥሬ አዋጥተው እነባብሮ ይጋግራሉ። ንፍሮ ይቀቅላሉ። ቡና ተፈልቶ የቅምቅም አድባር ቅቤ ትቀባለች። ሰንደል ይጨሰባታል፣ የማሽላ ቆሎ የተበተነበት ቄጠማ ይጎዘጎዛል።

ከቀኑ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ መንደርተኛው ሁሉ ተሰብስቦ በብረት ምጣድ የተጠበሰውን የበግ ሥጋ ይታደላል። እነባብሮ፣ ንፍሮ... ሽማግሌዎች ተነስተው ስለአብሮነታችን ዲስኩር ያሰማሉ። ከዚህ በኋላ የደረሰላቸው ስለታቸውን ያስገባሉ፣ አንዳንዶቹ ለአመቱ ይሳላሉ። ከዚህ በኃላ መጠጡን መጠጣት ይጀመራል። እስከዚህ ሰዓት ድረስ ኃይለሚካኤል አስተናጋጅና የሚሏቸውን ሰሚ ይሆናሉ። ወደ መጨረሻ አካባቢ ግን ይጠጡና «ዮብ ሀሁ። እኜ ኃየይሂኃየይ!» (ሬብ ሁሉ። እኔ ኃይለሚካኤል!) ማለት ይጀምራሉ። ይሄኔ መንደርተኛው ወደ የቤቱ መከተት ነው። የእፋፋ መደምደሚያ አድባሯን ከቦታዋ አንስተው ትቦ ውስጥ ከትተው ከሷ ጋር ሲጣሉ ማደር ነው። «ሬብ ሁሉ! ለድንጋይ እየሰገዱ፣ ሬብ ሌባ-ሁሉ!»

አድባሯ እሳቸው ከጣሉዋት ቱቦ ውስጥ የምትነሳው የዓመቱ ግንቦት ልደታ ሊደርስ አካባቢ በእሳቸው ነው። ቦታዋ መልሰው አካባቢውን እየደለደሉ ያስተካክሉታል። ከዚያም በከሸፈ የፊደል ጥይት «እድባር አውጡ! እድባር አውጡ!» እያሉ ይለፍፋሉ ማታ መልሰው ካድባሯ ጋር ሊጣሉ።

# ፫

መንደራችን በሁለት የሥሜት ግንፍልታ ውስጥ ቁልጭ ቁልጭ ትላለች:: ለምታደላው ግራ ስትጋባ አልቀረችም:: ከቤታችን በስተጓሮ አንዲት እወዳት፣ እሸከማት የነበረችና ያደገች ትንሽ ልጅ ተድራ ይሁን ቀለበት አስራ ይጨፈራል:: ከበስተፊት-ለፊት ደግሞ በቅርብ ጊዜ በመኪና አደጋ ወንድማቸውን ያጡት ረታች ወ/ማሪያም በምን ቅልብሽ አንዳላቸው'ኛ ያለቅሳሉ::

መቼም የእማማ ረታች ለቅሶ ለቅሶ ነው ማለት ይከብዳል:: ለአፍ መከፈት የቀረበ ነው:: አመል ብሎባቸው ሲሰዳደቡ፣ ሲጠራሩና ሲያለቅሱ የመንደሩ ሰው ቧሬ አፋቸውን ከፈቱ ነው የሚላቸው::

«ተውኙ፣ ምነው ረታች!» የማለት ልምድ አለባቸው:: እኛ ልጆች በነበርንበት ጊዜ መተት እየሰራን እበራቸው ስንጥል በስንጥሩ እግራቸው ላይ የተከመረ ሰውነታቸውን እየወዘወዙ ተሳድበው፣ አስፈራርተው በመጨረሻ ሲያለቅሱ የአተር-ፍሬ ከሚያካክሉት ዓይኖቻቸው የሚፈልቀው የእንባ ጎርፍ አይጣል ያሰኛል:: አንድ ቀን በእንባቸው ፈረሰኛ አይኖቻቸው ተፈነቃቅለውና ተጠራርገው ጡታቸው ሥር እንዳይገኙ ያሳስባል::

ባለቤታቸው ገረመው ሲበዛ ቀልደኛ ነበሩ:: የመንደሩ ሰው ይወዳቸዋል:: «አባ-ብዳው» እያሉ በቅጥል ስም ይጠሩዋቸዋል:: ደስ ነው የሚላቸው:: እሳቸው ካሉ ሐዘን ቤቱ ፌሽታ ቤት ሆኖ ነው የሚያመሸው:: አብዛኛው ለቅሶ ደራሽ «አባ-ብዳው» እያለ ስለ ብልግና እንዲያወሩ ይገፋፋቸዋል::

«ቺ!» የማለት ልምድ አላቸው «ቺ! እኔ ገሬ፣ አልዋሽም! ያጥፋኝ አልዋሽም!!» ይሉና የጠቧት ሳትቀር እያወሩ ለቅሶ ደራሹን ያስቁታል:: በእርግጥም ኑሮአቸውን እራሱን የምር የሚኖሩ ሳይሆን ለለቅሶ-ቤት ቀልዳቸው የሚፈጥሩበት ተመክሯቸው ነው የሚመስለው::

ባለቤታቸው ይወግሩዋቸዋል -- ሲፎክሩ'ኳ:-

«እኔ ገሬ፣ ሚስቱ የምትመታው!» እያሉ ነው:: ሁለቱ አይስማሙም:: ልጆች በነበርንበት ጊዜ አባ ገሬ ቤት እንሄድና ከባለቤታቸው ጋር ሲሰዳደቡ እንሰማ ነበር::





«አንቺ የብርቄ ልጅ!» ይላሉ አባገሬ «እናትሽ በሞቶችና እድሬን በበላሁ»

«አንተ የወይኒቱ ልጅ!» ይላሉ ረታች:: ሁለቱም የባለቤቶቻቸውን ወላጆች ባሮች ናቸው እያሉ ነው የሚሳደቡት:: በመጨረሻ ሲካረሩ እማማ ረታች ጉልቤ በመሆናቸው ያስፈራራሉ:-

«ዋ! ዋ-አጥረገርከሃለሁ፣ እውሉኝ ብቻ ይሄ አስኮናኝ፣ የሰው አስኮናኝ» ይሏቸዋል::

ይሄ አባ-ገሬ አንጀታቸው እርር እያለ ሽበቶ ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ እንደልማዳቸው «ቺ!» ይሉና በጨረፍታ ያጨበጭባሉ «አንቺ ወንድ እኔ ሴት!»

ሁለቱ ባልና ሚስት ካሉ የሁለቱ ፀብ አገር ያውካል:: በእርግጥም አባገሬ ሲያወሩ «ልጆችም ሆነን አዘናግቼ ካልሆነ አልችላትም ይቺ ባሪያ ይላሉ:: አባ ገሬ በየዋህነታቸው፣ በግልጽነታቸው፣ በቀልደኝነታቸው የመንደሩ ሰው ሲበዛ ይወዳቸዋል::

«አልዋሽም! ያጥፋኝ አልዋሽም» ካሉ አይዋሹም:: አብዛኛውን ጊዜ መንደርተኛውን በሳቅ የሚያፈርሱት ስለመወገራቸውና ስለሴት አይምሬነታቸው እያወሩ ነው:: በይበልጥ በሚስታቸው ስለመወገራቸው::

«አንድ ቀን የምችላት፣ የምችላት መሰለኝና ምናባቷ ብዬ በሩን ዘጋሁ:: በኋላ ያዝ ሳደርጋት ሲሌዬን ለቀም አድርጋ አልጋው ላይ ድብ! አደረገችኝ:: ‹ሖ› እያለች በምን ልቻላት:: በጓሮ በር ጎረቤታችን ገባ:: እሱን ሳየው አፈርኩና በአዝማሪ ቋንቋ ከላዬ ላይ እንድትነሳልኝ ለመንኳት ‹ሖ› እያለች እምቢ ብትለኝ ወደ ጎረቤታችን ዞር ብዬ እኔ ሚስቴን ስቀጣ አትምጣብኝ አላልኩም? ብዬ ተቆጣሁታ!...» ቤቱ ያወካል::

«አንድ ጊዜ ደሞ...» ይቀጥላሉ «አንድ ጊዜ ደሞ ቀን ሥራ ድንጋይ ሸከማ ገባሁና ሰራርቼ ስመጣ እንደው ለካከፈችኝ:: ብስጭት ብዬ መቆሚያ ጣቢያ ወጥቼ እንደቆምኩ አንድ ወፈፌ ብጤ የጠጅ ቤት ጓደኛዬ መጣና ምን እንደሆንኩ ጠየቀኝ:: ብስጭት ብዬ ብነግረው «ና-ምናባቷንስና» ብሎ ፊት-ፊት ቀደመኝ:: እኔም «ጎሽ የወንድ እጅ አሳይልኝ» ብዬ ተከተልኩት::

«ስንደርስ ረታች በር ላይ ቁጭ ብላለች:: «አንቺ?» አላት «ምን ሆነሽ ነው ለፍቶ ሲመጣ የሚበላው የምትከለክይው?»

«ና! ወንድ ከሆንክ ሌማት ከፍተህ አንተ ስጠው» አለችው «ሂድ የወንድ እጅ እሳይልኝ» አልኩት:: ጓደኛዬን ስገፋፋው ቢያቀምስልኝ እንዴት አንጀቴ ቅቤ በጠጣ ነበር:: ገና ጠጋ ሲላት እ አለችና ጠቅልላ ተወችው!!» ቤቱ ያውካካል:- ፀቡ ላይ የነበሩ ቀሪ ነገር ይጠይቃሉ:: «ታዲያ ያኔ ጓደኛዎት ሲመታ እርስዎ ምን አሉ?»

«ምነው እኔ ብቻ፣ አንተም ቅመስ'ጂ አልኩታ»

ለቅሶ ቤቱ የፌሽታ ቤት መስሎ ቁጭ ይላል::

አባ ገሬ ሲበዛ ደግ ናቸው:: ባለቤታቸው ኋ እንደዛ እየደበደቧቸው ትንሽ ፍራንክ ያገኙ እንደሆን «አቦ ያቺ ረታች ባዶ ቤት ሳትሆን አትቀርም» ብለው ወስደው ይሰጧቸዋል:: ብዙ ጊዜም ቤታቸው ጽዋ ገብቶ ሲደገስ ማህበርተኛ ከመግባቱ በፊት የድግሱን ምግብ እየጨረሱ ባለቤታቸውን አስለቅሰዋል:: እንዲሁ የአመት በአል ጊዜ ረታች ከቤት ወጣ ያሉ እንደሆነ ገልብጠው ማብላት ነው::

አባ ገሬ ከደግነታቸውና ከቀልደኝነታቸው ውጪ የሴት አመል አለብኝ እያሉ በግልጽ ይናገራሉ:: አርጅተው እንኳ ደንደን ያለ የሴት ዳሌ ያዩ እንደሆን ወደ አፍንጫቸው ጥግ ተቀራርበው በተርታ የተሰለፉ ትናንሽ ዓይኖቻቸውን ተከለው አይነቅሉም:: ሰው አይቶ ከሳቀ «አያምስልባትና ውሽማዬ የነበረችው የእንጀራ እናቴን ትመስላለች» ብለው ወጋቸውን ይቀጥላሉ::

እርግጥም ሴት ካገኙ አይምሩም:: አንድ ጊዜ የውብነሽ የምትባል ቆንጆ ሰካራም ሴት ቤታቸው ተዳብላ አንቀው አስጨኸዋታል:: ካደረጉም ከማውራት ወደኋላ አይሉም:: ለሳቸው:- ኑሮ የቀልድ ምንጭ ነዋ ምን እውነት አለበትና በሚስጥር ይጠበቅ? አንድ ሰሞን አናቂውን ሚስት አበቡን ቀምሰው ኖሮ አናቂው እንደለመዱት «ያዬ ፋሲል ዘር!...» እያሉ ስካር ቀመስ ወግ ሲጀምሩ አባገሬ በግጥም እንዲህ ብለው ዝም ያሰኟቸዋል::

- «አንተ ቀሚስ ግዛ እኔ መቀነቷን፣
የጋራ ሚስታችን አትሂድ እራቁቷን፣»

አባገሬ ግልፍተኛም ናቸው:-





አንድ ጊዜ ቀበሌ ስብሰባ ላይ አንድ አብዮት ጠባቂ ስለሥራው ሪፖርት ሲያቀርብ የኛን መንደር «አዝማሪ ሠፈር» ብሎ ስለጠራ በሕዝብ መሀል ግልፍ ብሏቸው በመሳደባቸው ከርቸሌ ሊወርዱ ነበር አሉ::

በግልፍተኝነት ላይ ደግሞ ማዘናጋትና ማጥቃትም ያውቃሉ:: በፀብ ጊዜ «እኔ ገሬ አዘናግቼ ነው!» ይላሉ:: በእርግጥም አዘናግተው አይለቁም:: ሚስታቸውን እንኳ አዘናግተው ብዙ ጊዜ ይፈነክቷቸው ነበር:: አንድ ጊዜ አቦዬ አዝማሪው ከገሬ ጋር ይጣላና አዘናግተው ይፈነክቱታል::

የከዚህ ቀደም ገደብ ስለነበራቸው ከከሰሳቸው መቅለጣቸው በመሆኑ ያቺን አንድ ሌሊት እንደምንም አሳልፈው ወደ መርሃቤቴ ለመሸፈት አውቶቢስ ተራ ይሄዳሉ:: አውቶቢሱን አግኝተው እንደተሰለፉ ያ-ገደብ ጥሰው የፈነከቱት አቦዬን እዚያው ያዩታል:: ለካስ እሱም የአባገሬን ዛቻ «እንደጀመርኩ እጨርሰዋለሁ» ያሉትን ፈርቶ መሸሹ ኖሯል:: አባገሬ ነገሩ ይገባቸውና «የታባቱ!» ብለው ወደቤታቸው ሲመለሱ አሁንም አቦዬ ቀድሟቸው መጥቷል:: ለካስ እሱም አይቷቸው «በቃ ሸሽቷል» ብሎ ወደቤቱ መመለሱ ኖሯል:: ከዚያ ሁለቱም ልብ ለልብ ተግባብተው አርፈው ተቀመጡ::

እንዲሁ አንድ ጊዜ አባገሬ ከኃይለሚካኤል እፉፉ ጋር ተጣልተው:- «አንተን ማን እጅ በእጅ ይያያዛል? አዘናግቶ ነው'ጂ» ብለው ማታ እፉፉ የቀኑን እረስተው አገር ሰላም ብለው የተኙበት አባገሬ በሩን ከፈት አድርገው እፉፉፈን ሦስት ቦታ ፈንክተዋቸዋል በድንጋይ ጨበጣ::

ከአባገሬ አስቂኝ ባህርይና የዋህነት አንድ በጣም ግርም የሚለኝ ነበር:: አንድ ጊዜ በልጅነቱ አገራቸው ጥለውት የመጡት ልጃቸው ከመርሃቤቴ ይመጣል:: ቁጭ ብለው ሲያወሩ በመሃል የከነከናቸውን ፍንጭ ጣል ያደርጋሉ:- «አባትህ ደህና ናቸው-ለጤናቸው?» ብለው ይጠይቁታል:: ልጁም:- «እንዴ? አባቴ አንተ አይደለህም?» ሲላቸው እንደ አዲስ እንደገና ተነስተው እያለቀሱ ሳሙት:: ለካ አባ ገሬ ባለቤታቸው ከሳቸው ደብቀው ከሌላ የወለዱት መስሏቸው ነገር ቋጥረው ኖሯል::

አንድ ጊዜ አምሽቼ ወደቤት ስገባ አባ-ገሬ ቤት ጫጫታ ሰማሁና ቆም አልኩ:: አባ ገሬ እራሳቸውን እየነጩ ያለቅሳሉ:: ብውስጥ ሱሪ እራቁታቸውን ናቸው::

ከመረሃቤቱ መጥቶ ውትድርና ጦርሜዳ ቆስሎ የተመለሰው ልጃቸው ከእናቱ የወረሰውን አተር አይን እያቀለጨለጨ «እህ! ምን ማለታችሁ ነው? አባት ይመታል'ዴ?» ይላል፡፡

አባ ገሬ ይዋሻሉ የሚል የለም፡፡ እንባቸው እየተናነቃቸው ደጋግመው «ቺ!» ይላሉ፡፡ «ወርውሮ ጣለኝ ያጥፋኝ አልዋሽም!» እንደባህሪያቸው «አዘናግቼ...» አላሉትም፡፡ ልጃቸው ነዋ፡፡

የዚች መንደር ደረቅ የአኗኗር ሳሏን በቀልዳቸው የሚያለዝቡት አባ ገሬ ናቸው፡፡ በወንደላጤ ኑሮ የተሰላቸው ከምሩ አባገሬን ስለሚስት ሲያማክራቸው መልሳቸው፡-

«ጥቁር ናት'ጂ የኔ ሚስት አለችልህ» ነው

የአባገሬ አዘውትረው የሚያወሩትን አንድ ገጠመኝ ልንገርሽ፡፡ አንድ ጊዜ አባገሬ በአቡንደጅ በር ላይ ሲያልፉ አቡንደጅ ቤቷ የገባ ወንድ አልወጣ ብሏት ትሟገት ነበር፡፡ «ገሬ፤ ገሬ...» ብላ ትጣራና «ጥለ'ሽኝ ትሄድ? ኧረ ስለነፍስ» ትላቸዋለች፡፡

አባገሬ ጠጋ ብለው በበሩ ቀዳዳ «አትወጣም?» ይላሉ

«አልወጣም!» ይላል ወንዱ፡፡

«ቺ! ምነው ገሬ!» ይሉና ግልፍ ብሏቸው ዱላቸውን ለምኩቶሽ አስተካክለው በሩን በመበርገድ ይገባሉ፡፡ ወንዱም ቶሎ ብሎ የቤቱን መቀርቀሪያ ያነሳል፡፡ ይገጥማሉ፡፡ ለካ ሰውዬው እንደ አባ ገሬ ስሙ ገረመው ኑሮ «ገሬ! የማለት ልምድ አለበት... ገሬ! ገሬ! እየተባባሉ ትንሽ እንደተመካከቱ በመጨረሻ አባገሬን «ገሬ!» ብሎ እናታቸው ላይ መቀርቀሪያውን ያሳርፍና የተጋደሙበት ተራምዷቸው ወጥቶ ይሄዳል፡፡

«ቢሆንም እንዳሰብኩት ከቤት አስወጥቼዋለሁ» ይላሉ አባገሬ በወሬያቸው መደምደሚያ ላይ፡፡





# ፬

ሴት አያቴ እናቴን ወለዱ፤ እናቴም እኔን ወለደች በቃ፡፡ ይቺው ናት የዝምድና ሐረጋችን ርዝመቱ፡፡ እኔም እንደ እናቴ ያለ ወንድምና እህት አያቴ ቤት አደኩ፡፡ እናቴ አያቷ ቤት በማደጓ ለእናቷ ያላት ስሜት እኔ ለሷ ካለኝ ስሜት የተለየ አይመስለኝም፡፡ «እትዬ» ብላ ነው የምትጠራቸው፡፡ እኔ እሷን በስሟ ስጠራት አያቴን ደግሞ «አንቱ እማማ»

በልጅነቴ ሲበዛ ታማሚ ነበርኩ፡፡ አያቴ ሲያወሩ አንድ ጊዜ ሳንባ ነቀርሳ ሐኪም ቤት ይዘውኝ ሄደው ሲመለሱ የጆሮና የአንገት ወርቃቸውን በተስፋ መቁረጥ አውልቀው ለሐዘን በመዘጋጀት ነበር፡፡

ሴት አያቴ ለኔ ዝምድና ማሳየት የጀመሩት እየበረታሁ መታየት ከጀመርኩ ወዲህ ነው፡፡ እናቴ እኔን ለመውለድ ከአምስት ቀን በላይ አምጣለች በመጨረሻ ስትገላገል አያቴ ከኔ ይልቅ ለልጃቸው ነበር ትኩረት የሰጡት፡፡ እኔ በከርታስ እንደተወለድኩ ወዲያ ብለውኝ ልጃቸውን በስስት መመልከት ጀመሩ፡፡ አሁን ድረስ «አከስቴ» እያልኩ የምጠራት የከርስትና አባቴ ሚስት «ውይ ነፍስ አለው!» ትላለች፡፡ ማንም ስለኔ የተጨነቀ አልነበረም፡፡

አያቴ፡- «እንኳን ልጄን የለቀቃት ጂ የራሱ ጉዳይ!» ይላሉ፡፡

«አከስቴ» ናት አንስታ ያጣጠበችኝ፡፡

እንግዲህ ዛሬ ለአያቴ ከልጃቸውም በላይ ዓለም ላይ ያለሁት አንድ ብቸኛ ዘመዳቸው እኔ ብቻ ሆኛለሁ፡፡ በአፋቸው ባይናገሩትም እኔ አንድ መሆኔ በውስጣቸው ያብሰለስሉታል፡፡ ካወጡትም የቆጫቸው ላለመምሰል እየተጠነቀቁ ነው፡፡ «የልጄን ሆድ ረግጦ ወጥቶ» ይላሉ፡፡ አንድ ልጅነቴ ሕይወታቸውን እንስፍስፍ አድርጎታል፡፡

ትዝ ይለኛል እድጌ የትም በምዞርበትና እንደውም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በገባሁበት ዕድሜዬ አያቴ እኔን አቅፈው እንጀራ ይጋግሩ ነበር፡፡ ጎረቤቶች ሲያዩ ይስቃሉ፡፡ «እኔን ካልከበደኝ...» ነው የመልሳቸው መከፊቻ፡፡ አንዳንዴ መቼ ይሆን የምከብዳቸው? ብዬ አስባለሁ፡፡ አሁንም ቢሸከሙኝ ለአካላቸው'ጂ ለመንፈሳቸው አልከብዳቸውም እርግጠኛ ነኝ፡፡

በሽታዬን በልጅነቴ አጣጥሜ ሳድግ ሙሉ ጤነኛ ሆንኩ:: ቢሆንም በምትኩ ከፍተኛ የመሞላቀቅ በሽታ ያደረብኝ ልጅ ሆንኩ:: ሴት አያቴን ከፋኛ ስበጠብጣቸውና ግራ-ግብት ሲላቸው እጄን ይዘው ወደ ማዕድ ቤት ያስገቡኝና ከታሰረው የሴት ሸከም ቅጠል ላይ እርጥብ አመልማሎ ይመዛሉ:: ይሄ እርጥብ ቅጠል የሚመዘዘው በስንት ጥናት ተገላብጦ ታይቶ ነው:: የደረቀና ቅጠሉ የረገፈ ከሆነ አንደኛ አንጀት ውስጥ ገብቶ ያንሰፈስፋል ሁለተኛ ልጅ በደረቅ አይመታም፣ በእርጥብ ከሆነ ግን ወዲያውም ምርቃት ነው ብለው ያስባሉ::

እንግዲህ በዚያ አመልማሎ «ቸብ! ቸብ» ማድረግ ይጀምራሉ:: አያምም እኔ ግን አንዴ ቸብ! ሲያደርጉኝ እለፈልፋለሁ ወይየው! ሞትኩ ሞትኩ! በሁለተኛው እወድቅና ጩኸቴን አግለበልበዋለሁ:: በሶስተኛው ቸብታ ግን ሩሁን እንደሳተ ሰው ፀጥ እላለሁ::

አያቴ ከፋኛ ይደነግጣሉ::

«ሙሉዬ? አንተ? ምናባቱ...» ውኃ አምጥተው ያርከፈከፉብኛል:: በዚህ ሁኔታዬ ትንሽ ብቆይ እንደሚጮሁ አውቃለሁ:: እንደመባተት ስል ያንጋጥጡና «ተመስገን! እኔ ተው እጄ መጥፎ ነው አለዋለሁ:: አይሰማኝ...» እያሉ አቅፈው እያንዘለዘሉ ቤት ይወስዱኛል::

እርጎ የማይቀር ቢሆንም ሌላ የምፈልገውን ተጨማሪ ይገዙልኛል:: እስካሁን ድረስ «ያንተን ነፋስ ደግፎ ያቆየው እርጎ ነው» እያሉ ያወሩልኛል:: ትንሽ የህመም ስሜት ከተሰማኝ እርጎ እንድጠጣ ይመከሩኛል:: ይሄ ምክራቸው ለኔ እንዴት ያለእርጎ የሆነ ትዝታ ይቀሰቅስብኛል መሰለሽ?

የአያቴን ቁመና እንዴት ልገልፀው እንደምችል አላውቅም:: እንደ እናቴ ባይሆንም ረጅም ሴት ናቸው:: ጠይም:: የፊት አንድ ጥርሳቸው ወልቋል ስፈራችን ጤነኛ አይደለምና ሰከረው እንዳይመስልሽ:: ድሮ ወንድ አያቴ ቤት ውስጥ እስሮ ከሚቀልባቸው በጎች ውስጥ አንዷ በለጡ ትባል ነበር:: አታርፍም:: የታሰረችበት ሆና ከግራ ቀኝ ስትወዘወዝ መሽቶ ይነጋል:: የታሰረችበት ገመድ በጠዘት ከሳምንት በላይ አይቆይም፣ ይበጠሳል:: ታዲያ እማማ እሰሯ ምን እንደሚሰሩ እንጃ እንዳጎነበሱ ነበር





በጭንቅላቷ ገጭታ ጥርሳቸውን ያወለቀቻቸው:: በወቅቱ አያቴ ሰው ሰራሽ ጥርስ ቢያስተክልላቸውም አሁን በጊዜ ብዛት እየላላ መውለቅ ጀምሮ ከወራት በፊት ጠፋ::

ከዚህ ሌላ እማማ እንዴት ሊገለፁ እንደሚችሉ እንጃ:: ሰልካካ አይደሉም:: ፉንጋም አይደሉም:: ብቻ የአፍንጫቸው ቀዳዳዎች በፊት ለፊት ቁልጭ ብለው ይታያሉ:: እረጋ ያለ፣ ብዙ ጊዜ ከራሳቸው አልፈው ስለሰው የሚያፍሩና በይበልጥ ለኔ አስተሳሰባቸው የሚስማማ:: እንጃ ብቻ ...የእግራቸው መጫሚያ ከመተለቁ የተነሳ ሽፋፋ ሳያስመስላቸው አይቀርም:: እንዳንዴ የቻይና ሽራ ጫማ ልገዛላቸው ስል ለእሳቸው የሚሆን ቁጥር በመከራ ነው የሚገኘው:: 40 ቁጥር 39 እየጠበበ...

ወንድ አያቴ ሲበዛ ጨቁኗቸው ስለኖረ በይበልጥ ጭቅጭቅ አይወዱም:: አንዳንዴ ጎረቤቶቻችን ንዝንዝ ከሰሙ «ጭቅጭቅ ምንድነው? አንዴ ተማቶ ማረፍ ይሻላል!» ይሉና ይንገፈገፋሉ::

ወንድ አያቴ እውቅ ጨቅጫቃ ነበር:: በይበልጥ አቅም እያነሰው በመጣበት ሰዓት ላይ አርባ ስምንት ሰዓት የመነዛነዝ ጉልበት አበጅቶ ነበር:: መልስ ሲሰጠው «ዝም በሉ!» ዝም ሲባል «ንቀት ነው?» በሁሉም መንገድ ጭቅጭቁ ማብቂያ የለውም ነበር:: ለዚህ ነው እሱ ንዝንዝ አጥግቦን ዛሬ ቤታችን ውስጥ ከሦስት ምልልስ በላይ የሚዘልቅ ያለመግባባት ንግግር የለም::

ቤታችን ገነት ናት ንዑስ

ወንድ አያቴ የወንድነት መለኪያው ማሸበር የሚመስለው ሞገደኛ አዋኪ ሰው ነበር:: እማማ ሲያወሩ እሱ ከሥራ ሲመጣ ለማሞቅም ቢሆን ድስት እሳት ላይ ተጥዶ ማየት አይፈልግም:: ካጋጠመው አዲዮ! ብዙ ጊዜ በካልቾ ብሎ ወጡን ለግድግዳ ዳርጎታል:: በዚህም አያበቃም ዱላ ያስከትላል:: እማማ ከሱ ጋር ከተጣሉ ለመሸምገል የሚሞክር መንደርተኛ የለም:: እማማ ሲያወሩ ሌላው ቀርቶ እቤቱ እንድንገባበት የሚፈልግ የለም ይላሉ:: ይሄንን አንስተው አሁን ሲጫወቱ እየሳቁ:-

«ምናምን እንደቀመሰ ውሻ እኔ ስሄድበት ሁሉም ደጃፉን ይዘጋል» ይሉና ሳቃቸው ጠየም ብሎ «አንድ ቀን መሐል እናቴን ተርከከውኝ ብቻዬን ፎሊስ ጣቢያ ስሄድ በኋላ አማሮች ቢገድሉኝም ይግደሉኝ ብላ ቲከተለችኝ» ይላሉ:: ወንድ አያቴ ፀብ ያለሽ በዳቦ ስለሆነ ሰው ሁሉ ይጠነቀቃል::

የአያቴ አንድ ግርም የሚለኝ ባህርይ ነበረው፡፡ ከቤቱ አልፎ ተርፎ የሰው ልጆች ይቀጣል፡፡ ይሁን ልጆች ናቸው፣ የሰው ሚስትም የሚደበድብበት ጊዜም አለ፡- «ምናባቷ ሆና ነው ወንዱን ልጅ እንዲህ አድርጋ የምታዋርድ ይቺ ውሻ ሻጭ!» ይላል በገዛ ባሏ፡፡

ወንድ አያቴን በቅጡ የማስታውሰው በጡረታ ተገልሎ ቤት ውስጥ መዋል ከጀመረ ወዲህ ነው፡፡ ከዚያ በፊት «ሊጋባ ቢሮ» ከሚባለው መሥሪያ ቤቱ ወስዶ ሜዳው ላይ ሲለቀኝ... ይዞኝ ጠጅ ቤት ይገባና ለኔም አንድ ብርሌ የሚያስቀዳልኝ... ነበር «ልጅ አይደለም'ዴ?» ሲሉ አያቴ ያፈጥና «ምናገባህ? ወደሥራህ!» ሲላቸው፡፡ ያቺን አንዷን ብርሌ ገንጨዬ ስመጣ፣ እማማ ሲያዩኝ እንደሰከረ የምሆነው... እ-ማማም «ልቡን አፈንድተው ይግደሉት» እያሉ አያቴ ሳይሰማ የሚያልጎመጉሙትና በጠዋት ተነስተው እርጎ የሚያዘጋጁት...

ከዚህ ሁሉ በምሬት የማስታውሰው የቤተክርስቲያኑን ነው፡፡ በቅዳሴ ሰዓት ሲነሱ ቆሜ... ሲያጎነብሱ አቀርቅሬ... ሲንበረከኩ ተንበርክኬ... ከዚህ ዝንፍ ካልኩ «ቋ» ኩርኩም፡፡

ወንድ አያቴ ሲበዛ ጥንቁቅና ጠርጣሪ ነበር፡፡ በሱ አስተያየት የወንድ ልጅ መስፈርቱ ብዙ ነው፡፡ «ወንድ ልጅ እንዴት ደጃፍ ሳያዘጋ ሱሪውን ያወልቃል?» ይላል፡፡ የኛ በር የሚዘጋው ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ ነው፡፡ «ከዚህ በኋላ የሚመጣ እኔ ነኝ ብሎ አስከፍቶ ይግባ የተባረረ ይመጣል፤ እየሰከረ ያበደ ይመጣል...» ከዚያች ሰዓት በኋላ የሚገባም ሆነ የሚወጣ የለም፡፡

ቤቱ አስራ ሁለት ሰዓት ሆኖ በሩ ከተዘጋ በኋላ ሁሉም ነገር በሱ ቁጥጥር ስር ይውላል፡፡ ፀጥ! እረጭ! አልጋው ላይ ቁጭ ይልና እግሩን እግዳሚ በርጩማው ላይ ያስቀምጣል፡፡ እኔ ፈጠን ብዬ ጫማውንና ካልሲውን አውልቄ ለእግሩ ድልዳል አበጅቼ አስቀምጠዋለሁ፡፡ ሁሉም ነገር የየራሱ ስርዓት አለው፡፡ ሌላው ቀርቶ ያቺ እግዳሚ በርጩማ አስራ ሁለት ወርቅማ ምስማሮች በአንድ ተርታ ተመተውበታል፡፡ ያ-የወርቅማ ምስማር ድርድር አቅጣጫው መሆን ያለበት ወደ በሩ ነው፡፡ ተሳስቶ ወደ ውስጥ ከሆነ ከፉኛ ይቆጣል ከተደጋገመ ይማታል፡፡ ከዚያ እማማ ሲያዙኝ ለጣት ውኃ አቅርቤ አስታጥባለሁ፡፡ የፍቅሩን ፊቴ ላይ ውኃ ፈንጠቅ ማድረጉ የተለመደ ነው፡፡





ከዚያ እማማ እራት ያቀርቡና እየተበላ በተለመደ አባባል «አሳንቀህ ትገድለኝ?» ይለኛል፣ ቀደም ብዬ የገዛሁትን ጠጅ እንድቀዳለት፡፡

ጠጁን ስቀዳለት «ቅመሰው» ይለኛል፡፡ እቀምሰዋለሁ ነው የሚባለው አጋምሰዋለሁ፡፡ ከወንድ ልጅ መስፈርት አንዱ ሳያስቀምስ አለመጠጣቱ ነው፡፡ ወንድ ጠርጣሪ መሆን አለበት ያጎርሰኝና ከጓዳ እወጣለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ሁለቱ አያቶቼ እራት በልተው ሲጨርሱ እዚያው ቦታ ላይ ገበታው ከፍ ሳይል እኛ ልጆቹ እንጠራለን፡፡ ከእራት በኋላ አያቴ እጁን የሚታጠበው በጠጅ ነው፡፡ ሲያብራራ፡-

«ጠላ ጂ ጠጅ ግፍ የለውም፡፡ አገራችን ሴቶች ደጅ ይወጡበታል» ይላል፡፡ ይሄ አባባሉ አይቀርም፡፡ ከዚያ ጠጁን እየጠጣ ልጅ ልጆቹን ማብላት ይቀጥላል «ጎሽ-ጎሽ፣ ይቺን-ጎሽ፣ እኔ እስካለሁ ብሉልኝ ከዚያ በኋላም የራሳችሁ ጉዳይ...» ይላል፡፡ ሊያልቅ ሲል እማማ ላይ ያፈጣል «ጨምሪላቸው!» ሳንጨርስ በቃን ካልን ደሞ «ይሄንን አስተርፋችሁ ምን ታደርጉት?» ይልና ያፈጣል፡፡ አንዳንዴ እያለቀስን የምንበላበት ጊዜ አለ፡፡ ይሄኔ ተጣልቶን ነው ከገበታ ላይ የሚነሳው፡፡ «በሉ ባልኩ ለቅሶ?? ወይ አባቴ ያስብላችሁ...»

ሁልጊዜም ከኮዳዋ ላይ የምትተርፈው ግማሽ ብርጭቆ ጠጅ የኔ ናት፡፡ ከዚህ በኋላ ሻይ በአበሻ አረቂ ጠጥቶ ነው የሚተኛው ሬዲዮ ከፍቶ እያዳመጠ የጠጣውን ሻይ በአረቂ ከግማሽ ትንሽ ዝቅ ሲል በማንኪያ የሚጠጣበትን ትልቅ የቻይና ሸክላ ሲኒ ይንኳኳል፡-

«ቂጨል!»

በዚህ ሰዓት ካለነው ከሦስታችን ተሽቀዳድመን መቀበል ነው፡፡ እኔ በሴቶቹ ከተቀደምኩ አሣሬን እያታለሁ፡፡ «ፈዛዛ! በሴት ትቀደም? አፈር ብላ!» ከቀደምኩ ደግሞ እራሴን እየደባበሰ እግሩ ሥር አግዳሚው በርጩማ ላይ ቁጭ ብዬ በክብር እጠጣለሁ፡፡ «ጎሽ ልጄ! የታባታቸውና ደሞ ሴቶች ይቅደሙህ?»

የአያቴ ወግና ሥርዓቱ ብዙ ነው፡፡ እነዚህን ወግና ሥርዓት የተላለፈ አሣሩን ያያል፡፡ በይበልጥ እኔ ልብ ስላልነበረኝ ለቅጣቴ እንደተጋለጥኩ ነበር፡፡ አንድ ጥፋት ካጠፋሁና ጥፋቱ ከበድ ካለ «በይ እራቱን ስጪው» ብሎ ያዛል፡፡ እኔ እራቴን የምበላው እንደወትሮው ከእሱ ፊቱ የተነሳውን አይደለም፡፡ ያ-ለኔ እንደ አንድ ቅጣት

አድርጎ ያስበዋል፡፡ የታጠፈ ንፁህ እንጀራ ቀርቦልኝ ከቤተሰቡ ቀድሜ ከበላሁ በኋላ «በል ዘነበችን አምጣ» ይለኛል፡፡ (ዘነበች ከቆዳ የተሰራች ባለብረት እጀታ አለንጋ ናት፡፡) ደብቄ ከሆነ ደብቄ ካስቀመጥኩበት አመጣታለሁ፡፡

ይህንን ሁሉ ደረጃ በደረጃ ሲያዝ ረጋ እንዳለ እየሳቀ ነው፡፡ በዚህ ሰዓት ለተመለከተው ሰው ምህረት ሊያደርግ የተዘጋጀ አድርጎ ይወስደው ይሆናል፡፡ ግን በፍፁም! ልክ አለንጋዋ እጁ ስትገባ ፊቱ ይለዋወጥና መግረፍ ይጀምራል፡፡ የቤታችን በር ግልጥጥ ብሎ የተከፈተ ቢሆን'ኳ እኔን ለመገላገል የደጃፋችንን ደፍ የሚያልፍ የለም፡፡ እማማ ከፉኛ ይርገበገባሉ፡፡ ይወጣሉ ይገባሉ፡፡ ገርፎኝ ሲያበቃ ፊት-ለፊት ያስቆመኝና የተወሰነች ደቂቃ ይሰጠኛል፡፡ እንባዬን እጠርጋለሁ ታግዬ ስርቅርቅታዬን አቆማለሁ፡፡ ከዚያ የመጨረሻ ጥያቄ፡-

«እራት ትበላለህ?» ድጋሚ መሆኑ ነው «በቃኝ» ያለ ኩርፊያ አለበት ማለት ነው፡፡ አልለቀቅም በግዴ እበላታለሁ፡፡

ለቀላል ጥፋት ደግሞ ቅጣቴ አያቴ አልጋው ላይ ተቀምጦ ወይንም ተኝቶ ረጅም ዘንግ አጠገቡ ያስቀምጥና ይጠብቀኛል፡፡ እኔ ተንበርክኬ እጆቼን ግራና ቀኝ እዘረጋለሁ፡፡ እጆቼ በድካም ዝቅ ሲሉ በዚያ ዘንግ «ቋ!» ለምን ያህል የጊዜ ርዝመት እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ይሄ ሲያበቃ አቆምና ወደ ላይ እንድዘል ያዘኛል፡፡ ስዘል እሱ እንዲህ እያለ ያወጣልኛል፡፡

«ቢጨንቀኝ ነው በል»

«ቢቸንከኝ ነው!»

«ቢጠበኝ ነው»

«ቢጠበኝ ነው»

«እሬን በላሁ» ያወጣልኛል

«እሬን በላሁ!»

«ፈሴን ጠጣሁ»

«ፈሴን ጠጣሁ!» ይቺን ያስደጋግመኛል፡፡ በመጨረሻ ምህረት ይደረግልኛል፡፡ በዚህ ሰዓት ከኔ የሚጠበቅ ነበር አለ፡፡ መጀመሪያ መሬት መሳም፡፡





ከዚያ ከአያቴ ጀምሬ ቤቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሁሉ የልጆቹንም ጉልበት መሳምና እጅን ወደ ኋላ አድርጎ ምከር ተቀበሎ መቀመጥ፡፡

የዚህ ሁሉ እልሄን በአያቴ ላይ የምወጣበት አንድ ዘዴ ነበረኝ፡፡ ውሪ ጓደኞቼን እለምንና ማታ የቤታችንን ጣሪያ በድንጋይ ማስቀጥቀጥ፡፡ እያረፈ እያረፈ የቤቱ ጣሪያ በድንጋይ ሲበን አያቴ «የጠቅል አሽከር!» እያለ ሲፎክርና «መቼም አታድጉ...» እያለ ሲራገም እኔ በሆዴ ደስታዬን መኮምኮም፡፡ ታዲያ የዚህን ጦር ወረራ ቀድሜ ለእማማ ሹክ እላቸዋለሁ፡፡ እንዳይደነግጡ እንዳይናደዱ፣ እሳቸውም፡-

«ዋ-ያወቁብህ ጊዜ ነፍስህን ነው የሚያወጡት» ይሉኛል፡፡

# ፳

ልጅ ሆና ሰው ቤት ትገባና «ውጪ» ሲሏት ድርቅ ብላ «አልወጣም» የምትል ትንሽ ልጅ ነበረች:: እናቷ ለልጆቻቸው ግድ የሌላቸው አዝማሪ ነበሩ:: ከግዴለሽነታቸው የተነሳ ማታ ለማዘመር ሲሄዱ «የት ወደቅሽ? ምን ትበያለሽ?» ሳይሏት ነው ለባብሰው እብስ ታዲያ እኛ ቤት አምሽታ እራቷን በልታና አባዬ እግሯን አሳጥቧት ከፍት የተተወ ቤቷ ወስደን እናስተኛታለን:: እናቷ በጠዋት ተነስተው መንደርተኛውን መሳደብ ይጀምራሉ...

«እዚህ ጠቅጥቀው ጠቅጥቀው ቅዘናኗ መከራ!»

«ይጠቅጥቅሽ አባሽ!» ይላል አያቴ ግልፍ እያለው ሸንጋራዋ እናት ፀጥ ይላሉ «አፈር ብይና ልጅ ማሳደግ እንዲህ ነው?... ቆይ» ብሎ ይዝታል:: እንደማይለቃቸው ስለሚያውቁ ለተወሰነ ጊዜ በሸንጋራ ዓይናቸው ይጠነቀቃሉ:: ሴይጣን ከበረደ በኋላ ግን ሳያስበው እግሩ ላይ ይወድቃሉ:: ወይንም አማላጅ ይልካሉ:: እሱም ሲያንገራግር...

«ጠቅጥቀህ ጠቅጥቀህ ትበለኝ?» ይላል::

ወንድ አያቴ ሊያሰርጽብኝ ከሚጥረው ባህርይ ውስጥ አንዱን ብቻ እስከ ዛሬ ድረስ እደግፈዋለሁ:: ከኛ ከልጆቹ ውስጥ ሲያልፍና ሲያገድም የሰው ቤት መለስ ብሎ የተመለከተ ልጅ አሳር ፍዳውን ያያል::

«አንተ ውሻ! የሰው ቤት ምን ያሳይሃል?! ውሻ ነው የሰው ቤት የሚመለከት!!» ይላል ተቆጥቶ:: የሚገርመው ግን ከመንደሩ ልጆች ውስጥ እኛ ቤት ውለው የማያመሹት በጣም ጥቂቶቹ ናቸው:: አያቴ ከኛ ከልጆቹ ይልቅ ለተጎሳቆሉት የመንደር ልጆች ከፍተኛ ፍቅር ነበረው:: በዚህም የሚቀርቡት ሁሉ እሱን «አባዬ» እማማን ደግሞ «እማዬ» ብለው ነው ያደጉት:: በዚያ ለምደው አሁን ድረስ አንድ አምስት የሚሆኑ የወለዱና ትልቅ የሆኑ ልጆች እማማን «እማዬ» እያሉ ይጠሩዋቸዋል::

አያቴ ልዩ የሆነ ባህሪው ይበዛ ነበር ማለት ይቻላል:: እድሜ ልኩን ውኃ ጠጥቶ አያውቅም:: ውኃ ወደአፉ የሚገባው ሊጉመጠመጥ ሲል ብቻ ነው:: የውኃ





ጥሙን የሚያረካው ጠጅ በመጠጣት ነው:: ከዚህ ሌላ አያቴ ከሰሩት ምግብ ውጪ ቤት ውስጥ ሲበላ ታይቶ አይታወቅም::

ጎረቤቶቻችን ደግሰውኳ በስህን ይዘውለት ሲመጡ ለኛ አስተላልፎ ይሰጣል'ጂ ሰዎቹን ለማስደሰት'ኳ አይቀምሰውም:: እኛም ብንሆን

«አትበሉም?» ብሎ ይጠይቀናል

«አንበላም!» እንላለን በትከሻችን ንቅናቄ:: አያቴ አይቆጣም:: እንደውም ደስ ይለዋል:: «የሰው ቤት እህል ፈስ ነው:: የሰው ቤት ምግብ የሚበላው ውሻ ብቻ ነው» ይለናል:: በራችን ላይ የታሰረችውን ከብሪትን ፈቶ የምትመገብበት ስህን ላይ በማድረግ «ጎሽ በዩ» እያለ በስንጥር ገፋ-ገፋ ያደርግላታል:: እሷ እምቢ ካለች ኩራቱ ይጨምራል... «ጎሽ የኔ ልጅ» ይላታል «እሷኳ ነፍስ አውቃ... ውሻ አይደለችምኮ...» ስለውሻዋ የግማሽ ቀን ትንታኔ ያደርጋል::

የዚህ ባህሪው ተፅዕኖ በኔ ላይ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጎልቶ ይንፀባረቅብኝ ነበር:: ሰው ቤት ሄጄ ምግብ ያቀርቡ ይሆን? የሚለው ስጋቴ ሰቅዞ አያዝናናኝም ነበር::

አያቴ ኩራትንም ነው ያስተማረኝ:: ልጆች እያለን አሁን መሰብሰቢያ አዳራሽ የተሰራበት ፓርላማ ፊት ለፊት ካለው ሜዳ ላይ ኳስ ስንጫወት የቤተ-መንግሥት ወታደሮች ይጠሩንና ምግብ በትሪ ላይ ዘርግፈው በአጥር ላይ ይሰጡናል:: እኔ ጓደኞቼ ለበሉት ይተናነቀኝ እንደነበር ትዝ ይለኛል:: ፊቴን አዞራለሁ.... አታምኚኝ ይሆናል አንዳንዴ ያስታውከኛል:: ጓደኞቼ ቅልጥም የተጋደመበትን የቤተ-መንግሥት ምግብ ተሻምተው ከበሉ በኋላ ወደ ጨዋታ ሲመለሱ እነሱን መንካት ኳን ይቀፈኝ ነበር::

አያቴን በዚህ በዚህ እወደዋለሁ:: የሰው በሆነ ነገር አለመጓጓትን የኔ አድርጎልኛልና:: ከሱ ባህርይ የምጠላው የገንዘብ አያያዙን ነበር:: ይሄ ባህርይው የኔ ባለመሆኑም እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ያስብለኛል::

አያቴ የጫማ-ቀለም ገዝቶ የማስቀመጥ ባህርይ አለው:: ያንን ቀለም በብሩሽ የምቀባለት እኔ ነኝ:: ታዲያ በወር የሊስትሮ አስር ሳንቲም ደሞዝ አለኝ:: በፍቅር እጠብቃት እንደነበር አስታውሳለሁ:: ታዲያ «ደሞዜን» ከተቀበልኩ በኋላ ደግሞ ጣር ይሆናል:: እንደምን አድርጌ ላጥፋት!? አያቴ ይገድለኛላ!!

«አባዬ ከረሜላ ልግዛ?»

«ከረከር ውረድ»

«ኬክ ልግዛ»

«አከክ በገንዘብ አልገዛም!»

«እሺ ዳቦ?» ይሄኔ ቱግ ይላል... ምናምን ይደብድብ አባትክ!! ዳቦ ቤት ውስጥ ጠፋ??»

ሳንቲሟን በመዳፌ ታቅፌ ወዬ ማደር ነው፡፡ ለሁሉም ነገር ማጥላያ አያጣም፡፡ «ባሰቴ? ጨሎ በእግሩ ያቦካውን ነው ምግብ ብለህ የምትበላ? ቱ! ቱ! ቱ!...»

ከሳምንት ጭቅጨቃ በኋላ እየገፈታተረኝ «ሂድ! ሂድ! ወትውቶ ገደለኝ አይደለም?...» ይልና ከቁጣ ጋር ይፈቅድልኛል፡፡ እኔኮ የምፈልገው በሳንቲሟ ምናምን ገዝቼ መብላት አልነበረም፡፡ ብቻ ገንዘቧን ማጥፋት! አንዳንዴ አያቴ እያየ ሳንቲሟን ለለማኝ የምሰጥበት ጊዜ ነበር፡፡ ታዲያ በዚህ ድርጊቴ የሁለት ወር ደሞዜን እቆነደዳለሁ፡፡

አያቴ አገሩ ጎጃም ዳሞት ነው፡፡ ከአገሩ የወጣው ገና የአሥራ አራት ዓመት ልጅ ሳለ አንድ ቄስ ደብድቦ ቄሱ በነፍስ በሚጠበቅበት ጊዜ ነው፡፡ ጨካኝ ነበር፡፡ ጨካኝነቱን የምትገነዘቢው ስለ ሀገሩ በሚያወራበት ጊዜ የመጨረሻ ልጅ መሆኑንና ከሰባት ወንድሞቹ ውስጥ በመጨረሻ አገሩን የለቀቀው እሱ መሆኑን አውርቶ የወላጅ መካን የሆኑትን ወላጆቹን ሲያነሳ ምንም የሐዘን ስሜት አይሰማውም፡፡

«ይሙቱ ይኑሩ አላውቅም፡፡ እስካሁን ይኖሩ ብላችሁ?» ይላል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ፍቅር እስከ መቃብርን ሳነብ የበዛብህን ወላጆች የሱ እንደሆኑ ሆኖ ስለተሰማኝ «አይ ጎጃም» እላለሁ፡፡

ሌላው የአያቴ ጨካኝነት የሚታየኝ ብዙ ጊዜ ከቤታችን በግ አይጠፋም፡፡ ግልገል ገዝቶ ያሳድጋል፡፡ በጎቹ እሱን ከመልመዳቸው የተነሳ ምሳ እስኪበላ ጠብቀው እጁን የጠራረገበትን እንጀራ ይጎርሳሉ፡፡ አያቴ በጎቹም ቢሆኑ ሥርዓት እንዲኖራቸው ይፈልጋል፡፡ የሚታሰሩበትን ገመድ አንገታቸው ላይ ይጠመጥምና ወደመናፈሻ አስከትሏቸው ይሄዳል፡፡ አንዳንድ ሰዎች በጎቹን ከኋላ ያዝ ሲያደርጓቸው ይጮኃሉ፡፡ አያቴ ዞር ይልና «እባክህ ልቀቀው» ይላል፡፡





አያቴ በዚህ አይነት ለብዙ አመታት በጎችን እንደ ልጅ አድርጎ ቢያሳድግም ጊዜያቸው ሲደርስ ለማረድም ወደኋላ አይልም፡፡ እማማ «ቀድሞ አለማቅረብ፣ ካቀረቡ በላይ ማረድ ደግ ነው?» ይሉታል፡፡ «ዝም በይ!» ይላል አያቴ «ከብት ነው ሌላ ምን መሰለሽ? ካልታረደ አዝለሽው ልትዞሪ ነው?» አያቴ ዝም ይሉታል ይፈሩታል!

አያቴ መልኩ የጥቁር መልአክ ነው፡፡ ሸበቶ እሪዙን ያሳድጋል፡፡ ሉጫ ነጭ ፀጉሩንም ወደኋላ ማጅራቱ ላይ ያደርሳል፡፡ አፍንጫው ከዓይኖቹ መካከል ተነስቶ የሚተኮስ ሮኬት ይመስላል፡፡ ዓይኖቹ የንስር ናቸው፡፡ ጎላ ጎላ ያሉ ጥርሶች አሉት፣ መካከለኛ ቁመት፡፡ ዘወትር የተቋጠረ ቅንድብ!!

አብዛኛውን ጊዜ በራችን ላይ ወንበር አውጥቶ የመቀመጥ ልምድ አለው፡፡ ነጯ ከብሪት እግሩ ሥር ትተኛለች፡፡ ከኛ ከልጆቹ የበለጠ ውሻዋ ትሽቆጠቆጥለት እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ከመፈታቷ በፊት ሌላ ቀርቶ ሽንቷን ከሸናች ቤት አስገብቶ በር ዘግቶ ነው የሚገርፉት፡፡ ስትፈታ መንደሩን በሩጫ ታካልለዋለች፡፡ ሽንቷንም ምንም ራቅ ብላ ጨርሳ ትመጣለች፡፡

አያቴ በኔ ሲናደድ «ካንተ ከብሪት ትሻላለች» ይለኝ ነበር፡፡ እውነቱን ነው ልበል? እሷ ከኔ የበለጠ ትመካበት ነበር፡፡ እሱ አጠገቧ ከተቀመጠ ለለመደችው ሰውኳን ቁጡ ትሆናለች፡፡ እሱም ቢሆን እሷ ከተቆጣች «ተው ዞር በል!» ነው የሚለው፡፡ እሷን አይገስጥም «ዞል በል፣ ምን ገተረህ?» በዚህ ሊለምኑ የመጡ የኔ ብጤዎችን ይደበድብ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡

«ሂድ!! አታስጨህብኝ» ይላል የኔ ቢጤውን፡፡

«ስለገብርኤል» አይሰማም ለማኙ፡፡

«አንተንኮ ነው አትሄድም?»

«ስለመላኩ ገብርኤል!»

አያቴ ቀስ ብሎ ይነሳል፡፡ ፊቱን በማየት ከፋት ማሰቡ አይታወቅም፡፡ ዘክሮ ሊያባርር ይመስላል፡፡ ጠጋ ብሎ የኔ ብጤውን ወደ ከብሪት እየገፈተረ «በል ከደፈርክ አይቀር እንዲህ ጠጋ ብሎ ነው፡፡ እራቅ በማለት እያስጮሁ አይደለም» ይላል፡፡ ለማኙ ይዘነጠላል፡፡

አያቴ ኃይለኝነትን በጣም አድርጎ ይደግፋል:: እኔ ልጅ ሆኜ በሰፈራችን ልጆች ከተመታሁና ከሰማ አሳሬን ያሳየኛል:: «አንተ ንፍሮ! አፈርአባክ ብላና ሊጥ ነው የምትጠጣው?» ከዚህ በኋላ አንዱን ፈንክቼ ስሜን እስካድሰው ድረስ ጠጋ ባልኩት ቁጥር «ዞር በል አንተ ሴታሴት ሂድ እዚያ እናትህ ጋ ወጥ አማስል!» ብሎ ያባርረኛል::

እኔም የሚፈነከት ልጅ መፈለግ ነው:: ካገኘሁ ወላጆቻቸው ለአቤቱታ ይመጣሉ:: «የት አባቱ ነው ያለው?» ይላል አያቴ እኔን ወደጓዳ እየከተተ «ቆይ ይምጣ ፈሱን ባላስጨርሰው» እያለ ሸንጋግሎ ሰዎተኞቹን ከሸኘ በኋላ...

«ና ወዲህ... ና... መርበትበቱን ተወው ምናባቱ! እንዴት አርገህ ፈነከትከው? እ-እ እንዲህ ነው ልጅ ማለት! እኔ አንተን ሳክል ወፍ ባጠገቤ አያልፍም ነበር:: ንግግርማ? ምናባቱ የቆረጠው!...» አውሬ መሆን ይነሰኝ? በየቀኑ ግዳይ እጥል ጀመር:: «ና ወዲህ...» አይቀርም «መፈንከት ትላልቁን'ነው:: እኩዮችንማ ትግል መግጠም ነው...»

ከቤት ወጥቼ ከቆየሁ ግርፊያ ስለሚጠብቀኝ ፀብ አንስቼ ተፈናክቼ መመለስ አለብኝ:: እየሮጥኩ እቤት ስገባ «ና-ና ወዲህ» ይለኛል በቁጣ «የት ነበርክ?» እኔም እወሻክታለሁ:: የሰፈሩን ትልቅ ልጅ እየጠቀስኩ «ቢሰድበኝ ጊዜ እስከሚመቶኝ ድረስ አድፍጬ ስጠብቀው» እላሁ::

«አንት መልቲ!»

«አባዬ ሙት!»

«እህስ? ...ታዲያ? ፈነከትከው?»

«አዎና»

«አንት ዋሾ»

«አባዬ ሙት!»

«ጎሽ የኔ ልጅ!...» ወደ ጓዳ!





# ፯

የሰው ልጅ የተሰጠውን ዘር ያበቀይ ዘንድ የተዘጋጀ ማሳ ነው:: ያበቀየውንም ለፍሬ ይለው ዘንድ ውዴታ አለበት እርግጥ ነው:: የሰው ልጅ ከሚያድግበት አካባቢ ወግና ልማድ የተለየ ከየት አባቱ የራሱ የሆነ ባህል ይፈጥራል? ከየትም!!

ይህንን የምልሽ ልጅነት እኛ መንደር ውስጥ ያላትን ደረጃ እና ወሰን በማሳየት አራት ኪሎአዊው የወጣቶች ባህርይ ምንጩን እንድትረጂልኝ ነው::

እኛ መንደር ውስጥ የሚያድጉ ህፃናት ያላቸው አቀባበል ከውሻ ቡችላ ጋር ተነጻጽሮ ነው የሚታየኝ:: አንዲት የመንደር ውስጥ ውሻ ስትወልድ ቡችሎቿን ወሳጅ ይበዛል:: እያንዳንዱ መንደርተኛ በቡችሎች ላይ የባለቤትነት ጥያቄ ያነሳል:: ውድድሩን በአሸናፊነት በመደምደም ቡችላ የደረሳቸው ቤታቸው በር ላይ በካርቶን በማድረግ ማሳደግ ይጀምራሉ:: ቡችላዋ አድጋ ሆዷ እየሰፋና ሰፌ መጠለያ እያስፈለጋት ሲመጣ በዱላ ከመንደር ውጪ ወደ ባቡር መንገድ ትባረራለች::

«ለቃቅማ ትብላ፣ ማን እሷን አስቀምጦ ይቀልባል? ሥጋዋ አይበላ!»

የመንደሩ ልጆች ደግሞ...

አንድ አዲስ ልጅ ሲወለድ «ና ወደኔ!» የሚለው ይበዛል:: እየተቀባበሉት ይዞራሉ:: የኛ ሰፈር ሕጻናት አስፓልቱን ለይተው ቤት አንቀመጥም ብለው ማልቀስ የሚጀምሩት ገና በሦስት ወር ዕድሜያቸው ነው:: አፉ በሚጣፍጥበት ጊዜ የተለያየ ስድብ ያስተምሩታል::

«በስብስ በል»

«ብብሽ» --ይሳቅለታል

«እናትሽን በል»

«እና...» ያውኩለታል?

ልጆቹም ፈጣኖች ናቸው:: ሁለት አመት ሳይሞላቸው አቀላጥፈው «ብስብስ፣ እናትሽን» ማለት ይጀምራሉ:: ይሄኔ «አ!? ባለጌ!» ይመጣል:: ቆንጣጩና ተቆጪው ይረባረባል::

«ኧረ የታባቱ! ይሄ ባለጌ ቢሉት!»

ከዚህ በኋላ አዲስ ወደተወለደው (አፉ ወደ ሚጣፍጠው) ትኩረት ይሰጥና ይሄኛው ይተዋል። «በስብስ» ይቅርና «ዳቦ!» ማለቱ የስድብ ያህል የሚያስኮረኩመው ይሆናል።

«መኪና ይጠብቅ! ማስቲካ ይሸጥ! ሲጃራ ይቸርቸር! የሱ ባልንጀሮች ልብሳቸውን ችለው ነው፣ ትምህርታቸውን ችለው ነው፣ ይሄ ሰፈር እያውደለደለ...» አስተያየት ሰጪው ይበዛል።

የአሁኖቹ ልጆች ከኛ ጊዜ ልጅነት የከፋ ኑሮ ላይ ያሉ ይመስለኛል። ህጻናቱም እንደ አሸን ነው የፈሉት። አንዳንዶቹ «በሞተር ነው የተፈለፈሉት» እያሉ ይቀልዳሉ። እኛ ልጆች ሆነን ቢያንስ እስከ አስር አመታችን ድረስ ተመልካችና ሰሚ አናጣም ነበር።

እኔ ልጅ ሆኜ አንድ «ባሌ» እያሉ ያሳደጉኝ ሴት ነበሩ። ባፈና ይባላሉ። ሸፋፋ፣ ሲሄዱ በሆዳቸው መሬት ለመጥረግ ያሰቡ ይመስል እግራቸውን ፈርከክ አድርገው ነው። ታዲያ ድንገት ሳላስበው ስጫወት ከበስተኋላዬ ይመጡና በእጃቸው አፌን ነካ ያደርጉታል። ወይንም አይቼአቸው ከሮጥኩ ከጭናቸው መሀል የቦጨቁ በማስመሰል ወደ አፌ አቅጣጫ እንደመወርወር ይላሉ። እኔ በእርግጥም የወረወሩት አፌ ውስጥ የገባ ይመስለኝና አፌን ቶሎ ቶሎ እጠርጋለሁ። ምራቄን እተፋለሁ።

«ለባለቤቱ ቁርሱን ሰጠሁት» ይሉና በአካባቢው ሰዎች ያስቁብኛል። አለቅሳለሁ። አሁን አሁን ታዲያ ሲያገኙኝ «ባለቤቱ እምሴን አብልቼ አሳድጌ» ይሉኛል። አሁን ድረስ ሴት አያቴን የሚጠሩዋቸው «እማቴ» እያሉ ነው።

ልጅ ሆኜ ጅል ነበርኩ ልበል? የእውነት ወደፊት እሳቸውን የማገባቸው ይመስለኝና ጭንቅ ይለኛል። «እምሴን አብልቼ አሳድጌ ማ-አባቷ ናት አንተን ባሌ የምትል?» ይሉኛል ቆጣ ብለው። ብዙ ጊዜ ስለሚጨንቀኝ እማማን ጠጋ እልና፡-

«እማማ ባፈናን አላገባም» እላቸዋለሁ

«ለምን?» ይሉኛል ሳቃቸው እየመጣ

«አሮጊት ናቸዋ» እላለሁ

«እኔ ይሄንን አላውቅም! -- እያበሉ አሳድገው ነውር አይደለምዴ?» ይሉኝና እየሳቁ ለእማማ ባፈና ይነግሩብኛል።





--መሳቂያ ነበርኩ ማለት ነው።

ከድሮ ጀምሮ እኛ መንደር ውስጥ ህፃናቶችና አዋቂዎች ያላቸው ግንኙነት የተወሰነ ገደብ የለውም። አዋቂዎቹ ህፃናቶቹን ሲተዋወቁ «ሚስት ትፈልጋለህ? አንድ ቆንጆ ልጅ አለችኝ፣ ባል ትፈልጊያለሽ አንድ ቆንጆ ልጅ አለኝ...» እያሉ ነው። ከዚህ ሌላ ከመንደራችን እፍግፍግነት የተነሳ ሁሉም ተደበላልቆ ነው የነገር ማዕዱን የሚያቦካው። አዋቂዎቹ ሲሰዳደቡ፡- ህፃናቶች አፋቸውን ከፍተው ያጠናሉ። ወይንም አንዷ ትንሽ ከፍ ያለችው ልጅ ለእናቷ እረድታ ጎረቤቷን በስድብ ታቦን ዘንድ የሚከለከላት ደንብ የለም። ደግሞስ የስድቡ ሥነ-ልቦና?

«ሽርሙጣ!» ለሚለው «የቆንጆ ወጉ ነው፣» የሚል ወደ መጥፎ ምግባር መሪ መልስ አለው።

ልጆች ሆነን ስለነበረን የብልግና ነፃነት አንዱን ላጫውትሽ

መንገሻ ዘውዴ የሚባሉ አዝማሪ ናቸው። አንገታቸውና ማጅራታቸው በሎከሎከ ሥጋ የታፈነ ነው። ግን በልተው አይደለም። ሁልጊዜም የሚበሉት የግዢ ደረቅ እንጀራ በቃሪያ ኮርሽም እያደረጉ ወይንም በጥሬ ጎመን ላይ ጥሬ ጨው ነስነስ አድርገው ወይንም በድፍን ቲማቲም እየገመጡ ነው። ማሲንቆአቸውን በአንድ እጃቸው ይዘው ቀስ እያሉ ሲሄዱ ከበስተኋላቸው እንደርስባቸውና፡-

«አባባ መንገሻ አዘፍኑን?» እንላቸዋለን። ይህን ጊዜ የመንደሩ ሴቶች ተሰብስበው ማዳመጥ ይጀምራሉ ዘፈኑም

«የብሳና ገብስ!» ይሉናል ሲያወጡልን ማሲንቋቸውን እየገዘገዙ «የብሳና ገብስ!» እንላለን

«ወንድሞቼን ሁሉ!»

«ወንድሞቼን ሁሉ!» እንቀበላለን

«ፈጃው እም...!» ይሉናል። እኛም የመጨረሻዋን የስንኝ መድፊያ እየደጋገምን መዝለል ነው። ይቀጥላሉ...

«የብሳና ዱላ»

«የብሳና ዱላ»

«እህቶቼን ሁሉ»

«እህቶቼን ሁሉ»

«ፈጃቸው ጂ...!» አሁንም የመጨረሻዋን ቃ እየደገምን እንዘላለን:: ቆመው የሚያዳምጡት ሴቶች «አፈር ብሉ!» ብለው እስኪያባርሩን (ከልባቸው ባይሆንም) እንቀጥላለን::

«ሴት ወይዘሮ ሁሉ፣»

«ሴት ወይዘሮ ሁሉ፣»

«ድንኳኑ ጠቧቸው!»

«ድንኳኑ ጠቧቸው!»

«ምነው ወደ ጓሮ፣»

«ምነው ወደ ጓሮ፣»

«በዳስ ቢያደርጓቸው» እየደጋገምን መዝለል ነው:: አባባ መንገሻ በሞት እስኪለዩን ድረስ ሲያዘፍኑን ነበር:: ነፍሳቸውን ለገነት ያብቃውና::

የሰው ልጅ አዕምሮ ጠማማ-ፍጥረት ነው:: ለመጥፎ ነገር ቀና የመሆንና የመቀበል ባህርይው ይጎላል:: እኔ ስለምን እስከዛሬ ይህንን ግጥም አልረሳሁትም? ይገርመኛል:: እኛ መንደር ካዋቂዎቹ የሚዝረከረኩ ለህፃናት የማይበጁ ብዙ ግማግም ነገሮች ሞልተዋል:: ደግሞስ በእነሱ (በአዋቂዎቹ) እንዴት ይፈረዳል? ሳሎኑ፣ መኝታ ቤቱና ዕቃ ቤቱ አንድ ክፍል በሆነበት ቤት፣ መዝናኛው መስሪያውና መዋያው አንድ እፍግፍግ መንደር በሆነበት ስንቱ ተጠንቅቆበት ይዘለቃል? በቃ ለህፃናቱ የተለየ የሕይወትና የአኗኗር ማዕድ እንዳይኖር የሆነበት ብዙ ሺህ ምክንያቶችን መደርደር ይቻላል:: በዚህም ይመስለኛል እኛ መንደር ውስጥ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ህግ ተፋልሶ ልጆች አካላቸው ሳይዘገጃጅ አዕምሯቸው ቀድሞ ፍትወትን ይረዳና ለመጥፎ ምግባር ሲገፋፋቸው የሚታየው:: ልታምኝ አትችይ ይሆናል፡- ትላንትና ሁለት ሕፃናቶች (ወንዱ የሶስት ሴቷ የሁለት አመት ልጆች) ብልግና ሲሰሩ ተያዙ:: ይሄ ተደጋጋሚ ድርጊት በመሆኑ አዋቂዎቹ ተሰብስበው ህጻናቶቹን እየገረፉ ማሳቅ ነው:: ሆሆሆይ — ኧረ አፈር ብሉ! ማን አሳያቸው! እየተባባሉ:: ከዚያ ወዲያ ህፃናቶቹንም ለማብሸቅ የሚጠሩት በባልና በሚስትነት ነው:: ‹ባልሽ› «ሚስትህ» ይባላሉ::





# ፯

«በመረበ-ፍትወት፣ በመስህበ-ወሲብ፣ ተብትበህ-ተብትበህ አሻጥረኛው አንተ-ምን አርግ ትለኛለህ?»

(ዑመር ኻያም በተስፋዬ ገሠሠ እንደበት)

ፍትወት የጥጋብ ውጤት ተደርጎ ይቆጠራል:: ፍጹም ስህተት! ቅንዝረኝነት የድህነት ውጤት ነው:: ወሲብ በማጣት ይገናል...:: አለበለዚያማ እኛ መንደር ዝር ባላለ፣ አንድስምኳ ችግር ማለዘቢያ ባልተገኘ ነበር::

ወሲብ የመንደራችን ቅመም ነው:: የማይገባበት ቦታ የለም! እግዚአብሔር የሰው ልጅ ችግሩን ቀብቅቦ የታሰበበት የሚያደርስ አጋሰስ ያደረገው በወሲብ ነው ያልኩት የኛን መንደር ሰዎች ሳስታውስ ነው:: የሰው ልጅ አካል ምን ያህል ቢደክምም ለፍትወት የሚሆን ኃይል አያጣም:: ከየትም ከየትም ብሎ እንጥፍጣፊዋን አጠራቅሞ ለዚያችው ያውላታል::

አንዳንድ ጊዜ መንደራችን የፍየሎች ጋጥ መስላ ትታየኛለች:: በወሲብ ሁሉም እኩል ነው:: ወጠጤው ከአውራው ጋር እየተጋፋ ከንፈሩን ገሽልጦ ሴቶች ጭራ ሥር ይገኛል:: እንደነገሩ የሆነ ትዳር ያላት ጨዋ መሰል ሴት ደጅ ልትወጣ ብቅ እንዳለች ካንዱ የመንደር ጎረምሳ ጋር ተጣምዳ ትታያለች...

«ውይ ምን ነካት?» ይባላል ለወጉ ያህል:: ትታማለች ሐሜት ወርተራ ነውና ዛሬ የሐሚቱ አሟሟቂ ነገ የምትታማ ትሆናለች::

መንደራችንን በፍትወት እንፈትሻት ከተባለ አባገሬን (ገረመውን) ማንሳት ግድ ነው:: እሳቸው ያሉበት አየሩ ወሲብ ወሲብ መሽተቱ አይቀርም:: ሴት ባዩ ቁጥር «ለያምስልባትና ያቺ ውሽማዬ የነበረችውን የእንጀራ እናቴን ትመስላለች» ይላሉ:: ከዚያ ገና እረኛ እያሉ አባታቸው ወጣት ሴት አግብተው እንዴት ሲቋ አጥምዳ ውሽማዋ እንዳደረገቻቸውና ይቀርብላቸው ስለነበረው ረቂቅ ምግብ ዘርዝረው ያወራሉ::

አባ ገሬ ብዙ የወሲብ ግጥም ያውቃሉ:: ማሲንቆዋቸውን እንደነገሩ እየገዘገዙ ያንን ወሲብ ነክ ግጥማቸውን ያንዶለዱሉታል::

«የበቅሎ ማሰሪያው አጭር ነው ገመዱ፣

ልጅቱ እስከትገኝ እናቲቱን ብ---!»

ደሞ ያደርጉታል:: ልጅቷ ከጠፋች እናቲቱን አይለቁም:: የተግባር ሰው ናቸው ለማለት ነው:: ድንገት ማንኛውዋም ሴት የሆነ ቦታ ከተገኘች የስንዴ ፍንካች የማያካክል ጠባብ ዓይናቸውን በልምምጥ አጥፍተው «ሙች ሙች የቡና ማፍያ እሰጥሻለሁ:: አልቆይም፣ ጎንበስ ትያለሽ ቸለስ አድርጌብሽ በቃ!» ይላሉ:: ወጣቶቹን ሳይቀር:: እሽ ከተባሉ ያላቸውን ገንዘብ ሁሉ ከመስጠት ወደኋላ አይሉም:: «ያጥፋኝ አልቆይም!» ለማግባባት ይሞክራሉ::

ወሲብ ለአባገሬ «ፈርስ» ነው:: እውነት ማለዘቢያ «ከፍተኛ የሴት አምሮት አለብኝ» ይላሉ በግልጽ:: እውነትም ሰውነቷ ሞላ ያለ ሴት ሲያዩ መርፌ ዓይናቸው አብሮ ይንከራተታል:: «ጥሎብኝ ሴት እወዳለሁ» አይደብቁም...

..አባ ገሬ ሴት ይወዳሉ ብቻ መባል የለበትም፣ ያመልካሉ:: ከፈጣሪያቸው በላይ አድርገው ያያሉ ማለት ይቻላል:: ሌሊት ነጭ ጋቢያቸውን ነጭ እራሳቸውን አከናንበው ቤተክርስቲያን ቢሄዱም ልባቸው የሚያመልከው ሴት ነው:: «አንድ ጊዜ» ይላሉ እራሳቸው ያወሩታል:: ቤተክርስቲያን ሲሄዱ «ጠይም የመሰለች ሴት ወይዘሮ አገኘሁ:: አዛውንት መሰዬ ተጠጋኋት:: መጀመሪያ አልጠረጠረቻቸውም:: እያዋሩ እሷም ለመሳለም ስለነበር ወደ ቤተክርስቲያን ሄዱ:: ምን እንዳወሩ እንዴት እንዳግባቧት እንጃ ወደ ባለወልድ መቃብር አስጉበተው አንዱን ኃውልት አሲዘው «ጠሀይ የመሰለ ቂጧን ገልቤ እያየሁ...:: በጨዋታችን መሀል «አንቺ» አልኳት

-ምነው? አለችኝ

-ይሄ የተደገፍሽው ሰውዬ ቀብሩን ፈንቅሎ ቢነሳስ?

-ቱ! ቱ! ምን አልኮት... ይልቅ ይከውኑና ወደ ጠሎታችን እንሂድ (እንዲህም አርጎ ጠሎት የለ!) ያሽሚጥጣሉ:: ቀጥለው ጨዋታቸውን Present (የአሁን ጊዜ) ለማድረግ «ያንን የመሰለ ቂጥ እስከዛሬ ገጥሞኝ አያውቅም ምናልባት የሷ!» ወደ አንዷ ይጠቁማሉ... «አፈር ብሉ!» የሚል የቀልድ ምላሽ ይሰጣቸዋል::





አባገሬ በሚስጥር ውስጥ ለውስጥ ቢሄዱ የምትከለክላቸው ሴት አልነበረችም:: «ግን አፋቸው አያርፍም ያወሩታል:: ያም ሆኖ አንዳንዶቹ አይከለከሏቸውም» ያጥፋኝ! የሷን የመሰለ ዕቃ አልገጠመኝም!!» ይላሉ በነጋታው::

አንድ ጊዜ ሲያንቀዠቅዣት የአናጢው አሰፋ ሚስት ታቀምሣቸዋለች:: እናጢው የተወለወለ ጀበና የመሰለ ፊታቸውን ፈገግ አድርገው ሲሰከሩ እንደሚያዘወትሩት «የፋሲል ዘር!» እያሉ ሊያስተዛዝኑ የለቅሶ ድንኳን ሲገቡ አባ ገሬ...

«አንተ ቀሚስ ግዛ እኔ መቀነቷን፣

የጋራ ሚስታችን አትሂድ እራቁቷን» ሲሉ ገጠሙ:: ሚስጥሩ ቀድሞ የደረሳቸው ሳቁ... ተንከተከቱ::

አባገሬ ነፍስ ያለችው ዕቃቸው ላይ ናት:: ያቺ ዕቃቸው የበቀለችው ደግሞ ግንባራቸው ላይ ይመስላል:: ግንባር ይሸሸጋል እንዴ? በፍጹም! እሳቸውም ግድ የላቸውም:: ብቻዋን የሆነች ሴት ካጋጠማቸው የሚያማልሏት ድንገት አውጥተው በማሳየት ነው «ነይስኪ ጨብጪው፣ አቤት ሲሞቅ!» ይላሉ:: ተሰቷት ከሰጠች የጥዋት ዜና ትሆናለች:: ሌላው ሁሉ ከዚህ ሰማይ ስር በመሆኑ የማይወራ የለም አዲዮስ::

እኚህ የወሲብ ጳጳስ ምግባራቸውን የሚገልጽ የፈረስ ስም ወጥቶላቸዋል:: «አባ ብዳው» ይሏቸዋል:: ደስ ይሰኛሉ::

«የቅቤውን ማንኪያ ማር አታስነካው፣

የሁላችን ወንድም ገሬ አባብዳው»

ግጥም የሚሰጠው በጠጪዎች ነው:: ገሬ በግጥሙ ስለሚረኩ የተሸለሙትን ገንዘብ እዚያው ጨርሰው ባዶ እጃቸውን አጨብጭበው ይገባሉ:: ሥምና ግብር ብቻ ሳይሆን ሰያሚና ተሰያሚን ያፋቀረ ሥም ይሉሻል:: «ገሬ አባብዳው» ነው::

ገርዬ ሲሏቸው «ልንፋሽ አባብዬ» ማለት ያዘወትራሉ:: ያጥፋኝ ለነፍስ እሆንሻለሁ ስጪኝ:: መንደሩ ውስጥ ስለመሳሪያቸው ኃያልነት በግልጽ ይወራል:: «ቢሆንም ከፃ አለቃ በየነ አይበልጥም ኡ-የሱ ትልቅ ነው::» ይባላል::

* * *

ፃ አለቃ በየነ ማነው? ማነው እሱ ገሬ አባ ብዳውን የሚበልጥ?

ነባር ኪስ አውላቂነት የት እንደዘመተ የሚታወቅ ነገር የለም። ፺ አለቃ ነኝ አለ። ፺ አለቃነቱ ፀደቀለት። በፊት እኛ ሳንፈጠር በጨቤ የሚሞሻለቅ አመፀኛ ሌባ ነበር አሉ። እሱ እንደ ጦር ሜዳ ቁስለኛ የሚቆጥረው ጠማማ አፍንጫ ነበረችው። ለቃላት የሚያስፈልግ የአፍንጫ ውስጥ አየር ስለሌለው ወደ መነፋነፍ ያደላል።

፺ አለቃ በየነ እኛ ነፍስ እያወቅን ስንሄድ እድሜና ካቲካላ እየተጫጫነው ሰውን ፊት-ለፊት ከመግጠም ይልቅ ከወደ ምላሱ አድልቶ ነበር። ይሳደባል። ጉልበት ያነሰው ለሴቶችም ጭምር ነበር። ድሮ ተሸከሞ ወደፈለገበት እንዳልወሰደ አሁን ልቡ እየከጀላቸው ስለማይችል «ጅብዳ»ውን እያወራ ሊያማልላቸው ይሞካከራል፡-

«እኔ ፺ አለቃ? ስንቱን ሴት ወይዘሮ አሰግጃለሁ መሰላችሁ» ይልና እንደ መኩራት ብሎ «ባሸከር ነበር መልዕክት የሚደርሰኝ። እሜቴ ይፈልጉዎታል ስባል አመሻሽቼ እሄዳለሁ አይ ኩራቴ!! ለእግሬ ውሃ እስኪሞቅ የዶሮ ዓይን ከመሰለ ጠላ ጋር እራት ይቀርብልኛል አይ ጥጋቤ! ከዚያ እንዳይደርስ የለም ጊዜው ይደርሳል አይ መንቀባረሬ!...

«...እንደዘለሉ ጥልቅ ማለት የለም። መጀመሪያ ዳር-ዳሩን አጠዳለሁ፣ አጠዳለሁ...» እጁን መስተወት እንደሚወለውል ሰው አስመስሎ ያሽከረከረዋል «...አጠዳለሁ፣ አጠዳለሁ። ዓይኗን ነው የማየው አይ ብላቴ!! እያለሁ-አጠዳለሁ። መስለምለም ስትጀምር ሰደድ አደርገዋለሁ። ልቧ ሲጠፋ ይታወቀኛል ይሄኔ እነፍጋታለሁ አይ ክፋቴ!! ምነው ፺ አለቃዬ ምነው? ትላለች። ረጋ በይ እላታለሁ አይ መንቀባረሬ!! አሁን ዳር ዳሩን ማጥዳት የለም ሡትትትት-ት አድርጌ እከተዋሁ። ከዚያ ሰባቱን ጉጥ እቆጥራለሁ። ሰባተኛውን ጉጥ ደርሼ ስነካካው ይሳሙኝ ይሳሙኝ ፺ አለቃዬ ማለት ትጀምራለች አይ ንፍገቴ!! ንክች አላደርገውም። እኔ ሳልፈልግ እሷ ሙጥኝ ስትል እጠብቅና የመጨረሻ ኃይሌን ተጠቅሜ እለቅባታለሁ። የት እንዳለች ትዘነጋዋለች...» ከ፺ አለቃ የወሲብ ወሬ ጋር መሸቶ ይነጋል። ሴቶቹ አፋቸውን ከፍተው እየተሳሳቁ ያዳምጣሉ። «አፈር ብላ!» አንዳንዴ ለወሬው ማጀቢያ የጋለ «ብረቱን» አውጥቶ ያሳያቸዋል። «አፈር ብላ- አፈር ብላ» እየተባባሉ በተሸፋፈኑበት ነጠላቸው ጓሮ ይመለከታሉ።

«ቱ! ምኑን አሽከሞታል ልጄ? አበስኩ ገበርኩ»





በነጋታው በበራቸው ሲያልፍ «፺ አለቃ! ፺ አለቃ!» ጥሪ ይበዛበታል። ያኔ አይ ኩራቱ!! እንደ አሳማ አፍ ወደ ላይ የተገለበጠ ከንፈሩን ፈልቀቅ አድርጎ አዳፋ ኮቱን ያስተካክላል። ወደ መጨረሻ አካባቢ ጨዋታው በጠጅ ግብዣ ሆነ። ምን ያህል ቢስማማቸው ይሆን?»

፺ አለቃ ትረካ ውስጥ ሁሉም ሴት ገፀ-ባህሪዎች ወይዘሮዎችና ተሸናፊዎች ናቸው። «ይሳሙኝ-ይሳሙኝ» ይላሉ። በስተመጨረሻ እሱ ሁልጊዜ አሸናፊና ኩሩ ነው። ፍትሃዊነት የጎደለው የፍትወት ግንኙነት ነው ትረካው።

ትረካው ያማለላቸው አንዳንድ የመንደሩ ሴቶች ሳይሞክሩት አልቀሩም። የአፉን ያህል «ሙያ» እንደሌለው ይወራ ጀመር። «ብልቱ ግን ብልት ነው ታዲያ ምን ያደርጋል?» እውነትም ፺ አለቃ በየነ የቀረው አፍ ብቻ ነው። መጥፎ ስድቦችን ያዥጎደጉዳል። የወንድ የበላይነት የተንፀባረቀበት ግልጥልጥ ያለ የወሲብ ታሪኩን ያወርዳል። በስተመጨረሻ የበከተ ስድቡ ወደ በከተ ምግባር ተለወጠ። መሀል አስፋልት ላይ በጠራራ ፀሐይ፣ ህዝብ እየተመላለሰ ይፀዳዳ ጀመር «ደሞ ለሐበሻ» ሱሪውን አጥልቆ ይሄዳል። ምን አይነት ፍልስፍና ጭንቅላቱ ውስጥ እንደገባ እንጃ። በፈረንጆች አደባባይ መፀዳዳት አንድ የፍልስፍና ዘርፍ ነው። የውሻ ባህርይ የሚያላብስ የፍልስፍና ድምዳሜ cynicism ይሉታል ዲዬጋን የተባለው ሰው የዚህ ምሳሌ ነው። እንደዲዬጋን ሁሉ ፺ አለቃ በየነም በጉልበቱ ረትቶት የነበረውን ህብረተሰብ በድከሙቱም ዳግመኛ አሸነፈው። የመጨረሻው መጨረሻ ሕይወቱ ሲያማርረው የነበረው እንጥፍጣፊ አቅም ጭራሽ ከድቶት በቂጡ እየተንፏቀቀና ከሩቅ እየሸተተ መኖር ጀምሮ ነበር። የት እንደገባ እንጃ ጠፋ።

* * *

እኛ መንደር በሴት ላይ የሚደርብ ወንድ ላይ ላዩን ይጠላ እንጂ በውስጠ-ታዋቂ ይከበራል። «ወንድ እሱ ነው!» ይባልለታል። የመንደሩ ወንድነት ሚስቶቻቸው የሚያድሩበት እከል ከገጠማቸው አንድም ብትሆን ያቺን ሌሊት ብቻቸውን አለማደር ነው። ሲያንጋፍፉ አንዷን ይዘው በልጆቻቸው እናት አልጋ ላይ ማንፈላሰስ ነው። ይሄም ላይ ላዩን ያስጠላል እንጂ በወንድነት ያስከብራል። ሚስት ብትኖርስ? እሷ

እቤት ተቀምጣ «አባወራው» የቀጣዩን ሴተ ላጤ በር ሲቆረቁር አያፍርም፡፡ ይሄ ሁሉ የወንድነት ስራ ነው፡፡

የወንድነት ሥራ ያልሆነው የተገላቢጦሹ ነው፡፡ ሱሪ ታጥቆ ሴት ስታናግረው ካልሞቀው፣ በቀልድም ቢሆን ተሻሽቶ አካሏን ከአካሌ ጋር አነካክቶ ግሉቱን ካላስመዘገበ፣ ጭለማ ሲገናኙ አፈፍ አድርጎ ቢያንስ ካላስለመነ፣ ከመንደሩ ሴቶች ቢያንስ በግማሹ ካልታማ እሱ ላይ ላዩን ይወደዳል ውስጥ ውስጡን ይናቃል፡፡ «ዕቃ ያለው አይመስለኝም» ድምዳሜው ነው፡፡ ቀስ በቀስ ሐሜት መሆኑ ቀርቶ «የለውም! የለውም!»

በዚህ ለብዙ አመት ሲጠረጠር የነበረው ፍቃዱ (እንቃቅሊት) ነበር፡፡ እንቃቅሊት የተባለው እንቁራሪት እላለሁ ብሎ እንቃቅሊት ስላለ ነው «አይ! እሱ ሙግት ብቻ! ምንድነው ሙግት!» ይሉታል ሴቶቹ፡፡ ዲያቆን ነበር፡፡ የሚያከራክር አይቶ አያልፍም፡፡ ሌላው ቀርቶ ከተወራ ቀልድ ውስጥ የሎጂክ ጥያቄ አንስቶ ይከራከራል፡፡ «ጢምና ዕቃ አልፈጠረበትም» ይሉታል፡፡

እንቃቅሊት ድሪያ ያውቃል፡፡ ሊላፋም ይሞካከረዋል፡፡ ቀልዱ ግን ከቀልድነት አይዘልቅም፡፡ ወዲያው ኮስተር ብሎ ወደ ክርክር ያመራል፡፡ አይግለው፣ አይሞቀው፡፡ ሴቶቹ ብስጭት ይሉና ማበሳጪያ ይፈልጋሉ፡፡

«እንቃቅሊት፣ ድንግላዊ ነህ?»

«እንዴት?» ለክርክር ያቆበቁባል፡፡

«ለመሆኑ አለህ? እስኪ አውጣው?»

«ነይ ግቢና ላሳይሽ» ይሄ ስለት ንግግራቸው ሳይጎዳው ያልፈዋል፡፡ በአንዲት ሴት ሳይጠረጠር በመጨረሻ ሸንጋራ አገባ፡፡ የመንደሩ ሴቶች ጉድ! አሉ፡፡ ሲመሻሽ ቤቱ ግድግዳ ላይ ተለጥፈው ያዳምጣሉ፡፡ ምንም ማረጋገጥ አልቻሉም፡፡ ደባሉ ወደሬን ይጠይቋቸዋል፡፡

«ኦ-ሆሆይ፣ ደሞ እዚህ ውስጥ ምን ዶለኝ?» የሳቸው መልስ ነው፡፡ ማረጋገጥ ባለመቻል ሰልችተው የተዉት ይመስለኛል፡፡ ሚስቱ ቅዝዝ ያለች በመሆኗ እንቃቅሊት «ሥራ» ባይሰራም የምታሳጣው አልነበረችም፡፡ የውስጥ ደዌዋን እንደምታዳምጥ ዶሮ የፈዘዘች ነበረች «ለአፈ ግም አፍንጫ ድፍን ያዝለታል» እንደሚባለው መሆኑ ይሆን?





# ድህረ ማስታወሻ

## አንድ

ወደ ሙሉጌታ ቤት የሄድኩት ፍቅርና አንድ የማስታወሻ ጥራዝ እንደሚጠብቀኝ ተስፋ በማድረግ ነበር፡፡ ግን ከዚያ ይልቅ ሙሉጌታ ከፉኛ ተደብድቦና ፊቱ ተነዳድሎ አገኘሁት፡፡ ሳየው ህዋሳቶቼ ፈዘዙብኝ፣ ማሰብ ተሳነኝ እንባዬ አይኔ ላይ እንደተደፋ ብርጭቆ ሆኖ ሁሉን አደበዘዘብኝ፡፡

«አይዞሽ-አይዞሽ -አይዞሽ» የሚል! የአፍ እሩምታ ተሰማኝ፡፡ ብዙ ሰዎች ነበሩ፡፡ ሙሉጌታ ድብዳብ የተነጠፈ ሳጥን ላይ ተቀምጧል፡፡ ሲያዩት ግማሽ ፍልሚያ ላይ በተሰጠው ጥቂት ጊዜ ለማረፍ የሚሞክር በከሰኛ እንጂ የተረታ ሰለባ አይመስልም፡፡ ግራ አይኑ ዙሪያ ዘጉኖ ከስሩ የተጎለጎለ የሥጋ እንቡጥ ይታያል፡፡ ለምን በቁስል ፕላስተር እንዳልሸፈኑት አልገባኝም፣ አፍንጫው ተደልድሎ ከጉንጮቹ ጋር ተቀላቅሏል፡፡ ለመተንፈስ እንደሱረት ሱሰኛ የጠበበው የአፍንጫው ቀዳዳ ይተናነቃል፡፡ ፈገግ ለማለት ሲሞክር የፊቱ ንቅናቄ ቁስሉን ስለቆሰቆሰበት ስቃይ ተነበበት፡፡

«ነይ እዚህ ነይ እዚህ-ነይ እዚህ» የሚል ሩምታ ተተኮሰብኝ፡፡

«እሱው'ጋ ትሁን» አሉ አንድ ጠና ያሉ ሰው፡፡ አስተያየታቸው ሴትነትን ያስታውሳል፡፡ ሁለት ሴቶች መካከል ተወሽቀው ሌላ ሴት ላይ ዓይናቸውን ያንገዋልላሉ፡፡

የሙሉጌታ እያት ባለሶስት እግር በርጩማ ሳጥኑ አጠገብ አስቀመጡልኝ፡፡ ሙሉጌታ ከደቀመዝሙሮቹ ጋር በመጨረሻ እራት ላይ ያለ መሰለኝ፡፡

ዛሬ አባቴ-ፊቴን ሲያጠና የነበረበት ሁኔታ አሁን ገባኝ፡፡ በሙሉጌታ ላይ ያደረሰውን የጥቃት መጠን ሲፈትሽ ኖሯል፡፡ አባቴ ድንገት ከሕይወቴ፣ ከመውደዬ ውስጥ ምንጥቅ ብሎ ስተፋው ታወቀኝ፡፡ ዶክተር ማርቆስ ላይ እንደሚዝተው ሁሉ ሙሉጌታንም እያስፈራራ ስለመቁለኝ ቁብ አልሰጠሁትም ነበር፡፡

ከጠያቂዎቹ መካከል ድንገት «ቺ! ያጥፋኝ እንዲህ ያደረገውን አውቀዋለሁ» የሚል ድምጽ ስሰማ ባነንኩ:: ሁለቱ ሴቶች መካከል የተወሸቁት ጠና ያሉ ሰው ነበሩ:: አባገሬ መሆናቸውን አልተጠራጠርኩም::

«ገሬ አባብዳው» አለች አንዲት መጠጥ ያነበዛት ሴት ከወደበሩ «እርሶ'ኮ ከዚያ ጉዳይ በቀር ሌላ አያውቁም:: ነገር እንዳያበላሹ» አፏን በነጠላ ሸፈነች:: ለመከላከል ያሰበችው የመጠጥ ሽታ ግን ቀድሞ ወጥቶ ነበር::

«ያጥፋኝ አልዋሽም እንደግዲህ መጠጥ ቤት ብር ሲያወጣ አይቶት ነው» አሉና «ቺ!» በጨረፍታ አጨበጨቡ::

ከሙሉጌታ ጋር ተያየን:: ድንገት መጽሐፍ ላይ የማውቃቸው ገፀ ባህርይ ኑሮዬ ውስጥ ጥልቅ ያሉ ያህል ግርታ ተሰማኝ:: ከዚህ በኋላ የራሴን ጉዳይ እያብሰለሰልኩ የተጨዋወቱትን አላዳመጥኩም:: ሙሉጌታ ፊት ላይ የማየው የአባቴን ጨካኝ ገጽታ ነበር:: አባቴ የሚፈልገውን ለማግኘት አውሬ እስከመሆን ይዘልቃል ብዬ ጠርጥሬ አላውቅም ነበር::

ምን ማድረግ እንዳለብኝ አወጣሁ አወረድሁ:: አባቴ በእኔ እንጂ በሌላ በማንም ላይ እንዳልዘመተ ተረድቻለሁ:: ማጥፋት የፈለገው ሙሉጌታን ሳይሆን የእኔን መንገድ ነው ስል አሰብኩ:: ይጥቀመኝም ይጉዳኝም መንገዴ ብዬ የያዝኩት አቅጣጫ ከአባቴ ፍላጎትና ጥምቅ ጋር ስላልገጠመ ብቻ የሚጎዳ ሰው፣ የሚበጠበጥ ቤተሰብ መኖሩ ጨነቀኝ:: አባቴ ዘና ባለ መንፈስ ቁልፎቹን እጆቹ ላይ እንደለማኝ ሳንቲም እያንቀረቀበ እጅ እንድሰጥ የጠየቀኝ መሰለኝ::

«የእንቺ እሱንና አካባቢውን ሙተው መድህኑና ህይወቱ ነው» ሐብሉ አይንተገተግም ወርቃማ ሰዓቱ የኮቱ እጅጌ ወስጥ አድፍጧል::

አንድ አዛውንት ድንገት መጥተው ከሐሳቤ አናጠቡኝ:: የሚሉት ጠርቶ አይሰማም:: ኃይለሚካኤል እፉፉ መሆናቸውን አልተጠራጠርኩም ሙሉጌታ መመለስ ስለተሳነው እያቱ...

«ከፉ ቀን! ከፉ ቀን!» አሉ:: ከእሳቸው መልስ ጥያቄውን ገመትኩ::

የማየው ነገር ሁሉ ወቀሳ ሆኖ አሸበረኝ:: እዚህ የተሰበሰቡና ሌሎቹም መንደርተኞች ሁሉ የአባቴ የግብታዊነት ሰለባ ሆነው በደላቸውን የሚያስጎበኙኝ





መሰለኝ:: ሙሉጌታን ቀና ብዬ አየሁት:: ለመተንፈስ ሲተናነቅ ሲጢጢጥ የሚል የአየር መጨናነቅ ይሰማል:: ከዚህ ቦታ ሚሄድ አማረኝ:: እያቱን ተከትዬ ወደጓዳ ገባሁ:: ምን ያህል ብር እንደያዝኩ አላውቅም:: በጭለማ ውስጥ የታከሲ አስቀርቼ ሰጠኋቸው:: እየተግደረደሩ እንቢ አሉኝ:: አልጋው ላይ አስቀምጬ ወጣሁ::

ሙሉጌታ ሐሳብ እንዳፋፋመው ዲዳ ሆኖ ነበር:: እንደምንም ብሎ «ብዙ የምናወራው አለ» ብሎ አቋረጠ:: ቤቱ ውስጥ ያሉት ምንትያ ፊቶች በተመሳሳይ አትኩሮት እንደሚመለከቱን ልብ አልኩ:: ሙሉጌታ ጥቂት ህመሙን አስታግሶ:-

«ከተነጋገርን በኋላ ሁሉም ይደርሳል» አለ::

ውስጤ ምን አነበበ? እኔ በውል ያላወኩትን ውሳኔ አየ?

«ከዚያ በፊት ምንም እንዳታደርጊ ሌላው ቀርቶ ምንም እንዳታስቢ»

ልወጣ ስል ብዙ ጥያቄዎች «የውሻ ቁስል ያድርግልህ» እያሉ ውልቅ ውልቅ አሉ «የውሻ ቁስል፣ የውሻ ቁስል፣... እንደ ውሻ ባሰኘ ሰዓት ላይ መቀጥቀጥ:: ሰው... የውሻ ቁስል... የውሻ ዕድል...»

* * *

ከአባቴ ሁብል ጋር በህቡዕ ተፋጠናል:: ቦቹ ለጥ ብሏል::

እኔን መናር ስላልደፈረ ኮምፒዩተሩ ላይ እየቀጠቀጠ ያጉረመርማል:: አልፎ አልፎ አጠገቡ ያለውን ስልክ እያነሳ የተለያዩ ሰራተኞቹ ላይ ይጮሃል:: ሦስቱ ሞባይሎቹ ጠረጴዛ ላይ ተበትነዋል:: ሁለቱ ተዘግተዋል አንዱ ብቻ ክፍት ነው:: ይሄን መስመር ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ነው የሚሰጠው:: አለመረጋጋቱ አረጋጋኝ:: የተረበሸ ሁኔታ ውስጥ መሆኑ የጨበጠው ነገር እንዳመለጠው ሆኖ ተሰማኝ:: ከፊቴ ላይ መጎዳት፣ መሰበር እንዳያነብ ሆኜ ተጠንቅቄ ተቀመጥኩ:: ወዲያው ጭንቅላቴ ውስጥ "Human fatherhood is a social invention" የሚለው የማህበራዊ ጥናት ባለሙያዎች ድምዳሜ ብሶቴን ቆስቁሶት አለፈ:: ገና ሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለሁ ይሄንን ርዕስ በመቃወም ተከራክሬያለሁ:: ዶክተር ማርቆስ በግርምት እያዩኝ «ሚስ እርጥባን፣ የአባትነት ግዴታ የትኛውም እንስሳ ላይ አይስተዋልምና ነው ምሁራኑ ማህበረሰቡ የፈጠረው ሰው-ሰራሽ ነው ያሉት» አሉኝ::

«የእንስሳት ባህሪ ለሰው ልጅ ማህበራዊ አደረጃጀት ምሳሌ ሆኖ መቅረቡን ጭምር ነው የማልቀበለው» እላቸዋለሁ ድድር ብዬ «ለምሳሌ ይሁን ቢባል እንኳን እንቁላሎቻቸውን በጋራ የሚታቀፉትን የወፍ ዝርያዎች የት ልትጥሏቸው ነው? ጫጩቶቻቸውን በጋራ እየመገቡ ያሳድጉ የለም?...» እየጋልኩ ስሄድ ይታወቀኝ ነበር:: ክርክሬ አባቴን ከባዕድነት ነፃ የማውጣት የሞት ሽረት ትንቅንቅ ነበር::

«አንዳንድ ኋላ ቀር ማህበረሰብ ዘንድ እንደማርጋሬት ሚድ ያሉ ባለሙያዎች ረዥም ጥናት አድርገው እዚህ ማህበራዊ አቋም ላይ ደርሰዋል:: ይላሉ ዶክተር ማርቆስ «ሜል ኤንድ ፊሜል» የተሰኘውን መጽሐፍ አላነበብሽም? እንድታነቡት ኮርስ አውት ላይን ላይ ጠቁሜ ነበር»

«አንብቤዋለሁ:: እኔ ግን የምለው ዶክተር ሚድ ደቡብ ፓስፊክ ውስጥ ያሉ የባሊ ሆነ የሳምዋ ማህበረሰቦችን ኋላ ቀር አኗኗር ከዚህ ተመሳሳይ ነው ብሎ ለመደምደም አያመችም:: ከዚያ አልፎ አባትነትን ፈጽሞ እውቅና የሚነሳ አቋም ለመያዝ ሳይንሳዊነቱን ፈተና ላይ ይጥለዋል::»

ያኔ ሽንጤን ገትሬ ተከራከርኩ:: አባቴ በእኔ አስተዳደግ ላይ እጁን ማስገባቱ ከተፈጥሯዊነት ይልቅ በማህበራዊ ጫናነት መፈረጁ ያለኝን ቤተሰባዊ ዋጋ የሚያሳንስብኝ ሆኖ ስለታየኝ ነበር:: ትዝ ይለኛል ይሄንኑ ርዕሰ ጉዳይ እንድንተነትን የሚጠይቅ ፈተና መጥቶ ነበር:: እኔ አቋሜ ሳይለወጥ ወንድ ተፈጥሯዊ ኃላፊነቱ ለሴቷ ዘር በማቀበል ብቻ እንደማይጠናቀቅ አስረግጬ መለስኩ:: ከዚያ በኋላም የወንድ ቤተሰባዊ ተሳትፎ በማህበራዊ ስምምነት የመጣ ነው ብዬ እንደማላምን ጭምር:: ውጤቱ ምን እንደሆነ አውቀው ነበር::

ዶክተር ማርቆስ ቢሯቸው ጠርተው የመልስ ወረቀቴን ለረጅም ጊዜ ሲመለከቱ ቆዩና «ሚስ እርጥባን፣ ይሄ የአካዳሚ ትምህርት ነው:: አንዳንዴ ተመሳሳይ ምሁራዊ አቋም እንዲያዝ የሚጠይቁ ጉዳዮች አሉበት:: እንደወታደራዊ ትዕዛዝ እንድንቀበላቸውና እነሱኑ እንድንደግማቸው የምንገደድባቸው:: እዚህ የመልስ ወረቀት ላይ አቋምሽን ገልፀሻል:: ጥሩ የሚሆነው የክፍል ውይይት ውስጥ ብቻ ነው:: ይሄን ጥያቄ አውቀሽ በመሳትሽ አስር ነጥብ አጥተሻል:: አጠቃላይ ውጤትሽም ከኤ ወደ ቢ ወርዷል:: ይሄንን ባልለውጠውም አንቺን ማድነቄን ግን አልሸሽግሽም» አሉኝ::





ያኔ አባቴን ለአስር ነጥብ አይደለም ለአጠቃላይ ትምህርቴ እንደማለውጠው ለራሴ ነግሬ ነበር:: ዛሬ ታዲያ ለምን? ምክንያቱም አባቴ ይሄን እኔጋ ያለ መብቱን በአግባቡ አልጠየቀምና ነው እንቢታ ውስጤ የተፈጠረው:: በደፈናው በኃይል ለመጣስ የሚሞክረው ነገር በዛ:: በመጀመሪያ ደረጃ ለምን አራት ኪሎ ላይ ጥናቴን እንዳልሰራ ፈለገ? ይሄን ለማስረዳት ከመሞከር ይልቅ መንገዴን ባሻገር መደብደብ ጀመረ:: ለምን? ለምን? ለምን?

አባቴ በስልክ ሠራተኞቹን ማስጨነቅ ቀጥሏል:: «ለምን አልጋውን አምጥቶ ሥራ ላይ እንዲተኛ አትፈቅድለትም?» ይላል:: ፊቱ የበለጠ ከስቶ ታየኝ:: ስልኩን ከጆሮው ላይ ሳይነቅል በሌባ-ጣቱ የመዝጊያውን ምላስ ተጫነና ቁጥሮቹን ነካካ::

«አ-የዚያን ሰው ጉዳይ እንዴት አደረክ?» አለ መቼም አባቴ ከድሮ ጀምሮ ከማያውቃቸው ነገሮች ዋነኛው የስልክ ሥነ-ሥርዓት አንዱ ነው:: ምናልባትም ሀብቱ የሰጠው መብቱ አድርጎ ስለሚወስደው ይሆናል:: «ቀድሞህ ከሰሰ? ጥሩ ነዋ:: መብላትና መሸከም ብቻ ከሚያውቅ አህያ ጋር ችሎት መቋቋምን እንደሆነ ለምደነዋል::» ጠበቃው ላይ እንደሚጮህ ገባኝ

እኔን ላለማየት ይመስላል ኮምፒዩተሩ ላይ እየተመለከተ «አንቺስ? ስራሽን ለምን አልጀመርሽም?» አለኝ::

ነገር ቁስቆሳው ልቤን አስጋለበው:: ለመጋፈጥ የቆረጥኩ ቢሆንም ልቤ እውነት እንደሌለው ሌባ ሩጫው ፍርሃት ለቀቀብኝ::

«ጥናቴ...»

«ጥናትሽ ገደል ይግባ!» ብሎ ቆመ

የእውነተኞች፣ የሐቀኞች ድንበር ጠፋኝ:: ምናልባትም «እናትሽ አንቺን ስትወልድልኝ ደስ አለኝ:: ሴት ነበር የምፈልገው» ያለው እንዲህ በጭቦ ተነስቶ እውነትን ለመግሰስ ሴት ስለምትመች ይሆናል:: ሲቆም በመካከላችን የነበረው የፊት ለፊት እርቀት ወደላይና ወደታች ሆነ:: ቀና ብዬ አየሁት፣ አዘቅዝቆ አየኝ::

«ለምን አትተይውም?» አለኝ በተነሳበት ግለት መቀጠል የፈለገ አይመስልም «ይሄ ጥናት ምናምን የምትይውን እከከ መፎክት ለምን አትተይም?» የመጀመሪያ

ኃይለቃሉ ነበር፡፡ ይህንን ከመሰሉ ቃላት ስሽሽና ሳፈገፍግ ኖሬያለሁ፡፡ እንደ ዕጣ ፈንታ እንዲህ የማይቀሩ መሆናቸውን ባውቅ...

«ለምንድነው የምትወው? አትነግረኝም? አልኩት

«መተውማ ያለብሽ እኔ አባትሽ ስለሆንኩና ብዙ ስለማውቅ...» ሀብሉ በመስኮቱ የሚገባውን ብርሃን ተቀብላ አንጸ ፈለቀች

«የምታውቀውን አሳውቀኝ፡፡ ህፃን አይደለሁም፡፡ ብዙ አውቃለሁ፡፡» ቦቼ ጭንቅ ብሎት የአሮጌ ሳንቃ ድምፅ አሰምቶ ወደጠረጴዛው ስር ገባ፡፡

«ተይ ማለቴ በራሱ ዋጋ የለውም ማለት ነው?»

«አይ አም ኖት ኤ ኪድ ኤኒሞር»

«አይ አም ኖት ዩር ፋዘር እኒ ሞር ብልሽስ?» ቀና ብዬ አየሁት፡፡ አይኔን ፈርቷል፡፡ አልሞት ባይ ተጋዳይ መሰለኝ፡፡

«አባትነትህን እስከትቀበል ቤትህን ለቅቄ እሄዳለሁ»

«የት?» ጦፈ «እዚያው እጎሬሽ? ሽረሪት ቅፍቅፍ እዚያ ግድግዳ ስንጥቅ ውስጥ ለመኖር? አይሆንም! ገድዬሽ...»

አሁንም ቀና ብዬ አየሁት፡፡ እንደ ቦቼ ፀጉራም የሆነ እጁን በአየር ላይ ወደኔ ተኩሶት ነበር፡፡ ከመዳፉ ኃይል የተነሳ እንደ እርጥብ ጭቃ በየጣቶቹ መካከል ፍጥርቅ ስል ታየኝ፡፡ ምንም ሳያደርግ እጁን ወደ ደረቱ ልኮ ያንን ሀብሉን በጥሶ ወረወረው፡፡ ከበር ጋር ተጋጭቶ ሿ! የሚል ድምጽ ተሰማ፡፡ ምንም እንዳልተፈጠረ ቀዝቀዝ እንዳልኩ አየዋለሁ፡፡

«የምታደርጊውን ሁሉ አውቃለሁ፡፡ በንጽህናና በተስፋ አሳድጌሽ እንደ አባብ ልጅ ወደ ጉድፍና ስንፍና ትሳቢያለሽ» ወደ መቀመጫው አመራ፡፡

«ምናልባት ፎቶዋን'ኳ እንዳላይ የከለከልከኝ እናቴ...»

እላስጨረሰኝም ጠረጴዛ ላይ ከተበተኑት ሞባይሎች ውስጥ አንዱን አንስቶ ወረወረ፡፡ ግድግዳ ላይ ብትንትን አለ፡፡ ከብትንትኑ ውስጥ አንዷ ስንጥር ከዓይኔ ዝቅ ብላ ተሰካች፡፡ ደሜ ኮለል ሲል ዓይኔ የጠፋ መሰሎኝ ነበር፡፡ ቦቼ የተመታ ያህል ከፍ አድርጎ አለቀሰ፡፡

* * *





በገና እንደሆንኩ ይሰማኛል፣ ንጉስ ዳዊት እንኳ ለመደርደር ያዳገተው ዘለሰኛ ውስጤ አለ፡፡ የብቸኝነት ቁራኛ፣ የሰው ቀበኛ፡፡ የማለቅስበት አድባር የሌለኝ፡፡ የምጨብጠው ሁሉ የሚያጠራጥረኝ፡፡ ዘሬን መዝሪያ ኩርማን ያጣሁ፣ ተንገዋላይ-ስሬን እሰድበት አጥቼ ቅጠሎቼ የተጠሙ፣ መሄድ አምሮኝ-መሄጃ ያጣሁ፡፡ አካባቢውን አየሁ፡፡ የሚወጣ የሚወርደው ቅዠት ለማድመቅ ህላዊ የነሳ የህልም ገፀ-ባህርይ መሰለኝ፡፡

«አራት ኪሎ ስድስት ኪሎ» ይላል ወያላው፡፡

«ዓለም ሁሉ ወደ አራት ኪሎና ስድስት ኪሎ ያመራል፡፡» ስል አሰብኩና ወደ ታክሲው ውስጥ ገባሁ፡፡ ሦፌ የሻማ ቱታ አድርጌ ኮፍያ ደፍቻለሁ፡፡ ቁስሌ ያን ያህል የሚጋነን ባይሆንም ልቤ ላይ የተወው ጠባሳ ለሞት የሚያደርስ ሆኖ ተሰማኝ፡፡ ዛሬ አንድ ኮርስ ነበረኝ አንትሮፖሴንትሪዝም ይሰኛል፡፡ የሰውን አምክሎአዊነት የሚተነትን ነው፡፡ ተውኩት፡፡ በባይተዋርነት እየታመምኩ የሌሎችን ማህበራዊ ሀብት ማስላት ውስጤ አልቀበለው አለኝ፡፡

መውረድ የፈለኩት አራት ኪሎ ነበር፡፡ ሳትኩት፣ ስድስት ኪሎ ደረስኩ፡፡ ዶክተር ማርቆስ ብቻ እንደ የካቲት አስራ ሁለት መታሰቢያ ሀውልት መሀል አደባባይ ላይ ተተክለው የሚታዩበት ቦታ፡፡ ሌላ ማን አለ? ሸዊት? እሷ የካምፓስ ውስጥ ቦቼ ናት፡፡

«ሚስ እርጥባን» አሉኝ የቾክ ብናኝ ከእጃቸው ላይ ለማራገፍ እያጨበጨቡ፡፡ ሳያቸው ቆሌ እንዳረፈበት ዋርካ ብሰግድላቸው፣ ውስጤ ያለውን ሁሉ ባነባላቸው ወደድኩ፡፡ እሳቸው ግን ጥናት ጥናት-ጥናት ብለው ሊሞቱ ነው፡፡ ቢሯአቸው ገባን፡፡ ውጭ የተመለከትኩት ወዳጃዊ ስሜታቸው ቢሯቸው ውስጥ ሲሆን የጠየመ መሰለኝ፡፡ አኮረፉ?

«ጥናትሽ ጥሩ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አልጠራጠርም፡፡ ያላጣደፍኩሽ አንቺ ያለሽ ስጋት እኔን ስላላሳመነኝ ነው፡፡ አባትሽ ምን ያህል መንደርተኞቹን ለማዘዋወር ቢጣደፍ'ኳ ተፈጥሯዊ ገደቦች እንዲቆይ ያስገድዱታል፡፡ ምክንያቱም መንደርተኞቹን ለማዛወር ቢያንስ ቤቶቹ ተገንብተው ማለቅ አለባቸው እና ነው...»

ሰው ሲያወራ እንዴት አድማጩን አያጤንም? ስል አሰብኩ:: እንደወትሮው ማስታወሻ ለመያዝ አለመጣሬን'ኳ ልብ አላሉም:: ገረመኝ «ይልቅስ» አሉ «ይልቅስ አንድ ነገር እየከነከነኝ ነው:: ለጥናቱ ላይጠቅም ይችላል:: ግን ከአስፈፃሚ ግለሰቦች አንፃር ካየሻቸው ዓለማቀፋዊ ጉዳዮች'ኳ ግለሰባዊ ግብ አያጡም:: እስኪ አባትሽን...»

ታከተኝ፣ እያወሩ ቢሮውን ከፍቼ ወጣሁ:: የምዕመኑን ስሜት ካለጤነ እንኳን ሰው ፈጣሪ እራሱ አያስፈልግም ስል አሰብኩ:: ሁለት የተሰፋ እርግቦቼን በተስፋ መቁረጥ ወንጭፍ እንደጣልኩ ገባኝ:: ወደ መጨረሻው አመራሁ:: ሸዊት ስታየኝ እንደ ቦቹ ቱስ ቱስ እያለች ከወደ ላይብረሪ መጣች:: ቆም ብዬ አፈጠጥኩባት:: ሰላም'ኳ ሳትለኝ ተመለሰች:: ወደ ሙሉጌታ...

ሙሉጌታ እኔን መስሎ ጠበቀኝ:: ሰሞኑን የገዛሁለትን ሻማ ቱታ ለብሷል:: ቁስሉ ላይ ለማሳረፍ የሚረዳ የጨርቅ ኮፍያ ደፍቷል:: በአለባበሳችን መመሳሰል የሰዎችን ትኩረት ሳንስብ አልቀረንም:: እንደ መንገድ ዳር ዝንብ ብዙ ዓይኖች አረፉብን «እ..ሽ» ብላቸው በወደድኩ:: እነዚህ ዓይኖች መካከል አባቴን በማየት የሚያገለግሉ እንዳሉ ሳስታውስ እጄን ከንዱ መካከል ወሸቅሁ:: እየተራመድን እራሱን እራሴ ላይ አንተራስ:: ኮምሬድ እንኳ ቅዝዝ ብሎ እየተመለከተን እንደነበር ልብ አልኩ::

የተለመደው የቀበሌ መዝናኛ ነበር የወሰደኝ:: የደበዘዘ የካኪ ሸርጥ የለበሱ አስተናጋጆች ይራወጣሉ፤ ሁለታችንም ለስላሳ አዘዝን:: ሙሉጌታ ምንም ሳይናገር እንደማሳጅ ሰውነት በሚያዝናና እይታ ያከመኛል:: ሌላው ቀርቶ ስለቁስሌ እንኳ አልጠየቀኝም::

ተስፋ መቁረጥ እንደብርድ ያፈዘዘው አካሌ ነፍስ መዝራት ጀመረ:: ቆዳዬ ውጫዊ ስሜቶችን ወደ ውስጥ በማስተላለፍ ስራ ተጠመደ:: ልቤ እንደ ልክፍታም ህፃን ሞታ ተነሳች:: ፍቅሬ አንሰራራ:: ጠይም ብርሃን ከበበኝ::

ሙሉጌታ ሁሉንም ትቶ ስለአስደናቂ ነገሮች ያወራልኝ ጀመር::

መዝናኛው ውስጥ «ሐኪሜ ነሽ» የሚል ዘፈን ተከፍቷል:: እዚህ ቤት ቴፕ ስለመኖሩም ከዚህ ቀደም ልብ አላልኩም ነበር:: ሙሉጌታ ሲንፏቀቅ ስለተደበደበበት





ቀን ማውራት ጀመረ:: ይሄንንም ቢሆን ለኔ አስገራሚና አዝናኝ አድርጎ ነበር ያቀረበልኝ:: ስለመከራ ማውራት እንዴት ያዝናናል?

«አንዴ ሲመቱሽ ድው! የሚል ድምጽ ነው ቀድሞ የሚሰማሽ:: ከዚያ ብልጭ የሚል ብርሃን ይከተላል:: አየሽ ዱላ ከብርሃን ድምጽ ይቀድማል:: ይሄን ተረድቻለሁ:: ከመብረቅ እንደተገኘው ሳይንስ ቢሆን ብልጭታ መቅደም ነበረበት::»

ሳቅሁ:- ቀጠለ

«ከዚያ ሁለተኛ ሲመቱሽ እራስሽን ትስቺያለሽ:: ቀጥሎ ያሉት እልፍ ዱላዎች ለመቺዎቹ መጠጥ የተሞላ እቅማዳ እያገላበጡ እንደመነረት ያለ አድካሚ ይመስለኛል:: አይሰማሽም ዕዳው ሩህሽን ስታውቂ ይወራረዳል:: መመታቴ ትዝ ያላለኝ ቦታ ሁሉ ያመኛል:: አንዳንዴ አካላቴ መቼም አያውቀው እያለ ሳይመታ የሚያመኝ ጭቦኛ ይመስለኛል::»

ምንድነው ይ'ኼ ሰው? ስል አሰብኩ:: ከግራ አይኑ ስር ያለው እንቡጥ ቁስል ፈንድቶ ወደ መከሰሙ አድልቷል:: ብሩህ አፍንጫው ቀስ በቀስ እንደሚጎላ የድንጋይ ቅርጽ ወደቦታው በመመለስ ላይ ነው:: «እንዲህ ላደረጉት ሰዎች ይቅርታ አድርጓል ማለት ነው?» ስል አሰብኩ:: በመለኮታዊ ኃይሉ ስቃዩን ተቋቁሞ «የሚያደርጉትን አያውቁምና...» ሲል ለጠላቶቹ ምህረት የተለማመነው ዝቅ ብሎ ሲውለበለብ ታየኝ::

«ፍቅር እሲያዝከኝ» አልኩት ከርኑ ውስጥ እጄን አጠላልፌ ወደ ጀሮው በመጠጋት:: ስለፍቅሬ ስነግረው የመጀመሪያዬ ነበር::

«አይዞሽ ፍቅር እሲዘሽ ነው የያዘሽ» አለኝና ጠይም ብርሃኑን ቦግ አድርጎ «አጥፍቶ እንደመጥፋት:: የፍቅር አሸባሪ! ይሄም ቢሆን ወንጀል ነው::»

ስሜቴን ማዳመጥ ቀጠልኩ:: ይሄን ነበር የምፈልገው:: በሰው የተከበብኩ፣ ባይተዋርነቴ እየተነቃቀለ የተጣለ መሰለኝ::

«ለአባቴ ይቅርታ አደረክለት?»

«አዎ፣» አለኝ

«ለምን እኔ ይቅርታ አላደረኩለትም?» አልኩት

ዝም አለኝ

«ለኔ አልወረወረም:: ለንዴቱ ግድግዳ ነው የመታው:: ደሞ መድማቴን ሲያይ ደንግጧል:: አንተንም ቢያይህ የሚደነግጥ ይመስለኛል::»

«እርግጥ ይፀፀታል፣ ግን'ኮ አላጠፋም»

ቀና ብዬ አየሁት፣ በሁለት ሻማ ልብሶቻችን አልፎ ሙቀቱ ተሰምቶኝ ኖሮ አካሌን ካካሉ ስነጥል በረደኝ:: እርግጠኛ ነኝ እሱንም በርዶታል::

«አንድ አንቺ የማታውቂውን ልንገርሽ::» አለና በእጁ ወደ እርሱ ሳብ አድርጎ አስጠጋኝ:: በእርግጥም አካሌ ሲለየው በርዶታል ማለት ነው:: «ድህነት ለብዙ ሰው የሚታየው ምንም የማይፈቅድ ንቁግ ሆኖ ነው:: የሕይወት እጅ እግር የሚታሰርበት ሰንሰለት ይመስላቸዋልም:: መቅመስ፣ ማየት፣ መዳሰስና ማሽተት ላይ ማዕቀብ የሚጥል አድርገው ደምድመዋል:: ግን አይደለም:: እንደውም ባለፀጋነት ላይ ያለው ውስንነት ይገዝፋል:: ድህነት ነፃነት ነው:: በሀብት ጡብ የተገነባ የሕይወት ዘብጥያ ውስጥ በቁም እስረኝነት የሚንጠራወዙት ባለፀጋዎች ናቸው፤ በተፈጥሮ ከተፈቀደለት እጅ እግሩ በተጨማሪ ሌላ ትርፍ አካል ያበቀለ ነው ባለሀብት:: ጥጃዋ እንደታሰረባት ላም ወዳሻው የማይሄድ ግዙተኛ ባለፀጋ ነው::

«ድህነት ከተቀበልሽው ህብረ ዝማሬ ነው:: ድህነት የሕይወት ምንኩስና ነው:: መንጦዝጦዝ የሌለበት ወዳሻን የሙበረር ፈቃድ ነው:: ኑሮ ገዳም በሆነበት ቦታ ነፍስን ከማበልፀግ ውጭ ምን ትፈልጊያለሽ? በቀን፣ እፍኝ የተራሰ ባቄላ፣ በቃ! ከዚህ ዓለም ሀበት የምንቋምጥላት ይቺው ናት:: ከዘመሩ ወፎች ጋር ዘምረን፣ ካሸበሸቡ ዛፎች ጋር እስከስታ ወርደን፣ ለሚያጨበጭቡ ወንዞች ከበሮ ደልቀን፣ ለሚታደሙልን ከዋክብት አክብሮት ሰጥተን የህይወት ጠበልተኛ መሆን::

«የሰው ልጅ ሁሉንም ነገር ሲያጣ ለሁሉም ነገር መጨነቅ ትቶ የደስታ ከህነት ይቀበልና ከሕይወት ለቀረፀው ታቦት እርገት ይወርዳል:: ፅናፅሉን፣ መቋሚያውን፣ ማጥንቱን፣ ጥምጣሙን፣ እጣኑን፣ ዘቢቡን... ተፈጥሮ ታቀርባለች:: ባይኖርም ግድ የላት:: የኛ አምላክ እዚህ ወረብ ላይ የሚታደመው ነው:: አበክሮ «ገንዘብ የሀጢያት ሁሉ ሥር ነው» ይለናል:: ከባለፀጎቹ አምላክ ይለያል:: ባለፀጎቹን ወደ ኤደን እፀዱ ከሚያስገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብትሾልክ ይቀላል ይላል::





«የባለፀጎች አምላክ ከተፈጥሮ ጋር ፀብ ነው:: ስለዚህም እኛ ድሆችን ይጠላል:: ምቀኛቸውም ሲል ያዘዛል:: «ላለው ይጨመርለታል፣ ከሌለው ያለውም ይወሰድበታል» ይላል:: ዘሮቻችን እንዲበሉን የተፈረደብን እኛ ድሆች ብቻ ነን:: ሽኮና ድፍን፣ የማያመስኳ፣ የምድር ተንፏቃቂን እንጂ እኛ ድሆችን በምዕመኖቹ ከመበላት አልታደገንም:: ስለዚህ ከገሀነም የከፋ የከበርቴ አፎች ሊውጡን ተከፍተዋል:: ከመዋጥ የማይሚሉ፣ ከማስገባት የማይሰንፉ ሆዶቻቸው ያጉረመርማሉ:: ከዛፎቻችን፣ ከወፎቻችንና ከወንዞቻችን ጋር ወደ መጥፊያዎቻችን እንሰደዳለን:: ከከተማ ወጣ ብለን እናልቃለን::»

«ላለመነቀል ለምን አታምፁም?» ስል አሰብኩ:: ያሰብኩ መሰለኝ እንጂ ለካ ተናገርኩ::

«የራሳችንን ከበርቴዎች ካልተቀበልን ጨርሶ ዘር ማንዘራችንን የሚያወድም ባዕስ ከበርቴ ይመጣብናል:: ያው ቢሆንም አንዴ ከሚጎርሰን እንደጨው እየላሰ የሚያሟሟን በጉርብትና የያዝነው የኛው ጭራቅ ይሻለናል:: አሁን የሚያስፈልገን ወደባርነታችን መናኸሪያ ወደ «ግብጽ» በሰላም የሚመልሰን ሐሰተኛ ሙሴ ነው»

ስሜቴን ወደ ሌላ አቅጣጫ ይዞት ሄደ:: ስለምፅአት ቀን እንደሚሰብክ ባህታዊ ዓለምን የመከራ ቋት አደረጋት:: የለም አለም እሱ እንደሚለው ለድሆች ወደ እሳት የመነዳት ብቸኛ አማራጭ አይደለችም::

ይሄን ሁሉ በሥራ ለመለወጥ ለምን አትታገሉም? ድህነት ከስንፍና ጋር መቆራኘቱ ነው አሁን ለምትለው የሚያጋልጠው:: ቀኑን ሙሉ መተኛት...» አቋረጠኝ

«ድህነት ምንጩ ቀኑን ሙሉ መተኛት አይደለም:: የማያስፈልግ ሰው መሆን ነው:: ርካሽ ነገር ላይ ጉልበትንና ጊዜን ለማባከን መገደድ ነው:: የትምህርት፣ የዕውቀት፣ የሀብት መነሻ ሳይኖርሽ የጋማ ከብቶች የሚሰማሩበት የሥራ መስክ ላይ ከእነሱ ጋር የመጋፋት ውጤት ነው:: በምድረ በዳ በመጮህ ሰሚ አይገኝም:: የምድረ በዳ ሰባኪ መሆን ነው ድህነት::»

ትንሽ ሲተካከዝ ቆይቶ «ለምሳሌ እኔን እይኝ» አለኝ:: «በትንሽ ብር ተቀጥሬ ገጠር ሄድኩ:: ማስተማር ጥሩ ነበር:: ነገር ግን እዚያ ሆኜ እንኳን እያቴን ልረዳ ለራሴም አይበቃኝ:: በዚህ ላይ ጠኧያቴ ያለኋቸው እኔው ነኝ:: ስለዚህ አያቴ በሁለት

ተጎዱ:: ሳይረዱም፣ እኔንም አጥተው:: ወዲያውም አራት ኪሎ ናፍቃኝ ሥራውን ጥዬ መጣሁ:: ይኸው ሁለት አመቴ:: ሥራ የለም:: ከሰባት በላይ ትምህርት ቤቶች ማመልከቻዬ ላይ ተኙበት::»

ቀና ብሎ አየኝ:: የተጨነቀ መሰለኝ «ሌላው ቀርቶ ድንጋይ ለመሸከም ሞከርኩ:: እጆቼን እያዩ ይመልሱኛል:: በቅናሽ እንኳ እኔን ለመቅጠር ፈቃደኞች አይደሉም:: እንዲህ አንዳንዴ እህያ የመተካት ሥራም ይነፈግሻል:: ማንበብ ማንበብ በቃ::»

የአንተ ስራ መሆን ያለበት እንደ ኢየሱስ እየዞሩ ማስተማር ነው ስል አሰብኩ:: እንባዬ ወረደ? እኔ እንጃ? ለምን ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይጨክናል? ያውም ክፋት በሌለው ሰው ላይ?

«የሚገርም አስተሳሰብ እዚህ ዘመን ላይ በቅሏል:: ድህነትሽን ይዘሽ በተቀመጥሽ «እበላሻለሁ፣ ህግ ይፈቅድልኛል፣ ተፈጥሮ ችሎት ላይ ረትቼሻለሁ» የሚሉ የዳርዊን አቀንቃኞች ጎጆሽን ያንኳኳሉ:: በእነሱ አስተሳሰብ ተሸናፊነትን መቀበል ለመኖር አለመፍቀድ ነው:: እንደ ሼክሽር ገፀ-ባህርይ እንደሻይሎክ በተፈጥሮ የመበላላት ህግ ካራውን እየሳለ ከሰውነትሽ ላይ ሙዳ ስጋ ይገባኛል የሚል ከሳሽ ከበርቴ በእያንዳንዱ ደሃ ላይ ተመድቧል::

እንደ እግዚአብሔር መምጪያ ጊዜው ያልተቆረጠ ረጅም ፀጥታ ሆነ::

ከፀጥታ ጋር ቆዳን የሚቆጠቁጥ ትኪታ...

«የእኔም ትኪታ ይቆጠቁጠው ይሆን?» ስል አሰብኩ:: አልመሰለኝም ታዲያ የሱ ብቻ ለምን? ግንኙነታችን የረቂና የተረቂ አይነት እየሆነ የመጣ መሰለኝ:: ካላበልኩ በስተቀር ይህ ደግሞ ገሀድ ነው:: ከእኔ እየተቀነሰ ለእሱ ይጨመር ይመስል ሚዛናችን እያጋደለ መጣ::

«ጥሩ ነው አለኝ ድንገት ምኑን እንደሆን አልገባኝም:: ፋታ ወስዶ ቀጠለ::

«ጥሩ ነው፣ ሰብአዊነትሽ የሚወደድ ነው:: ግን ደግሞ አንዳንዴ ዝም ብለሽ ማየት ያለብሽ ትንቅንቅ እንዳለ ተረጂ:: ተፈጥሯዊ ትንቅንቅ:: ሚዳቋ ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለነብርም ጭምር ነው የተፈጠረችው:: ይሄንን ተፈጥሮ ደንግጎታል:: በእነሱ መካከል ለገላጋይነት መግባት ከንቱ መታከት ነው:: አንቺም በኛ መካከል ገብተሽ





ከንቱ አትታከች:: ጅብ አህያን እንዳይበላ የመከላከል ሰማዕትነትሽን አልወደድኩትም::» አለኝ::

# ሁለት

ሁለመናው በሚያንፀባርቅበት ጊዜ ነበር አራት ኪሎ የደረስኩት፡፡ የፓርላማ ሰዓት የደደረ ደውል ድምፁን ያሰማል፡፡ ቀና ብዬ አየሁት፣ ሙሉ ጨረቃ የመሰለ ፊቱ ላይ የደመና ሰበዝ በመሰሉ መጠቆሚያዎቹ ስምንት ሰዓት ላይ ያሳያል፡፡ ባሰኘኝ ሰዓት ወደ አራት ኪሎ የመምጣት መብት ለራሴ መስጠቴ አስገርሞኝ ፈገግ አልኩ፡፡

አርበኞች ሀንፃ አካባቢ እንደደረስኩ ብርሃን የሚታለብ ነጭ የሻማ ቱታ በጨረፍታ አይቼ ደነገጥኩ፡፡ ምን ያስደነግጠኛል? ላገኘሁ የመጣሁት ሙሉጌታን አይደል? በቅጡም ሳልዞር ሰውየው እሱ አለመሆኑን አወቅሁ፡፡ ልብሱ ግን እኔ የገዛሁት እራሱ ነበር፡፡ ጎብደድ ብሎ ወደ ስላሴ ቤተክርስቲያን አቅጣጫ መንገድ የሚያቋርጠው ኮምሬድ መሆኑን ወዲያው ለየሁት፡፡ በድን እግሩን እየጎተተ ሙብራት የለቀቃቸውን መኪናዎች ይሸሻል፡፡ ቱታው ባለላስቲክ ወገብ ቢኖረውም ልማድ ሆኖበት በቀኝ እጁ ጨምድዶ እንደያዘው ነበር፡፡ ከትራፊክ ሙብራቱ በላይ አልፎ አይቼው ስለማላውቅ ከአለባበሱ ጋር እሱ መሆኑን ተጠራጠርኩ፡፡ አስፓልቱን ተሻግሮ እንደጨረሰ ደፋ ደፋ ማለቱን ትቶ ሽ-ጠ-ጥ-ን በሚል አረማመዱ ወደ ቤተክርስቲያኑ አመራ፡፡

ብስጭት ውልብ አለብኝ፡፡ ልብሱ እኔ የገዛሁት መሆኑን አልተጠራጠርኩም፡፡ «ለምን ሰጠው?» በዚህ መናደድ ደካማነት መሆኑን አስታውሼ ራሴን እስክገስጥ ድረስ ተበሳጨሁ፡፡ ወዲያው ሙሉጌታን ባገኘው ምን እንደምለው አላወኩም፡፡ ቢያንስ በየሜዳ ለሚንከባለል ሰው ነጭ ልብስ መስጠት ምክንያቱ የማባከን ፍላጎት ብቻ መሆን አለበት ስል አሰብኩ፡፡

ሙሉጌታ ኮሌታውን ቀና አድርጎ፣ የድሮውን ሆኖ መጣ፡፡ ከንዴቴ ጨርሼ ስላላገገምኩ ሲነካኝ መጥፎ ስሜት ወረረኝ፡፡ ልብሱን የሰጠበትን ምክንያት ለማወቅ ፈለግሁ፡፡ ከዚህ በፊት ኦቴሎ ዴዝዴሞናን ስለአንዲት መሐረብ መግደሉ አይዋጥልኝም ነበር፡፡ አሁን የገባኝ መሰለኝ፡፡

«ኮምሬድ ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄድ አየሁት» አልኩት፡፡ ዞር ብሎ በትከሻው ንፅፅርሽ አየኝና «እ» ብሎ ዝም አለኝ፡፡ የኦቴሎ መንፈስ - የዴዝዴሞና ጦስ...





«እ» አለኝ ደገመና፡፡

አምሮበታል የሚቆሰቁሰኝ ነገር አለ፡፡ ላለመቆስቆስ ብፈልግም፡፡

«እ» አለ ወደ ቀበሌው መዝናኛ ሊመራኝ እየሞከረ፡፡ «ለምን እንደሆን እንጃ በእንዲህ አይነት ጊዜ ቤተክርስቲያን ያዘወትራል፡፡» ላለመሄድ ስለተቋቋምኩት ቆም አለ ወሬውን ሳያቋርጥ «እምነት ለከፋ ቀን የተማሰ መሸሸጊያ ጉድጓድ ነው፡፡ ሥጋችን ምን ቢሸፍት ነፍሳችን ከጉድጓዱ አካባቢ አትጠፋም፡፡»

ልብሱ ለእኔ ምን ነበር? ጨርቅ ሳይሆን አከብሮት? ፍቅር? ፀጋ? እንዲህ የተረጎምኩት እማይሆን ሰው እጅ ገብቶ ሳየው ይሆን?... ሙሉጌታ ላይ ሳላፈጥበት አልቀረሁም፡፡ ተገጣጥሞ ይሁን ወይም በመንፈስ እንባቢነቱ ተመርቶ ሳይገባኝ መልስ ሰጠኝ፡፡

«አንዳንድ ጊዜ ኮምሬድ ድንገት ይባንናል፡፡ ከእብደት ይነቃል ማለት ይከብዳል፤ እብድ አይደለም ግን በቃ! አካባቢውን ያገናዝባል፡፡ እና ያኔ አዳም የእግዚአብሔርን ፀጋ ሲገፈፍ እንደሆነው በሁኔታው ከፋኛ ያፍራል፡፡ ቀኑን ሙሉ ይተኛል የቀረበውን ሰው የሚጠይቀው መታጠቢያ ስፍራና ልብስ ነው፡፡ እኔን ጠየቀኝ...»

«እናም የእኔን ክብር፣ የእኔን ፍቅር አለበስከው?» ለማለት ዳዳኝ፡፡ በዚህ መካከል ደካማነቴ ውልብ አለብኝ፡፡ ትከ ብዬ አየሁት፡፡ ቁስሉ ምጥጥ ወደማለቱ እያዘነበለ ነው፡፡ አፍንጫው ግን እንደደነደነ ጎላ ብሎ ተኮፍሷል፡፡

አቅጣጫ እየቀየረ ወደ ላይ መራኝ «እንደውም እናግኘው» አለኝ፡፡

አልተቃወምኩትም፡፡ ኮምሬድን እንደዚያ እንደለበሰ ዳግም ባላየው ተመኝቻለሁ፡፡ ግን ተከተልኩት፡፡ የቤተክርስቲያኑ መግቢያ ግራና ቀኝ ግንቦች የፓርላማና የኢሕአዴግ ጽሕፈት ቤት አጥሮች ወደ ደረት ለማቀፍ የተዘጋጁ ሁለት እጆች ይመስላሉ፡፡ አስፓልቱ ከመጽዳቱ ጭር የማለቱ፣ የቤተክርስቲያኑ አፀድ አካባቢ ኮምሬድ አንድ እግሩን እንደዘረጋ ሌላኛው እግሩ ጉልበት ላይ ተደፍቶ ተቀምጧል፡፡ አዘንኩለት መሰል...

...እጠገቡ ስንደርስ አንዳች ነገር ከብዶት ቀና አለ፡፡ ተዘቅዝቆ ስለቆየ ፊቱ በደምስር ደፍርሶ ነበር፡፡ የግንባሩ ቆዳ ዕድፍ ለማስለቀቅ በተደረገ ትንቅንቅ ተፈግፍጎ

አኮፍፏል:: ብዙም ሳይቆይ የደምስር ረብሻው እየተረጋጋ መደመም ረበበበት:: ከዚህ ቀደም የማውቀው ሰው አልመሰለኝም:: እብደት እንደደመና ፊት ላይ የሚያንዣብብ ነገር ነው ስል አሰብኩ:: ያ-ዳመና ሲገፍ የጤናማነት ፀሐይ ትወጣለች::

ሙሉጌታ ምንም ሳይናገር አጠገቡ ተቀምጦ እኔን እንድቀመጥ ጋበዘኝ የመንደሩ ዳር ኮሪደር ላይ ተደረደርን:: አካባቢው ጭር እንዳለ ነው:: የሚጮኸው ከፀሐይ ጋር የሚተናነቀው ቁታው ብቻ ነው::

«ማን ናት?» አለ ኮምሬድ በለሆሳስ:: ንግግሩ ውስጥም የወትሮው ያለማገናዘብና ግዴለሽነት አይነበብም:: ጤናማ ነው:: ስላሰብኩት ይሆን?

«ጓደኛዬ ናት:: ያንተም ጓደኛ ናት» አለው

ጓደኛዬ ስላለኝ ያሳነሰኝ መሰለኝ:: ወደ ብስጭት ላመራ ዳዳኝ:: ግን ምን መሆኔ ነው?

«ያንተ ጓደኛ ከሆነች እርግጠኛ ነኝ የእኔም ነች» አለ:: አዲስ ነጠላ ጫማ ማድረጉን አሁን ልብ አልኩ የበድን ጣቶች ተሸቀዳድሜ አየሁ:: የግንድ ጉማጅ ጠብቄ ነበር:: የሚያማምሩ ጣቶች ግን መንቀሳቀስ እንዳቃታቸው ያስታውቃል:: ጥቂት ዝም እንደተባባልን ኮምሬድ እኔን እያየ ማውራት ጀመረ::

«ለምን እንደምወደው ታውቂያለሽ?» አለኝ:: ዓይኖቹ ግን እኔ ሙሉጌታን ለምን እንደምወደው የሚጠይቁ አይነት ናቸው:: ከኔ መልስ ሳይጠብቅ መለሰልኝ:: እውቀቴን ወደ ገንዘብ ስለሚለውጥልኝ የሚል ንግግር ጠበቅሁ:: ግን የሰማሁት ይሄን ይመስል ነበር::

«ብዙ ጊዜ እብደቴ እንዴት የማላስታውሰው ቦታና ሁኔታ ላይ ጥሎኝ ይሄዳል:: ያኔ ማንኛውም ጤነኛ ሰው የተነጠለው ወዳጁ መልሶ ሲያገኘው የሚያሳየውን ፊት የማገኘው እሱ ጋ ብቻ ነው:: ሌላው ሲፈራኝ፣ ሲጠረጥረኝ፣ ሲቀልድብኝ... እሱ ግን ግሩም እስታማሚዬ እንደነበር በሚገልፅ ሁኔታ አገኘዋለሁ::

ራሴን እንድጠይቅ አደረገኝ... ኮምሬድን አሁን እንዴት ነበር የቀረብኩት? ህመም ሆኜበት ነበር ማለት ነው? ወደ ሙሉጌታ አየሁ:: ስለእሱ መጨዋወታችን የሸገገው ይመስላል:: እኔ ደግሞ የጨዋታ ጅማሬው ጥሞኛል:: እኔ ጋ የጠፋ ነገር ነው





ኮምሬድ ጋ ያገኘሁት ለምን መውደድ እንደተቻለ ማወቅ ትልቅ መታደል ነው:: «በዚህ ብቻ ነው?» ጠየኩት:: ሙሉጌታ ቀና ብሎ ደስ ባለመሰኘት አየኝ::

ኮምሬድ የበሽተኛ እግሩን ጣቶች እያየ በግራ እጁ ጉንጩን ዳበሰ:: እንደ ሽቦ የጠነከሩና የወፈሩ ፀጉሮች ችፍ ያሉበት ሲዳስሳቸው እየተፈነጠሩ ቀና ይላሉ በቦዘዝ ባለ ድምፅ ማውራት ጀመረ::

«ዋናው ይሄ አይደለም፣ ዋናው ተስፋ መሆኑ ነው:: ሁኔታው የኛን ዘመን ያስታውሰኛል:: የእውቀት ሽሚያ የነበረበትን:: ለወገን መቆርቆራችን ሁሉ እሱ ውስጥ አለ:: ዛሬ እኛ የከሸፍን ጥይቶች ነን:: ይሄ ህዝብ ግን የከሸፈ ጥይት ባለቤት ብቻ አይደለም:: ገና ያልተተኮሰ ጥይትም አለው:: እንደሱ ያለ:: እኛ ለምን እንደከሸፍን እሱ ያውቃል:: ስለዚህ በግብታዊነት አይተኮስም:: በግብታዊነት ካልተተኮሰ ደግሞ በከንቱ አይከሽፍም::» በሽተኛ እግሩን በግራ እግሩ አንስቶ መልሶ አስቀመጠውና ቀጠለ...

«አብዮት ምንጊዜም አይቀርም:: የአንድ ዘመን አብዮት ስለከሸፈ ጨቋኞች ለዘልአለም እንደጨቆኑ ይኖራሉ ማለት አይደለም:: አመፅ አቅጣጫ እየለወጠ ግድብ ይጥሳል:: ዛሬም ፍትሃዊነት ከፍፍልን የሚሹ የኢሰብአዊነትና የስግብግብነት ሰለባዎች አሉ:: ለዘመኑ ጭቆና መፍትሄዎች ዘመን የተፋን እኛና መንገዳችን አንሆን ይሆናል:: ግን እንደሱ ያሉ አሉ፣ ፍፁም ተስፋ ሊጣልባቸው የሚገቡ...»

ሙሉጌታ የማይቋቋመው ሙገሳ ሆኖበት የሚያወራው ሳያዘጋጅ አቋረጠው «እ-እ» ብሎ ዝም አለ:: ኮምሬድ ጉብቶታል:: የተቀመጥኩበት የአስፓልት ደፍ አቁነጠነጠኝ:: አንዲት ነጠላ የተከናነበች ሴት መጥታ የቤተክርስቲያኑን አጥር በር ተሳለመችና ሳትገባ እንደመንበርከክ ብላ መፀለይ ጀመረች:: ሙሉጌታ ሲያያት ቆይቶ ወደ ኮምሬድ በመዞር ጥያቄ ጣል አደረገ::

«እምነት የመጨቆኛ መሳሪያ ነው ስትል ሰምቼ ነበር ልበል?»

«አዎ፣ ማርክስ ስላለው ሶሻሊስቶች ሁሉ ይሉታል» አለ መታከት ድምፁ ውስጥ ነበር:: ጉንጩን የሚዳስስበት ግራ እጁን አነቃቅቶ ግንባሩን በመዳፉ ሞልቶ አዘቀዘቀ:: ይሄን ሲመለከት ሙሉጌታ በስጋት ጨዋታውን ገታ አደረገ:: «ቀጥል ቀጥል ስንጫወት ይሻለኛል» አለ ኮምሬድ።

«ወደ ቤተክርስቲያን የመጣኸው...»

«አማኝ ሆነህ ነው?» ጨረሰለት፡፡

«እ» የልብ ፈገግታ አሳየውና ብድግ ብሎ ከመካከል በመውጣት በስተግራ በኩል ተቀምጦ ኮምሬድን መካከል ከተተው፡፡ የሙሉጌታ ሁኔታ ሳይ የርዕስ ጉዳዩ መቀየር ሳያስደስተው አልቀረም፡፡

ኮምሬድ ጉንጩን እየቀደደ የመጣ የሚመስል ኩርንችት ጺሙን በመዳፉ እያስተኛና እያፈናጠረ በለበጣ ፈገግ አለ፡፡ «ሙቼም አብዮት፣ ማርክስ፣ ኤንግልስ... እያሉ ቤተክርስቲያን መገኘት ቀልድ ነው፣ ጥሩ ቀልድ፡፡ ወጣት ሳለን ታጥቀን የተነሳንበት የባህል አብዮት እምነትም ላይ የዘመተ ነበር፡፡ ያንን የሚያውቅ ዛሬ እዚህ ወድቄ ሲያየኝ በመረታት ይተረጉመው ይሆናል፡፡ እውነቱ ግን ይሄ አይደለም...፡፡»

«ታዲያ ምን?» ሙሉጌታ ጠየቀ፡፡

በግራ እጁ ጣት የቀኝ ጆሮውን ኮረኮረ፡፡ ቀኝ እጁ ለምንም ነገር የማይጠቀምበት መሆኑ ገረመኝ፡፡ «ነገረኝ ካላችሁኝ እንዲህ ነው፡፡ ይሄንን ጉዳይ በሚመለከት አንድ መጽሐፍ ጽፌ ነበር ወይም ተርጉሜያለሁ፡፡ እንጃ ብቻ ኤሊባቦር መምህር ሳለሁ ጨርሼው ወደዚህ አዲስ አበባ ይገፌው መምጣቴ ትዝ ይለኛል፡፡ የት እንዳለ አላውቅም፡፡ ልጠይቃቸው የምችላቸው ሁሉ አልቀዋል፡፡» ፊቱ ተዘቅዝቆ እንደተነሳ ሁሉ አሁንም በደምስሮች ተደበላለቀ፡፡ ሙሉጌታን አየሁት እሱም እንደኔ ደንግጦ ነበር፡፡ ኮምሬድ ቀጠለ...

«ብቻ፣ መጽሐፉ የሚያተኩረው በቤተክርስቲያን ታሪክ ላይ ነበር፡፡ እኔን እንደገረመኝ ሌላውንም ለማስገረም መሰለኝ የጻፍኩት፡፡ ቤተክርስቲያን የከሸፈች የአብዮት ተቋም ነች፡፡ ክርስቲያኖችም አመፃቸው የተቀለበሰባቸው የመጀመሪያዎቹ ሶሻሊስቶች ናቸው፡፡» ንግግሩ ያሳደረብንን ስሜት ለመሰለል ቀና ብሎ ሁለታችንንም ግራና ቀኝ እያፈራረቀ አየንና ቀጠለ፡፡

«ክርስትናን ከክርስቶስ በፊት የጠነሰሱት ኢሴንስ ይባሉ ነበር፡፡» አለና ቃሉን በእንግሊዘኛ ፊደል በታተነው፡፡ «ኢ.ኤስ.ኤስ.ኢ.ኤን.ኢ.ኤስ እነዚህ እስራኤላውያን አገራቸው በባዕድ ገዢ መተዳደሯ ብቻ ሳይሆን ህዝቡ በኃይማኖት መሪዎች የሚደርስበት መበዝበዝ የሚቆጫቸው የሁብረተሰብ ክፍሎች ነበሩ፡፡ ባርነትንም





አጥብቀው ከመቃወማቸውም በላይ ፍትሃዊ የሐብት ክፍፍል እንዲኖር አጥብቀው ይጠይቃሉ ይሄንን ሲያመች በአመፅ ሳያመች በአኗኗራቸው ይገልፁታል፡፡

«የሚኖሩት በጋርዮሽ እንደነበር አንዳንድ የሮማ ታሪክ ጸሐፊዎች አስፍረውታል፡፡ በጋራ ይበላሉ፣ በጋራ ይሰራሉ፣ በጋራ ያበስላሉ፣ በጋራ እንግዳ ይቀበላሉ፡፡ ጆሴፈስ የተባለ ሮማዊ እንደውም የግል ሐብትን ፈፅመው ከመካከላቸው አስወግደው ነበር ይለናል፡፡ ልብስ እንኳ የግል አይደለም ያገኘነው የሚለብሰው፡፡ በመካከላቸው ያሉ ሴቶች ሳይቀሩ በግል የተያዙ አልነበሩም፡፡ ፍፁም ኮሙኒዝም!

«ኢሴኖች ሐብትን የሀጢያት ሁሉ ምንጭ አድርገው ያስቡ ነበር፡፡ በረሃ አካባቢ ያሉት ደግሞ ኑሮዋቸው እጅግ የቀለለ እንዲሆን ወደ ምድረበዳ ይሰደዱ ነበር፡፡ በረሃ ውስጥ ልብስ አያሻህም፣ ቤት አያስፈልግህም ምግብም አያሳስብህም የበረሃ አንበጣ እየተመገብክ መኖር ትችላለህ የሚል እምነት ነበራቸው፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ የእነዚህ አባል ነበር፡፡ የበረሃ አንበጣ እየበላ በምድረበዳ የሚጮህ» አሁንም ግንባሩን በግራ እጁ መዳፍ ምልቶ አቀረቀረና ቆየ፡፡

እኔና ሙሉጌታ በኮምሬድ ላይ አሻግረን ተያየን፡፡ ሰጋ ተናበብን፡፡

«መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን መለመለው፡፡ ኢየሱስም ለአርባ ቀን ወደ ምድረበዳ በመዝለቅ ነፍሱን በአሲኖች ደንብ አበለፀገ፡፡ አስተምሮቱም ከአሲኖች የተገኘ ነው፡፡ ገንዘብ የሀጢያት ሁሉ ስር ነው ይለናል፡፡ ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ ሀብትን በዚህ መንገድ የገለፁ እነሱ ብቻ ነበሩ፡፡ «ሀብታም መንግሥተ ሰማያ ከሚገባ ግመል በመርፌ መሹለክ ይቀለዋል» ይላል፡፡ ብዙሃኑ እስራኤላዊ በድህነት ስር ስለነበር ነው፡፡ የተከማቸ ሀብታችሁን አከፋፍሉ የሚል አቋም የተያዘው በእነሱ ነው፡፡

«የኢየሱስ ዓላማ የድሆች ተስፋ መሆን ነው፡፡ ተጨቋኞችን በጨቋኞች ላይ ማስነሳት ነበር እንጂ ከንቱ የእግዚአብሔርን መንግሥት መስበክ አልነበረም፡፡ ጥምቀትን የተጠቀመበት ሥነ-ልቦናቸው ለራሳቸው ካላቸው ግምት ጋር የወደቀውን ድሆች የእግዚአብሐር ልጅ በማድረግ በሞራል እንዲያንሰራሩ ለማድረግ ነው፡፡ ጥምቀት ስልት ከሰዱቃውያንና ከፈሪሳውያኑ ብቻ ሳይሆን ከገዢዎቹ ከሮማውያን በላይ የመሆን ስሜትን ወድቀው በነበሩ ድሆች ላይ የፈጠረ የመጀመሪያው መሪ ኢየሱስ ነው፡፡ በወቅቱ «አባት» ይባሉ የነበሩ የቤተ-መቅደስ ሹማምንቶችንና የመሬት

ግብር ሰብሳቢዎች ከተከበሩበት የድሆች ልብ ውስጥ በአንዲት ቃል አስወጥቶ ጥሏቸዋል፡፡ «ከሰማይ አባታችሁ ውጪ ማንንም አባት አትበሉ!» ብሎ በማስተማር፡፡

«ኢየሱስ እስራኤላውያንን አንቅቶ አደራጅቷል፡፡ በመጨረሻ ለማስታጠቅ ሲዘጋጅ ነው የተያዘው፡፡ ሁለት ሰይፍ ብቻ ነበረው፡፡ ኋላ እንደተሰጠው አምላክነት ከሆነ ኢየሱስ ሰይፍ ምን ሊያደርግለት ያዘ? ገንዘብንም እያነወረ በኢቃቤ ነዋይ ይሁዳ በኩል ያሰባሰብ ነበር፡፡ ለምኑ? መጥምቁ ዮሐንስ «እኔ በውሃ አጠምቃችኋለሁ በእሳት የሚያጠምቃችሁ ግን ይመጣል» ብሏል ምን ማለቱ ነው?

«በምድር ላይ ሰላም ለመስጠት የመጣሁ ይመስላችኋል? እላችኋለሁ፣ አይደለም፣ መለያየት እንጂ» ሲል ምን ማለቱ ይሆን? «ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም ሲል በገሃድ ተናግሮ የለምን?»

በራሱ ንግግር እራሱ እየተማረከ የሄደ መሰለ፡፡ እንደ እብደቱ ዘመን ልበ-ድፍንነቱ ብልጭ እያለ ሳይቆይ ይጠፋል፡፡

«በፊት መጽሐፍ ሳላገላብጥ የማስታውሳቸው ሁሉ ጠፍተውኛል፡፡ ያም ሆነ ይህ ቤተክርስቲያንና ክርስቲያኖች ጉዳያቸውን ተነጥቀው ያልወለዱትን የሰው ጉዳይ እንዲታቀፉ ተደርጓል፡፡ ይሄን ያደረገው ደግሞ ሮማዊው ቄሳር ቆስጠንጢኖስ በኒቂያ ጉባኤው ነው፡፡ ኢየሱስን ከግብፃውያኑ ጣኦት ኦሲሪስ ትንግርታዊ ውልደትን ሰርቆ ከድንግል የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ አደረገው፡፡ ኢየሱስ የተወለደው ከመደብ ትግል ነው፡፡ እንደማንኛውም አብዮተኛ ህዝቦቹን ለአመፅ አብቅቶ አልፏል፡፡ እሱ ያቀጣጠለው ትግል ነው ከጥቂት አመታት በኋላ እየሩሳሌማውያንን በገዢዎቻቸው ላይ አስነስቶ ከተማቸውን ያጠፋት፡፡»

በድን እግሩን በግራ እጅ ሰቅስቆ ካንዘፈዘፈ በኋላ ከስቃይ ጋር አነቃቃና እንዲህ በማለት ደመደመ «ክርስቲያኖችንና ቤተክርስቲያንን ሙጥኝ የምለው የጋራ ህመማችንን ለመጠያየቅ ነው፡፡ የተቀለበሰ አብዮት የሚበትነው ብዙ ወገን አለው፡፡ የእስራኤሎቹ የከሸፈ አብዮት መከራው ለህዝቦቹ ለሺህ ዓመት ተረፈ፡፡ የኛስ? ይሄን አወራለሁ እዚህ መጥቼ፡፡»

ጨዋታችን ይሄን በመሰለ ዙሪያ ሲሽከረከር ቆይቶ በመጨረሻ ኮምሬድን እዚያው ጥለን ሄድን፡፡





* * *

የሰው ልጅ ከተፈጥሮ የተሰጠውን ነፃ የመኖር ፈቃድ በግዢ የሚያገኝ ብቸኛው እንስሳ ነው፡፡ ለመኖር ስንት ብር ይፈጃል? ኮምሬድን ለማኖር ስንት ብር ያስፈልጋል? ለእኔ በጣም ጥቂት የሆነው ዋጋ ለእሱ እንዴት አዳገተው? የአንዱ የመኖር ዋጋ ተነጥቆ ሌላኛው እጅ የገባበት መንገድ የቱ ይሆን? ለምሳሌ የእናቴ የመኖር ፈቃድ በአባቴ እጅ ገብቶ ነበር፡፡ ለምን? ለምን የአንዱ ነፃ ፈቃድ በሌላኛው የመርገጥ ፍላጎት ስር ይወድቃል? ለመኖር የሚያስፈልገው መጣርና መጋር የሆነበትን ዘመን አልፈነዋል፡፡ ለመጣርና ለመጋርም የሌሎች ፈቃድ የሚጠየቅበት ማህበራዊ አደረጃጀት ላይ ደርሰናል፡፡ ይሄ ማህበራዊ አደረጃጀት ማደግ ነው መዝቀጥ?

ብዙ አሰብኩ፣ እየተፈላሰፍኩ አይደለም፡፡ ከአካባቢዬ ጋ እየተዋወኩ ነው፡፡ ከልጅነቴ ጀምሮ በስሜ የተከማቸው ሐብት የሌሎች የመኖር ዋጋ መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ አሰብኩ፡፡ እንደ ኮምሬድ አይነቶቹ መኖር የሚያዳግታቸው የሀብት ፈሰሱ ወደ አንድ ወገን ስላጋደለ ነው፡፡ ታዲያ ምን ይሁን? እንደልቃቂት ጉልጉል ውሉ የጠፋ ሀሳብ ውስጥ ገባሁ ፡፡ግን ቢያንስ የማውቃቸውን መርዳት እንዳለብኝ ተሰምቶኛል፡፡ ጥቂት ወጪ ኮምሬድን ባለመጠለያ ባለልብስና ባለምግብ ያደርገዋል፡፡

በዚህ ቆርጬ ወደ ሙሉጌታ ጋ ሄድኩ፡፡ ሳማከረው እንደልጅ ያየኝ መሰለኝ፡፡ ዝም ብሎ ቆየ፡፡ የተወውን አውራ ጣት ማሾል ዛሬ ጀምሯል፡፡ ጺሙን ደጋግሞ ያስተኛል፡፡ አልተከላከልኩትም ዝም ብዬ አየሁት፡፡ ከቆይታ በኋላ «ኮምሬድ ራሱን ረድቷል፣ ረዳት አይፈልግም» አለኝ፡፡

«እንዴት?» ቾሮታዬን እንደ ንፉግ ምጽዋት የተመለከተው መሰለኝ፡፡

«ሞቷል»

«እ-እ-እንዴት? እንዴት ሞተ?» ያልኩት ይመስለኛል አላውቅም፡፡

«እሱን ተይው» አለኝ፡፡ «ማድረግ ያለበትን ነው ያደረገው፡፡ የማናግዘውን ተሸክሞ ብዙ መንገድ ተጉዟል፡፡ ታከተው፣ በቃ! እራሱን አጠፋ፡፡ እንደ ሲስፈስ ከዳር የማይደርስ የሕይወት ድንጋይ ሲገፋ ኖረ፡፡ ዘግይቶ ግን አወቀ፡፡ ድንጋዩን ከመግፋት እራሱ ላይ ለቅቆ ተጨፍልቆ መሞትን መረጠ፡፡ እንዲህ ማድረግ የለበትም የሚል ስቃዩን የተመኘ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ እራሱን ሰቀለ፡፡»

አዘንኩ፣ እጅግ ያሳዘነኝ ደግሞ ሙሉጌታ እኔ ላይ መቆጣቱ ነበር:: ቆይቼ ግን ቁጣው ከሐዘኑ መከፋት የመነጨ እንደሆነ ተገነዘብኩ:: ድንገት ሀሳብ ቀይሮ «የአባትሽን ፎቶ ይዘሻል? ሲል ጠየቀኝ::»

ግራ እንደተጋባሁ እንዳልያዝኩ ነገርኩት

«ነገ ይዘሽልኝ ነይ» አለኝ:: «ከዚያ አባትሽን አግኝቼ አነጋግረዋለሁ» አለኝ::

በደመነፍስ «እሺ» አልኩት:: መልሼ ሳስበው ግን አባቴን ሊያገኘው? የሳጥናኤል ሰይፍ ሲምዘገዘግ በሚካኤል ሰይፍ ምክቶሽ የሚፈጠረው ብልጭታ ታየኝ!!! አይሆንም፣ በፍፁም አይሆንም!!





# ጉርድ ማስታወሻ

ፎቶውን ስሰጠው አባቴን እንዳያገኘው ለመንኩት:: ፎቶውን በአንክሮ እያየ ዝም አለኝ:: ዝም ካለ እንቢ ማለቱ ነው:: ለመንኩት ዝም አለ::

ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላወኩም:: በምንም መንገድ ግን ሙሉጌታ አባቴን ማግኘት እንደሌለበት ወሰኛለሁ:: እኔ ካልረዳሁት በምንም መንገድ አባቴን ሊያናግረው አይችልም:: አውቃለሁ:: ቤት ቢመጣ ለወትሮው ፈዛዛ የሆኑት አዛውንት ዘበኛ ይኀለምሱና ለድብድብ ይጋበዛሉ:: ደሃማ ሲያዩ በሽታ አለባቸው:: ማጭድ፣ መኮትኮቻ፣ ጉማጅ እንጨት ያገኙትን ያዞራሉ:: ይገፈትራሉ የትኛውም ድርጅት ቢሄድ አባቴ ዘንድ ከመድረስ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ ይቀለዋል::

አባቴንና ሙሉጌታን አገናኝቼ ሁሉንም ነገር ከመሰረቱ ከምንድ ለተወሰነ ጊዜ ከፍቅሬ መራቅን መረጥኩ:: ያዳግታል:: ግን የግድ ይሻላል:: አባቴን ከሙሉጌታ አስበልጬ ላለመጥቀም እሱንም ላለማግኘት ወሰንኩ:: ትምህርት ቤት ሄጄ ወደ መኝታ ቤቴ:: ረጅም ጊዜ ያስመሰልኩት የሁለት ቀን ታሪኬን ነው::

መኝታ ቤቴ ውስጥ አልጋ ላይ እጋደማለሁ:: አንዳንዴ ቦቹ መጥቶ ጭራውን እያድፎነፎነ ያንኳኳል:: ዝም እለዋለሁ:: ወይም ባስገባውም «ልፈያ አልፈልግም» ብዬ እቆጣዋለሁ:: እንደ ድንክ ጎረምሳ እያጉረመረመ ይተኛል::

ሁለተኛው ቀን አመሻሽ ላይ አቁነጠነጠኝ:: ተደብቄ ሳያየኝ አይቼው ብመጣ ወደድኩ:: ወዲያው ደግሞ ራሴን ታዘብኩ «ምናለ ሦስት ቀን እንኳ ብሞላ?»

ከግቢው ወደ መኝታ ከፍሌ ጥሪ ተደረገልኝ:: ፈዛዛው አዛውንት ዘበኛ ነበሩ:: መልዕክት ሲኖረኝ እንዲህ ያደርጋሉ:: ሸዊት ትዝ አለችኝ:: እሷን እንኳን አያስገቧትም:: እየተነጫነጬችባቸው ሲፋጠጡ እደርሳለሁ::

«ጓደኛዬ ኮ ናት» እላቸዋለሁ::

«ምን ላድርግ፣ ኃላፊነት» ይላሉ የጨርቅ ኮፍያቸውን እየገፈፉ::

ወደጊቢው ወጣሁ:: የመኪና ዘር የለም:: ግቢው ውስጥ የተነጠፈው ለስላሳ ድንጋይ በመኪና ዘይት መበለሻሸት ጀምሯል:: ማዲያት እንደበላው የደሃ ፊት የተዥጎረጎረውን የድንጋይ ንጣፍ እየጠፈጠፍኩ ወደ በር አመራሁ::

«እኔ እመጣ ነበር እመቤቴ» አሉ ፈዛዛው ዘበኛ:: የጨርቅ ኮፍያውን ከጭንቅላታቸው ላይ እየገፈፉ:: ከቤት ደጃፍ እስከ በር መምጣቴን እንዳልተገባ ውለታ ቆጠሩልኝ::

በኪስ ወረቀት ውስጥ የተጠቀለለ ነገር እየሰጠኝ «እነሆ፣ አንድ ልጅ አግር አኑሮት ሄደ» አሉኝ::

«ሙሴ!» የሚል ጩኸት ውስጤ ተሰማኝ:: ልከተለው ባስብም እንደምንም እራሴን ተቆጣጥሬ ተውኩት:: የመንደሩን ታሪክ ነበር የተወልኝ:: በሦስት አግራፍ የተከፋፈሉ ማስታወሻዎች:: ለመጀመሪያ ጊዜ ፍቅሬ ሲል ይጀምራል:: አ-ቤ-ት የተሰማኝ መደንገጥ!





# ፩

ፍቅሬ:-

ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀባዠረ ዝናብ ጣለ:: ተሳስቶም አይመስል ከምሩ ነው የዘነበው:: ከፉኛም ብርድ ይሰማኝ ጀምሯል:: «ልጅና ፊት አይበርደውም» የሚባልልኝን ዘመን አርቄ ማለፌን ልብ እንድል አድርጎኛል::

ልጆች ሆነን በእንደዚህ ያለ ክረምት ወቅት ፓርላማ ፊት ለፊት የመሰብሰቢያ አዳራሽ የተሰራበት ሜዳ ላይ ኳስ እንጫወት የነበረው ያለ አንድ እራፊ ጨርቅ እራቁታችንን ነበር:: ምክንያቱም ልብሳችን ከበሰበሰ አሣር ማየት ስለሚከተል መላ ልብሳችንን እናውልቅና ትላልቅ ድንጋይ አንከምርበታለን:: ወይም ለፓርላማ ዘብ ፖሊሶች እንሰጥና እርቃናችንን መጫወት ነው::

...ፊታቸውን የሚሸፍነውን ዝናብ ቶሎ ቶሎ በእጃቸው እየጠራረጉ የላስቲክ ኳስ ተከትለው ግር የሚሉ ብዙ ደራቁቻ እርቃን ሕፃናት:: ዝናቡ ሲቆም ጭቃው ልጆቹን ከጭቃ ተድቦልቡለው የተሰሩ ሲያስመስላቸውና አብዛኛውን ጊዜ የአቅራቢያችን ቤተ-ክርስቲያናት የኔ ቢጤዎች የሚታጠቡበት ምንጭ ላይ ገላቸውን ለመለቃለቅ ግር እያሉ የሚሽቀዳደሙ... እግዚአብሔር ፍጥረትን እንደገና ከጭቃ ጠፍጥፎ መስራት የጀመረ ቢመስል አያስገርምም... እነዚህ ሕፃናቶች መሀል እኔ መኖሬን እጠራጠራለሁ ግን አለሁ::

አይ ልጅነት!!

ይኸውልሽ እነዚህ ህፃናት ታሪኳን ለጀመርኩልሽ ለዚያች አስገራሚ መንደሬ የራሳቸው አስተዋፅኦ አላቸው:: በመንደርተኛው የዕለት ተዕለት አኗኗር ላይ በልጆች በኩል ከተመለከትሽው መንደራችን ቅርጿን እንዳትስት፣ ይዘቷን እንዳትለቅ ጥረት የሚያደርጉ ሊመስል ይችላል::

ፍቅሬ:-

መንደራችን የድሆች መንደር ናት ብዬሻለሁ:: ድህነት በይበልጥ በፀጋ ላልተቀበሉት አንገፍጋፊ ነገር ቢሆንም የድሆች ፈጣሪ ደግሞ ይሄንን አንገፍጋፊ ሸክም ፍጡሮቹ ችለው እስከ ዕለተ ሞቷ ይዘልቁ ዘንድ ማባበያ አለው:: ምኞት::

የመንደራችን ነዋሪዎች ዘንድ ሳይዳላ የተካፈሉት ይህ የከፍተኛ ምኞት ጥሪት ነው:: ምኞታቸው ደግሞ በየትኛውም አቅጣጫና እምነት ይሁን ብቻ እንዲሳካ ነው የሚሹት:: ስለዚህ የመንደራችን አብዛኛዎቹ ነዋሪዎች የሚያመልኩት ሁለቱንም ቃልቻንና እግዚአብሔርን ነው:: ወደ አንዱ ብቻ ወግነው ከሌላው የሚሰጠው በረከት እንዲጣመልጣቸው አይሹም:: ዛሬ የማሪያምን ጽዋ አውጥተው ነገ ቃልቻ ቤት ቢያድሩ አዲስ ነገራቸው አይደለም:: ከመንደራችን ነዋሪዎች ቃልቻ ቤት የማይሄዱት በጣም ጥቂቶቹ ቢሆኑ ነው:: እነሱም ለቃልቻ ያላቸው ከበሬታና ፍርሃት ቤቱ ከመሄድና ከመስገድ የሚያስንቅ ነው::

ታዲያ ይሄ እምነት ለኛ ለውሪዎቹ የቀልድ መፍለቂያ ምንጫችን ይሆናል:: በትንሽ እራፊ ጨርቅ ላይ አመድ፣ ነጭሽንኩርት፣ የእንቁላል ቅርፊት፣ ኮረሪማና የተቆላ ቡና አድርገን አንዷ በር ላይ መጣል ነው:: በቃ ሰፈሩ ይታመሳል:: የተመለከተ ሁሉ እንዳይጠረጠር በመፍራት ባሊ ውኃ እያመጣ እዚያ ሟርት ላይ ሲቸልስ ይውላል:: እንዲህ ያለው ቀልድ የምናዘወትረው የጠላ-ኮማሪቷ ረታች ላይ ነው::

ረታች ልብስ ደራርበው መልበስ ይወዳሉ:: ታዲያ ከላይ ይከመሩና እግራቸው ጀምረሽ ስታያቸው ባለላባ ሰው ይመስሉሻል:: እስፒል አይን አላቸው:: እንባቸው ከነዚያ የአተር-ፍሬ ዓይኖቻቸው የሚወጣ አይመስልም:: በአንገታቸው ምቀኞቻቸውን አብዝተው ይገምቷቸዋል:: ስለዚህ እሳቸው በር ላይ ሟርታችንን ከጣልን ድምጻቸውን ቀጠን-ዘለግ አድርገው ሁብታቸው እንደማይገኝ ከተነተኑ በኋላ እሳቸው የሚሄዱበት አዋቂ (ጠንቋይ) ለእንዲህ ያለው ስራ አጠፌታውን እንደሚያከብደው ዘርዝረው በመጨረሻ ሆድ ብሷቸው ያለቅሳሉ::

ይሄ ሁሉ ለኛ ለውሪዎቹ ቲያትራችን ነው:: ቀልዳችን በሌላ መልኩ ጠቀሜታ እንደነበረው አሁን አሁን ይታወቀኛል:: እኛ ለጨዋታ የሰራነው ሟርት ብዙ የመንደሩን ሰዎች አነካክቶ አሳምቶ፣ አዋቂ ቤት ድረስ አስጎትቶ በመጨረሻ በአንዷ ላይ ይላከካል:: ይሄንን የሚያደርጉት «አዋቂ» የተባሉት ጠንቋዮች ናቸው::

እማማ ረታች ቡና ለመጠጣት ከሄዱ ወሬያቸው ይሄው ይሆናል:: «ይሄንን ያደረገችው ቀይ ናት፣ አንቺ ላይ ከፍተኛ ምቀኝነት አድሮባታል:: ለሕይወትሽም የምትመለስ አይደለችም... ወዞት» ተብያለሁ:: እያሉ ይንጨረጨራሉ:: ይዝታሉ





«አውቄያታለሁ!» ይቺ ለሕይወታችን ጠቀሜታ ያላት ጉዳይ ናት:: ምናልባት ያ ልምዳችን አንድ ዕውነት ባይፈነጥቅልን ኖሮ እንደ ሕፃናቶቹ ከወላጆቻቸው ጋር ጠንቋይ ቤት ማደር ይሄኔ ጥንቆላን ውርሳችን አድርገነው ውሎአችን አዋቂ ቤት በሆነ ነበር::

ትምህርት ሰጪ ኮሜዲ ድራማ የተገኘው ግሪክ ሳይሆን እኛ መንደር ነው ብል ማጋነን ይሆናል? በኔ በኩል አይሆንም!

የዚህ የጥንቆላ ሥራ ጉዳይ ሁልጊዜም ቀልደኛና ውሸት ነው ማለት አይቻልም:: አንዳንዴ በመንደርተኞቻችን ላይ ሲበረታ ሲገዝፍ በገሃድ ትመለከቺዋለሽ:: አንዳንዴ ምን አስባለሁ መሰለሽ ጠንቋይና እግዚአብሔር የሚለያዩበት ነጥብ በጣም ጥቂት ነው:: እሱም እግዚአብሔር በጭንቅላቱ ጠንቋይ በሆዱ ስለሚያስቡ ብቻ ነው::

እያቴ «ቃልቻና ሕፃን በሰው ገንዘብ ያለቅሳል» የሚሉትን ነው እየደገምኩልሽ ያለሁት:: ሕፃን የዳረ አስተሳሰብ ስለሌለው ነው:: ቃልቻም እንደዚሁ...:: ለዚህ ይመስለኛል በኛ መንደር የደከመ አኗኗር ውስጥ ገብቶ አንዷን አጥፊ ሌላዋን ጠፊ የሚያደርገው:: ጭንቅላት ቢኖረው ኖሮ...::

ይኸውልሽ ፍቅሬ እኛ መንደር ውስጥ አራት ሴቶች በዚሁ የጥንቆላ እሽከርክሪት ውስጥ ገብተው ሦስቱ ሲያልቁ አንዷ ብቻ በመከራ ልትተርፍ ችላለች:: እሷም ብትሆን ጭንቅላቷን ነካ አድርጓት ስትዞር መኪና ድጧት በመከራ ሕይወቷ ከተረፈ በኋላ አገሯ ሰላሌ ሄዳ ድና ተመልሳለች:: የመንደራችን ሴቶች ለሷ ያላቸው ፍርሃት ከፍተኛ ነው:: (ሻምፒዮን ሺፕ) እንደማለት ነዋ! እሷ የሄደችበትን የአገሯን ውቃቢ በጣም አድርገው ይመኙታል:: ሶስቱን በጥሎ ማለፏ አረታች!

እነዚያ-የዚች ሴት ተጋጣሚዎችን አሟሟት ተከታትየዋለሁ:: አማሟታቸው ፍርሃት የሚለቅ ነበር:: በይበልጥ የመጀመሪያዋ ሐኪሞች ጤነኛ መሆኗን እየነገሯት ነው ታማ የሞተችው:: ጤንነት እሞ ይገላል'ዴ? ሁለተኛዋም ቢሆን በቁርጥማት በሽታ ሰበብ እያወሩ ነው ሕይወታቸው ያለፈችው:: ቁርጥማት ያውም እጅ ላይ በጥቂት ጊዜ ውስጥ አሳምሞ ሲገድል-ከዚያ በፊት ሆነ በኋላ አላየሁም፣ አልሰማሁም::

ሦስተኛ ዋ ግን ለሦስት ዓመታት ያህል በአደገኛ ሁኔታ ታመዋል ዛሬ ነገ፣ ሲባል ሦስት ዓመት።

በመሠረቱ የሰው ልጅ ምቀኝነት የሚመነጨው በሁለት መንገድ ነው ይባላል። አንዱ በሀብት፣ ሌላው በፍቅር። የኛ መንደር ነዋሪዎች ግን የምቀኝነታቸው ምንጭ ምን እንደሆነ አይገባም። ሀብትም ሆነ ፍቅር የላቸውም። ግን ምቀኝነት ሲያድፈጠፍጣቸው ትመለከቻለሽ። ከሀብትና ከፍቅር ሌላ ሰው፣ ሰው መሆኑ ብቻ ነው የሚቀረው። ይሄ ይሆን ምቀኝነታቸውን ሊያስነሳ የሚችለው?... ነው ወይንስ እንደ የሰው ልጅ ሲፈጠር እንደ ፍቅር ሁሉ ምቀኝነት ቅልቅል ነውና በዚያ የምቀኝነት ስሜት መጠቀም ስላለበት?... እንጃ ነው የሚቀለው!!





# ፱

ዛሬ...

...ሠፈራችን ታምሷል። በምን እንደሆነ ለማጣራት ጠጋ ስል ኮከቤ «አገር ይያዝ» እያለች ታለቅሳለች። እንባዋ በአራት መንታ ይቀዳል። በወፍራም ፊት ከግብዳ ከንፈር አኩል በሆነው ሽፋሽፍት የተዋጠው ዓይኗ ደፍርሶ ያስፈራል። ስትስከርም ዓይኗ ይንለጎልና ዳር ወጥቶ ቁጭ ይላል። አፏ አያርፍም «ወላዲትን» እያለች ሳያስምሏት ትምላለች።

በምን እንደምታለቅስ ለማወቅ ብዙ ጥንድ ጆሮዎች አቆብቁበዋል። ለቅሶዋ አሳዛኝ ሳይሆን ወደ አስቂኝነት ያደላ ነበር። ሁሉም ሳቁን አፍኖ «ምን ሆነሻል?» ይላታል።

«ተወኝ! ተወኝ! ተወኝ!»

«እኮ ምን ሆንሽ?»

«መሞቴ ነው!»

«ምን ሆንሽ?»

«ጠጅ አልስማማሽ አለኝ። አለርጂክ ሆነብኝ። ለራሴ ውሃ በጉሮሮዬ አይወርድ እግዚአብሔር ምን ፈረደብኝ። ጠጅ የጠጣሁ እንደሆን ሦስት ቀን ሙሉ እታመማለሁ...»

ሠፈርተኛው ሳቀ...

...እኔ ግን አዘንኩ። ፍቅሬ፡- አዘንኩ።

ከጠጅ ጋር የተቆራኘ ስርዎ-ኑሮ አለብን። አብዛኛዎቹ የኛ መንደር ነዋሪዎች ጠጅ አፍቃሪያን ናቸው። ፍቅራቸው ደግሞ እስከመቃብር ድረስ።

አንዱን እንይ። ውቡ ዘለቀ ይባል ነበር። ከአዝማሪዎች ሁሉ ንጹህ እሱ ነበር። ቁመናው ለሱፍ ሆነ ለባህል ልብስ የተስማማ። ትላልቅ የቱሪስቶች ሆቴል ውስጥ «ይጫወታል» (ይዘፍናል)። የመንደሩ መኪታ ነበር። እንደ ዘመድ የቆጠራትን ሴት ባል ሲነጫነጭ ካጋጠመው እንደ ልጅ ይገርፈዋል። ሰፈር ውስጥም እንደዚያው...

...እና ወፍራም ፊት፣ ጡብደል ከንፈርና ድፍርስ ዓይኖች ነበሩት፡፡ ለራሱ የሚሰጠውም ግምት ከፍተኛ ነው፡፡ አንዲት ሞልቃቃ ሚስት ነበረቸው «ውቡዬ!» እያለች ትጠራዋለች «ልትሄድብኝ ነው?» ማሲንቆውን ይዞ ሲወጣ የስፖንጅ ፍራሽ ቅርዳጅ የመሰለ ከንፈሩን ሸሸት አድርጎ ያያታል፡፡ «እምቢ! አትሂድብኝ» ትለዋለች፡-

ጠጅ አፍቃሪ ነበር፡፡ ብዙ ገንዘብ የሚያገኝ ቢሆንም ወዳጁን (ጠጅ) አልከዳትም፡፡ መጨረሻ ላይ ታማሚ ሆነ፡፡ አካሉ ረገፈ፡፡ ሐኪም መጠጥ እንዳትጠጣ ቢለውም እየተንቀጠቀጠ ከአልጋ ተነስቶ ጠጅ ቤት ይሄዳል፡፡ ሚስቱና ወዳጆቹ ከጠጅ ቤት እየተነጫነጩ ይዘውት ይመጣሉ፡፡ ከንፈሩን መሰብሰብ አቅቶት ሙሉ አካሉን እያዝረበረበ እነሱ ላይ ያሳርፍና «መልሱኝ፣ ወደ ጠጅ ቤት መልሱኝ» እያለ ተሸካሚዎቹን ያማርራል፡፡

ውቡ እየባሰበት በመሄዱ የአልጋ ቁራኛ ሆነ፡፡ ያም ሆኖ ወዳጁ ጠጅን አልዘነጋትም፡፡ ኧረ እዛው ልሙት ጠጅ ቤት የሚወስደኝ ወዳጅ እንዴት ልጣ? እያለ አላፊ አግዳሚውን በጣዕረ ሞት ፊቱ ይማፀናል፡፡ «ስለገብርኤል ጠጅ ቤት ውሰዱኝ!» በመጨረሻ እራሱን ሳተ፣ አካባቢውን ዘነጋ፡፡ ቢሆንም ጠጅን ፈፅሞ አልረሳትም ነበር፡፡ «ጠጅ-ጠጅ» ይላል ጠጅ ቤት እንዳለ ሁሉ «እዚህ ቅዳ!» ከወዳጁ ጋር ሳይገናኙ ሕይወቱ አለፈች፡፡ ፍቅር እስከ መቃብር አንድ!

ፍቅር እስከ መቃብር ሁለት፡- ደበበ ደምሴ ይባሉ ነበር፡፡ ጥርሰ ወርቅ፣ ሲስቁ «ቂ-ቂ ቂ-ቂ» እያሉ በብዙ «ቂ» ነው፡፡ ነጠላ ያዘወትራሉ፡፡ የሰፈሩ ሴቶች «ደበበ ደምሴ-ውሃ ቅዳ ለእምሴ» ይሏቸዋል፡፡ ወንድነታቸው ላይ ጥርጣሬ አለ ማለት ነው፡፡ ሚስታቸው አረጋሽ ሠይፉ የምትባል ጠንጋራ ሴት ነበረች፡፡ ሲጣሉ «የወንድ እህት!» እያለች በመሮከር እላያቸው ላይ ጉብ ብላ በከርን ትደቀድቃቸዋለች «የወንዶቹ እህት! የወንዶቹ እህት!» ከድብድብ በኋላ ደበበ በተቀደደ ነጠላቸው ደማቸውን እየጠራረጉ ሚስታቸውን በስድብ ይገጥሟታል-አቅማቸው እሱ ነዋ! ማታ ባማላጅ ይቅርታ ጠይቀው ይገባሉ፡፡

ደበበ «ጠጅ» ማለት አይችሉም ነበር «ጠይ» ይላሉ «ጠይ ቤት ነኝ» መልዕክት ሲያስቀምጡ፡፡ አንድ ጊዜ (ሚስታቸው ደብድበዋቸው ነው ይባላል) በጠና ታመው ከአልጋ ዋሉ፡፡ ማታ ዘፋፍነው ጠይ መጠጣት ቀረ፡፡ ታዲያ ሰው





ሊጠይቃቸው ቤታቸው ሲገባ እጅግ የታመሙ መስለው ጠያቂው ላይ ሐዘን ከዘሩ በኋላ ከራስጌያቸው ጠርሙስ በማውጣት ጠጅ እንዲገዛላቸው ይማፀኑታል፡፡ «ጠይ ከቀመስኩ ድፍን ሳምንቴ፣ እንደው ውል እያለ አስቸገረኝ፡፡ ልሞት ይሆን?» ሞትን አይፈሩም፡፡ የሚፈሩት ከጠይ ጋር ተቆራርጦ በሕይወት መቆየት ነው፡፡ እራሳቸውን መቆጣጠር ተስኗቸው አልጋ ላይ እየተፀዳዱ እራስጌያቸው ከአልጋ ብረት ጋር ያሰሯትን የጠይ ላስቲክ አይዘነጓትም «ገርገጭ» አድርገው መልሰው ይከድኗታል፡፡ በመጨረሻ እኩለ ሌሊት እየተንቀጠቀጡ በር ይከፍቱና መሄድ አቅቷቻ ደጅ አድረው ጠዋት ይገኙ ጀመር፡፡ «ለምን ወጡ?» ሲባሉ በብርድ ጥርሳቸው እየተንገጫገጨ «ጠይ ቤት ልሄድ» ይላሉ፡፡ ተነስቶ ለመሽናት ሰንፈው ለፍቅረኛቸው ጠይ የመጨረሻዋን የኃይል እንጥፍጣፊ ይጠቀሙ ነበር፡፡ ሞቱ፡፡

ፍቅር እስከ መቃብር ሦስት፡- ካሴ ይባላሉ፡፡ ዝም ስለሚሉ ምሁር ይመስላሉ፡፡ ዝምታቸው ከብራቸውንም አስጠብቆላቸዋል፡፡ አዝማሪዎች እርስ በእርስ ሲሸራደዱ ሌላው ቀርቶ አይስቁም፡፡ ሲዘፍኑም እንደዛው ዝምታ እንደነገሰባቸው ነው፡፡ ዕድሜያቸውን በወንደላጤነት ነው ያሳለፉት፡፡ ከተለያዩ ሴቶች ጋር ይዘፍናሉ፡፡ ተካፍለው ፋንታቸውን ይዘው ወደ ቤት ይገባሉ፡፡ ስካራቸው'ኳ ፀጥታ የነገሰበት ነው፡፡ ገድገድ ሲያደርጋቸው ቆም ይሉና ተረጋግተው መልሰው ጉዟቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ቆም ሄደት ቆም-ሄደት የመጨረሻው ሳካር ገብቶ ለጥ፡፡

ረጅም ናቸው፡፡ ደባደቦ ፊት አላቸው፡፡ ጥርሳቸው እንዷ በልዛ ሌሏ ተሸፍናለች፡፡ ትላልቅ ዓይናቸው ትንሽ ሸንገር ይላል፡፡ በምን እንደሆነ እንጃ ከዝምታ ወደ መፍዘዝ ተሸጋገሩ፡፡ በሽታውን እንደሚያዳምጥ በግ፣ ዓይናቸውን አቡዝዘው መሬት መሬት ያያሉ፡፡ መዝፈኑን ተውት፡፡ አንዳንዴ ተኝተው ውለው ተኝተው ያነጋሉ፡፡ የሚገርመው ጎረቤት የሚበላ ሲወስድላቸው ንክች አያደርጉትም፡፡ የሚቸግራቸው ጠጅ ብቻ ነው፡፡ እየተንቀጠቀጡ ጠጅ ቤት በራፍ ላይ ይቆሙና በዚያው በዝምታ ቋንቋቸው ይለምናሉ፡፡ የገባው ይዟቸው ይገባል፡፡ ጠጅ! ጠጅ! ጠጅ!.... ደማቸው ውስጥ ጠጅ ብቻ፡፡ ያለቀች እራፊ ነጠላቸውን እንደተከናነቡ በዱላ ተደግፈው የመቆም አቅማቸውን እሚጠው ቁጭ እያሉ የጠጅ አማልከታቸው እዚያው የተቀመጡበት አምጥታ እያንበሸበሸቻቸው ሕይዎታቸው አለፈች፡፡

...እና ኮኮቤ ጠጅ አልስማማት ቢል በቁም የመሞት ያህል ቆጥራው ለራሷ ሙሾ አወረደች፡፡ በእርግጥም የሚፈልጉትን ከማጣት የከፋ ምን አለ? መኖራችን ለምንፈልገው አይደለምን? የሰው ልጅ አፈጣጠር ይሄው ነው፡፡ አንድ አሾ የተባለ ህንዳዊ የፃፈው ሁልጊዜም ውስጤ ይኖራል፡፡ አንድ ሰው ይላል ሙዚቃ አድምጦ ለውዝዋዜ ከመቀመጫው ይነሳል፡፡ እና ያሟሙቃል... ይወዛወዛል፣ ይወዛወዛል፣ ውዝዋዜው ውስጥ ይሰጥማል.. ይሰጥማል... ይሄ ነዋ ሰው ወዶ በገባበት ውስጥ ሰጥሞ፣ ማሙቶ የማለቂያ ሂደቱ፡፡ እና ኮከቤ ወዳ ጠጅን ጠጣችው፣ ጠጣችው፣ ወደደችው፡፡ በስተመጨረሻ ኮከቤ ጠፍታ ጠጁ ብቻ ቀረ፡፡ ያለ ጠጅ ኮከቤ አለች? እንዴት ተደርጎ?... ተፈላሰፍኩ ይሆን?





## ፫

የአቡንደጅ እንግዳ ትባላለች፡፡ ሲበዛ ወፍራም ናት፡፡ እግሮቿ ሁለት ኤሊ ባይመስሉ ኖሮ ያንን ግዙፍ አካል ለመሸከም ባልቻሉ ነበር፡፡ የአቡንደጅ ተራራ ከመምሰሏ የተነሳ እሷ እንኮኮ ያለችው ድፍን አዲስ አበባን እያየ የሚዝናና ይመስላል፡፡ ሴተኛ አዳሪ በመሆኗ እሷ ቤት የሚገቡት ወንዶች በእርግጥም ፍትወት ፈልገው ሳይሆን «ጉዷን እንዳይላት» የሚሉ ነው የሚመስሉኝ፡፡ የብሽሽቷና የብብት ስጋ ድርብርብ ስለሆነ እግሮቿና እጆቿ አይገጥሙም፡፡ እንደዋናተኛ እየቀዘፈች ደርከክ-ደርከክ እያለች ነው የምትሄደው፡፡ ሁልጊዜም ማሰሪያው የተፈታ ሸራ ጫማ ታደርጋለች፡፡ ጫማው የሚያልቅባት በአዲስነቱ ከምላሱ መጋጠሚያ ወደ አፍንጫው ተተርትሮ ነው፡፡

ሲበዛ ንጹህ ስትሳደብ ኳ «ሸታታ!» እያለችና እየተፀየፈች ነው፡፡ ንፁህናን የወረሰችው ትላልቅ ሰዎች ቤት ትሰራ ስለነበር ነው ይሏታል፡፡ እንደውም አንዳንዶቹ ብዙ ልጆችን ከታላላቅ ሰዎች ወልዳ ለአባቶቻቸው አከፋፍላ ብቻዋን ቀረች ይሏታል፡፡ ይሄ እንኳን የተጋነነ ይመስላል፡፡ ሁሉም የሚስማሙት ግን አንድ ወንድ ልጅ እንደነበራትና ካደገ በኋላ አባቱ እንደወሰዱት ነው፡፡

እኛ ውሪዎች ሆነን ከቤቷ ስር እንጠፋም ነበር፡፡ ከወንድ ጋር ስትተኛ አፏ አያርፍም «ኡ-እ-ኡ-ኡ፣ አፈር ብላና ቀስ አትልም እ-እ-ኡ-ኡ» ትላለች በቤቷ ቀዳዳ የተሰየምነው ስንገፋፋ ይንዳዳል የአቡንደጅ ጩኸቷን ገታ አድርጋ «ማነው?» ትላለች እኛ ውሪዎቹም ድምፃችንን አቅጥነን የሴት በማስመሰል «እኔ» እንላታለን፤፡ ይሄኔ መአቱን ታወርዳለች፡፡

«እንኳን አንቺ እኔም አልቻልኩት፡፡ እችላለሁ ካልሽ ነይ ግቢና ተሰኪ...» ትልና ወደተቋረጠው ኡኡታዋ ትመለሳለች፡፡

መቼም በስድብ የሚስተካከላት የለም፡፡ በራፏ ላይ ያለው የተቀበረ የድንጋይ ሙቀጫ ላይ ቁጭ ትልና አንዷን በስድብ ከጠመደች መሽቶ ይነጋል፡፡ አይደከማትም፡፡ ሴቶቹ በስድቧ ሲበሽቁ የተቀመጠችበት ራቅ ይሉና በመጥረጊያ «ቹብ! ቹብ!» ያደርጓታል፡፡ ቶሎ መነሳት ሸለማትችል ቁጭ ብላ መጥረጊያውን ለመያዝ

ትሞክራለች፡፡ ስትይዝ ጥለውላት ይሄዳሉ፡፡ ለእልኋ ማብረጃ መጥረጊያውን በጥርሷ ትበታትነዋለች፡፡

የአቡንደጅ ቤቷ የገባውን ወንድ ኪስ መበርበሯ የማይቀር ነው፡፡ ወንዱ መሰረቁን አውቆ ፀብ ከፈጠረ ቶሎ ትጮሃለች፡፡ የእኛ መንደር ሰው ግልብጥ ብሎ ያሰፈስፋል፡፡ የአቡንደጅም ብትሞት መስረቋን አታምንም፡፡ ለእኛ ለውሪዎቹ ትልቁ ትርኢታችን ከዚህ የሚቀጥለው ነው፡፡

«ብሩን ሰርቄ የት አገባሁት? ውሸቱን! እንደዚህ እርቃኑን ነው የተኛሁት?» ትልና ቀሚሷን ገልባ እራቁቷን ትቀራለች፡፡ ደፍሮ አካሏን የሚመለከት አዋቂ የለም፡፡ ይዘገንናቸዋል፡፡ እኛ ውሪዎቹ ግን እያጎነበስን ለመመልከት እንሞክራለን፡፡ የተራራ ግማሽ የሚያክል አካሏ የተደራረበ ሥጋ፣ እጥፋቱ ብዙ... በይበልጥ ሆዷ ያለው ጉልበቷን ደገፍ ብሎ ነው፡፡ ታዲያ ከዚህ የስጋ እዝልዝሎሽ ሥር ያለ ነገር ለማየት መሞከር ቂም ማትረፍ አይሆንም?

የአቡንደጅ ለሚገባቢት እንደምትነግረው ብሩን የምትደብቀው በአካሏ አንዱ እጥፋት ውስጥ ነው፡፡ ፖሊስ ቢመጣም ደንታ የላትም፡፡ እየደጋገመች «ፈትሹ!» እያለች ቀሚሷን መግለብ ነው፡፡

ወደ መጨረሻ አካባቢ የአቡንደጅ አልቻለችምና ቤቷን ለሴቶች አከራይታ ውሎዋ ጠጅ-ቤት በር ላይ ሆነ፡፡ መመላለሱ ጭንቅ ስለሚሆንባት እዛው እሳት አያይዛ ምግብ ማብሰልና በልታ እዛው ጠጇን መጠጣት ያዘች፡፡ ስትሰክርም አላፊ አግዳሚውን «አንሱኝ!» እያለች ትማፀናለች፡፡ ጠጪነቷ ስለጨመረና ከቤቷ ስለራቀች ንፅህናዋን በቅጡ መጠበቅ ተሳናት፡፡

የአቡንደጅ በውፍረቷና በጠረኗ ምክንያት ተሸከሞ የሚያነሳት ማጣት ጀመረች፡፡ ስለዚህ አብስላ መብላት ብቻ ሳይሆን አዳሯም እዚያው ጠጅ ቤት በራፍ ላይ ሆነ፡፡ ቤቷን የተከራየችው የቀን ሂሳቧን እዚያው ጠጅ ቤት በር ላይ እየወሰደች ትሰጣታለች በጎደለ ትለምናለች፡፡ በመጨረሻ ታመመች፡፡ በዚህ ሰዓት ላይ እንኳ «ቤቴ ውሰዱኝ!» እያለች ብትወተውትም እሷን ለመውሰድ የደፈረ ታጣ፡፡ የሰፈራችን ሰው የሆነ በዚያ ጠጅ ቤት በር ላይ ሲያልፍ፡-





«እናንተ እያላችሁ ኢደጅ ልሙት?» እያለች ትወቅሳለች፡፡ ትዝ ይለኛል ወቅቱ ክረምት ነበር፡፡ የአቡንደጅ በጠና ታመመች፡፡ መላ አካላቷ ዘነነ፡፡ ሠፈርተኛው እሷን ተሸከሞ ከማጣት ይልቅ እዚያው ያለችበት ቦታ ላይ ትንሽ ከለላ መስራትን መረጠ፡፡ ከለሉላት፡፡ ለአንድ ወር ያህል ታማ እዚያው አረፈች፡፡

ለስንቱ ይታዘናል?... እኛ መንደር ውስጥ እየተኖረ ስለመንደርተኛው በሐዘን መሰበር አጉል-ጠቢብ መሆን አይደለም?... ስለኑሮአቸውና አሟሟታቸው መቆጨትም ሆነ መታዘብ ፈጣሪን ለመተካከል መሞከር አይሆንም?

የመንደራችን ሕይወት ጎርፍ ነው፡፡ አፈር-ቅልቅል ድፍርስ ጎርፍ! በዚያ በሚጋሽብ የሕይወት ወንዝ ውስጥ ተሁኖ ማነው ማንን ቆም ብሎ ማስተዋል የሚቻለው?... የትኛውስ ነው አብሮት ለሚደፈቅ ባልንጀራው አዘኔታ ሊሰማው እንዲገባ ተደርጎ የተፈጠረ?... ማንም!!

ይሄ ድፍርስ የሕይወት ጎርፍ ወደዳር የሚተፋውኳ ከአብሮነት ውጪ ይሆናልና ውጣ-ውረዱን ሊታዘብ አይገባውም፡፡ አንዳንዴ ሐዘኔታዬን እራሴን አተልቄ የመመልከቴ ከንቱነቴ አድርጌ እወስደዋለሁ፡፡ በእርግጥም ማዘንና መቆጨት አይገባኝም ስል ራሴን መምከር ይቃጣኛል፡፡ አዎ እኔም ለዚህ የሕይወት ተውኔት ለአንዱ አሳዛኝ ክፍል የታጨሁ ተዋናይ እሆን ይሆናል፡፡ እንዴት መጪ ሕይወቴን እገፋለሁ? በእንዴት ያለ ሁኔታስ ነው ይህቺን ዓለም የምሰናተው? አላውቅም!! በሌሎቹ የመንደሬ ነዋሪዎች ላይ የደረሰው አሳዛኝ ፍፃሜ በኔም ላይ እንዳይደርስ ለመከላከል ምንም የመተማመኛ ፍንጭ የለኝም፡፡ ትንሽም በአሁኑ ሰዓት ላይ አለኝ የምለው ወጣትነቴን ብቻ ሊሆን ይችላል እሱም ቢሆን ቋሚ የኔነት የለበትም፡፡

እ-ና--- የራሴን የማላውቀው የትወና ተግባ ትቼ ስለምን ስለሌላኛው ተዋናይ ዕጣ ፋንታ እጨነቃለሁ? ደግሞስ ጭንቀቴና አዘኔታዬ የሚያመጣው ልዩነት እምኑ ላይ ነው? ሲኖረኝ መስጠቴና ሳይኖረኝ መቀበሌ አንድ የተዋናይነት ተግባሬ'ጂ የማዘንና የመቆጨት እንዲሁም የመርዳት መለኪያዬ ሊሆን አይችልም፡፡ እኔ የሚሰማኝ ይህ ነው፡፡

## ፬

የመንደራችን እጅ ከወንዶች ይልቅ በሴቶቹ ላይ ሳይከፋ አይቀርም፡፡ ሕይወታቸው ቶሎ ተግ ብሎ ቶሎ ይከስማል፡፡ በእርግጥ እንደነ መሳፍንት ከንቱ ሁሉ ሴቶቹም የሚበቅሉት ከአንድ የችግር ማጥ ውስጥ ነው፡፡ ቢሆንም ችግር ፆታዊ አመሳሰዋን ባለሙተዋ ቅጣቷ በነሱ ላይ ይከፋል፡፡

አንድ ከነመኖሯ የማትታወቅ ሴት ልጅ በአንድ ቀን ጀምበር ድንገት ፈከታ ውበቷ ችግሯን አሸንፎ ሲንፎለፎል ይስተዋላል፡፡ መዝረክረኳ ይቀርና ሁሉም ነገር በጥንቃቄና በንጽህና ይያዛል፡፡ በቀን አስር ጊዜ ተረከዟ ከድንጋይ ጋር እየተፈተገ ይታጠባል፡፡ ቫዝሊን ይዘወተራል፡፡ ጥፍር ቀለም የግድ ነው... ያም ሆኖ ውበቷ ዕድሜዋ ነው «ንቦች» ስለውበቷ ያንጉበባሉ፡፡ የሆነ ሰዓት ላይ ያ የተማመነችበት ውበቷ መሀል ሜዳ ላይ ለጅብ ጥሏት ገለል ይላል፡፡ እሷና ዲቃላ፡፡

ሴተኛ-አዳሪ ለመሆን የምታንገራግር አትኖርም፡፡ ከምን የመነጨ ባህርይ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ መንደራችን ውስጥ ሴተኛ አዳሪነት የተነወረ ሥራ ተደርጎ አንድም ቀን አይወራም፡፡ እንደውም በስድብ መሀል «ሸርሙጣ!» ላለችው መልሷ «የቆንጆ ወጉ ነው!» ይሆናል፡፡ ይሄንን ትንንሾቹ «ገንቦዎች» በትላልቅ ጆሮዎቻቸው ይቀዳሉ፡፡ ምናልባት መልኳ የከፋው ሸርሙጣ ለመሆን «ባለመታደሏ» ሳትከፋ አትቀርም፡፡

ትዝ ይለኛል ልጆች በነበርንበት ወቅት ሴቶቹ እንደሴተኛ አዳሪ፣ እኛ ወንዶቹ ደግሞ እንደዘማች ደንበኞቻቸው ሆነን የምንጫወተው ጨዋታ ነበረን፡፡ ሲደረግ እንዳየነው እኛ ወንዶቹ ኮራ ብለን የቆሙ ዕኩዮቻችንን በትከሻ ገጪት አድርገን በጀንያ የተጋረደ የዕቃ-ዕቃ «ቤት» ውስጥ እንገባለን፡፡ ይከተሉናል፡፡ ዋጋ እንደራደርና የከረሜላ መጠቅለያ ወረቀት ቆጥረን እንከፍላለን፡፡ ከዚያ በኋላ ትዝ አይለኝም...

...እንዲህ አይነት ጨዋታ የሚወድዱ ብዙ ውሪ ሴቶች ነበሩ፡፡ አንዳንዴ እንደኮርማ ወንድ «ተደባደቡ እንጂ» ብለውን ባልጠና ጡንቻ ግብግብ ስንገጥም «ኡ-ኡ-ኡ» እያሉ ያጅቡናል፡፡ የዚያች መንደር እንቡጦች የዚያ መንደር ዛሬዎች፣ ምኞትና ግባችን ይሄ ነበር፡፡ እግዚአብሔር «የለመኑትን የማይነሳ» የሚባለው ይሄንን ግባችንን





እውን በማድረጉ ይመስለኛል፡፡ ሴቶቹ ከአጎጠጎጤአቸው ጋር እኩል የሚደርሰው የኑሮ ቁልቁለት እያዳፋ ሲመኙ ወደ ኖሩት የሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ይዘፍቃቸዋል፡፡ ወንዶቹም ከልጅነት ጀምሮ እንደራስ ምታት ኪኒን የሚውጡት ፀያፍ ድርጊት ይላመዱትና በኑሯቸው ውስጥ ስከሰት የማይቆረቁር የማይጎረብጥ ይሆንባቸዋል፡፡ ለዚህ ነው ብዙ ወጣቶች «ትዳር» የሚይዙት ከሴተኛ አዳሪዎች ጋር ነው፡፡

የኛ መንደር ልጆች የሚከታተል መንፈስ አለብን፡፡ ዛር! ካላድፈጠፈጠ የማይለቀን፡፡ ልጅነት በሚጥለው ግዴለሽነት የተነካካነው ቆሻሻ አድገን አፈር እስክንገባ አይለቀንም፡፡ ከረሜላ ወረቀት መስለን የተጫወትንበት ስናድግ ኑሮ ሆኖ ይጫወትብናል፡፡ እኛ ብቻ አይደለም ወላጆቻችንን አባብሎ ገበያ ባያወጡንም በ«ጋቢቻ» ሥም የሚቸበችቡን የልጆቻቸው ቸርቻሪ ያደርጋቸዋል፡፡

ነገሩ ትዝ የሚለኝ እንደ ህልም ነው፡፡ የአሥራ አንድና አስራ ሁለት አመት ልጅ ሳልሆን አልቀርም፡፡ በእኔ ዕድሜ ውስጥ ያለች ልጅ ለመዳር መንደሯ በስራ ተወጥራ ነበር፡፡ ልጅቷ አግለብልቦ ያጠነከራት ባትሆን ኖሮ መከራውን የምትቋቋም ባልሆነች ነበር፡፡

ተዋበች አበጀ ትባላለች፡፡ በቀጭን ወገቧ ላይ እንደሙቀጫ የምትንከባለል ደዘደዝ እህቷን አዝላ በፊት ለፊት ደግሞ መንትያዋን ትደግማለች፡፡ መንደሩን ስታስስ የምትኖረውእንደሚዛን ወደፊትና ወደኋላ እየተወዛወዘች እንዲህ ነው፡፡ እናቷና አባቷ አዝማሪዎች በመሆናቸው የመንታ ልጆቻቸው ሞግዚት አድርገው እሷን ሾመዋታል፡፡ ጠዋት ጀርባና ደረቷ ላይ፣ ማታ ጀርባና ደረቷ ላይ፡፡ ዲሞ እና ድብብቆሽ ስትጫወት እንኳ አዝላና አቅፋ ነበር፡፡ በዚህ ላይ የአባቷ አሽሙርና የእናቷ ዱላ፡፡ አባቷ አበጀ «ዞጦ» የሚል ቅጥል መጠሪያ የተበጀለት ፊተ ጨፍጋጋ ሰው ነበር፡፡ ፊቱ አይጠራም ጠባብ አፉን የከበበ ችፍርግ ጢም አለው፡፡ እንደአስፈሪነቱ ፀበኛ አይደለም፡፡ አንድ ስህተት ካስተዋለ አምባጓሮ ከመፍጠር በነገር መወጋጋት ይቀለዋል፡፡ በዚህም «አሽሙረኛ ነው» ይሉታል፡፡

አንድ ጊዜ ሚስቱ ውሽማ መያዛቸውን ይደርስበታል፡፡ እንደባል ፀብ አላስነሳም፡፡ እንደ አዝማሪ ባሎች ማሲንቆ አልመታልሽም አላለም፡፡ ብቻ በየዘፈኑ መካል ደጋግሞ የሚገጥማት ግጥም ሔዘጋጀ...

«ከጤፍ አቅም ሸርኮት-
ካንቺ አቅም ውሽማ፣
ተሾፈ አይደለም ወይ-
ይሄን ሰሞንማ»

ሚስቱ በቋቁቻ የተዥጎረጎረ ቀይ ፊታቸውን እያመሳቀሉ «አንተኮ ከብር አይወድልህም!» ይሉታል፡፡ አበጀ ዙጦ የጨፈገገ ፊቱ ፈካ የሚለው ያበሽቃቸው በሽቀው ሲያያቸው ብቻ ነው፡፡ ይሄኔ ተካሰ ማለት ነው፡፡

የቤተሰቡ አኗኗር በ"Fastfood" ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ ቤት ውስጥ የሚበስል የለም፡፡ እንደበሰለ ይገዛል፡፡ ሽልጦ፣ እንጀራ፣ ሻሜታ፣ የተበጠበጠ በሶ... እናትና አባት ማታ ወደስራ ሲሄዱ «ተዋበይ» ይሉና እናት ከብብታቸው ሥር ሰርስረው መሃረባቸውን ያወጡና የ"Fastfood" መግዣ ይሰጧታል፡፡ ያም ሆኖ ልጆቹ ቀና ብለው የሰው ቤት አያዩም፡፡ በዚህ የተመሰገኑ ነበሩ፡፡

አንድ ቀን ባል ተገኘላት ተባለ፡፡ ሰፈሩ በጉዳዩ ላይ ለሁለት ተከፈለ፡ ተከራከረ...

«እህል በላች ብለው ነው?»

«አይ የሴትና የማሰሮ ትንሽ የለውም»

«ኧረ ግፍ ነው!»

«ከትዳር ጋር ታድጋለች፡፡ ከዚህ በላይ ማጋጣ ነው የምትሆነው፡፡ በዚህ ኑሮ ላይ ዲቃላ አምጥታ»

ተዋበች ነገሩ የገባት አትመስልም፡፡ እህቶቿን ሳታወርድ፣ እላይዋ ላይ የበቀሉ መስለው እጇን ደባደቦ ያደረገውን እከከ ትፎክታለች፡፡ ለሁኔታው ተመቻቸች፡፡ ብትቃወም ኖሮ እየተፈራገጠችም ቢሆን «መታረዷ» አይቀርም ነበራ!

የሠርጉ እለት አዝማሪዎች የከት ልብሳቸውን አወጡ፡፡ እናቷ በቋቁቻ የአሳ ገላ የመሰለ ፊታቸውን ፈካ አድርገው «የዛሬን ቀበሩኝ!» ሠፈርተኛው አላሳፈራቸውም፡፡ የሚደበቀውን ደብቆ መታየት ያለበት አዋጥቶ ፊት ለፊት አወጣው፡፡





ተዋበች በአበሻ ቀሚስ ተሞሸረች፡፡ ፀጉሯም ተተኩሷል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ እህቶቿ ከላይዋ ላይ ወርደው ታዩ፡፡ ቢሆንም እንቅልፍ የወሰደው ልጅ እንዳዘለች ሁሉ ለምዶባት ወደ ግራ እንዳዘነበለች ነች፡፡ አበጀ ዙጦ እንደአባትም እንደሽርዳጅም እያደረገው አንዴ መሐል አንዴ ዳር ይላል፡፡ የሴት ወገን አዝማሪ ሙያውንና ዝምድናውን በትክክሻው ያሳይ ገባ፡፡

መምጣት አይቀርም ሙሽራው መጣ፡፡ ዕድሜው ከ48 የሚያንስ አይመስልም፡፡ ከአበጀ ዙጦ ይበልጣል፡፡ በዚህ ላይ አኮርዲዮን ይኑረው'ጂ ያው አዝማሪ ነው፡፡ የሁለት ወገን አዝማሪ ጉድ በዚህ «ሰርግ» ታየ፡፡

ተዋበች እኛን በዓይኗ እየፈለገች የዕቃ-ዕቃ ሙሽራ ይመስል «ኑ!» ትለናለች፡፡ ደስ ብሏታል፡፡ ማታ ምን እንደሚከተል የተረዳች አይመስልም፡፡ ሙሽራው በዕድኔም በአካልም የከሰረች ሚስቱን እያስጨፈረ አዙሮ-አዙሮ ከኛ መንደር ጓዳ (ኮባ ሰፈር) ያለው ቤቱ ይዟት ገባ፡፡

ትዳሩ ግን አልፀናም፡፡ አዛውንቱ ሙሽራ የለመደ ኖሮ እሷን ፈትቶ ሌላ ልጃገረድ በሠርግ አገባ ተባለ፡፡ ምን ያህል በዚህ ድርጊቱ እንደቀጠለ እንጃ የተዋበች እናት ግን በለመደ እጃቸው ለሌላ ሰው ዳሯት፡፡ በመዳራቸውም ሳይፎክሩ አይቀርም «የኔ ልጅ ቆማ የምትቀር መሰሎት ኖሯል?»

ሁለተኛ ባሏ መሀን ናት ብሎ ፈታት፡፡ ኑሮዋ እዚያው እናቷ ቤት ሆነ፡፡ ከዚህ በኋላ ምን ያህል ፈትታ ምን ያህል ጊዜ እንዳገባች እንጃ፣ ግን ብዙ ጊዜ፡፡ በመጨረሻ አካባቢ በተስፋ መቁረጥ ሴተኛ አዳሪም ሆና ነበር፡፡ ሳትጠቀምበት የጭንቀት በሽታ ያዛት፡፡ አበደች፣ የመንደሩን ወንዶች በሙሉ እየጠራች ውሽሞቿ እንደሆኑ ትናገር ጀመር፡፡ ጉድ ተባለ፣ ሌሊት ፍራሿን ተሸክማ ጉዞ ትቀጥላለች፡፡ በኋላ አቅም እያጣች ስትመጣ በነጣቂ ሰው ድንገት እንደተያዘ ሰው «ኡ! -ኡ» እያለች መንደር ማመስ ጀመረች፡፡ በመጨረሻ ተገላገለች፡፡ ታሪክ ባልከተበው በአንዱ ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች፡፡ አበቃ፡፡ ሰፈራችን አፈራቻት ያለወቅቷ አብስላት፣ አጣጣመቻት፡፡

በእንዲህ ዓይነት ታሪክ ምን ያህል እጓዝ ይሆን?

* * *

እመት ወደሬ ድፋባቸው ይባላሉ:: እሳት የመሰሉ ቀይ ንቅሳታም:: የአንገታቸው ቆዳ ተትረፍርፎ ሲታይ የመነጽር መጥረጊያ የላሸቀ የውሻ ቆዳ ይመስላል:: ድሮ የጌታ ሚስት ነበሩ:: ስልክክ ብሎ የወረደ ፊት አላቸው:: አሁንም የእመቤትነት እርጋታቸውና ጥንቃቄያቸው የጉድ ነው:: በፊት የጌታ ሚስት ሳሉ ብዙ ባሪያዎች ነበሩዋቸው:: ከእነዚህ ባሪያዎች መካከል አንዷ ቅርብ ጊዜ ድረስ ትጠይቃቸው ነበር:: ሁለቱም ዘመን በአዋጁ እኩል እንዳላደረጋቸው ሁኔታቸው ያስታውቅ ነበር:: አሁንም ባሪያና እመቤትነት እነሱ ዘንድ ይሸትታል::

መሐኒቱ እመት ወደሬ «ልጅና ችጋር አልወድም!» ይበሉ'ጂ ሆዳቸው ሕጻናትን ስለመጥላቱ እጠራጠራለሁ:: ምክንያቱም ልጆች በነበርንበት ጊዜ «ቡሄ» ስንል በመደዳ በየቤቱ ጨፍረን እሳቸውን ስለዘለልናቸው ከፉኛ አልቅሰዋል:: ሴት ግን ከልባቸው ነው የሚጠሉት:: ጠላቸው ኾምጠጥ ይደፋል እንጂ ሴት ይዞ ለመጣ ወንድ አይሸጡም::

መንደርተኛው «እሳቸው ያለድመት የሚወዱት የላቸውም» ይሏቸዋል:: በእርግጥም ድመት በጣም አድርገው ይወዳሉ:: ሲስሙ እንኳን አፋቸው ላይ ነው:: ሲያቆላምጡ ልክ እንደ ልጅ እያቀፉ ነው:: ድመቶቻቸውም ሲበዛ ንፁሆችና ጨዋዎች ናቸው:: ከእሳቸው ጋር ድብዳብ ላይ በማዕረግ የሚቀመጡ::

ኃይለሚካኤል አፉፉ በሰከሩ ጊዜ «ይቺ የድመት እናት!» ይሏቸዋል:: ይህን ጊዜ እመት ወደሬ «የድፌ ያለህ፣ ይቺ ቺ የኔ ናት» ይሉና ድመታቸውን አቅፈው ድብዳባቸውን ይዘው ወደቤታቸው ይገባሉ::

እስካሁን አንድ ከሆዴ የማይጠፋና ድህነቴን የማማርርበት አጋጣሚ አለኝ:: እመት ወደሬ ከመሞታቸው ትንሽ ቀደም ብሎ በኑሮ መሸነፍ ያዙ በፊት ጥንቁቅና የማንንም ዕርዳታ የማይሹ ነበሩ:: ጥንት በባለፀግነታቸው ጊዜ የነበራቸውን ቅርስ ሸጠው ጨረሱ:: በወጣትነታቸው ጊዜያት ይይዙት የነበረው ቦርሳ፣ ያደርጉት የነበረው መጫሚያ እና አንዳንድ አልባሳት ዞሮ ዞሮ የአሁን ዘመን ፋሽን ሆኖ መምጣቱን የመንደራችን ሴት ወጣቶች በመደነቅ ሲያወሩት አስታውሳለሁ:: ብዙ ዓመታት የተቀመጠ ደረቅ ብስኩት (ኮሾሮ) ሳይቀር ሸጡ:: በመጨረሻ መረታት ያዙ...:: አዳብለውት የነበረው ወንደላጤ መንግሥት መጠሪያ ቦታ ካለው ይወስዳቸው ዘንድ





ማመልከቻ አፃፈ (ለዚህ ለዚህ የኛ ሰፈር ሰዎች ጥሩዎች ናቸው ለማለት እደፍራለሁ) በአድማ ሰውየው ሀሳቡን እንዲቀይር አስገደዱት «ለምን ቀባሪ ያጣሉ? እዚሁ የኖሩበት እኛ እንቀብራቸዋለን» አሉ:: በእርግጥም መንደርተኛው ከመቅበር ሌላ ማድረግ የቻለው አልነበረም::

አንድ ቀን ከቤት ወደ ውጭ ስወጣ እመት ወደሬ አልጋቸው ላይ ቁጭ ብለው በመስኮት ውጭ ውጭውን እያዩ ልክ እንደ ህፃን ልጅ «እ-እ- እ» እያሉ ያለቅሳሉ:: ጠጋ ብዬ ምን እንደሆኑ ጠየኳቸው::

«እራበኝ!» አሉኝ::

ይሄንን ገጠመኝ ሳስበው እንባዬ ይመጣል:: (አሁን እንኳን እያለቀስኩ ነው የምጽፈው) ለዚያ ቀን እኪሲ የነበረችውን አንዲት ብር አውጥቼ ትንሽ ልጅ አስልኬ የሚበሉት አስገዛሁላቸው:: ይህ የመጨረሻ አልሆነም:: በተደጋጋሚ ገንዘብ በሌለኝ ሰዓት ላይ ያ-እንጀት የሚበላ ለቅሷቸው አጋጥሞኛል::

እመት ወደሬ ብዙም ሳይቆዩ በዚያው አካባቢ አረፉ፣ አሁንም ቢሆን መተላለፊያዬ ላይ ያለው መስኮታቸው የሐዘኔ መነሻ፣ የፀፀቴ መንገሻ ነው::

ፍቅሬ:-

ሁሉም ነገር የከንቱ ከንቱ - ከንቱ ሆኖ የሚታየኝ ይሄን ጊዜ ነው:: የሰው ልጅ! ትልቁ የሰው ልጅ መሄጃ መንገዱንና ማረፊያ ቦታውን እያወቀውም» ጓዙ-ጉዝጓዙ ይበዛል'ጂ ነፍሱ ያደረችበትን የሥጋ ቤቱን'ኳን የትም እጉድፍ ላይ ጣጥሎት ነው የሚነጉደው:: ሌላው ይቅርና እራሱ እንኳን የራሱ አይደለም፤ ይሄን ሳምሰለስል «የሰው ልጅ ታላቅነት እምኑ ላይ ነው?» ብዬ ሰው ለሚለው ቃል የተጣጣለ ትርጓሜ እሰጠዋለሁ::

ፍቅሬ:-

አንቺ ከዚህ አኗኗር የተገደብሽ ነሽ:: ምናልባት ኑሮ ምቾቷን አልነፈገችሽምና ለሰው አፈጣጠር ያለሽ ከበሬታ ታላቅ እንደሚሆን አውቃለሁ:: ይህ እንደ ቅዠት ያለ ስሜት የመረረ እውነታን ላለማስተዋል:: ጥሩ ጠቀሜታ አለው::

የራስሽን ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ሕይወት የምትኖሪው እንደኛ ባለ የጎስቋሎች መንደር ውስጥ ነው:: ጥጋብሽ ጎረቤት ያለውን ረሃብ አስታውሶ

ስለጥጋብሽ ፈጣሪሽን ከማመስገንና ከመደሰት ይልቅ ስለጎረቤትሽ ፈጣሪሽን እንድትወቅሽው ያስገድድሻል፡፡ ከግራ ቀኝ የምትሰሚው «ተመስገን፣ ይቺን ቀመስከ ብለህ ፆሜን አታሳድረኝ» የሚል የሥጋት መማፀኛ ነው፡፡ አንዳንዴ ይሄ መማጠኛ ከሌሊቱ ስድስትና ሰባት ሰዓት ሊሰማ ይችላል፡፡ ይታይሽ በእኩለ ሌሊት «ይቺን ቀመስከ ብለህ ፆሜን አታሳድረኝ» የሚል የመማጠኛ ፀሎት፡፡ ይህንን በተደጋጋሚ ስትመለከቺ ደግሞ «ሰው ማለት ሆዱ ነው» ወደሚለው መደምደሚያ ታመሪያለሽ፡፡ ሰዎች ይለፋሉ፣ ይማስናሉ፣ ከሆድ ሌላ ጠብ የሚል ግን አይታይም፡፡ ስለነገ ሆድ ደግሞ ይታሰባል፡፡ የሚገርምሽ ለልጆቻቸው የሚያወጡት የቤት ስም እንኳን ከሆድ ጋ የተያያዘ ነው «ሆዶ፣ ጋሙዳ፣ ገልብጥ...» እያሉ፡፡ እንዲህ ይባል ይባልና በመጨረሻ ያ ሲሸሹት የከረሙት ረሃብ የጉልበትን መሰነፍ ምክንያት አድርጎ ከነጓዙ መጥቶ ይሰፍናል፡፡

ፍቅሬ፡-

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ተጣልቶ ከኤደን ተራራ ሲያስወጣ «ጥረህ-ግረህ ብላ» ማለቱን አጠራጠራለሁ፡፡ ዝም ብሎ ሆዱን ነው የሰጠው፡፡ ይሄ የስጋ መቃብሩን ነው ያሸከመው! ከዚያማ ምን «ጥረህ ግረህ...» ማለት ያስፈልጋል?





# ፫

ዛሬ መንደራችን ላይ አንድ አሳዛኝ ነገር ተከሰተ፡፡ ይኸውልሽ አንድ የቀበሌ መኖሪያ ቤቷን በከርከር የተነጠቀች ሴት በየሰው ቤት ስትንከራተት ቆይታ ዛሬ ወደ 9፡00 ሰዓት ላይ ህይወቷ አለፈ ያሳዝናል፡፡ ለካ ለሕመምተኛ ትልቁ መሰረታዊ አስፈላጊ ነገር መድኃኒትና ምግብ አልነበረም መጠለያ እንጂ፡፡

የሟች ባለቤት ላስታውስሽ፡፡ እመት ወደሬ በኑሮ መዳከም ሲጀምሩ ደባል ያስገቡት ወንደላጤ መንግሥት ወደ መጠለያ እንዲወስዳቸው ማመልከቻ አፃፈ... ብዬሽ ነበር፡፡ እሱ ነው ከዚህ ወዲያ አግብቶ፡፡

ሥሙ ፈቃደሥላሴ ይባላል እኛ ግን እንቁራሪት እላለሁ ብሎ እንቃቅሊት በማለቱ የምንጠራው «እንቃቅሊት» እያልን ነው፡፡ እንቃቅሊት ሲበዛ እውቃለሁ ባይና ሁከተኛ ነው፡፡ «ያው እንግዲና...» ብሎ ነገር ማስረዘም ይወዳል፡፡ ጎራዳ አፍንጫ ያለው ድፍንፍን ደባደቦ መልኩን ፊት ለፊት ጋርጦ ከርከር ከገጠመ መሽቶ ይነጋታል'ጂ ተሸነፍኩ አያውቅም፡፡

ፍቅሬ፡-

ይኸውልሽ እመት ወደሬ ከሞቱ በኋላ ቀበሌው በሳቸው ፋንታ ሌላ ደባል ለማስገባት ወስኖ አንድ ሰው አስገባ፡፡ በዚህ ጊዜ እንቃቅሊት አልተስማማም፣ ከላሰር ቢጤ ይዞ መታየት ጀመረ፡፡ ብዙ አማራጭ ቀረበለት «እምቢኝ!» አለ፡፡ እንደውም ቀበሌው በጉቦ በላዩ ላይ ሰው አስገባ ብሎ ከሰሰ፡፡

በሰፈር ሽማግሌ ተለመነ

«እምቢኝ!»

በመጨረሻ ቤቱ ለሁለት ተከፍሎ እንቃቅሊት የፊት-ለፊቱን መርጦ ቢገባም ነገሩን አልተወም፡፡ እንደውም ነገሩን ፍርድ ቤት አደረሰው፡፡ ከሁለት ዓመት በኋላ መሆኑ ነው በእንቃቅሊት ላይ የተፈረደበት፡፡ ለካ ህጋዊ የሆነ ቅጽ-ፎርም በቤቱ ነዋሪነት አልሞላም፡፡ እሱ የተዳበለው ከተከራይዋ ወደሬ ድፋባቸው፡፡

ቀበሌ ከፖሊስ ጋር መጥቶ ቤቱን አሸገው፡፡ እንቃቅሊት ከነሚስቱ ውልቅ! ይህም ሆኖ እንቃቅሊትና ከላሰር አልተለያዩም፡፡

ሰዎች ያገኘና ስለሁኔታው ሲጠይቁት «እኔ ሙች ተሸንፌ? ጉቦ! ጉቦ እንጂ... አሁንም የበላይ አለ ይግባኝ እላለሁ፡፡» ይላል፡፡

በመጨረሻ ለነገር ቢያመቸኝ ብሎ ይሆናል ዕቃውንም ሳይረከብ ቀርቶ እየተቆጠረ ወደ ቀበሌ ተጋዘ፡፡ ነገር ሲደራረብበት ከስራውም በዚሁ አመሉ አባረሩት አሉ፡፡ የሚሰራው አንድ ድርጅት ውስጥ ነበር፡፡ ብሔራዊ ውትድርና ያለዕድሜ ማማሏያ አድርገውት ታፍሶ ከዘመተ በኋላ ሲመለስ ተከራክሮ ስራው ይገባል፡፡ በመጨረሻ ደግሞ እንደገና የሶስት አመት ቁታ፣ ሳሙናና ወረቀት ይሰጠኝ ብሎ ከከሰሳቸው፡፡ ውጭ ሆነህ ተከራከረን ብለው አባረሩት፡፡ ያሳዝናል፡፡

በዚህ ቀውጢ ጊዜ ነው ሚስቱ የሞተችው፡፡

የእንቃቅሊት ሚስት ሞት በመንደራችን እንደተሰማ ሰፈራችን ከሁለት ተቢድና ፀቧን ጀመረች፡፡ እንቃቅሊት በሚሚገትበት ወቅት ለሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ቲፎዞ የነበሩቱ ናቸው አሁን የሚወነጃጀሉት፡፡

«እንዲህ አላልሽም??»

«እንዲህ ብልሽ - እንዲህ አላልሺኝም??»

ጫጫታው አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ ሴት የኮማሪቷ ረጳች ድምጽ ዘለግ ብሎ ይሰማል፡፡ ፈርዶባቸው ቀስ ብሎ ነገር አይሆንላቸውም፡፡ «ተ-ው-ኒ ምነው ረቴ!» ይላሉ ደጋግመው ደጋግመው ይቺኑ ነው፡፡ ከአንዷ ጋር ወደ ግል እንኪያ-ሰላንቲያ ሊሸጋገሩ ነው ማለት ነው፡፡

የቅምቅም አድባር ሞቅ-ሞቅ አለች - ጭዳዋ ፀብ ነዋ!

መንደራችን የድሮ የፀብ «ግርማ ሞገስዋ» እጥታለች፡፡ ጥላዋ ተገፏል፡፡ በፊት በእያንዳንዱ ምሽት በስድብ መቧነንና ድብድብ አይጠፋም ነበር (ይህንን የማነሳው በቁጭት ነው)

«የገብሬ ባቄላ አድባር ሞቅ-ሞቅ አለች» ይባል ነበር፡፡ አድባሯ ፀብ ታፈቅር ነበራ! ጭዳዋ የሰው ደም... መካሰስ ነው - ተፈሳፍሶ ወደ ቤት! ለግልግል የወጣውም ባለመግባባ ተደባድቦ ነው የሚመለሰው፡፡

እነ አባይነሽ ዲናሞ ከውጭ ቀምቅመው ሲመጡ የፀቡ መነሻ ምን እንደሆነ ሳያረጋግጡ ነው ምስግ የሚሉት «እኔ ቀጭኗ! ፈሩ ፈሩ ማጀት አሩ» ትላለች፡፡ ፈሊጥ





ብላው'ጂ ፈርታ'ኮ አታውቅም፡፡ «እንቆቆ ሁሉ! ዞር በይ ከመንገዱ!» ነገር የምትፈልጋትን ሴት ገፍትራ ትወረውራታለች፡፡ መተንኮስ፡፡ በቃ ሰፈሩ ይጫጫሳል ውሪዎች «ሆ!» እያሉ ይፈነድቃሉ፡፡

...መደማመጥ አለመኖሩ እራሱ ውበት ነው፡፡ አየሩ በስድብ ብስብስ-ጥንብት ይላል፤፡ ግሩም የሚያሰኝ ይሆናል'ጂ አያስከፋም፡፡ ታፍሮና ተከብሮ የኖረው ውድ ገላ በድብድብ እርከስክስ ብሎ እዛም-እዛም ቁጭ ብሎ እንደመናፈሻ አበባ ይፈካል... (መንደራችን የፓንት ዘመን ላይ ገና አልደረሰችም) ...የሚገርመው ባል ሚስቱ ስትደባደብ ለመገላገል ከመሞከር ይልቅ የተደባዳቢዋን ባል ፈልጎ ፀብ መጀመር ነው የሚቀናው ይህ ነው የመንደራችን ወግ፡፡

ነፍሱን ይማረውና ኃ/ማርያም ኢዶ የሰፈራችን ዋነኛው ተንኳሽ ነበር፡፡ ሰክሮ ሲመጣ ወዲያና ወዲህ እየተላጋ ቢሆንም ወድቆ አያውቅም፡፡ እንደዚያ ሰክሮ ሲደባደብ አይወድቅም፡፡ የሚያከር ስካር ነው ያለበት፡፡ እንጨት ይሆናል፡፡

ከውጪ ሰክሮ ሲመጣ ጫጫታ ካጋጠመው፡- «ቆይ አንድ ሀጢያት እሰራለሁ» ይልና ወደ ቤቱ ገብቶ የስፖርት ቱታውን ይለብስና የእግር ኳስ መጫወቻ ባለ ጡት ጫማ አድርጎ ይወጣል፡፡ ከዚያማ ካጋጠመው ጋር መጋጠም፡፡

ኃ/ማርያም ቢያጣ-ቢያጣ ደባ ባልና ሚስቶችን ሳይደበድብ እንቅልፍ አይወስደውም፡፡ ደባሎቹ እማማ ብርቄና ባላቸው አቶ ደምሴ ካቲካላ አፍቃሪያን ነበሩ፡፡ ሴትዮዋ እንጀራ እየጋገሩ ይሸጣሉ፡፡ ባላቸው አቶ ደምሴ ደሞ ጥልፍ ይጠልፋሉ፡፡ እኔ ልጅ ሆኜ እስራቸው ተቀምጬ የሚጠልፉትን ስመለከት «አየህ» ይሉኛል በኩራት «እኛ'ኮ አንፀድቅም፡- ምክንያቱም ፈጣሪን በስራው ገብተውን እየተፎካከርነው ነንና» ይላሉ፡፡ ምጥጥ ያለ ቀይ ፊት አላቸው፡፡ ሲስቁ ቀይ-ድድ-የፂም ጅማሬውም የለባቸውም፡፡ ከሳቸው ይልቅ እማማ ብርቄ ፂም ነበራቸው፡፡ አቶ ደምሴ ሁልጊዜ የሚጠልፉት ፊቶ ከቦች፣ ወገብ የሌላቸው ሙቀጫ እግር ሰዎችን ነው፡፡ ከስር የሚያስጠልፈውን ሰው ስም ጠቅሰው፡- «ረታችን ቅዱስ ገብርኤል ይጠብቃት» የሚል ላይ ታች የተንጨፈረረ ጽሁፍ ያከሉበታል፡፡

ኃ/ማርያም ሰክሮ ላይ ታች እየረገጠ እና በጠማማ አፍንጫው የሚተናነቀውን አየር እያስወጣ ሲጨጣ መጀመሪያ የሚጠራው ሚስቱን ነው፡-

«ስንዱዬ ሚስቴ ናት!... ውዷ ባለቤቴ!» እያለ ይጮኻል፡፡ ሚስቱ ስንዱ በጣም አድርጋ ትችለው ነበር፡፡ ጴንጤ ብትሆንም አንዳንዴ የሰፈሩ ወግ እንዳይቀርባት ወጥታ መጣላቷ እንደውም መደባደቧ አይቀርም፡፡ ስንዱ ውፍር ያለ ፊት አላት፡፡ ግንባሯ እንኳን የሚገመስ ስጋ አለው፡፡

ኃ/ማርያም ቤቱ እንደገባ በምን መንገድ ፀቡን እንደሚጀምረው'ኛ ሁለቱን ባልና ሚስቶች ማንሜጫት ይጀምራል፡፡ ብዙ ጊዜ እራሳቸውን የሚስቱት ዝርግፍግፏ ሚስት ናቸው፡፡ እኛ ተሯሩጠን ስንደርስ መጋረጃው ተበጥሶ አቶ ደምሴ በረጅሙ የውስጥ ሱሪያቸው (በቡታንቲ) ቀጭን ማማሰያ የመሰለች ዱላ ይዘው አልጋ ላይ ቆመው መሬት የወደቁ ሚስታቸውን፡-

«ብርቄ፤ ሞተሻል ገሎሻል እንዳትነሽ» እያሉ ሞራል ይሰጣሉ፡፡ ኃ/ማርያም ጥርሱን «ሲጢጢጢጥ» እያደረገ በጠማማ አፍንጫው ለሙተንፈስ ይታገላል፡፡

እኛ ውሪዎቹ በመስኮት ተንጠልጥለን በደምሴ ላይ እንስቅባቸዋለን፡፡

ይሄኔ ወደኛ ዞር ይሉና «ቤንጤ! ቤንጤ ሁሉ» እያሉ ምጣጣ ፊታቸውን እያመላገጡ እኛን ለማብሸቅ ይሞክራሉ፡፡ ይበልጥ እንስቅባቸዋለን፡፡ እንደ ሕፃን ልጅ አልጋው ላይ እየዘለሉ ይንፈጨፈጫሉ፡፡

በኃ/ማርያምና በደምሴ መሀል የእማማ ብርቄ አወዳደቅ የሚያስቅ እንደነበር ትዝ ይለኛል፡፡ ሆዳቸውንና ከምሩ ጡታቸውን ወደ ላይ ገልብጠው በጀርባቸው ይንጋለሉና ያንከራፋሉ፡፡ አንዷ እውቅ የመንደራችን ሽርዳጅ ይሄንን አወዳደቃቸውን አይታ «ፍታቱን የጨረሰ ከበሮ አስመሰላቸው አይደለም?» እያለች ተሰብሳቢውን ስታስቅ ትዝ ይለኛል፡፡ እማማ ብርቄ በዚህ ሁኔታ ሌሊቱን ሊያነጉት ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ መንደርተኛው በመስጋ ተሸክሞ ቀበሌ ይወስዳል ለአምቡላንስ ይደወላል፡፡

(በዚህ መሀል እኛ ውሪዎቹ ለሳንሳ ተይዘው የሚሄዱትን ብርቄ ከስር ከስራቸው እንቆነጥጣቸዋለን፡፡ ምንም ነቅነቅ እንኳን አይሉም፡፡ ጨለማጋ ስንደርስ ጢማቸውን እንነጫለን-ዝም፡፡ ብቻ ወፈራም ከናፍራቸው ያጨበጭባል ስንመነጭቃቸው)

እኛ ስንመለስ ኃ/ማርያም ነፍሱን እያውቅም ይተኛል፡፡





የመንደራችን ታሪክ 90 እጅ ፀብ ነክ ነው፡፡ አንዳንዴማ «እስኪ ሰፈሩ ይሟሟቅ» ብለው የቆየ ፀበኛቸውን ስድብ የሚገጥሙ ሰዎች እንደነበሩ አስታውሳለሁ፡፡

...በእርግጥ አኗኗራችን ለሰላማዊ ሕይወት የተስማማ አይደለም፡፡ እኛ መንደር እየተኖረ ማንንም አልነካም ማለት ዘበት ነው፡፡ የኑሮአችን ዘይቤ እዝልዝሎሽ በመሆኑ ሳትፈልጊ በግድ ለፀብ እራስሽን ማዘጋጀት አለብሽ፡፡ የፍሳሽ መውረጃው በደጃፍሽ ላይ ይሆናል፡፡ ፍንጣሪው ቤትሽ ጉብቶ አልጋ ላይ እስከሚወጣ ቆሻሻ ውኃ የምትደፋ ባለጌ ትኖራለች ዝም አትያትም፡፡ የልብስ ማስጫያ ሽቦው የጋራ በመሆኑ ያንቺን እርጥብ ጨርቅ ሰብስባ የምታሰጣ ደፋር፤ አለበለዚያም መጠጥ ባለው ጨርቅሽ ላይ እርጥብ ጨርቅ የምትደርብ ትመጣለች ዝም አትያትም፡፡ እንዲሁም ግድግዳዎቹና ጣሪያዎቹ የተያያዙ በመሆናቸው መጋረጃ ለመስቀል፤ ፎቶ ለማንጠልጠል ብላ ባለ በሌለ ኃይሏ ስትወግረው ግድግዳው ይናዳል፡፡ ጥቀርሻው ይረግፋል - ዝም አትያትም፡፡ ይህን ሁሉ ዝም ብትይ በልጅ ሲመጣ...

-ከዚህ ሌላ የመንደራችን ሁሉ ሙብራት ከአንድ ቆጣሪ ላይ የተጠለፈ በመሆኑ መንደራችን ሲያባላት የቆየ ጉዳይ ነበር፡፡ ዛሬ በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው በዚያ እርጌ ቆጣሪ በጋራ የሚጠቀሙት፡፡ በፊትማ የቆጣሪው ተጠቃሚ አምፑል እስከ 53 የሚደርስበት ጊዜ ነበር፡፡

ወሩ ሲደርስ... እፉፉፈ ድምጻቸውን ዘለግ ያደርጉና «መያት! መያ!» (ሙብራት! ሙብራት!) ይላሉ፡፡

«ስንት ቆጠረ?»

ይነገራታል

«ስንት - ስንት ደረሰብን?»

«በስንት አምቦል?»

«አንድ ነዋ! ስንት አለኝ?» ትቆጣለች

ሌላዋ ድንገት በነገሩ ውስጥ ትሰነቀርና፡- «ሁለት አምቦል ነው ያላት! ...ሴት ተቀን የምታንተገትጊው አንሶ እንደገና አንድ አምቦል ታጭበረብሪ?»

«ማነው አጭበርባሪ?»

ፀብ ማለት ይሄ ነው፡፡

መብራት በመጣ ቁጥር ወቀሳው መአት ነው «ካውያ የሚጠቀሙ እኔ የደረስኩባቸው አሉ... ምድጃ...»

የታየቸው ሴት «አቃጣሪ!» ብላ ታልጎመጉማለች፡፡ ተናጋሪዋ ከሰማች ቱግ ትላለች «አቃጣሪ?... እንደውም አንቺ ነሽ...»

«ደግ አደረኩ! አ-በ-ጀ-ሁ!»

አንድ ጊዜ እፉፉን የመብራት ሂሳብ ሲሰበስቡ ሀጎሥ ይጠይቃቸዋል፡፡ ይነግሩታል፡፡ ቤቱ ሄዶ አካፍሎ የአስር ሳንቲም ትርፍ ይመጣለታል፡፡ «ዋእ ይ!» ይልና እፉፉን እንደሌባ ይመለከታቸዋል፡፡ እፉፉ ይበሳጫሉ ሰላልሰከሩ ይችሉታል፡፡ በሆዳቸው «ቆይ ልስከር!» ሳይሉ አይቀሩም፡፡ ሀጎስ ይባስ ብሎ ባለፈው ለመብራት ከተዋጣው ገንዘብ ውስጥ ተርፎ የተቀመጠውን ያስታውሳል፡፡ በዚሁ አንድ ሁለት ሲባባሉ እፉፉ ብልጭ ብሎባቸው «እኔ ኃይለሚካኤል» ብለው በዚያ ብረት እጃቸው በኩርኩም ቅል-እራሱን ቋ! ያደርጉታል፡፡

ሀጎስ ለተወሰነ ደቂቃ ጉንፉን እንደያዘው በግ ፈዞ ይቆማል፡፡ እንደ መንገዳገድም ይቃጣዋል፡፡ እፉፉ «ፉቭ ፉቫ» ይሉና ፈንገል-ፈንገል እያሉ ወደቤታቸው...

ሀጎስ ፈዞ-ሲበቃው፣ እራሰን እያሻሸ «ዋአይ!- ዋአይ!» እያለ ወደቤቱ ገብቶ የቡና ዘነዘና ይዞ ይወጣል፡፡ እፉፉ የሉም፡፡ ብስጭትጭት እንዳለ ወደ ቤታቸው ሲሄድ በሩን ይዘጉበታል፡፡ የንዴቱን እየተንገዳገደ ትልቅ ድንጋይ በሁለት እጁ አንስቶ የእፉፉን በር ለመምታት ሲወረውር ፊት-ለፊቱ ያለውን ስቶ ድንጋዩ እማማ ወደሬ ቤት በመስኮት ገባ፡፡ ያልሳቀ ሰው አልነበረም፡፡

«የድፌ ያለህ!» እሙት ወደሬ

«እንዴት ይለበልባል-ዋ አይ!» እያለ ተመለሰ፡፡





# ጉርድ ድህረ ማስታወሻ

ፍቅር ውሻ የመሆን በሽታ ነው፡፡ መልከስከስ አለበት፡፡ እኔ እውነተኛ ፍላጎቴ ሙሉጌታን መራቅ ነው፡፡ ግን ውሻ አፈጣጠር ያለብኝ ይመስል አፍንጫዬን ቀስሬ እያነፈነፍኩ ጉያው ውስጥ እድፎነፎናለሁ - እንደ ቡቹ፡፡ ቁጭ ብዬ፣ አልሄድም!... አልሄድም! እላለሁ፡፡ እየሄድኩ እንኳን!! አልሄድም!... አልሄድም!... እላለሁ፡፡ እያገኘሁትም!... አላገኘውም!... አላገኘውም!... እላለሁ፡፡ ሳሳዝን፡፡

ሙሉጌታ ደግሞ ሲያገኘኝ ቶሎ ወደ ጨዋታ ያደላል፡፡ የት ነበርሽ?! ለምን ጠፋሽ?! ደብዳቤው ደረሰሽ? አይልም፡፡ ቶሎ ወደ ጨዋታ፡፡ ሌላው ቀርቶ የሸሸሁበትን እያወቀ መልሶ አያነሳብኝም፡፡ ሌላ ሰው ቢሆን «እንቢ አልሽ? እ?» እያለ ይፈጥራል፡፡ ከዚያ ያኮርፋል፡፡ ሙሉጌታ ግን...

ሁኔታውን እንደወደድኩለት አውቋል ማለት ነው ስል አሰብኩ፡፡ ድብብቆሽ እየተጫወተ ግን የተደበቀውን ሰው የማይፈልግ ልጅ ቢኖር ምን ትሉታላችሁ? ተፈላጊው ተደብቆ፣ ተደብቆ ሲሰለቸው የሚመጣበት ቦታ ሆኖ ይጠብቀዋል፡፡ «በምንም አይሸነፍም» ስል አሰብኩ፡፡

ሲያገኘኝ አሳሳሙን ጠበቅ አድርጎ ጉንጬ ላይ ቆየ፡፡ ደስ አለኝ፡፡ ሰው የበዛልኝ፣ የተከበብኩ መሰለኝ፡፡ ለባርነት የምፈነገለው እነዚህን ስሜቶች እንደ ክፍያ ቆጥሬ ነው፡፡ የተለመደው ቤት ቁጭ እንዳልን ትንሽ ቆየት ብሎ ፊቱን አስገረመና፡-

«ዛሬ አንድ አዛውንት አዝማሪ የመሰንቋቸውን ጭራ በዕጣን እያሟሹ የተቀመጡበት ሆነው አዩኝ፡፡ እንዲህ በማለት ግጥም ገጠሙ» እንጋጠጠና ለማስታወስ እየሞከረ...

«ሊቃውንት፣ እዋቂ ከሆናችሁማ፣

በሉ ቀን ፍጠሩ ሳይውጠን ጨለማ፣»

መልሶ ፊቱን ከመደነቅ ወደ መደበብ ወሰደው፡፡ የሚለቃቅመው እውቀት ብቻ ሳይሆን የሚሰካበት ስስ ብልት እያስገረመኝ ነው፡፡ ይሄን ግጥም ለምን እንደነገረኝ አውቃለሁ፡፡ እኔንም ስለሚመለከት ነበር፡፡ በእርግጥም ለሚፈጠረው የመንደሯ ምስቅልቅሎሽ ሳይሆን እኔን ለሚዌለከቱ ሁለት ሰዎች ብቻ አሰብኩ፡፡ እዚያ መንደር

ውስጥ አራትና አምስት መቶ ሰዎች «ጨለማ ሲውጣቸው» እኔ «ቀን እየፈጠርኩ» ያለሁት በአባቴና በፍቅረኛዬ ልብ ውስጥ ለራሴ ብቻ:: በረጅሙ ተነፈስኩ ደበተኝ::

ሙሉጌታም እንደደበተኝ አውቆ የተወኝ መሰለኝ:: በሁለት እግሬ ባለ ተቃራኒ የፍቅር ለመንጠላጠል እየሞከርኩ ነበር:: አባቴ... ሙሌ... አሁንም የታየኝ የሳጥናኤል ሰይፍ ስንዝራ፣ የመልአኩ ሰይፍ ምክቶሽ.. የሁለቱ ሰይፍ ግጭት የሚፈጥረው ብልጭታ...

* * *

ጨንቆኛል:- ጧ! የሚል የጥይት ድምጽ ከሩቅ የሚሰማኝ ይመስለኛል:: መስኮቴን ከፈትኩ:: በመኝታ ቤቴ ላይ ያለኝ ባይተዋርነት አድሮ በመውጣት እየተገለፀ ነው:: እንደኪራይ መኝታ ቤት፣ አልጋ አንጥፌና ከፍሉን አናፍሼ አለማወቄ ከስንት ጊዜ በኋላ ከነከነኝ:: ስሟ የመጥሪያው ድምጽ የሚመስል የቤት ሰራተኛ በተለዋጭ ቀልፏ አዘገጃጅታ ትሄዳለች::

ውጭው ጨፍግጎታል:: እንግዶች እንደተስተናገዱበት ገበታ ሰማዩ ተዝረከርኳል:: ዛፎች ብርዱን ለመቋቋም ቅጠሎቻቸውን አስተቃቅፈው ፈዘዋል:: አልፎ-አልፎ ጧ! የሚል ድምጽ ይሰማኛል:: ቀልቤን አቀባብዬ ዓይኖቼን ተኮስኩ:: ሁለት ዳለቻ እርግቦች በክንፎቻቸው እየተጠፋጠፉ ነው:: በመንቆራቸው ይጠቃጠቃሉ:: ምን አገናኛቸው ይሆን? ስል አሰብኩ:: ለቅም ለመር ሕይወት?

ጨንቆኛል:- ጧ! ይላ የእርግቦቹ ክንፍ::

ከእያንዳንዱ ህዋሳቴ የተጠረቃቀመ ስሜት ወደ ሽንትነት የተለወጠ ይመስለኝና ቦቱ እያደነቃቀፈኝና ስረግጠው እየጮኸ መፀዳጃ ቤት እሄዳለሁ:: ምንም የለም:: ከፍሉ የታፈነ ይመስለኛል:: መስኮቴን ስከፍት የሚለወጥ ነገር የለም:: የገዛ አካሌን ጥያቄ አልተረዳሁለትም ሙዚቃ?... ምግብ? ...መጠጥ?...

ጧ!

እጁን የሰጠች ተፋላሚ እርግብ ሸሸች:: አሸናፊዋ በእልህ ተከተለቻት:: ምናለበት ብትተዋት? የሰዎችም ከፋት ላይ የተፈጥሮ ደመነፍሳዊ ግፊት ያለበት መሰለኝ::

ጨንቆኛል:- አሁን ፀጥ ብሏል





ሙልዬን ለመንኩት:: አባቴን እንዳያገኘው:: እኔ በምፈራው በአባቴ ኃይለቃል አስፈራራሁት:: ሙልዬ ግን በጠይም ብርሃን የታጀበ ታሪክ ነገረኝ::

«የቻይናው መምህር ኮንፌሽስ የሥነ-ምግባር ትምህርት ከሚሰጣቸው ደቀመዝሙሮቹ አንዱ ድንገት ተነስቶ «ትምህርትህን ላስፋፋ ወደሩቅ ግዛት መሄዴ ነው» ይለዋል::

«ወዴት?» ይላል ኮንፌሽስ

በታውን ይናገራል ደቀመዝሙሩ::

«እሱማ የአመፅ ከተማ ነውና አትችልም» ይለዋል::

«እችላለሁ ብሎ ድርቅ አለ»

«እንግዲያው ለትምህርት ያለህን ፅናት ላረጋግጥ ብሎ የፈተና ጥያቄ ያቀርብለታል» እነዚህ ሰዎች ስታስተምራቸው ቢያላግጡብህ ምን ትላለህ?

«ስላልሰደቡኝ አመሰግናቸዋለሁ» ይላል ደቀመዝሙሩ::

«ቢሰድቡህስ?»

«ስላልመቱኝ አመሰግናቸዋለሁ»

«ቢመቱህስ?» ይላል ኮንፌሽስ

«ስላልጎዱኝ አመሰግናቸዋለሁ»

«ቢጎዱህስ?»

«ስላልገደሉኝ አመሰግናቸዋለሁ»

«ቢገድሉህስ?»

«ማንም የማያደርገውን ሽኝት ስላደረጉልኝ አመሰግናቸዋለሁ» ጉንጩን ቆንጠጥ አደረገኝ:: ነፋስ እንደገፈፈው ነጠላ ብቻኝነት ከላይ ላይ ተነስቶ ሲንሳፈፍ ታወቀኝ «እናም ኮንፌሽስ ደቀመዝሙሩን ወደዚያ ግዛት እንዲሄድ ፈቀደለት»

ዓይኖቼ አሁንም የተዝረበረበው ሰማይ ላይ ነው:: ጉሙ አስደናቂ ትርኢት በማሳየት ላይ ያለ ይመስላል በነፋስ ኃይል ቅርጹን ይለዋውጣል:: አንዴ የሰው ቅርጽ ይመጣል፣ ሌላ ጊዜ እንደጉድ ውልድ ሁለት ራስ ያለው ጥጃ:: ቆየት ብሎ ደግሞ የአበባ ዝንጣፊ...

ጆሮዬን ወደ ሳሎን ላኩት ምንም ይዞ አልተመለሰም፡፡ ሆዴ ውስጥ የሚፈርስ፣ የሚናድ፣ የሚርድ መሬት ያለ መሰለኝ፡፡ ወደ ሳሎን አመራሁ፡፡ አባቴ ሰሞኑን ከቤት ወጥቶ አያውቅም፡፡

እኔ ስገባና ስወጣ እንደሚጄዱሳ ፀጉሩ እባብ የሆነ ይመስል ሲንቀሳቀስ ይታየኝ ነበር፡፡ በአንድ ቀልብ ከሚያነበው መጽሐፍ ላይ ውሃ እንደተጎነጨ ዶሮ ቀና ብሎ ሀሳቡን ይውጥና መልሶ ያቀረቅራል፡፡ ወይም ስልክ ይደውልና ያስታወሰውን ለሰራተኞቹ ያስታውሳል፡-

ሳሎን ስገባ አባቴ ከሚያነበው መጽሐፍ ላይ ለአመል ተፋትቶ አየኝና መልሶ ንባቡ ላይ ዓይኑን ጣደ፡፡ እግሮቹን ጠረጴዛ ላይ አጣምሮ ትከሻውን አስደግፎ ቀና እንዳለ ነው የሚያነበው፡፡ የለበሰው ተመሳሳይ ነጭ ሸሚዝና ሱሪ ከጥቁር ሴዘሩ የሶፋ ልብስ ጋር ተነጻጽሮ አባቴን አየር ላይ የተንጋለለ አስመስሎታል፡፡ መጽሐፉ ወደሱ ስለተደፋ ልባሱ በደንብ ይታየኝ ነበር «ኦርበናይዜሽን ኤንድ ኢንቨስትመንት» ይላል፡፡

አባቴ አፍረት የማብዛቱን ጉዳይ አውቀዋለሁ፡፡ አሁን ድርጅቶቹ ሁሉ እራሳቸውን እየቻሉ ነው «እንደ ልጅ ነው ድርጅት» ይላል «ማዘል የሚያስፈልግሽ ዕድሜ አለው፣ የምትታቀፊው፣ የሚድህበት፣ ቆሞ የሚሄድበትና እንቺን መልሶ የሚደግፍበት ማቹርድ ፔሬድ አለው» አሁን አብዛኞቹ ድርጅቶች ከትትል ቢያስፈልጋቸውም እሱን ሙጥኝ አይሉትም፡፡ ይሄን ሁኔታ አባቴ የሚወድደው አይመስልም፡፡ ስለዚህ አዲስ አራስ ድርጅት አቋቁሞ ወደ ማዘሉ ይሸጋገራል፡፡ የአራት ኪሎው ፕሮጀክት ለአባቴ አዲስ ውልድ መሆኑ ነው፡፡

ሳሎኑ ተጫጫነኝ፡፡ ሽንቴም የመጣ መሰለኝ፡፡ ሙሉጌታ በቅርብ ደቂቃ ውስጥ ከአባቴ ጋ ሊፋጠጥ ይመጣል፡፡ሙቼም ወዳጃዊ ውይይት ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡ አባቴ ለሙሉጌታ ያለው መስተንግዶ የታወቀ ቢሆንም ሙሉጌታ እንዴት ሊስተናገድ አሰቦ ይሆን?

«እባክህ ሙልዬ አትምጣ»

ወደ መጸዳጃ ለመሄድ በማመንታት ላይ ሳለሁ የግቢ መጥሪያ ጮኸ፡፡ አባቴ በመጽሐፉ አናት አስታኮ አየኝ፡፡ የልቤ ምት ሐዘን እንደገባው ሰው ወደፊት ገፋ-ገፋ እያደረገ ሲንጠኝ ታወቀኝ፡፡





ደግሞ ጮኸ፡፡ ነፍሴ ስቅቅቅቅ ሲለው ያሰማው ድምጽ መሰለኝ፡፡

ወደውጪ ልወጣ ስነሳ ቦቹ ከወደ ጓዳ እንደቁልቁለት ላይ ኳል እየተንከባለለ መጣ፡፡ ደውሏን ሲሰማ በር ሊከፈት እንደሆነ ያውቃልና ለአፍታ ነፃነት ካለበት ቦታ ይመጣል፡፡ በሩን ስከፍት ቀድሞኝ ወጥቶ የማድያት ጉም የሚያንዣብብበት የድንጋይ ንጣፍ ላይ የውሻ ወጉን ለማድረስ መልከስከስ ጀመረ፡፡

አባቴ ቤት ሲውል ታስሮ የሚቆየው ሾፌር አለባበሱን አሳምሮ ጋዜጣ ያነባል፡፡ እኔን ሲያይ ጋዜጣውን እጥፍ ከወገቡ ዝንጥፍ ብሎ ሰላምታ ሰጠኝ፡፡ ፈዛዛው ዘበኛ ሰው እኔን ከፈለገ በደወል እንዲጠሩኝ የነገርኳቸው ቢሆንም እንግዳውን በመጠርጠር ወደጊቢው አላስገቡትም፡፡ የሰው መውጪያውን በር ገርበብ አድርገው ይመረምሩታል፡፡

«ይግባ» አልኳቸው፡፡ ኮፍያቸውን ከራሳቸው ላይ ገሸልጠውልኝ በሩን በጥቂቱ ለቀቁለት፡፡ ዘበኛው ሁልጊዜም ሰው አስገቡ ሲባሉ ቅር የሚላቸው ነገር አለ፡፡

«እባክህ ሙሌ» አልኩት በዓይኔ፡፡ ዓይኑ ዝም አለኝ፡፡

ሳንነጋገር ወደ ሳሎን በር ቀደምኩ፡፡ ቦቹ አዲስ ሰው ሲመለከት የውሻ ወጉን ለማድረስ ጮኸ፡፡ የገረመኝ ደግሞ እንደትልቅ ውሻ ለማስፈራራት ማጉረምረም ይደባልቃል፡፡ ሆን ብዬ ቦቹን ወደውጪ አስቀርቼው ገባን፡፡

ሙሉጌታ ለጊቢውም፣ ለቤቱም፣ ለሳሎኑም ቁብ ሳይሰጠው በዓይኑ ሰው ይፈልግ ነበር፡፡ በአጋጣሚ እዚህ ቤት የሚመጡ እንግዶች ቀድሞ አድናቆታቸውን የሚገሰው ጊቢውና ሥነ-ስርዓቱ ነበር፡፡ እንደውም አንዳንዶቹ ሳሎን ሲገቡ ምንጣፉን እያየ ጫማ ካላወለቅን እያሉ ይገላገላሉ፡፡ ሙልዬ ግን....

አባቴ ተከታትለን ስንገባ በመጀመሪያ በግርታ እኔን አየኝ፡፡ ሙሉጌታን ስላላወቀው ይመስላል አቤቱታ አቅራቢ መስሎት ሳሎን ይገኘው ስለገባሁ በዓይኑ እኔን ወቀሰኝ፡፡ ቀጥሎ ሙሉጌታ አእምሮው ውስጥ ትውስታ እየገዛ ሲሄድ ሰማዩ ላይ ያየሁትን የጉም ትርኢት የመሰለ የቅጽበት መለዋወጥ ፊቱ ላይ ተነበበ፡፡ እያንዳንዱ የስሜት ለውጥ በገሃድ ታየኝ፡፡ ግር መሰኘት፣ ግር ከመሰኘቱ በኋላ ወገግ እያለ የሚሄድ የመደነቅ ጅንበር ፊቱ ላይ ወጣች፣ መደነቁን መደፈር ገሰሰው፡፡ ከዚያም

ንዴቱን ለእኔም አካፈለኝ፡፡ መጽሐፉን ቀስ አድርጎ አጠፈ፡፡ ጠረጴዛው ላይ ከተዘሩት ሞባይሎች ጋር አስቀመጠ፡፡ ቀስ ብሎ እግሮቹን አወረደ፣ ቀስ ብሎ ተነሳ፡፡

ሙሉጌታ ስንገናኝ ያደረገውን ኮት ከነአህያ ጀሮ ኮሌታው ለብሷል፡፡ ታጥቦ ያልተተኮሰ ሱሪ ታጥቋል፡፡ ከዓይኑ ሥር ያለው ቁስሉ እርጥብ ኩበት መስሎ አኮፍኩፏል፡፡ ፊቱ ላይ ምንም አይነት ስሜት አይነበብም፡፡ ፍፁም እንደተረጋጋ ነው፡፡ በዓይኖቹ ሰይፍ የተቀመጠው መጽሐፍ ላይ አኮብኩቦ አባቴን መመልከት ጀመረ፡፡

እኔ መሀል ላይ ውሃ ሆንኩ፡፡

«ከሰሰከኝ?» አለ አባቴ «መጥሪያ አመጣህ?»

«አዎ» አለ ሙሉጌታ፡፡ ለአባቴ መጥሪያ ለመስጠት ያታለለኝ መሰለኝ፡፡ ግን ቀጠል አድርጎ «ከስሻለሁ፣ አንተን ለራስህ ከስሻለሁ፡፡»

«ልትፈላሰፍ ባልሆነ የመጣኸው» ምን ማድረግ እንዳለበት ባለመገንዘብ ይመስላል ለጥቂት ደቂቃ ፀጥታ ሰፈነ፡፡ ሁለቱም ተቋቁመዋል፡፡ ከዚያም አባቴ መቁነጥነጥ ጀመረ፡፡ በዓይኑ የሚወረወር የሚፈልግ መሰለኝ፡፡

«የደሃ ነገር የራስህ አማራጭ ሆነህ መጣህ? ልጅህን ስጠኝ ልትል ባልሆነ...» የሚወረወር ሲያጣ እያመሳቀለ መመልከት ጀመረ፡፡

«አይደለም በፍጹም» አለ ሙሉጌታ፡፡

«ታዲያ ንገረኛ» ጠጋ ማለት ጀመረ «እዚህ ቤት ያመጣህን ንገረኝ! የፈረንሳዩ የድሆች አብዮት እዚህም አገር ሊደገም ይሆን? እሱን ለኔ ተውት ብለህ በግብታዊ አብዮተኝነት ልትገድለኝ መጣህ?»

የአባቴን መጠጋት አልወደድኩትም፡፡ ጣቶቼ ጨበጥ ፈታ ይላሉ፡፡ ጨነቀኝ ልናገር ስንተባተብ ወደኔ ዞሮ «ዝም በይ!» ብሎ ጮኸብኝ «ይሄ ለኔ ስድብ ነው፡፡ ንቀት!!» ሙሉጌታ ሲገባ ባለበት ሁኔታ ነው፡፡ የአባቴ ወርቅማ ሰዓት በእሱ ላይ የምትንተገተግ መሰለኝ፡፡ ሀብሉን ፈለኳት የለችም፡፡

«ልጄ እንደ አጼ ቴዎድሮስ ሚስት እንደምንትዋብ ባሏን በአባቷ ላይ አሳምጻ ይዛ መጣች፡፡ ግሩም ነው፡፡ እዚሁ ብገድልህ ጠያቂ እንደሌለኝ አታውቅም?» ይበልጥ ቀረበ፡፡





«እስኪ መጀመሪያ ለምን እንደመጣ ጠይቀው» አልኩ ስድቡንና ሽሙጡን ብቻ ሳይሆን ዱላውንም ወደኔ ማዞር አሰኘኝ፡፡

«የመጣውማ መኝታ ቤትሽን ለመጎብኘት ነው፡፡»

«ታፊ!» አልኩት በስንት ግዜዬ? «ታፊ እንዲህ አከፋፍተህና አራክሰህ አትናረኝ» ጋብ ያለ መሰለኝ፡፡ ለአፍታ ስሜቱ የተገሰፀ፡፡

«ለአመጽም፣ ለከሰም፣ ለጋብቻም አልመጣሁም» አለ ሙሉጌታ፣ ጲላጦስ ፊት እንደቀረበው እስረኛ መወገሩን መፀፋቱንና መሰቀሉን ከቁብ ሳይቆጥር፡፡

«ለምንም ና» አለ አባቴ ስሜቱን በገዛ እኳኋን «አሁን ውጣልኝ፣ ሰበብ ሳትሆንብኝ ውጣ!»

ዝም ብሎ ቆመ

«ውጣ!» አለ እየቀረበው፡፡

«የመጣሁበትን ልናገር»

«ውጣ!» ብሎ ጉብ አለበት፡፡ የኮቱን ክሳድ በግራ እጁ እንደጨመደደ ወዝውዞ ለቦክስ የጨበጠውን እጁን ዘረጋግቶ በጥፊ አጮለው፡፡ ሙሉጌታ አልተከላከለም፡፡ እጆቹ እንደታጠበ ሽሚዝ እጅታ ወደታች እንደተንጠለጠሉ ነበር፡፡ አባቴ አሁንም «ውጣ!» ብሎ በቀኝ እጁ በቃሪያ ጥፊ ደገመው፡፡ ይሄኔ መጮኅግ የጀመረው ቁስሉ ተገሽልጦ የእሳተ ገሞራ ሽንቁር መሰለ፡፡ የቁስሉ ቅርፊት ጎርፍ እንደገፋው ደለል ተንፏቀቀ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ከአፍንጫው ደም መንጠባጠብ ጀመረ፡፡

የተወጋርኩ፣ የተገረፍኩ፣ የተሰቀልኩ ያህል ሆነብኝ፡፡ ከሆዴ የሚነሳውን እንባዬን አይኔ ላይ ለማድረስ በደረቁ ተንሰቀሰኩ፡፡ እድባሬ በመጥረቢያ የተፈለጠ፣ ታቦቴ የተማገደ ያህል አመጽ ተቀሰቀሰብኝ፡፡ መሀል ልገባ ስል ሙሉጌታ በእጁ «ተይ» የሚል ምልክት ሰጠኝ፡፡ ሌላኛው እጁን አፍንጫው ላይ ደቀነ፡፡ ደም ሞላው፡፡

አባቴ «ውጣ! ውጣ! ውጣ አንተ ሰውዬ» እያለ ለቆት ወደነበረበት ቦታ ተመለሰ፡፡ የሚያየው ስለረበሸው ይመስላል ፊቱን ወደ መስኮቱ መልሶ ቆመ፡፡ ቆይቶም በቀኝ እጁ ዓይኖቹን ሸፍኖ በጣቶቹ መካከል ጣሪያ የሚያይ መሰለ፡፡

ሙሉጌታን ለመርዳት ስጠጋ በእጁ ገፋ አድርጎኝ «በማድፋፋት እውነት አትብከነከንም፡፡ ይልቅ ረጋ ብለን እንነጋገር» አለ፡፡ ድምጹ ተኮናኩኗል፡፡

የአፍንጫውን ደም ለማቆም ቀና አለ:: እንደሱረት ሱሰኛ በአፍንጫው ደጋግሞ አየር ሳበ::

«ያንተ እውነት» አለ አባቴ ፊቱን ሳይመልስ «እንደ ቶልስቶይ መሬትህን ለብኩናን አከፋፍልና በድህነት ባቡር ፌርማታ ላይ ሙት ልትለኝ ነው? ይሄ የደሃ ቃልቻ ስብከት ነው...»

«ተፈጥሯዊው ህግ እንዲገሰስ አማላጅ ሆኜ አልመጣም» አለ ሙሉጌታ:: ምን እንዳገኘ ያላወቅሁትን ነገር አፍናጫው ውስጥ እየጠቀጠቀ «አህያ ጅብን አትብላኝ እንዳለችበት ተረት ይሆናል ይሄማ:: ተሸናፊዎች ነን እንድንበላ ህግ ይፈቅዳል:: የእግዚአብሔር ሰው እንደሚባለው አንተ የእግዚአብሔር ጅብ ሆነህ ሳበላን ብታልፍም ሌላ የእግዚአብሔር ጅብ ያልሆነ ጅብ ይበላናል:: ዕጣ ፈንታችን መንገድ ዳር እንደተጣለ ሙዳ መበላት ብቻ ነው:: ይሄን የማይረዳ ጭንቅላት የለኝም:: የአዲስ ዘመን መለከት ነው ለኛ የምፅአት ጥሪ የሆነብን::»

«ታዲያ?»

ሙሉጌታ አፍንጫውን ጠቅጥቆ እንደጨረሰ እጆቹን በመጠየፍ ተመለከተ:: የሚያደርገው ቢያጣ ወደኋላ አጣመረና ዘና ባለ አኳኋን ቆመ::

«ተናገራ?» አለው

«እውነት ሆኜ መጣሁ::» አለ ሙሉጌታ:: ምን ማለቱ እንደሆነ ለኔም አልገባኝ::

አባቴ ግን የተግባባ ይመስላል:: በማሽሟጠጥ «እውነት ትሆን ይሆናል፣ መንገድ ግን አይደለህም» አለው::

«እኔ ላንተ እውነትም መንገድም ነኝ» አለው::

ግራ ተጋባሁ፣ በልሳን የሚነጋገሩ መሰለኝ:: በዚህ መካከል አባቴ ረጋ ባለ ድምጽ «እርጥባን ወደ መኝታ ቤትሽ ግቢ» አለኝ::

«አትገባም!» ሲል ሙሉጌታ በሙሉ ስልጣን ተከላከለ «ጉዳዩ እሷንም ይመለከታል»





አባቴ ጀርባውን እንደሰጠ ዝም አለ:: ፍርሃቱን፣ ጭንቀቱን፣ መረታቱን፣ ሁለመናውን ፊቱ ላይ ላለማስነበብ ሆኖ ተሰማኝ:: ግን ምን? ስል እራሴን ጠየኩ:: ሙሉጌታ መናገር ጀመረ:-

«እኔ ቢለወጡ ደስ የሚሉኝ ግን እውነት በመሆናቸው ብቻ የተቀበልኳቸው ብዙ የኋላ ታሪኮች አሉኝ:: ለምሳሌ የሽርሙጣ ልጅነቴ:: እናቴ አያቴ አውቆ እስኪያባርራት ድረስ መቆሚያ ጣቢያ የምትቆም ሴተኛ አዳሪ ነበረች:: በእውኔ ስትቆም አይቻት ባላውቅም አሁንም የብርሃን ዘንግ መስላ እንደቆመች በህልሜ ትመጣለች:: ይሄን አውራ ጣቴን ያወረሰኝን ባለቀይ አውራ ጣት ዘማች አባቴን ባላውቀውም ስለውርስ አውራ ጣቱ ምስጢር አግኝቼ ብጠይቀው እመኛለሁ:: እውነት ነውና ምን ላድርገው? ዛሬም ቢሆን እውነቶች ውስጥ ነኝ:: አያቴ የዕለት እንጀራችንን በምፅዋት የሚያመጡ ለማኝ ሆነዋል:: ይሄን በሐሰት ለውጬ ምን ላድርገው?»

ምንድነው የሚያወሩት? ወዴት ነው የሚሄዱት? በማለት ነፍሱ አልወጣ እንዳለችው ሰው ጣዕሬ በዛ::

«በቃ» አለ አባቴ የማስፈራራት ሳይሆን የልመና ነበር «ይብቃህ»

ሙሉጌታ እንዳልሰማ ሆኖ ቀጠለ «አንተም ብትሆን መንደራችንን በማድፋፋት፣ መንደርተኞችን እየጫሩ በመበተን እውነትህን ለማብከንከን አትሞክር:: ተቀበል:: እኔ ሀብት ስለሌለኝ አይደለም እውነቶቼን የተቀበልኩት:: እውነት እውነት ስለሆነ ነው:: አንተ እንደምትገምተው እኛ መንደር ውስጥ ስላንተ አይወራም:: ማንም የተገናዘበ ሐሜት ላይ አይሰማራም:: አንተ ግን እራስህ እውነትህን አደባባይ አውጥተህ ተቀበል:: የአቡንደጅ ልጅ ነኝ! በል:: ድምጽህን ከፍ አድርገህ:: እየመከርኩህ አይደለም:: ቂጥኛም ከውርዲያም እንደሚጫወተው እያጫወትኩህ ነው::» ብሎ ከቤት ለመውጣት ተዘጋጀ::

ለጊዜው ተምታታብኝ:: የጠራውን ስም ማስታወሻ ውስጥ አውቀዋለሁ:: የአቡንደጅ... አዎ... ሴተኛ አዳሪዋ የአቡንደጅ... ወፍራሟ የአቡንደጅ... ቤቷን ለሴተኛ አዳሪ ያከራየቻው የአቡንደጅ... ጠጅ ቤት በራፍ ላይ የወደቀችው የአቡንደጅ... እዚያው

የሞተቸው የአቡንደጅ... እና? እሷ የአባቴ እናት? የእኔ አያት? እንዴት?... እንዴት? ...እንዴት?

ሲወጣ ተከተልኩት:: ቦቹ የሱሪውን ጫፍ ይዞ እየነዘነዘው ነበር:: ምንም ሳይናገር ከኮት ኪሱ ውስጥ ሁለት ፎቶዎች አውጥቶ ሰጠኝ:: አንዱ እኔ እራሴ የሰጠሁት የአባቴ ፎቶ ነበር:: ሁለተኛው ግን እጅግ ያረጀ:: አትኩሬ ተመለከትኩት አንዲት ወፍራም ሴት ከትንሽ ልጅ ጋር የተነሳችው ነበር:: እሷ እንደ ደብር ተኮፍሳ ተቀምጣለች:: ፀጉሩን የከፈለው ልጅ ግን ቆሟል:: ቁምጣ ሱሪ ለብሷል:: አግድሞሽ የተኸጎረጎረ ሹራብ ላይ የቁምጣው ጥብጣብ ቁልቁል ተጋድሟል:: መልኩ መልኩ ያስታውቃል:: አለቀስኩ፣ በእንባዬ ውስጥ ህፃኑ የተንቀሳቀሰ መሰለኝ:: አባቴ::



ዓለማየሁ ገላጋይ፥ ከአጥቢያ እስከ ወሪሳ በዘጠኝ መጻሕፍት ተደራሲያንን አስደምሟል።
አስረኛዉን - አንድ አብይ ልቦለድ - ነገ ልንመሰጥበት ከአሳታሚ ጋር እየተዋዋለ ነዉ።
እንዴት አያሌ አንባቢያን ለመመልመል በቃ ? በቋንቋዉ ጥበባዊና ዘይቤያዊ ዉበት ይሆን ? በሚመረጠዉ
ጥልቅ ዕዉነታዊና ምናባዊ ጭብጥ ? በድኅረ-ዘመነኛ ሆነ በተለመደዉ የአተራረክ ክህሎት መካኑ ? ... አንባቢና
አድናቂ የየግሉን ምክንያት እየፋቀ ያስተዉላል። ልክ ነብይ መኮንን እንደተቀኘዉ "በጥላ በጣዩ ረክቶ በጥሞና
ለሚኖረዉ / እያንዳንዱ ማታና ቀን፥ የየራሱ ዘላለም ነዉ።"
ዓለማየሁ ጊዜን ለመነፈካከት ዳር አልቆምም፤ በህላዌ
ጉዳይ ተማስሎ አቃስቷል።

አጥቢያ አንዱ በጥሞና ተመስጦ፥ ሌላዉ ልቡ ተንጠልጥሎ በጥድፊያ የሚያነቡት ልቦለድ ነዉ። ዉብ የአራተኛ አመት
የማኅበረሰባዊ ጥናት ተማሪ -እርጥባን- ከአባቷ ጋር ለብቻቸዉ በተኮፈሰ ህንፃ ተገልላ በድሎት ኖራለች፤ በአራት ኪሎ
ደሳሳ ቤቶች ለድግሪ ማሟያ የመመረቂያ ጽሑፏን ለመስራት መወሰኗ፥ ከኑሮ ፊትና ጀርባ ያላትማታል። ሙሉጌታ
እየመራት የመንደሩን ገመና፥ ብርቅነት፥ ስጋትና ህልም ... ስታጤን ነፋስ እንደ ገፈፈዉ ነጠላ የዋህነት ጥሏት ለሌላዉ
ትብሰከሰከች፤ አንድ ተባዕት በማፍቀሯ ዉስጣዊ ዝምታዋ ተገጣጠበ። ግለሰብ የልጅነቱን አስከፊ ታሪክ እዉስጡ
እያጉረ ግልባጩን ቢኖርም፥ ከሆነ የኑሮ ኩርባ ሰቆቃዉ ሰብሮ ሲወጣ፥ ወሽባ መግባት አያስጥለዉም። የነባር አኗኗር
እልህና የለዉጥ ጉልበት ሲፋተጉ የሰከነዉ ህይወት እሳት ይጋይበታል። የሰዉ ሥነልቦናዊ፥ ማኅበራዊ እና የጋራ
እጣ ፈንታ ከፍቅር እስከ ጥላቻ የተመሳቀለበት ልቦለድ፥ ድንበሩ - ከበቡ- አጥቢያዉ ይናድ ይሆን ?

አብደላ ዕዝራ

ዋጋ 45.60

Bemela Printing